# መጽሐፈ ዜና መዋዕል- ሁለተኛ

## መግቢያ

**የ1ዜና ይመ ፡፡**

**በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ውስጥ የተወሳው የቤተ መቅደሱ ሕንጻ ሥራ**

የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ የዳዊትንና የሰሎሞንን ዘመነ መንግሥት ታሪክ በሚጽፍበት ጊዜ፣ የአምስቱን ብሔረ ኦሪት (የአምስቱን የሙሴ መጻሕፍት) ታሪክ እንደ ሞዴል አድርጎ በመውሰድ ተጠቅሞበታል፡፡
1. የምስክሩን ድንኳን ለመሥራት ኀላፊነቱን የወሰዱት ባስልኤልና ኤልያብ ነበሩ (ዘፀ35፥30-36፥7)፤ እነርሱም ለሰሎሞንና ለኪራምአቢ ግንኙነት እንደ ሞዴል አገልግለዋል (2ዜና 2፥13)፤ የባስልኤል ስም ከዘፀአት መጽሐፍ ውጭ የተወሳው በዜና መዋዕል መጻሕፍት (1ዜና 2፥20፤2ዜና1፥5) ላይ ብቻ በመሆኑ እንደ ትልቅ ነገር ታይቶአል፡፡

ሰሎሞን አዲሱ ባስልኤል ነው፤ (1) ሰሎሞንና ባስልኤል በስም ተጠርተው በሚሠሩት ሥራ ላይ በእግዚአብሔር የተመደቡ ሰዎች ናቸው፤ ለተመደቡበትም ሥራ በስም የተመረጡትም እነርሱ ብቻ ናቸው (ዘፀ 31፥2 ፤35፥30-36፥2፤ 38፥22-23፤ 1ዜና28፥6)፡፡ (2) ሁለቱም ሰዎች ከይሁዳ ነገድ ናቸው (ዘፀ 31፥2፤ 35፥30፤ 1ዜና2፥20፤ 3፥10)፡፡ (3) ለሁለቱም ሰዎች መንፈስ ቅዱስ የጥበብን ስጦታ ሰጥቶአቸዋል (ዘፀ 31፥3፤ 35፥30-31፤ 2ዜና 1፥1-13)፤ ሰሎሞን በገባዖን ያየው ራእይ (2ዜና 1፥1-13) ከቤተ መቅደሱ ሥራ በፊት እንደ መግቢያ ሆኖ ለተነገረው ታሪክ ጉልህ ስፍራ አለው (2ዜና 2፥7)፡፡ (4) ሁለቱም ሰዎች ለቤተ መቅደሱ ግሩም የሆነ የናስ መሠዊያ ሠርተዋል (2ዜና 1፥5፤ 4፥1፤ 7፥7)፤ የናሱ መሠዊያ ኪራምአቢ ከሚሠራው ከዋና ዋናው የሥራ ዝርዝር ውስጥ አልተጠቀሰም (4፥12-16)፡፡ (5) ሁለቱም ሰዎች በቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚያስፈልጉትን የመገልገያ ዕቃዎች ሠርተዋል (ዘፀ31፥1-10፤ 37፥10-29፤ 2ዜና4፥19-22)፡፡

በተመሳሳይ መንገድ ኪራምአቢ አዲሱ ኦሆሎያብ ተብሎአል፡፡ (1) በመጽሐፈ ነገሥት ላይ የቤተ መቅደሱን ሕንጻ ሥራ በተመለከተ የተጻፈውን ታሪክ ስንመለከት የኪራምአቢ ስም ተጠቅሶ የምናገኘው ዋናው የቤተ መቅደሱና የቤተ መንግሥቱ ሕንጻ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ነው (1ነገ 7፥13-45)፡፡ በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ግን እንደ ኤልያብ ሁሉ፣ ኪራምአቢም ገና ከመጀመሪያው አንሥቶ በሕንጻው ሥራ ላይ ተሰማርቶ እንደ ነበር ተገልጾአል (ዘፀ 31፥6፤ 2ዜና 2፥13)፡፡ (2) መጽሐፈ ነገሥት የኪራምአቢ ሙያና ችሎታ ናስ አቅልጦ መሥራት ብቻ መሆኑን ሲናገር (1ነገ7፥14)፣ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ሙያውንና ችሎታውን ዘርዝሮ የሚያስቀምጠው ግን፣ ልክ እንደ ኤልያብ ሙያና ችሎታ አድርጎ ነው ( ዘፀ31፥1-6፤35፥30-36፥2፤38፥22-23፤ 2ዜና2፥14፡፡ (3) መጽሐፈ ነገሥት የኪራምአቢ እናት መበለትና ከንፍታሌም ነገድ እንደ ሆነች ይናገራል (1ነገ 7፥14)፤ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ግን ከዳን ነገድ መሆኗን ጽፎአል (2ዜና2፥14)፤ በዚህ ዐይነት ኪራምአቢን ወስዶ ከኤልያብ ዘር ግንድ ጋር ያያይዘዋል (ዘፀ 31፥6፤ 35፥34፤ 38፥23)፡፡ የ2ዜና 2፥13 ማብ ይመ፡፡

2. የምስክሩ ድንኳንም ሆነ የቤተ መቅደሱ ንድፍ በቀጥታ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነው (ዘፀ25፥1-30፥37፤ 25፥9፡40፤27፥8፤ 1ዜና 28፥11-19 ይመ፤ ይህ ጉዳይ በመጽሐፈ ሳሙኤልና በመጽሐፈ ነገሥት ውስጥ አልተጠቀሰም)፡፡

3. ከጦርነት ብዝበዛ የተገኙ ዕቃዎች በምስክሩ ድንኳንም ለቤተ መቅደሱ ሕንጻ ሥራ የዋሉበት ጊዜ አለ (ዘፀ3፥21-22፤12፥35-36፤ 1ዜና18፥6-11 ይመ፤ ይህ ጉዳይ በመጽሐፈ ሳሙኤልና በመጽሐፈ ነገሥት ውስጥ አልተጠቀሰም)፡፡

4. ለምስክር ድንኳኑም ሆነ ለቤተ መቅደሱ ሕንጻ ሥራ ሕዝቡ ያደረገው መዋጮ በበጎ ፈቃድ የተደረገ ነው (ዘፀ 25፥1-7፤ 36፥3-7 ፤ 1ዜና29፥1-9 ይመ፤ ይህ ጉዳይ በመጽሐፈ በሳሙኤልና በመጽሐፍ ነገሥት ውስጥ አልተጠቀሰም )፡፡

5. የክብሩ ደመና የምስክሩ ድንኳንና ቤተ መቅደሱ በተመረቀበት ጊዜ ሲወርድ ታይቶአል (ዘፀ40፥34-35፤ 2ዜና 7፥1-3)፡፡

## ሰሎሞን ጥበብ እንዲሰጠው ጠየቀ

1፥2-13 ተጓ ምብ-3፥4-15
1፥14-17 ተጓ ምብ—10፥26-29፣ 2ዜና9፥25-28

1 አምላኩ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ
ነበር፣ እጅግም ስላገነነው፣ የዳዊት ልጅ
ሰሎሞን በመንግሥቱ ላይ ተደላድሎ ተቀመጠ።
2ከዚያም ሰሎሞን ለመላው እስራኤል፣
ለሻለቆች፣ ለመቶ አለቆች፣ ለዳኞች፣ ለእስ
ራኤል መሪዎች ሁሉ እንዲሁም ለየቤተ ሰቡ
አለቆች ተናገረ። 3የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ
በምድረ በዳ የሠራው የእግዚአብሔር የመገናኛ ድንኳን
በዚያ ስለ ነበር፣ ሰሎሞንና መላው ጉባኤ በገባዖን
ወዳለው ኰረብታ ሄዱ። 4በዚያ ጊዜ ዳዊት
የእግዚአብሔርን ታቦት ከቂርያትይዓሪም በኢየሩሳሌም
ድንኳን ተክሎ ወዳዘጋጀለት ስፍራ አምጥቶት
ነበር፤ 5ይሁን እንጂ የሆር ልጅ፣ የኡሪ ልጅ
ባስልኤል የሠራው መሠዊያ በገባዖን በእግዚ
አብሔር ማደሪያ ድንኳን ፊት ለፊት ይገኝ
ነበር፤ ስለዚህ ሰሎሞንና ጉባኤው ይህንኑ
ፈለጉ። 6ሰሎሞንም በእግዚአብሔር ፊት
በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ወዳለው ወደ
ናሱ መሠዊያ ወጥቶ በላዩ ላይ አንድ ሺህ
የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ።
7በዚያው ሌሊት እግዚአብሔር ለሰሎሞን
ተገልጦ፣ "እንድሰጥህ የምትፈልገውን ሁሉ
ጠይቀኝ" አለው።
8ሰሎሞን እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፤
"ለአባቴ ለዳዊት ታላቅ በጎነት አድርገህለ
ታል፤ እኔንም በእግሩ ተክተህ አንግሠኸኛል።
9አሁንም እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፤ ያነገሥኸኝ
ብዛቱ እንደ ትቢያ በሆነ ሕዝብ ላይ ስለ ሆነ፣
ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸው ተስፋ ይጽና።
10ይህን ሕዝብ ለመምራት እንድችል፣ ጥበ
ብና ዕውቀትን ስጠኝ፤ ይህ ካልሆነ ይህን
ታላቅ ሕዝብህን ማን ሊገዛ ይችላል?"
11እግዚአብሔርም ሰሎሞንን እንዲህ አለው፤ "የልብህ

1፥1 ዘፍ21፥22፤ 39፥2፤ ዘኍ14፥43፤ 1ነገ2፥12፤1ዜና29፥25፤2ዜና12፥1
1፥2 1ዜና9፥1
1፥3 ዘፀ40፥18፤ ዘሌ17፥4፤ኢሱ9፥3
1፥4 2ሳሙ6፥17፤ 1ዜና15፥25
1፥5 ዘፀ31፥2፤ 38፥2፤1ዜና13፥3
1፥7 2ዜና7፥12
1፥8 1ዜና23፥1
1፥9 ዘፍ12፥2፤ 2ሳሙ7፥25፤ 1ነገ8፥25
1፥10 ዘኍ27፥17፤ 2ሳሙ5፥2፤ ምሳ8፥15-16
1፥11 ዘዳ17፥17
1፥12 1ዜና29፥12፡ 25፤ 2ዜና9፥22፤ ነህ13፥26
1፥14 1ሳሙ8፥11፤ 1ነገ9፥19
1፥15 1ነገ9፥28፤ ኢሳ60፥5
2፥1 ዘዳ12፥5፤ መክ2፥4

መሻት ይህ ስለ ሆነ፣ ብልጥግናና ሀብት
ወይም የጠላቶችህን ነፍስ ወይም ረጅም
ዕድሜ ስላልጠየቅህ፣ ነገር ግን ባነገሥ
ሁህ ሕዝቤ ላይ የምትገዛበትን ጥበብና
ዕውቀት ስለ ጠየቅህ፣ 12ጥበብና ዕውቀት
ይሰጥሃል፤ እንዲሁም ከአንተ በፊት የነበረ
ማንኛውም ንጉሥ ያላገኘውን፣ ከአንተ በኋላም
የሚነሣው የማያገኘውን ብልጽግና፣ ሀብትና
ክብር እሰጥሃለሁ።"
13ሰሎሞንም የመገናኛው ድንኳን ካለበት
ከገባዖን ኰረብታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ፤
በእስራኤልም ላይ ነገሠ።
14ሰሎሞን ሠረገሎችንና[ሀ] ፈረሶችን ሰበሰበ፤
እርሱም አንድ ሺህ አራት መቶ ሠረገ
ሎችና ዐሥራ ሁለት ሺህ ፈረሶች ነበሩት፤
እነርሱንም በሠረገላ ከተሞችና እርሱ ባለበት
በኢየሩሳሌም ከተማ አኖራቸው። 15ንጉሡም
ወርቁና ብሩ በኢየሩሳሌም እንደ ተራ ድንጋይ
እንዲበዛ፣ ዝግባውም በየኰረብታው ግርጌ
እንደሚገኝ የሾላ ዛፍ እንዲበዛ አደረገ። 16የሰ
ሎሞንም ፈረሶች የመጡት ከግብፅና[ለ] ከቀዌ
ነበር፤ ከቀዌ[ሐ] የገዟቸውም የንጉሡ ነጋዴዎች
ነበሩ። 17ከግብፅ ያስገቧቸውም አንዱን ሠረገላ
በስድስት መቶ ሰቅል[መ] ብር፣ አንዱን ፈረስ
በአንድ መቶ አምሳ ሰቅል[ሠ] ብር ገዝተው ነው።
እንዲሁም ደግሞ ለኬጢያውያንና ለሦርያውያን
ነገሥታት ሁሉ ይሸጡላቸው ነበር።

## ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የተደረገ ዝግጅት

2፥1-18ተጓ ምብ-1ነገ5፥1-16

2 ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ስም ቤተ መቅደስ፣
ለራሱም ቤተ መንግሥት እንዲሠራ አዘዘ።

ሀ14 ወይም ሠረገለኞች ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
ለ16 በዚህና በቍጥር 17 ላይ የተጠቀሰችው በኪልቂያ አውራጃ የምትገኘው ሙዙር ልትሆን ትችላለች።
ሐ16 ምናልባት ኪልቂያ ናት።
መ17 7 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
ሠ17 1.7 ኪሎ ግራም ነው።

*1፥1-9፥31፡* ስለ ሰሎሞን ዘመነ መንግሥት የሚያወሣው ታሪክ የሚጀምረው፣ ከማናቸውም ነገር ይልቅ ሰሎሞን ቅድሚያ የሰጠውን የቤተ መቅደሱን የሕንጻ ሥራ በመጥቀስ ነው (ም2-7)፤ ጥበብን ከእግዚአብሔር ለመቀበል የታደለበት ዋናው ምክንያት፣ የቤተ መቅደሱን የሕንጻ ሥራ በቀላሉ ለማከናወን እንዲችል ነው። በነገሥት መጻሕፍት የተጻፉትን ከቤተ መቅደሱ ሥራ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸውን ብዙ ነገሮች የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በመጽሐፉ ውስጥ አልጠቀሳቸውም፤ ለምሳሌ ያህል፣ በወለዷቸው ሕፃናት ምክንያት በሁለቱ ጋለሞቶች መካከል ስለ ተሰጠው ፍርድ (1ነገ 3፥16-28) ወይም ስለቤተ መንግሥቱ ሕንጻ ሥራ (1ነገ 7፥1-12) አልጠቀሰም።

1፥1 *ተደላድሎ ተቀመጠ፤* እንዲህ ዓይነት ሐረግ ወይም ከዚህ ጋር የሚመሳሰል አገላለጽ በዚህ መጽሐፍት ውስጥ ብዙ ቦታ ይገኛል (12፥13፤13፥7-8፡21፤15፥8፤16፥9፤17፥1፤21፥4፤ 23፥1፤ 25፥11፤27፥6፤32፥5፤1ዜና11፥10፤19፥13)። እዚህም ሆነ በ21፥4 ላይ የተጻፈው ጠላቶቹንና የዙፋን ተቀናቃኞቹን ማጥፋቱን ያካትታል (1ነገ2 በተለይም ቍ46 ይመ)።

1፥2-13፤ (1ነገ 3፥4-15 እና ማብ ይመ። ከቍ 2-6 ያለው በዚህ የዜና መዋዕል መጽሐፍ ብቻ የሚገኝና ጸሓፊውም ልዩ ትኵረት ካደረገባቸው ነገሮች ጥቂቱን የሚያመለክት ነው፤ ይኸውም። (1) ለመላው እስራኤል የሚለው (ቍ2) አጽንዖት ተሰጥቶታል፤ ከ1 ዜና መግቢያ "ዓላማና መሪ ሐሳብ" የሚለውን ይመ)። (2) የመጽሐፈ ነገሥት ጸሓፊ ሰሎሞን በማምለኪያ ኰረብታ ላይ መሠዋቱን ቅር በመሰኘት የሚገልጽ ሲሆን (1ነገ3፥3)፤ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን ይኸው ጸሓፊ ሙሴ በምድረ በዳ የሠራው የመገናኛው ድንኳን በዚያ ስፍራ እንደ ነበር በመጥቀስ (ቍ3) የሰሎሞን ድርጊት ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ያመለክታል ዘሌ 17፥8-9።

1፥5፤ *ባስልኤል፤* በዚህ መጽሐፍ መግቢያ "የቤተ መቅደሱ ግንባታ በዜና መዋዕል" የሚለውን ይመ። ሰሎሞን በንጉሣዊ ሥልጣኑ ሕዝቡን ለማስተዳደር የሚያስችል ጥበብና ማስተዋል "ከእግዚአብሔር የተቀበለው ባስልኤል" በሠራው መሠዊያ ላይ (ዘፀ31፥1-11፤38፥1-2) መሥዋዕት ካቀረበ በኋላ ነው። ባስልኤል የላቀ የእጅ ጥበብ ባለሙያ በመሆን የመገናኛውን ድንኳን እንዲሠራ ጥበብን ከእግዚአብሔር እንደ ተቀበለ ሁሉ፣ ሰሎሞንም ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ጥበብ በቅድሚያ በቤተ መቅደሱ ግንባታ ላይ ማዋሉን የሚቀጥለው ታሪክ ያስረዳል።

1፥7 *እግዚአብሔር... አለው፤* ዳዊትም ሆነ ሰሎሞን እንደ ነቢይ ሆነው አገልግለዋል (7፥1፤29፥25፤ 1ዜና 22፥8፤ 28፥6፡19)።

1፥9 *ብዛቱ እንደ ትቢያ በሆነ፤* እግዚአብሔር ለአብርሃም ከሰጠው ተስፋ መካከል የተፈጸመውን ያሳያል (ዘፍ13፥16፤ 22፥17፤ እንዲሁም የ1ዜና 27፥23 ማብ ይመ፤ ከዘፍ28፥14 ጋር ያነጻጽሩ)።

*1፥14-17* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በ1ነገ 3፥16-4፥34 ላይ የሚገኘውን ታሪክ ዘሎታል፤ ከዚህ ይልቅ 1ነገ10፥26-29 ላይ ስለ ሰሎሞን ብልጽግና ወደሚናገረው ታሪክ ያመራል፤ ከፊሉ ግን በ2 ዜና 9፥25-28 ላይ ተደግሞአል። እዚህ ላይ የሰሎሞን ብልጽግና እንደገና መነገሩ፣ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ መፈጸሙን የሚያመለክት ነው (ቍ፡12)።

1፥16 *ከግብፅና፤* አማራጭ ትርጕሙን እንዲሁም የ1ነገ 10፥29 ማብ ይመ።

2፥1 *ቤተ መንግሥት፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ሰሎሞን ስለ ሠራው ቤተ መንግሥት ደጋግሞ ቢያወሣም (7፥11፤ 8፥1፤ 9፥11)፣

[2]እርሱም፣ የሚሸከሙ ሰባ ሺህ፣ ከኰረብታ ላይ
ድንጋይ የሚፈልጡ ሰማንያ ሺህ ሰዎችና ሦስት
ሺህ ስድስት መቶ የሥራ ተቈጣጣሪዎች
አሰማራ።
[3]ከዚህ በኋላ፣ ሰሎሞን ለጢሮስ ንጉሥ
ለኪራም የሚከተለውን ይህን መልእክት ላከ፤
"አባቴ ዳዊት የሚኖርበትን ቤተ መንግ
ሥት ሲሠራ እንደ ላከህለት ሁሉ፣ ለእኔም
የዝግባ እንጨት ላክልኝ። [4]ሽታው ደስ የሚ
ያሰኝ ዕጣን በፊቱ የሚታጠንበትን፣ የተ
ቀደሰ እንጀራ በየጊዜው የሚቀርብበትን፣
በየጧቱና በየማታው፣ በየሰንበቱና በየመ
ባቻው እንዲሁም በተወሰኑት በአምላካችን
በእግዚአብሔር በዓላት የሚቃጠል መሥዋዕት
የሚቀርብበትን ቤተ መቅደስ ለአምላኬ ለእ
ግዚአብሔር ስም ሠርቼ እቀድስ ዘንድ አስቤ
አለሁ። ይህም ለእስራኤል የዘላለም ሥርዓት
ነው።
[5]"አምላካችን ከሌሎች አማልክት ሁሉ ይበልጥ
ታላቅ ስለ ሆነ፣ የምሠራውም ቤተ መቅደስ
ታላቅ ይሆናል። [6]ነገር ግን ሰማይና ከሰ
ማያት በላይ ያለው ሰማይ እንኳን እርሱን
ይይዘው ዘንድ አይችልምና፣ ቤተ መቅደስ
ሊሠራለት የሚችል ማነው? በፊቱ ዕጣን
የሚታጠንበትን እንጂ ቤተ መቅደስ እሠ
ራለት ዘንድ እኔ ማን ነኝ?
[7]"ስለዚህ አንተ በወርቅና በብር፣ በናስና
በብረት፣ በሐምራዊና በደማቅ ቀይ፣ በሰ
ማያዊም ግምጃ ሥራ ዕውቀት ያለውን
እንዲሁም አባቴ ዳዊት ካዘጋጃቸው ከእኔ
የእጅ ባለሙያዎች ጋር በይሁዳና በኢየሩ
ሳሌም የቅርጻ ቅርጽ ጥበብ ሥራ የሚሠራ
ሰው ላክልኝ።
[8]ሰዎችህ ከሊባኖስ እንጨት በመቍረጥ
ሥራ ዐዋቂዎች መሆናቸውን ስለማውቅ፣
ከሊባኖስ የዝግባ፣ የጥድና የሰንደል ዕንጨትም
ላክልኝ፤ ሰዎቼም ከሰዎችህ ጋር አብረው
ይሠራሉ። [9]የምሠራው ቤተ መቅደስ ትልቅና
እጅግ ውብ መሆን ስላለበት፣ ብዙ ጠርብ
ያዘጋጁልኛልና። [10]ዕንጨቱን ለሚቈርጡ
አገልጋዮችህ ሃያ ሺህ የቆሮስ መስፈሪያ[a]
ስንዴ ዱቄት፣ ሃያ ሺህ የባዶስ መስፈሪያ
ወይን ጠጅና ሃያ ሺህ የባዶስ መስፈሪያ ዘይት
እሰጣለሁ።"
[11]የጢሮስ ንጉሥ ኪራምም ለሰሎሞን እንዲህ
ሲል በደብዳቤ መለሰለት፤
"እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለሚወድድ አንተን
በእነርሱ ላይ አነገሠህ፤ "
[12]ኪራምም በመቀጠል እንዲህ አለ፤
"ሰማይንና ምድርን የፈጠረ የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ! ለእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስን፣ ለራሱም ቤተ መንግሥትን
የሚሠራ፣ ብልኀትንና ማስተዋልን የተሞላ
ጥበበኛ ልጅ ለንጉሥ ዳዊት ሰጥቶአልና።
[13]"እጅግ ብልሃተኛ የሆነውን ኪራምአቢን
ልኬልሃለሁ፤ [14]እርሱም እናቱ ከዳን ወገን፣
አባቱም የጢሮስ አገር ሰው ነው፤ በወርቅና
በብር፣ በናስና በብረት፣ በድንጋይና በዕን
ጨት፤ እንዲሁም በሐምራዊና በሰማያዊ፣
በቀይ ግምጃና በቀጭን በፍታ ሥራ የሠለጠነ
ሲሆን፣ በልዩ ልዩ ቅርጻ ቅርጽ ሥራ ልምድ
ያካበተና የተሰጠውን ማናቸውንም ንድፍ
በሥራ መተርጐም የሚችል ባለሙያ ነው።
እርሱም ከአንተ የእጅ ሥራ ባለሙያዎችና
ከጌታዬ ከአባትህ የእጅ ሥራ ባለሙያዎች
ጋር አብሮ ይሠራል።
[15]"አሁንም ጌታዬ በሰጠው ተስፋ መሠረት
ስንዴውንና ገብሱን፣ የወይራ ዘይቱንና የወይን
ጠጁን ለአገልጋዮቹ ይላክ፤ [16]እኛም የሚ
ያስፈልግህን ግንድ ሁሉ ከሊባኖስ ቈርጠ
ንና አስረን እስከ ኢዮጴ ድረስ ቍልቍል
በማንሳፈፍ እንሰድልሃለን፤ አንተም ወደ
ኢየሩሳሌም ታስወስደዋለህ።"
[17]ሰሎሞን አባቱ ዳዊት ካደረገው ቈጠራ
በኋላ፣ በእስራኤል ምድር የነበሩትን መጻተኞች
ሁሉ ቈጠረ፤ ቍጥራቸውም አንድ መቶ

2፥2 2ዜና10፥4
2፥3 2ሳሙ5፥11፤ 1ዜና14፥1
2፥4 ዘፀ25፥30፤ 29፥42፤30፥7፤ ዘሌ23፥38፤ዘኍ28፥14፤ዘዳ12፥5፤2ዜና13፥11፤29፥28
2፥5 ዘፀ12፥12፤ 1ዜና16፥25፤22፥5
2፥6 ዘፀ3፥11፤ 1ነገ8፥27፤ኤር23፥24
2፥7 ዘፀ35፥31፤ 1ዜና22፥16
2፥10 ዕዝ3፥7
2፥11 1ነገ10፥9፤ 2ዜና9፥8
2፥12 ነህ9፥6፤ መዝ8፥3፤ 33፥6፤96፥5፤102፥25፤146፥6
2፥13 1ነገ7፥13
2፥14 ዘፀ31፥6፤ 35፥31፡35
2፥15 ዕዝ3፥7
2፥16 ኢሱ19፥46፤ ዮና1፥3
2፥17 2ሳሙ24፥2፤ 1ዜና22፥2

[a]10 4,400,000 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።
[b]10 440,000 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።

ስለ አሠራሩ በዝርዝር የጻፈው ነገር የለም (1ነገ 7፥1-12)።

*2፥2* ቍ 17-18 ይመ።

*2፥3-10፤* ሰሎሞን ከጢሮስ ንጉሥ ከኪራም ጋር ባደረገው የደብዳቤ ልውውጥ ዘገባ ውስጥ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ሥነ መለኮታዊ በሆነ ነገር ላይ ምን ያህል እንደሚያተኵር በግልፅ ይታያል። በመጽሐፈ ነገሥት ዘገባ መሠረት፣ ለደብዳቤው ልውውጥ መንሥኤ የሆነው ኪራም ነበር (1ነገ 5፥11)። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን ይህንና በ1ነገ 5፥3-5 የተጻፈውን ትቶ የራሱን ትኵረት በማን ጸባረቅ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ስለሚፈጸመው ሥርዐተ አምልኮ (ቍ 3-7) የሚያወሣ ታሪክ ከራሱ ጨምሮበታል።

2፥4 1ዜና 23፥28-31 ይመ።

2፥7 ከመጽሐፉ መግቢያ የቤተ መቅደሱ ግንባታ በዜና መዋልዕ የሚለውን ይመ። በመጽሐፈ ነገሥት በተጻፈው መሠ ረት ሰሎሞን የላቀ የእጅ ጥበብ ባለሙያ እንዲላክለት የጠየቀው ጥቂት ቈየት ብሎ ነው (1ነገ፤7፥13) የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ መጀ መሪያ በተለዋወጡት ደብዳቤ ውስጥ ኤልያብንና ኪራም አቢን አነጻጽሮአቸዋል፤ በተጨማሪም እዚህና በቍ 13-14 ላይ ከባስል ኤልና ከኤልያብ ችሎታ ጋር ለማመጣጠን፣ የኪራም አቢን ችሎታ ሰፋ አድርጎ ገልጾአል (በመጽሐፈ ነገሥት የተጻፈው ግን ናስ አንጥሮ ማውጣት መቻሉን ብቻ ነው)።

2፥10 እዚህ ላይ የተመለከተው ክፍያ በ1ነገ 5፥11 ላይ ከሚገኘው ይለያል ፤ ይሁን እንጂ ሁለቱም መጻሕፍት የሚናገሩት ስለ ሁለት የተለያዩ ክፍያዎች ነው። የመጽሐፈ ነገሥቱ የሚያ መልክተው ለኪራም ንጉሣዊ ቤተ ሰብ ባጠቃላይ የተደረገውን ዓመታዊ ክፍያ ሲሆን፣ በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ የተጠቀሰው ግን የዕንጨት ሥራ ለሚያከናውኑት ሰዎች የተደረገውን የአንድ ጊዜ ክፍያ ብቻ የሚያሳይ ነው። የተሰጡትም ዕቃዎች አንድ ዓይነት አይደሉም፤ በመጽሐፈ ነገሥት ላይ የተጠቀሰውም ዘይት ማለፊያው ዓይነት ዘይት ነው።

*2፥11-16* 1ነገ 5፥7-9፤7፥13-14እና ማብ ይመ ።

2፥13 *ኪራምአቢን* የቍ7 ማብ ይመ፤ የኪራምአቢ የት ውልድ ሐረግ አመጣጥ የንፍታሌም ወገን በሆነች በአንዲት መበ ለት በኩል መሆኑን መጽሐፈ ነገሥት ይገልጻል (1ነገ 7፥14)፤ መጽሐፈ ዜናም ከዳን ነገድ መሆኑን በመግለጽ ከኤልያብ ጋር እያነጻጸረ ሐሳቡን ያጸናል። በመሠረቱ እነዚህ ገለጻዎች እርስ በርስ አይጋጩም ምክንያቱም፣ (1) እናቱ የምትኖረው በንፍታሌም ምድር ቢሆንም ትውልዷ ግን ከዳን ነገድ ሊሆን ይችላል፤ ወይም (2) ወላጆቿ ከዳንና ከንፍታሌም ነገድ ሆነው ትውልዷ በሁለቱም በኩል እንዲቈጠር ፈቅደው ይሆናል። የዳን ሰዎች ቀደም ሲል ከፊንቄያውያን ጋር ኅብረት ፈጥረው እንደ ነበር ይታወቃል (መሳ18፥7)።

*2፥17-18* 1ነገ 5፥13-18 እና ማብ ይመ። የግዳጁን ሥራ እንዲሠሩ የተፈለጉት ሰዎች እስራኤላውያን ሳይሆኑ፣ በምድሪቱ የሚኖሩት መጻተኞች መሆናቸውን ጸሓፊው ለይቶ ዘግቦታል፤ 1ነገ 9፥20-22 መጻተኞች፣ በጕልበት ሥራ ላይ መሰማራታቸውን ቢያረ ጋግጥም (8፥8ይመ) ይህ በመጽሐፈ ነገሥት በሚገኘው ተጓዳኝ ምንባብ

አምሳ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ሆነ::
18ከእንዚህም ሰባ ሺውን ተሸካሚዎች፣ ሰማንያ
ሺውን በኰረብታው ላይ ድንጋይ ፈላጮች፣
ሦስት ሺህ ስድስት መቶውን ደግሞ የሥራው
ተቈጣጣሪዎች ሆነው ሰዎቹን እንዲያሠሩ
መደበ::

### ሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሠራ

3፥1-14 ተን ምብ —1ነገ6፥1-29

3ሰሎሞንም በኢየሩሳሌም እግዚአብሔር
ለአባቱ ለዳዊት በተገለጠበት በሞሪያ
ተራራ ላይ በኢያቡሳዊው በኦርና ዐውድማ
ዳዊት ባዘጋጀው ቦታ የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስ መሥራት ጀመረ:: 2በነገሠም በአ
ራተኛው ዓመት፣ በሁለተኛው ወር፣ በሁለ
ተኛው ቀን ቤተ መቅደሱን መሥራት ጀመረ::
3ሰሎሞን ለሕንጻው የጣለው መሠረት
በቀድሞው ስፍር ልክ ርዝመቱ ስድሳ ክንድ፣
ወርዱም ሃያ ክንድ[ሸ] ነበር:: 4በቤተ መቅደሱ
መግቢያ በር ላይ ያለው በረንዳ[ቀ] ርዝመቱ
በቤተ መቅደሱ ወርድ ልክ ሃያ ክንድ ሲሆን፣
ከፍታውም ሃያ[በ] ክንድ ነበር::
ውስጡንም በንጹሕ ወርቅ ለበጠው::
5የቤተ መቅደሱን ዋና ክፍል በጥድ እንጨት
አልብሶ በተጣራ ወርቅ ለበጠው፤ የዘንባባና
የሰንሰለት አምሳልም ቀረጸበት:: 6ቤተ መቅደ
ሱን በከበረ ድንጋይ አስጌጠው፤ የተጠቀመ
በትም ወርቅ የፈርዋይም ወርቅ ነበር::7የጣ
ራውን ተሸካሚዎች፣ መቃኖችን፣ የቤተ
መቅደሱን ግድግዳና መዝጊያዎች በወርቅ
ለበጠ፤ በግድግዳዎቹም ላይ የኪሩቤልን ምስል
ቀረጸ::
8እንደዚሁም ቅድስተ ቅዱሳኑን ሠራ፤
ርዝመቱ ከቤተ መቅደሱ ወርድ ጋር እኩል
ሲሆን፣ ርዝመቱ ሃያ ክንድ፣ ስፋቱም ሃያ
ክንድ ነበር፤ ውስጡንም በስድስት መቶ[ተ]
መክሊት የተጣራ ወርቅ ለበጠው:: 9የወርቅ
ምስማሮቹም አምሳ[ቸ] ሰቅል ይመዝኑ ነበር፤
የላይኛውንም ክፍሎች እንደዚሁ በወርቅ
ለበጠ::
10በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ የሁለት ኪሩቤል
ምስል አስቀርጾ በወርቅ ለበጣቸው:: 11ከዳር
እስከ ዳር ጉጥም የተዘረጋው የኪሩቤል ክንፍ
በጠቅላላው ሃያ ክንድ ነበር፤ የመጀመሪያው
ኪሩብ አንዱ ክንፍ አምስት ክንድ[ኀ] ሆኖ
የቤተ መቅደሱን ግድግዳ ሲነካ፣ ሌላው
አምስት ክንድ የሆነው ክንፉ ደግሞ የሁለ
ተኛውን ኪሩብ ክንፍ ይነካ ነበር:: 12እንደ
ዚሁም የሁለተኛው ኪሩብ አንዱ ክንፍ
አምስት ክንድ ሆኖ በአንጻሩ ያለውን የቤተ
መቅደስ ግድግዳ ሲነካ፣ አምስት ክንድ
የሆነው ሌላው ክንፉ ደግሞ የመጀመሪ
ያውን ኪሩብ ክንፍ ይነካ ነበር:: 13የተዘረጋው
የእነዚህ ኪሩቤል ክንፍ ሃያ ክንድ ሲሆን፣
ፊታቸውን ወደ ቤተ መቅደሱ ዋና ክፍል
አዙረው[ነ] በእግራቸው ቆመዋል::
14ደግሞም ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከደ
ማቅ ቀይ ፈትልና ከቀጭን በፍታ መጋረጃ
ሠርቶ፣ የኪሩቤልን ምስል በጥልፍ ጠለፈበት::
15በቤተ መቅደሱም ፊት ለፊት በአንድነት
ቁመቱ ሠላሳ አምስት ክንድ[ኘ] የሆነ፣ በእያ
ንዳንዱም ላይ አምስት ክንድ ጕልላት ያለው
ሁለት ዐምድ ሠራ::

2፥18 1ዜና22፥2፤ 2ዜና8፥8
3፥1 ዘፍ28፥7፤ 2ሳሙ24፥18፤ ሐሥ7፥47
3፥2 ዕዝ5፥11
3፥3 ሕዝ41፥2
3፥5 ሕዝ40፥16
3፥7 ዘፍ3፥24፤ ሕዝ41፥18
3፥8 ዘፀ26፥33
3፥9 ዘፀ26፥32
3፥10 ዘፀ25፥18
3፥13 ዘፀ25፥18
3፥14 ዘፍ3፥24፤ ዘፀ26፥31:33
3፥15 1ነገ7፥15: 22፤ ራእ3፥12

[ሸ]3 ርዝመቱ 27 ሜትር ወርዱ 9 ሜትር ያህል ነው::
[ቀ]4 በዚህና በቍጥር 8:11 እንዲሁም 13 ላይ 9 ሜትር ያህል ነው::
[በ]4 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞችና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጥ ግን አንድ መቶ ሃያ ይላል::
[ተ]8 21 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው::
[ቸ]9 0.6 ኪሎ ግራም ያህል ነው::
[ኀ]11 በዚህና በቍጥር 15 ላይ 2.3 ሜትር ያህል ነው::
[ነ]13 ወይም፣ *ወደ ቤተ መቅደሱ እያዩ* ተብሎ መተርጐም ይቻላል::
[ኘ]15 16 ሜትር ያህል ነው::

ውስጥ አልተጠቀሰም::

2፥18 *ሦስት ሺ ስድስት መቶውን ... የሥራው ተቈጣጣሪዎች፤* ቍ2 ይመ:: ይህን በተመለከተ በ1ነገ5፥16 ላይ የተሰጠው ቍጥር 3300 ነው፤ ይሁን እንጂ በአንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች የተጠቀሰው 3600 ነው:: እዚህ ላይ ጸሓፊው በወቅቱ ከነበረው የማሶሬቲክ ቅጅ የተወሰደውን የተለየ የመጽሐፈ ነገሥት ምንባብ ሳይከተል አልቀረም፤ ይሁን እንጂ (የ1ነገ.5፥16 ማብ ይመ)::

*3፥1-17፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በመጽሐፈ ነገሥት ውስጥ በሰፋት የተገለጸውን የቤተ መቅደሱን ግንባታ ታሪክ በተለይም በ1ነገ6፥4-20 ላይ ያለውን ፈጽሞ በመተው አሳጥሮ አቅርቦአል:: ታሪኩ በአጭሩ መጻፉ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ የተሠራው ቤተ መቅደስ ሰሎሞን ካሠራው ከመጀመሪያው ቤተ መቅደስ ጋር ሲነጻጸር እጅግ የሚያንስ (ሐጌ 2፥3) መሆኑን ተደራስያኑ በዝርዝር የሚያውቁ መሆናቸውን ይጠቍማል:: በሌላ በኩል ደግሞ ጸሓፊው በመቀጠል ስለ ቤተ መቅደሱ ጌጣጌጦችና መገልገያ ዕቃዎች በዝርዝር ይገልጻል (3፥6-9፤4፥1፡6-9 )::

3፥1 *በሞሪያ ተራራ፤* በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የጽዮን ተራራ ማለት የሞሪያ ተራራ ማለት እንደሆነ በግልጽ የተነገረው እዚህ ክፍል ላይ ብቻ ነው:: አብርሃም ልጁን ይስሐቅን እንዲሠዋበት የታዘዘውም በዚሁ ተራራ ላይ ነበር (ዘፍ 22፥2፡14):: *ዳዊት ባዘጋጀው ቦታ፤* 1ዜና 21፥18-22፥1 ይመ::

3፥2 *በአራተኛው ዓመት በሁለተኛው ወር፤* በ1966 ዓ.ቅ.ክ በጸደይ ወራት ማለት ነው (የ1ነገ 6፥1 ማብ ይመ)::

3፥4 *ለበጠው፤* ወይም "ከውስጥ ለበጠው" ቢባል ትክክለኛውን ሥዕላዊ መግለጫ ሊሆን ይችላል፤ ይኸውም ውስጡ ሙሉ በሙሉ ሳይሆን፣ የዘንባባውና የሰንሰለቱ ቅርጽ ያረፈበት ክፍል ከወርቅ በተሠራ ቅጠል መለበጡን ያመለክታል (ቍ5)::

3፥6 *የፈርዋይም፤* ወርቁ የመጣበትን ቦታ ስም (ደቡብ ምሥራቅ ዐረብ ሊሆን ይችላል) ወይም በዓይነቱ ከሌላው ሁሉ ብልጫ ያለውን ንጹሕ ወርቅ ያመለክታል::

3፥7 *የኪሩቤልን፤* ቍ10-14 እንዲሁም የዘፍ3፥24፤ የሕዝ1፥5 ማብ ይመ::

3፥8 *ርዝመቱ ሃያ ክንድ፣ ስፋቱም ሃያ ክንድ፤* ከፍታውም ሃያ ክንድ ነበር (1ነገ6፥20)፤ ይህም የቅድስተ ቅዱሳኑን ስፋት፣ ርዝመትና ከፍታ እንደ መገናኛው ድንኳን ሁሉ እኩል ያደርገዋል:: አዲሲቱ ኢየሩሳሌምም እንደዚሁ ስድስት ማዕዘን ያላት ትሆናለች (ራእ21፥16)፤ ከተማዋ በሙሉ "ቅድስተ ቅዱሳን" ስለ ምትሆንም ቤተ መቅደስ አያስፈልጋትም (ራእ 21፥22)::

3፥9: *የወርቅ ምስማሮቹም፤* በመሠረቱ ወርቅ እንደ ብረት ጠንካራ ማዕድን ባለመሆኑ ምስማር ከወርቅ ይሠራል ማለቱ ይከብዳል፤ ይህ ክብደቱ ወደ ስድስት መቶ ግራም የሚሆን አነስተኛ ወርቅ (አማራጭ ትርጉሙን ይመ)የወርቅን ቅጠል የምስማር ራስ መለበጫን የሚወክል ሊሆን ይችላል::

*3፥10-13* 1ነገ6፥23-27 እና ማብ ይመ::

3፥14: *መጋረጃ፤* ሁለቱን የመገናኛ ድንኳን ክፍሎች የሚለያይ ነው (ዘፀ 26፥31):: ከእንጨት የተሠሩ በሮችም ሊኖሩት ይችላል (4፥22፤1ነገ 6፥31-32፤ እንዲሁም ከማቴ 27፥51፤ ከዕብ 9፥8 ጋር ያነጻጽሩ)::

3፥15 *በአንድነት ቍመቱ ሠላሳ አምስት ክንድ የሆነ፤* "በአንድነት" የሚለው ቃል መጨመሩ ዐሥራ ስምንት ክንድ ተብሉ በ1ነገ 7፥15 ላይ ከተጠቀሰው ጋር ለማጣጣም ሊሆን ይችላል፣ ይህም በ2ነገ 25፥17 (አማራጭ ትርጕም ይመ) እና በኤር 52፥21 ላይ ተረጋግጦአል፤ የሰብ ሊቃናቱ ትርጕም ግን በኤር 52፥21 ላይ ሠላሳ አምስት ክንድ ቢልም ይህ ከቅጁ የገለበጡ ሰዎች ስሕተት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል::

3፥17: *ዐምዶቹንም፤* እንዲህ ዐይነት የዓምዶች ቅሬታ በፓሊስቲና በተደረጉት የብዙ ቤተ መቅደስ የሥን ቅርስ ቍፋሮዎች

[16]እርስ በርሳቸው የተጠላለፉ ሰንሰለቶች
ሠርቶ[ሀ] ከዐምዶቹ ጫፍ ጋር አገናኛቸው፤
ከዚያም መቶ የሮማን ፍሬዎች ሠርቶ
ከሰንሰለቶቹ ጋር አያያዛቸው::
[17]ዐምዶቹንም አንዱን በደቡብ፣ ሌላውን
በሰሜን አድርጎ በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት
አቆማቸው፤ በደቡብ በኩል ያለውን፤ "ያኪን"፣[ለ]
በሰሜን በኩል ያለውንም "ቦዔዝ"[ሐ] ብሎ
ጠራቸው::

## የቤተ መቅደሱ ዕቃዎች መሟላት

4፥2-6፡10-5፥1ተጓ ምብ—1ነገ 7፥23-26፡38-51

4 ርዝመቱ ሃያ ክንድ፣ ወርዱ ሃያ ክንድ፣
ቁመቱ ዐሥር ክንድ[መ] የሆነ የናስ መሠ
ዊያ ሠራ:: [2]እንዲሁም የጐኑ ስፋት ከጠ
ርዝ እስከ ጠርዝ ዐሥር ክንድ፣ ቁመቱ
አምስት[ሠ] ክንድ የሆነ ክብ በርሜል ቀልጠ
ከፈሰሰ ብረት ሠራ፤ ዙሪያውም ሲለካ ሠላሳ
ክንድ[ረ] ሆነ። [3]ከበርሜሉ ከንፈር በታችም
በእያንዳንዱ ክንድ ርቀት ላይ ዙሪያውን
ዐሥር የኮርማ ቅርጾች[ሰ] ነበሩበት፤ ኮር
ማዎቹም ከበርሜሉ ጋር አንድ ወጥ ሆነው
በሁለት ረድፍ ቀልጠው ተሠርተው ነበር::
[4]በርሜሉ በዐሥራ ሁለት ኮርማዎች ላይ
የቆመ ሲሆን፣ ኮርማዎቹም ሦስቱ ወደ
ሰሜን፣ ሦስቱ ወደ ምዕራብ፣ ሦስቱ ወደ
ደቡብ፣ ሦስቱ ወደ ምሥራቅ ይመለከቱ
ነበር:: በርሜሉ በእነዚህ ላይ ያረፈ ሲሆን፣
የሁሉም ጀርባ ወደ መካከል የዞረ ነበር::
[5]የበርሜሉ ውፍረት አንድ ስንዝር፣[ሸ] ከንፈሩ
ደግሞ የጽዋ ከንፈር ወይም የሱፍ አበባ
ይመስል ነበር፤ ይህም ሦስት ሺህ የባዶስ
መስፈሪያ[ቀ] የሚይዝ ነበር::
[6]እንዲሁም ዐሥር የመታጠቢያ ገንዳዎች
አሠርቶ አምስቱን በደቡብ፣ አምስቱን ደግሞ
በሰሜን በኩል አስቀመጠ፤ ገንዳዎች ለሚ
ቃጠል መሥዋዕት የሚቀርቡት ነገሮች የሚ
ታጠቡባቸው ሲሆኑ፣ በርሜሉ ግን ለካህ
ናት መታጠቢያ የሚያገለግል ነበር::
[7]በተሰጠው የአሠራር መመሪያ መሠረት፣

3፥16 1ነገ7፥17፡29
4፥1 ዘፀ20፥24፤ 40፥6፤1ነገ8፥64
4፥2 ራእ4፥6፤15፥2
4፥4 ዘኍ2፥3-25፤ሕዝ48፥30-34፤ራእ21፥13
4፥6 ዘፀ30፥18፤ ነህ13፥5፡9፤ ሕዝ40፥38
4፥7 ዘፀ25፥31፡40
4፥8 ዘፀ 25፥23፤ዘኍ4፥14
4፥9 1ነገ6፥36፤ 2ዜና33፥5
4፥11 1ነገ7፥14
4፥14 1ነገ7፥27-30
4፥16 1ነገ7፥13

ዐሥር የወርቅ መቅረዞች ሠርቶ ወደ ቤተ
መቅደሱ በማስገባት፣ አምስቱን በስተደቡብ፣
አምስቱን በስተሰሜን አኖራቸው::
[8]ዐሥር ጠረጴዛ ሠርቶም ወደ ቤተ መቅደሱ
በማስገባት አምስቱን በስተ ደቡብ፣ አምስ
ቱን ደግሞ በስተ ሰሜን በኩል አኖራቸው፤
ደግሞም አንድ መቶ ጐድጓዳ የወርቅ ሳሕ
ኖች ሠራ::
[9]የካህናቱንም አደባባይ ሠራ፣ እንዲሁም
ታላቁን አደባባይና በሮቹን ከሠራ በኋላ
በናስ ለበጣቸው:: [10]በርሜሉንም ከቤተ መቅ
ደሱ በስተደቡብ ምሥራቅ ባለው ማዕዘን
በቀኝ በኩል አኖረው::
[11]እንዲሁም ምንቸቱን፣ መጫሪያዎችንና
ጐድጓዳ ሳሕኖችን ሠራ:: ኪራምም ለቤተ
መቅደሱ አገልግሎት የሚውሉትን ዕቃዎች
ለንጉሥ ሰሎሞን ሠርቶ ጨረሰ፤ እነዚህም
[12]ሁለቱ ዐምዶች፣
በአዕማዱ ጫፍ ላይ ያሉት
ሁለት ባለ ሳሕን ቅርጽ ጒልላት
በዐምዶቹ ላይ ያሉትን ሁለቱን፣
ባለ ሳሕን ቅርጽ ጒልላት
የሚያስጌጡ ሁለት ዙር መርበቦች፤
[13]በዐምዶቹ ላይ ያሉትን ሁለቱን፣
ባለሳሕን ቅርጽ ጒልላት እንዲያስጌጡ
ለያንዳንዱ መርበብ ሁለት ዙር ሮማኖች
ለሁለቱም ዙር መርበቦች
በድምሩ አራት መቶ ሮማኖች፤
[14]መቆሚያዎች ከነመታጠቢያ ሳሕኖቻቸው፤
[15]በርሜሉና እርሱን የተሸከሙት ዐሥራ
ሁለት ኮርማዎች፤
[16]ምንቸቶችና መጫሪያዎች ፣

[ሀ]16 ወይም፣ *በቤተ መቅደሱ ውስጥ ሰንሰለት ሠርቶ* ተብሎ መተርጐም ይችላል፤ በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
[ለ]17ምናልባት *ያኪን* ማለት *እርሱ ለነጸ* ማለት ሊሆን ይችላል::
[ሐ]17ምናልባት *ቦዔዝ* ማለት *ብርታት በእርሱ ውስጥ ነው* ማለት ሊሆን ይችላል::
[መ]1ርዝመቱና ወርዱ 9 ሜትር ቍመቱ 4.5 ሜትር ያህል ነው::
[ሠ]2 2.3 ሜትር ያህል ነው::
[ረ]2 13.5 ሜትር ይህል ነው::
[ሰ]3 0.5 ሜትር ያህል ነው::
[ሸ]5 8 ሳንቲ ሜትር ያህል ነው::
[ቀ]5 66 ኪሎ ሊትር ያህል ነው::

ተግኝተዋል (ከራእ 3፥12 ጋር ያነጻጽሩ):: *ያኪን.. ቦዔዝ፤* አማራጭ ትርጒሙን፤ ይመ

4፥1 *የናስ መሠዊያ፤* በመጽሐፈ ነገሥት የሚገኘው የዚህ ክፍል ተጓዳኝ ምንባብ (1ነገ 7፥22-23) ዋናውን የቤተ መቅደሱን መሠዊያ አይጠቅስም፤ ሌሎች የመጽሐፈ ነገሥት ምንባቦች (1ነገ 8፥64፤ 9፥25፤2ነገ 6፥14) ግን ይጠቅሱታል ::

4፥2 *በርሜል፤* በመገናኛው ድንኳን ይገለገሉበት የነበረውን ጐድጓዳውን የናስ መታጠቢያ የሚተካ ነው (ዘፀ 30፥18)፤ ይህም ካህናቱ የመንጻት ሥርዐት ለማከናወን የሚጠቀሙበት ነበር (ቍ6፤ ዘፀ 30፥21):: የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይህን ሥርዐት የሚመለከቱት በክርስቶስ ላገኘነው መንጻት እንደ ጥላ አድርገው ነው (ቲቶ 3፥5፤ ዕብ 9፥11-14):: ሕዝቅኤል በራእዩ ባየው ቤተ መቅደስ፣ በደቡብ በኩል ከቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ያለው በርሜል (ቍ 10) ከቤተ መቅደሱ በስተደቡብ በሚፈሰው ሕይወት ሰጭ ወንዝ ተተክቶአል (ሕዝ 47፥1-12፤ እንዲሁም ከኢል3፥18፤ ከዘካ 14፥8፤ ከዮሐ4፥9-15፤ ከራእ 22፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ)::

4፥3 *ኮርማዎቹም፤* በ1ነገ 7፥24 ላይ "ቅል" ተብሎአል፤ ዕብራይስጡ ኮርማም ሆነ ቅል ለማለት የሚጠቀምበት ቃል ተመሳሳይ ነው:: ልዩነት ሊኖር የቻለው ግን ጥንት መጽሐፉ ከአንዱ ቅጅ ወደ ሌላው ሲገለበጥ ከተፈጸመው ስሕተት የተነሣ ሊሆን ይችላል::

4፥4 *በዐሥራ ሁለት ኮርማዎች፤* ዐሥራ ሁለቱን የእስራ ኤል ነገዶች ሊያመለክቱ ይችላሉ፤ እነዚሁ እስራኤላውያንም በምድረ በዳ ይጓዙ በነበሩ ጊዜ (ዘኍ2፤ ከሕዝ 48፥30-35 ጋር ያነጻጽሩ) ከአራት ቦታ ተከፍለው ሦስት ሦስቱ ነገድ በየድንኳኑ ማዕዘን ይሰፍሩ ነበር::

4፥5 *ሦስት ሺ የባዶስ መስፈሪያ፤* በ1ነገ 5፥26 ላይ የተጻፈው ግን ሁለት ሺህ የባዶስ መስፈሪያ ተብሎአል፤ ይህም በዚያን ጊዜ የነበሩት ጸሐፊዎች ሲያነቧቸው ተመሳሳይ በመሆናቸው በቀላሉ እንዲሳሳቱ ሳያደርጋቸው እንዳልቀረ ይገመታል::

4፥6 *ዐሥር የመታጠቢያ ገንዳዎች፤* 1ነገ7፥38-39 ይመ::

4፥7 *ዐሥር የወርቅ መቅረዞች፤* በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በነበረው በአንዱ ምትክ ማለት ነው (ዘፀ25፥31-40):: *የአሠራር መመሪያ፤* 1ዜና 28፥15 ይመ:: እነዚህ መቅረዞች በዘፀ25፡31-40 ላይ ከተገለጹት ይልቅ በዘካ 4፥2-6 ከተጠቀሰው የመቅረዝ ዓይነት ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው::

4፥8 *ዐሥር ጠረጴዛ፤* በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ግን አንድ ብቻ ነበር ዘፀ25፥23-30፤40፥4፤ ዘሌ 24፥5-9፤ 1ሳሙ 21፥1-6፤ ሕዝ 41፥22፤ ዕብ 9፥2:: እንዲሁም ከ2ዜና 13፥11፤ 29፥18 ጋር ያነጻጽሩ)::

*4፥11-16፤* 1ነገ 7፥40-45 ይመ::

*4፥17-22፤* 1ነገ 7፥46-50 ይመ::

4፥17 *በሸክላ ቅርጽ፤* በዮርዳኖስ ሜዳ ያለው የሸክላ ዐፈር

ሚንጦዎችና ከሌሎችም ጋር የተያያዙ ዕቃዎች።
ኪራምአቢ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
መገልገያ እንዲሆን ለሰሎሞን የሠራቸው ዕቃዎች
በሙሉ ከተወለወለ ናስ የተሠሩ ነበሩ።
[17]ንጉሡም እነዚህ ዕቃዎች በዮርዳኖስ ሸለቆ፣
በሱኮትና በጽሬዳ መካከል ባለው በሸክላ ዐፈር
ቦታ ቀልጠው በሸክላ ቅርጽ ተሠርተው እንዲ
ወጡ አደረገ። [18]እነዚህ ሰሎሞን ያሠራቸው
ነገሮች ሁሉ እጅግ ብዙዎች ስለ ሆኑ የናሱ
ክብደት ምን ያህል እንደሆነ አልታወቀም
ነበር።
[19]እንደዚሁም ሰሎሞን በእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ መገልገያ የሚሆኑትን ዕቃዎች ሠራ፤
እነዚህም፦
የወርቅ መሠዊያ፣
የገጸ ኅብስቱ ጠረጴዛ፣
[20]በተሰጠው መመሪያ መሠረት፣ በቅድስተ
ቅዱሳኑ ፊት ለፊት እንዲነድዱ፣ ከንጹሕ ወርቅ
የተሠሩ መቅረዞች ከነቀንዲሎቻቸው፣
[21]የወርቅ አበባ ቅርጽ ሥራዎች፣
ቀንዲሎችና መኮስተሪያዎች ከንጹሕ ወርቅ
የተሠሩ ነበሩ።
[22]ከንጹሕ ወርቅ የተሠሩ የመብራት ማጥፊ
ያዎች፣ ለመርጨት የሚያገለግሉ ጐድጓዳ
ሳሕኖች፣ ጭልፋዎችና ጥናዎች፣ እንደ
ዚሁም የቤተ መቅድሱ የወርቅ መዝጊ
ያዎች፣ ይኸውም የቅድስተ ቅዱሳኑ የው
ስጠኛው መዝጊያዎችና የቤተ መቅደሱ
ዋናው አዳራሽ መዝጊያዎች ከንጹሕ ወርቅ
የተሠሩ ነበሩ።

5 ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
የሠራው ሥራ ሁሉ ከተጠናቀቀ በኋላ፣
አባቱ ዳዊት የቀደሰውን ብሩንና ወር
ቁን፣ ዕቃዎቹንም ሁሉ አምጥቶ በእግዚአ
ብሔር ቤተ መቅደስ ግምጃ ቤት አኖራቸው።

## ታቦቱ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ

5፥2-6፥11 ተጓ ምብ— 1ነገ 8፥1-21

[2]ከዚያ በኋላ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን
የኪዳን ታቦት ከዳዊት ከተማ ከጽዮን እንዲ
ያመጡ፣ የእስራኤልን ሽማግሌዎች፣ የየነ
ገዱን መሪዎች ሁሉና የእስራኤላውያንን የቤ
ተሰብ አለቆች በኢየሩሳሌም ሰበሰበ። [3]የእስራ
ኤልም ሰዎች ሁሉ የሰባተኛው ወር በዓል
በሚከበርበት ጊዜ፣ በንጉሡ ፊት ተሰበሰቡ።
[4]የእስራኤል ሽማግሌዎች በተሰበሰቡም ጊዜ
ሌዋውያኑ ታቦቱን አነሡት፤ [5]ታቦቱን፣
የመገናኛ ድንኳኑንና በውስጡ ያሉትን የተ
ቀደሱ ዕቃዎች ሁሉ ይዘው ወደ ላይ ወጡ፤
ሌዋውያን የሆኑ ካህናትም ተሸከሟቸው። [6]ንጉሥ
ሰሎሞንና በአጠገቡ የተሰበሰበው መላው
የእስራኤል ጉባኤ ስፍር ቍጥር የሌላቸውን
በጎችና በሬዎች በታቦቱ ፊት ሠዉ።
[7]ካህናቱም የእግዚአብሔርን የኪዳኑን ታቦት
የቤተ መቅደሱ ውስጠኛ ክፍል ወደ ሆነው
ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ አግብተው ከኪሩቤል
ክንፍ በታች ባለው ስፍራው አኖሩት። [8]ኪሩ
ቤልም ክንፎቻቸውን ከታቦቱ በላይ ባለው
ስፍራ ላይ ዘርግተው፣ ታቦቱንና መሎጊያ
ዎቹን ሸፈኑ። [9]መሎጊያዎቹም በጣም ረጃጅም
ከመሆናቸው የተነሣ፣ ታቦቱ እስካ ለበት ድረስ
ያሉት ጫፎቻቸው ከቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት
ለፊት ይታዩ ነበር፤ ከመቅደሱ ውጭ ግን
አይታዩም ነበር፤ ዛሬም እዚያው ቦታ ይገኛሉ።
[10]እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡ በኋላ ከእነርሱ
ጋር ኪዳን ባደረገ ጊዜ፣ ሙሴ በኮሬብ ተራራ
በውስጡ ካስቀመጣቸው ከሁለቱ ጽላቶች
በቀር በታቦቱ ውስጥ ምንም አልነበረም።
[11]ካህናቱም ከቤተ መቅደሱ ወጡ፤ እዚያ
የነበሩት ካህናት በምድባቸው መሰረት
ባይሆንም፣ ሁሉም ራሳቸውን ቀድሰው ነበር።
[12]መዘምራን የነበሩት ሌዋውያን ሁሉ፣ አሳፍ፣
ኤማን፣ ሄማንና ኤዶታም፣ ወንዶች ልጆቻ
ቸውና የሥጋ ዘመዶቻቸው ሁሉ ያማረ
ቀጭን በፍታ ለብሰው፣ ከመሠዊያው በስተ
ምሥራቅ በኩል ቆመው ጸናጽል ይጸነጽሉ፣
በገና ይደረድሩና መሰንቆ ይመቱ ነበር፤
እነርሱም መለከት በሚነፉ አንድ መቶ ሃያ
ካህናት ታጅበው ነበር፡ [13]መለከት ነፊዎችና
ዘማሪዎችም በአንድነት አንድ ድምፅ ሆነው
ለእግዚአብሔር ውዳሴና ምስጋና አቀረቡ፤
በመለከት፣ በጸናጽልና በሌሎች መሣሪያዎች
ታጅበውም ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ
እግዚአብሔርን እያወደሱ፣
"እርሱ ቸር ነው፣
ፍቅሩም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።"
እያሉ ዘመሩ።
ከዚያም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በደመና

4፥17 ዘፍ33፥17
4፥18 1ነገ7፥23
4፥19 ዘፀ25፥23
4፥20 ዘፀ25፥31
4፥22 ዘሌ10፥1፤ ዘኍ7፥14
5፥1 2ሳሙ8፥11፤ 1ነገ6፥14
5፥2 ዘኍ3፥31፤ 1ዜና15፥25
5፥3 1ዜና9፥1
5፥5 ዘኍ3፥31፤ 1ዜና15፥2
5፥7 ራእ11፥19
5፥8 ዘፍ3፥24
5፥10 ዘፀ16፥34፤ ዘዳ10፥2፤ዕብ9፥4
5፥11 1ዜና24፥1
5፥12 1ነገ10፥12፤ 1ዜና9፥33፤13፥8፤፣2 5፥1፤መዝ68፥25
5፥13 ዘፀ40፥34፤ 1ዜና16፥34፤2ዜና7፥ 3፤20፥21፤ዕዝ3፥11፤ መዝ100፥5 106፥1፤107፥1፤118፥ 1፤136፥1፤ኤር33፥11

ከምችት፣ እነዚህን የናስ ዕቃዎች አቅልጦ መሥራት አመቺ ሁኔታ ፈጥሮአል።

*5፥1 አባቱ ዳዊት የቀደሰውን፤* የ1ዜና18፥1-20፥8፤22፥2-16፤29፥2-5 ማብ እንዲሁም 1ዜና 26፥26 ይመ።

*5፥2-14፤* 1 ነገ8፥1-11 እና ማብ ይመ።

*5፥2፤ ታቦት፤* ታቦቱ በዳዊት ወደ ኢየሩሳሌም ከመወሰዱ አስቀድሞ ከአርባ ዓመት በፊት በተዘጋጀለት ድንኳን ውስጥ ይኖር ነበር (1ዜና15፥1-16፥6)።

*5፥3 የሰባተኛው ወር በዓል በሚከበርበት ጊዜ፤* የዳስን በዓል ያመለክታል። ወሩ ከነዓናውያን ኢታኒም ብለው ባወጡለት ስም ይጠራል (1ነገ8፥2)፤ በዕብራይስጥ ቲሽሪ ይባላል። እንደ 1ነገ 6፥38 ከሆነ፣ የቤተ መቅደሱ ሕንጻ ሥራ የተጠናቀቀው 959 ዓ.ቅ.ክ ከመስከረም እስከ ጥቅምት ነበር። ይህም የሆነው ሰሎሞን በነገሠ በ11ኛው ዓመት በ8ኛው ወር ነው። የምረቃው በዓል የተከበረው አንድም የቤተ መቅደሱ ሕንጻ ሥራ ከመጠናቀቁ ከአንድ ወር በፊት ያለዚያም ከተጠናቀቀ ከአሥራ አንድ ወር በኋላ ነው የሚል ግምት አለ፤ ምናልባትም ለኋለኛው ግምት ክብደት ሳይሰጠው አልቀረም የ(1ነገ8፥2 ማብ ይመ)።

*5፥6 ዳዊት ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ማምጣቱን ከዚህ* ጋር ያነጻጽሩ 1ዜና 15፥26፤16፥1-3)።

*5፥9 ዛሬም እዚያው ቦታ ይገኛሉ፤* የ1ነገ8፥8 ማብ፤ እንዲሁም 8፥8፤10፥19፤20፥26፤21፥10፤35፥25፤1ዜና4፥41፡43፤5፥26፤13፥11፤17፥5 ይመ።

5፥10 ከሁለቱ ጽላቶች፤ ዘፀ.31፥18 እና ማብ ፤ እንዲሁም ዘፀ 32፥15-16 ይመ። ታቦቱ ከዚያ ቀደም ብሎ መና ያለበትን የወርቅ ማድጋ ( ዘፀ16፥32-34፤) እና የአሮን በትር (ዘኍ17፥10-11፤ዕብ 9፥4) በውስጡ ይዞ ነበር። እነዚህ ነገሮች ምናልባትም ታቦቱ በፍልስጥኤማውያን እጅ በነበረበት ጊዜ ሳይጠፉ አይቀርም።

5፥12 *ያማረ ቀጭን በፍታ፤* 1ዜና 15፥27 እና ማብ ይመ።

5፥14 *የእግዚአብሔር ክብር....ከደመናው፤* ከ7፥1-3 ጋር ያነጻጽሩ። የክብሩ ደመና እግዚአብሔር በዚያ መገኘቱን ያመ

ተሞላ:: 14*የእግዚአብሔር* ክብር የአምላክን ቤተ
መቅደስ ሞልቶት ስለነበር፣ ከደመናው የተነሣ
ካህናቱ አገልግሎታቸውን ማከናወን አልቻሉም::
6 ከዚያም ሰሎሞን እንዲህ አለ፤ "*እግዚ
አብሔር* ጥቅጥቅ ባለ ደመና ውስጥ እንደ
ሚኖር ተናግሮአል፤ 2እኔም አንተ ለዘላለም
ትኖርበት ዘንድ፣ ይህን ታላቅና ድንቅ ቤተ
መቅደስ ሠራሁልህ::"
3መላው የእስራኤል ጉባኤ እዚያው ቆመው
ሳሉ፣ ንጉሡ ዞሮ ባረካቸው፤ 4እንዲህም አለ፤
"ለአባቴ ለዳዊት በቃሉ የሰጠውን
ተስፋ በእጁ የፈጸመ የእስራኤል *አምላክ*
እግዚአብሔር ይመስገን፤ እንዲህ ብሎአልና፤
5 'ሕዝቤን ከግብፅ ካወጣሁበት ጊዜ ጀምሮ፣
ስሜ የሚጠራበት ቤተ መቅደስ ይሠራ
በት ዘንድ ከማናቸውም የእስራኤል ነገድ
ከተሞች አንድም አልመረጥሁም፤ ወይም
የሕዝቤ የእስራኤል መሪ ይሆን ዘንድ ማንንም
አልመረጥሁም:: 6አሁን ግን ስሜ በዚያ
እንዲሆን ኢየሩሳሌምን፣ ሕዝቤን እስራ
ኤልን እንዲገዛም ዳዊትን መርጫለሁ::"
7"አባቴ ዳዊት፣ ለእስራኤል አምላክ *ለእግ
ዚአብሔር* ስም ቤተ መቅደስ ለመሥራት
በልቡ አስቦ ነበር፤ 8*እግዚአብሔር* ግን፣
ለአባቴ ለዳዊት እንዲህ አለው፤ 'ለስሜ
ቤተ መቅደስ ለመሥራት በልብህ አስበህ
ነበር፤ ይህን በልብህ በማሰብህ መልካም
አድርገሃል፤ 9ይሁን እንጂ ቤተ መቅደሱን
የምትሠራው አንተ አይደለህም፤ ለስሜ ቤተ
መቅደስ የሚሠራልኝ ከአብራክህ የሚከፈለው፣
የገዛ ልጅህ ነው::'
10"*እግዚአብሔርም* የተናገረውን ቃል ፈጽሞ
አል፤ እኔም *እግዚአብሔር* በሰጠው ተስፋ
መሠረት በአባቴ በዳዊት እግር ተተክቼ፣
በእስራኤል ዙፋን ላይ ተቀምጫለሁ፤ ለእስ
ራኤል አምላክ *ለእግዚአብሔርም* ስም ቤተ
መቅደስ ሠርቻለሁ:: 11በዚያም *እግዚአብሔር*
ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገው ኪዳን
ያለበትን ታቦት አኑሬአለሁ::"

## ሰሎሞን በምረቃው ጊዜ ያቀረበው ጸሎት

6፥12-40ተጓ ምብ—1ነገ8፥22-53
6፥41-42ተጓ ምብ—መዝ132፥8-10

12ከዚህ በኋላ ሰሎሞን መላው የእስራኤል
ጉባኤ ባለበት *በእግዚአብሔር* መሠዊያ ፊት
እጆቹን ዘርግቶ ቆመ:: 13ሰሎሞንም ርዝመቱ
አምስት ክንድ፣[ግ] ወርዱ አምስት ክንድ፣ ከፍ
ታውም ሦስት ክንድ[ም] የሆነ የናስ መድረክ
በውጭው አደባባይ መካከል አሠርቶ ነበር፤
በመድረኩም ላይ ወጥቶ በመቆም በመላው
የእስራኤል ጉባኤ ፊት ተንበርክኮ እጆቹን
ወደ ሰማይ ዘረጋ፣ 14እንዲህም አለ፤
"የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
በፍጹም ልባቸው በመንገድህ ከሚሄዱት ባሪ
ያዎችህ ጋር የፍቅር ኪዳንህን የምትጠ
ብቅ በሰማይም ሆነ በምድር እንደ አንተ
ያለ አምላክ የለም፤ 15ለባሪያህ ለአባቴ ለዳዊት
የሰጠኸውን ተስፋ አጽንተሃል፤ በአፍህ
የተናገርኸውን ዛሬም እንደ ሆነው በእጅህ
ፈጽመኸው::
16"አሁንም የእስራኤል *አምላክ* እግዚአብሔር
ሆይ፤ ለባሪያህ ለአባቴ ለዳዊት፣ 'ልጆችህ
'አንተ እንደ አደረግኸው ሁሉ በሚያደርጉት
ሁሉ ሕጌን በመጠበቅ በፊቴ ቢመላለሱ፣
በእስራኤል ዙፋን ላይ በፊቴ የሚቀመጥ
ሰው ከቶ አታጣም' ብለህ የሰጠኸውን ተስፋ
አጽናለት:: 17እንግዲህ የእስራኤል አምላክ
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ለባሪያህ ለዳዊት የሰጠ
ኸው የተስፋ ቃል ይፈጸም::
18"በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር
ላይ ይኖራልን? እነሆ፤ ሰማያትና ሰማየሰ
ማያት እንኳ አንተን ሊይዙህ አይችሉም፤
ታዲያ እኔ የሠራሁት ይህ ቤተ መቅደስማ
ምንኛ ያንስ! 19ይሁን እንጂ እግዚአብሔር
*አምላኬ* ሆይ፤ የባሪያህን ጸሎትና ስለ ምሕ
ረት ያቀረበውን ልመና አድምጥ፤ ባሪያህ
በፊትህ የሚያቀርበውን ጩኸትና ጸሎት ስማ::
20ስምህ እንደሚጠራበት ወደ ተናገርኸው
ወደዚህ ቤተ መቅደስ ዓይኖችህ በቀንም
በሌሊትም የተገለጡ ይሁኑ፤ ባሪያህ ወደዚህ
ስፍራ የሚጸልየውንም ጸሎት ስማ:: 21ባሪ
ያህና ሕዝብህ እስራኤል ወደዚህ ስፍራ በሚ
ጸልዩበትም ጊዜ ልመናቸውን ስማ፤ ከማ
ደሪያህ ከሰማይ ስማ፤ ሰምተህም ይቅር በል::
22አንድ ሰው ባልንጀራውን ቢበድልና
እንዲምል ቢጠየቅ፣ እርሱም መጥቶ በቤተ
መቅደሱ በመሠዊያህ ፊት ቢምል፣ 23ከሰ
ማይ ሆነህ ስማ፤ አድርግም:: በደለኛውን፣
በደሉን በራሱ ላይ አድርገህ እንደ ሥራው
በመክፈል በባሪያዎችህ መካከል ፍረድ::
ንጹሑም በደለኛ አለመሆኑን አስታውቅ፤
እንደ ንጽሕናውም ክፈለው::
24"ሕዝብህ እስራኤል አንተን ከመበደላቸው
የተነሣ በጠላቶቻቸው ፊት ድል ቢሆኑ፣
ወደ አንተ ተመልሰውም በዚህ ቤተ መቅደስ
ውስጥ በፊትህ በመጸለይና ልመናቸውን
በማቅረብ ስምህን ቢጠሩ፣ 25በሰማይ ሆነህ
ስማ፤ የሕዝብህን የእስራኤልን ኀጢአት

5፥14 ዘፀ19፥16፤
29፥43፤ 40፥35፤
ራእ15፥8
6፥1 ዘፀ19፥9
6፥2 ዕዝ6፥12፤
7፥15፤መዝ135፥21
6፥6 ዘፀ20፥24፤
ዘዳ12፥5፤1ዜና28፥4፤
ኢሳ14፥1
6፥7 1ሳሙ10፥7፤
1ዜና17፥2፤
ሐሥ7፥46
6፥11 ዘዳ10፥2፤
መዝ25፥10፤50፥5
6፥13 ነህ8፥4፤
መዝ95፥6
6፥14 ዘፀ8፥10፤
15፥11፤ዘዳ7፥9
6፥15 1ዜና22፥10
6፥16 2ሳሙ7፥13፤
15፤2ዜና23፥3፤
መዝ132፥12
6፥18 መዝ11፥4፤
ኢሳ40፥22፤66፥1፤
ራእ21፥3
6፥20 ዘፀ3፥16፤
ዘዳ12፥11፤2ዜና7፥14
፤30፥20፤መዝ34፥15
6፥21 መዝ51፥1፤
ኢሳ33፥24፤
40፥2፤43፥25፤44፥22
፤55፥7፤ሚክ7፥18
6፥22 ዘፀ22፥11
6፥23 ኢሳ3፥11፤
65፥6፤ማቴ16፥27
6፥24 ዘሌ26፥17

[ግ]13 2.3 ሜትር ይሆል ነው::
[ም]13 1.3 ሜትር ይሆል ነው::

ለክታል:: ደመናው እስራኤላውያን ከግብፅ ሲወጡና በምድረበዳ
ሲጓዙ መርቶአቸዋል፤ ከመገናኛው ድንኳን በላይ ሆኖ ይታይ
ነበር (ዘፀ13፥21-22፤40፥34-38 ይመ፤ እንዲሁም ከሕዝ43፥1-5፤
ከሐጌ2፥9፤ ከዘካ 1፥16፤2፥10፤8፥3 ጋር ያነጻጽሩ)::
*6፥1-11፤* የ1ነገ 8፥12-21 ማብ ይመ::
*6፥8-9፤* ዳዊት በ1ዜና 28፥2-3 ካደረገው ንግግር ጋር ያነጻጽሩ::
*6፥12-21፤* የ1ነገ 8፥22-30 ማብ ይመ
*6፥13፤* ይህ በ1ነገ 8 ላይ አይገኝም:: የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ
ይህን የጻፈው ሰሎሞን "በመሠዊያው ፊት" ቆሞ (ቍ12) የክህነት
አገልግሎት አለመፈጸሙን ግልጽ ለማድረግ ነው የሚሉ አሉ::
*6፥18፤* ከ2፥6 ጋር ያነጻጽሩ::
*6፥22-39፤* የ1ነገ 8፥31-46 ማብ ይመ::
*6፥22-23፤* ዘፀ 22፥10-11፤ ዘሌ6፥3-5 ይመ::
*6፥24-25፤* ዘሌ26፥17፡23፤ ዘዳ 28፥25፡36-37፡48-57፡64፤
ኢሱ7፥11-12 ይመ::
*6፥26-27* ዘሌ26፥19፤ዘዳ 11፥10-15፤28፥18፤22-24ይመ::

ይቅር በል፤ ለእነርሱና ለአባቶቻቸው ወደ
ሰጠሃቸውም ምድር መልሳቸው።
26“ሕዝብህ አንተን ከመበደላቸው የተነሣ፣
ሰማያት ተዘግተው ዝናብ ባይዘንብ፣ አንተ
ስለ አስጨነቅሃቸው ወደዚህ ስፍራ ቢጸልዩ፣
ስምህን ቢጠሩና ከኀጢአታቸው ቢመለሱ፣
27በሰማይ ሆነህ ስማ፤ የባሪያዎችህን የሕዝብህን
የእስራኤልን ኀጢአት ይቅር በል፤ የሚኖሩ
በትን ቀናውን መንገድ አስተምራቸው፤
ለሕዝብህ ርስት አድርገህ በሰጠኸውም ምድር
ላይ ዝናብን ላክ።
28“በምድሪቱ ላይ ራብ ወይም ቸነፈር ወይም
ዋግ ወይም አረማሞ ወይም አንበጣ ወይም
ኩብኩባ በሚወርድባት ጊዜ፣ ወይም ደግሞ
በየትኛውም ከተማቸው ሳሉ ጠላት በሚ
ከባቸው ጊዜ፣ ወይም ማናቸውም አደጋ
ወይም ደዌ በሚደርስባቸው ጊዜ፣ 29ከሕዝ
ብህ ከእስራኤል ማንም ሰው ጭንቀቱና
ሕመሙ ተሰምቶት፣ እጁን ወደዚህ ቤተ
መቅደስ በመዘርጋት ጸሎትና ልመና
ቢያቀርብ፣ 30በሰማይ በማደሪያህ ሆነህ
ስማ፤ ይቅርም በል፤ የሰውን ልብ የምታ
ውቅ አንተ ብቻ ስለ ሆንህ ለእያንዳንዱ
እንደ ሥራው መጠን ክፈለው፤ 31ይህም
ለአባቶቻችን በሰጠሃቸው ምድር በሚኖሩ
በት ጊዜ ሁሉ አንተን እንዲፈሩህና በመ
ንገዶችህ እንዲሄዱ ነው።
32“ከሕዝብህ ከእስራኤል ወገን ያልሆነ ባዕድ
ሰው ስለ ታላቁ ስምህ፣ ስለ ኀያሉ እጅ
ህና ስለ ተዘረጋው ክንድህ ሰምቶ ከሩቅ
አገር በመምጣት ወደዚህ ቤተ መቅደስ
በሚጸልይበት ጊዜ፣ 33በሰማይ በማደ
ሪያህ ሆነህ ስማ፤ የምድር ሕዝቦች ሁሉ
እንደገዛ ሕዝብህ እንደ እስራኤል፣ ስምህን
በማወቅ እንዲፈሩህ፣ የሠራሁትም ይህ
ቤት ስምህ የሚጠራበት ቤት መሆኑን እን
ዲያውቁ ባዕዱ ሰው የሚጠይቅህን ሁሉ
አድርግ።
34“ሕዝብህ አንተ በምትልካቸው ቦታ ሁሉ
ጠላቶቻቸውን ለመውጋት በሚወጡበት
ጊዜ፣ አንተ ወደ መረጥኻት ወደዚህች
ከተማ፣ እኔም ለስምህ ወደ ሠራሁት
ወደዚህ ቤተ መቅደስ ወደ አንተ ቢጸልዩ፣

6፥26 ዘሌ26፥19፤ ዘዳ11፥17፤28፥24፤2ሳሙ1፥21
6፥27 ቍ30፥39፤ 2ዜና7፥14
6፥28 2ዜና20፥9
6፥30 ቍ27፤ 1ሳሙ2፥3፤መዝ7፥9፤44፥21፤ምሳ16፥2፤17፥3
6፥31 ዘዳ6፥13፤ መዝ34፥7፡9፤103፥11፡13፤ምሳ8፥13
6፥32 ዘፀ3፥19፡20፤2ዜና9፥6
6፥33 ዘፀ12፥43
6፥34 ዘዳ28፥7፤ 1ዜና5፥20
6፥36 ዘሌ26፥44፤ 1ነገ8፥46፤ ኢዮ11፥12፤ 15፥14፤መዝ143፥2፤ መክ7፥20፤ኤር9፥5፤13፥23፤17፥9፤ ሮሜ3፥9፤ኤፌ2፥3
6፥37 1ነገ8፥48፤ 2ዜና7፥14፤12፥6፡12፤30፥11፤33፥12፡19፡23፤34፥27፤ 36፥12፤ኢሳ58፥3፤ ኤር24፥7፤29፥13
6፥39 ቍ27፤ 2ዜና30፥9
6፥40 1ነገ8፥29፡52፤ 2ዜና7፥15፤ ነህ1፥6፡11፤መዝ17፥6፤116፥1፤130፥2፤ ኢሳ37፥17
6፥41 1ዜና28፥2፤ መዝ3፥7፤7፥6፤13፥6፤27፥13፤59፥4፤116፥12፤132፥16፤142፥7፤ ኢሳ33፥10
6፥42 መዝ2፥2፤ 89፡24፡2
7፥1 ዘፀ16፥10፤ 19፥18፤ዘሌ9፥24፤ 1ነገ18፥38፤ መዝ26፥8
7፥2 ዘፀ29፥43፤ 40፥35፤1ነገ8፥11
7፥3 1ዜና16፥34፤ 2ዜና5፥13፤ዕዝ3፥11

35ጸሎታቸውንና ልመናቸውን በሰማይ ስማ፤
የጠየቁህንም አድርግላቸው።
36“መቼም የማይበድል ሰው የለምና፣
አንተን በበደሉህ ጊዜ፣ ተቈጥተሃቸው ሩቅ
ወይም ቅርብ ወደ ሆነ አገር በምርኮ ለሚወ
ስዳቸው ጠላት አሳልፈህ ብትሰጣቸው፣
37በተማረኩበት አገር ሆነው የልብ ጸጸት
ተሰምቶአቸው ንስሐ ቢገቡና በምርኮ ሳሉ፣
‘ኀጢአት ሠርተናል፤ በድለናል፤ ክፉ ድርጊ
ትም ፈጽመናል’ ቢሉ፣ 38ተማርከው በሚኖሩ
በትም ምድር ሆነው በፍጹም ልባቸው፣
በፍጹምም ነፍሳቸው ቢመለሱና ለአባቶ
ቻቸው ወደ ሰጠሃቸው ምድር፣ አንተም ወደ
መረጥኻት ከተማና እኔም ለስምህ ወደ ሠራ
ሁት ቤተ መቅደስ ቢጸልዩ፣ 39ጸሎታቸውንና
ልመናቸውን በሰማይ በማደሪያህ ስማ፤
የጠየቁህንም አድርግላቸው። የበደሉህንም
የሕዝብህን ኀጢአት ይቅር በል።
40አሁንም አምላኬ ሆይ፤ በዚህ ስፍራ ወደ
ቀረበው ጸሎት ዓይኖችህ የተገለጡ፣ ጆሮዎ
ችህም የሚያደምጡ ይሁኑ። 41“አሁንም
እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ተነሥ፣ ከኀይልህ
ታቦት ጋር ወደ ማረፊያ ቦታህ ግባ። እግዚ
አብሔር አምላክ ሆይ፤ ካህናትህ ድነትን
ይልበሱ፤ ቅዱሳንህም በቸርነትህ ደስ ይበ
ላቸው። 42እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፤ የቀ
ባኸውን አትተወው፤ ለባሪያህ ለዳዊት ቃል
የገባህለትን ጽኑ ፍቅር አስብ።

## የቤተ መቅደሱ መመረቅ

7፥1-10ተጓ ምብ— 1ነገ8፥62-66

7 ሰሎሞን ጸሎቱን በፈጸመ ጊዜ እሳት
ከሰማይ ወርዶ የሚቃጠለውን መሥዋዕ
ትና ሌላውንም መሥዋዕት በላ፤ የእግዚ
አብሔርም ክብር ቤተ መቅደሱን ሞላው።
2የእግዚአብሔርም ክብር የእግዚአብሔር
ክብር ቤተ መቅደስ ስለ ሞላው ካህናቱ ወደዚያ
መግባት አልቻሉም። 3እስራኤላውያንም ሁሉ
እሳቱ ሲወርድ፣ የእግዚአብሔርንም ክብር
ከቤተ መቅደሱ በላይ ሲያዩ፣ በመተላለፊያው
ወለል ላይ ተንበረከኩ፤ በግንባራቸውም ወደ
መሬት ተደፍተው ሰገዱ፤ እንዲህ እያሉም
ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረቡ፤

*6፥28-31፤* ዘሌ 26፥16፡20፡25-26፤ ዘዳ28፥20-22፡ 27-28፡ 35፡42ይመ።

*6፥32-33፤* አሕዛብ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ለእግዚአብሔር እንደሚሰግዱ ነቢያት ተናግረው ነበር (ኢሳ56፥6-8፤ ዘካ 8፥20-23፤14፥16-21 ይመ እንዲሁም ከመዝ 87 ጋር ያነጻጽሩ)።

*6፥34-35፤* ዘሌ26፥7-8 ይመ። እግዚአብሔር በጦርነት ጊዜ የጸሎት መልስ ስለ መስጠቱ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ደጋግሞ ይገልጻል (ም13፤14፥9-15፤18፥31፤20፥1-29፤25፥5-13፤32፥20-22)።

*6፥36 መቼም የማይበድል ሰው የለምና፤* ኤር13፥23፤ ሮሜ3፥23ይመ። *ሩቅ...አገር በምርኮ፤* 36፥15-20፤ ዘሌ26፥33፡ 44-45፤ ዘዳ 28፥49-52፤2ነገ17፥7-20፤25፥1-21 ይመ።

*6፥40-42፤* የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በመጽሐፈ ነገሥት (1ነገ 8፥50-53) እንደተጻፈው ሰሎሞን ለጸሎቱ መዝጊያ ያደረገውን ክፍል ከመዝ132፥8-10 አምጥቶ እንጻለ ደግሞታል፤ መዝሙሩ ታቦቱ ወደ ቤተ መቅደስ ስለ መግባቱ የሚያወሣ ሲሆን፣ ይህም በዜና መዋዕሉ (2ዜና5፥2-14) ክፍል ለተጻፈው ታሪክ መሪ ሐሳብ ነው። በመጽሐፈ ነገሥት ላይ የቀረበው ጸሎት የሚደመደመው በሙሴ መሪነት ከግብፅ ባርነት ነጻ መውጣትን በማመልከት ሲሆን፣ የዜና መዋዕሉ ጸሎት ግን የሚዘጋው ለዳዊት የተሰጠውን ዘላለማዊ ተስፋ በማሳሰብ ነው።

*7፥1-22* የ1ነገ8፥54-9፥9 እና ማብ ይመ።

*7፥1-3፤* ይህ ክፍል በ1ነገ ም8 ላይ አይገኝም። መሥዋዕቱን እንዲበላ ከሰማይ የወረደውን እሳት ታሪክ በዚህ ክፍል መጨመሩ የመገናኛው ድንኳን በተመረቀ ጊዜ (ዘሌ9፥23-24) እና ዳዊት በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ ላይ መሥዋዕት ባቀረበ ጊዜ (1ዜና 21፥26 እንዲሁም ከ1ነገ 18፥38 ጋር ያነጻጽሩ) እንደሆነ ሁሉ መሥዋዕቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘቱ ምልክት ነው። ቍ1-3 በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ላይ ብቻ የሚገኝ ክፍል ሲሆን፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ፣ ሰሎሞን በዚያ የተሰበሰበውን ሕዝብ መባረኩን ግን የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዘሎታል (1ነገ8፥55-61)።

*7፥1፤ የእግዚአብሔርም ክብር፤* 5፥14 እና ማብ ይመ።

*7፥3፤ እርሱ ቸር ነው... ለዘላለም፤* ቍ6፤5፥13 ይመ።

*7፥6፤* ይህ ክፍል በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ብቻ ተጽፎ የሚገኝ ሲሆን፣ ሌዋውያኑ በተለይም መዘምራኑ የዜና መዋዕሉን

"እርሱ ቸር ነውና፤
ፍቅሩም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።"
እያሉም እግዚአብሔርን አመሰገኑ።
4ከዚህ በኋላ ንጉሡና ሕዝቡ ሁሉ በእግ
ዚአብሔር ፊት መሥዋዕት አቀረቡ። 5ንጉሥ
ሰሎሞንም ሃያ ሁለት ሺህ በሬ፣ መቶ ሃያ
ሺህ በግና ፍየል ሠዋ፤ ንጉሡና ሕዝቡም ሁሉ
በዚህ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቀደሱ።
6ካህናቱም እንደ ሌዋውያኑ፣ ንጉሥ ዳዊት
እግዚአብሔር እንዲወደስበት የሠራውንና "ፍቅሩ
ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል" በማለት እግዚአብሔ
ርን ባመሰገነ ጊዜ የተቀመጠበትን የእግዚአብሔ
ርን የዜማ መሣሪያ ይዘው በተመደቡላቸው ስፍራ
ቆሙ። ካህናቱ በሌዋውያኑ ትይዩ ሆነው
መለከቶቻቸውን ሲነፉም እስራኤላውያን ሁሉ
ቆመው ነበር።
7ሰሎሞን የሠራው የናስ መሠዊያ የሚቃጠ
ለውን መሥዋዕት፣ የእህሉን ቍርባንና ስቡን
መያዝ ስላልቻለ ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
ፊት ለፊት ያለውን የመካከለኛውን አደባባይ
ክፍል ቀድሰው፤ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና
የኅብረት መሥዋዕቱንም ስብ በዚያ አቃጠለ።
8በዚያን ጊዜ ሰሎሞን ከእስራኤል ሕዝብ
ሁሉ ጋር ለሰባት ቀን በዓሉን አከበረ፤ ሕዝ
ቡም ከሐማት መግቢያ እስከ ግብፅ ወንዝ
ድረስ ካለው ምድር የመጣ እጅግ ታላቅ ጉባኤ
ነበር። 9መሠዊያውን ለሰባት ቀን ስለ ቀደሱና
የሰባት ቀን በዓል በተጨማሪ ስላከበሩ፣ በስ
ምንተኛው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ አደረጉ። 10ሰሎ
ሞንም በሰባተኛው ወር፣ በሃያ ሦስተኛው ቀን
ወደየቤታቸው እንዲሄዱ ሕዝቡን አሰናበተ፤
ሕዝቡም እግዚአብሔር ለዳዊትና ለሰሎሞን
እንዲሁም ለሕዝቡ ለእስራኤል ስላደረገው
በጎ ነገር ሁሉ በልባቸው ደስ እያላቸውና ሐሤት
እያደረጉ ሄዱ።

## እግዚአብሔር ለሰሎሞን ተገለጠለት

7፥11-22ተጓ ምብ— 1ነገ9፥1-9

11ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስና
የቤተ መንግሥቱን ሥራ ጨረሰ፤ ለእግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስና ለራሱ ቤተ መንግሥት
ያደርግ ዘንድ በልቡ ያሰበውን ሁሉ ካከናወነ
በኋላ፣ 12እግዚአብሔር በሌሊት ተገልጦለት
እንዲህ አለው፤

7፥6 1ዜና15፥16፡ 24
7፥7 ዘፀ29፥13
7፥8 ዘፍ15፥18፤ ዘኍ13፥21፤1ዜና9፥1፤2ዜና30፥26፤ ነህ8፥17
7፥9 ዘሌ23፥26፤ 2ዜና30፥23
7፥11 1ዜና28፥20
7፥12 ዘዳ12፥5፡11፤ 2ዜና1፥7
7፥13 ዘዳ11፥7፤ አሞ4፥7
7፥14 ዘፀ10፥3፤ 15፥26፤ዘሌ26፥41፤ ዘኍ6፥27፡2ነገ17፥13፤1ዜና16፥11፤2ዜና6፥20፡27፡37፤30፥20፤ መዝ60፥2፤ ኢሳ30፥26፤ 53፥5፤55፥7፤57፥18፤ ኤር33፥6፤ ሕዝ18፥32፤ ዘካ1፥4፤ሚል4፥2
7፥15 1ነገ8፥29፤ 2ዜና6፥40፤ነህ1፥6
7፥16 ዘዳ12፥5፤ 2ዜና33፥7
7፥17 ዘሌ19፥37፤ 1ነገ9፥4
7፥18 2ሳሙ7፥13፤ 1ዜና5፥2፤17፥12፤ 2ዜና13፥5፤23፥3፤ ኢሳ9፥7፤55፥4፤ ኤር33፥17፡21፤ ሚክ5፥2
7፥19 ዘዳ28፥15፤ 1ዜና28፥9፤2ዜና12፥1፤24፥18፤ኤር9፥13፤ 11፥8
7፥20 ዘዳ28፥37፤ 29፥28፤1ነገ14፥15፤ ኤር12፥14፤16፥13፤50፥11
7፥21 ዘዳ29፥24፤ ኤር19፥8
7፥22 ኤር16፥11

"ጸሎትህን ሰምቻለሁ፤ ይህንንም ስፍራ
መሥዋዕት የሚቀርብበት ቤተ መቅደስ እንዲ
ሆን ለራሴ መርጬዋለሁ።
13"ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማያትን በምዘጋ
በት ጊዜ ወይም ምድሪቱን እንዲበላ አንበጣ
በማዝበት ጊዜ፣ ወይም በሕዝቤ ላይ ቸነ
ፈር በምሰድበት ጊዜ፣ 14በስሜ የተጠራው
ሕዝቤ ራሱን አዋርዶ ቢጸልይ፣ ፊቴን ቢፈ
ልግና ከክፉ መንገዱ ቢመለስ፣ ከሰማይ እሰ
ማዋለሁ፤ ኀጢአቱን ይቅር እላለሁ፤ ምድሩንም
እፈውሳለሁ። 15አሁንም በዚህ ስፍራ ወደ
ሚጸለየው ጸሎት ዓይኖቼ ይገለጣሉ፤ ጆሮ
ዎቼም ያዳምጣሉ። 16ስሜ ለዘላለም በዚያ
ይኖር ዘንድ ይህን ቤተ መቅደስ መርጫለሁ፤
ቀድሼዋለሁም። ዓይኖቼም ልቤም ዘወትር
በዚያ ይሆናሉ።
17"አንተም ደግሞ አባትህ ዳዊት እንዳ
ደረገው ሁሉ በፊቴ ብትሄድ፣ ያዘዝሁህን
ሁሉ ብትፈጽም፣ ሥርዐቶቼንና ሕግጋቴን
ብትጠብቅ፣ 18ለአባትህ ለዳዊት፣ 'ከዘርህ
እስራኤልን የሚገዛ አታጣም' ብዬ
በገባሁለት ቃል ኪዳን መሠረት የመን
ግሥትህን ዙፋን አጸናለሁ።
19"እናንተ ግን እኔን ከመከተል ተመል
ሳችሁ የሰጠኋችሁን ሥርዐቴንና ትእ
ዛዜን ብትተው፣ ሄዳችሁም ሌሎችን አማ
ልክት ብታገለግሉና ብታመልኩ፣ 20በዚ
ያን ጊዜ እስራኤልን ከሰጠኋቸው ምድሬ
እነቅላቸዋለሁ፤ ለስሜ የቀደስሁትን ይህን
ቤተ መቅደስ እተዋለሁ፤ በሕዝቦችም ሁሉ
ዘንድ መተረቻና መዘባበቻ አደርገዋለሁ።
21ይህ ቤተ መቅደስ አሁን እጅግ የሚ
ያስደንቅ ቢሆንም በአጠገቡ የሚያልፉ
ሁሉ በመገረም፤ 'እግዚአብሔር በዚህች
ምድርና በዚህ ቤተ መቅደስ ላይ እንዲህ
ያለውን ነገር ያመጣው ከቶ ለምን ይሆን?'
ይላሉ፤ 22ሕዝቡም፣ 'ይህን ሁሉ ጥፋት
ያመጣባቸው፣ ከግብፅ ምድር ያወጣቸ
ውን የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚ
አብሔርን ትተው ሌሎችን አማልክት ስለ
ተከተሉ፣ ስላመለኳቸውና ስላገለገሏቸው
ነው' ብለው ይመልሳሉ።"

ም7 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል

ጸሐፊ ትኩረት እንደሳበ ያንጸባርቃል (ከ29፥26-27 ጋር ያነጻጽሩ) እንዲሁም የ1ዜና6፥31-48 ማብ ይመ)። *እስራኤላውያን ሁሉ፤* ከ1ዜና መግቢያ "ዓላማና መሪ ሐሳብ" የሚለውን ይመ።

*7፥8 ከሐማት መግቢያ እስከ ግብጽ ወንዝ ድረስ፤* ለርእሳን አበው ከተሰጠው ተስፋ መካከል በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን በተሟላ ሁኔታ ፍጻሜ ያገኘው የዘራቸው መብዛት ብቻ ሳይሆን (1፥9፤ 1ዜና27፥23-24 እና ማብ ይመ)፤ የተስፋዪቱን ምድር መውረሳቸው ጭምር ነው (ዘፍ 15፥18-21)፤

*7፥9 በስምንተኛው ቀን፤* የዳስ በዓል የሚከበርበት የመጨረሻው ዕለት ነው (5፥3 እና ማብ፤ እንዲሁም ዘሌ 23፥36፤ ዘኍ29፥35 ይመ)። *ለሰባት ቀን ... የሰባት ቀን፤* የምረቃ በዓል ወር በገባ ከስምንተኛው እስከ ዐሥራ አራተኛው ቀን የሚካሄድ ሲሆን ፤ የዳስ በዓል ግን ከዐሥራ አምስተኛው እስከ ሃያ ሁለተኛው ቀን ይካሄዳል። የማስተሰረያው ቀን ደግሞ በሰባ ተኛው ወር በአሥረኛው ቀን ይከበር ነበር (ዘሌ16፤ከ1ነገ8፥65-66 ጋር ያነጻጽሩ)።

7፥12... *ተገልጦለት* እግዚአብሔር ለሰሎሞን ሲገለጥ ይህ ሁለተኛ ጊዜው ነው፤ መጀመሪያ የተገለጠለት በገባዖን ነበር (1፥3-13፤1ነገ9፥2)።

*7፥13-15፤* ይህ ክፍል በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ብቻ እንጂ በሌላ ቦታ አይገኝም። ይህ ምንባብ፣ "እግዚአብሔር ለበጎውም ለክፉውም እንደየሥራው እንደሚከፍል ጸሐፊው ያለውን እምነት በአጽንዖት ያሳያል (ከ1ዜና መግቢያ "ዐላማና መሪ ሐሳብ " የሚለውን ይመ)። የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ይህ መርኅ በነገሥታት ላይ እንዴት ይሠራ እንደነበር በተከታታይ አሳይቶአል።

*7፥14፤* ለምሳሌ 12፥6-7፡12 ይመ።

*7፥17-18፤* 1ነገ 9፥4-5 ይመ። እንደነዚህ ዐይነት ቃላት፣ በቀድሞ ጊዜ እስራኤላውያን ስለመሲሑ መምጣት ያላቸውን ተስፋ የሚያጠናክሩላቸው ነበሩ።

*7፥19-22፤* 1ነገ9፥6-9 ይመ።

*8፥1-18* 1ነገ9፥10-18 እና ማብ ይመ። ከቍ13-16 ያለው ምንባብ በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ብቻ የሚገኝ ሲሆን፣ ይህም ታሪኩ

## ሰሎሞን ያከናወናቸው ሌሎች ሥራዎች

8፥1-18ተጓ ምብ— 1ነገ9፥10-28

8 ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስና
የራሱን ቤተ መንግሥት የሠራባቸው
ሃያ ዓመት ከተፈጸመ በኋላ፣ 2ኪራም የሰጠውን
ከተሞች አድሶ እስራኤላውያን እንዲሰፍሩ
ባቸው አደረገ። 3ከዚያም ሰሎሞን ወደ ሐማት
ሱባ ዘመተ፤ ያዛትም። 4በምድረ በዳውም
ውስጥ ተድሞርንና ቀድሞ በሐማት ሠርቶ
አቸው የነበሩትን የዕቃ ቤት ከተሞች ሁሉ
ሠራ። 5እንዲሁም የላይኛውን ቤት ሖሮንና
የታችኛውን ቤትሖሮን የተመሸጉ ከተሞች
አድርጎ ከቅጥሮቻቸው፣ ከበሮቻቸውና ከመ
ዝጊያዎቻቸው ጋር ሠራ። 6ደግሞም ባዕላ
ትንና የዕቃ ቤት ከተሞቹን ሁሉ፣ ሠረገ
ሎችና[*] ፈረሶች የሚኖሩባቸውን ከተሞች ሁሉ፣
ባጠቃላይ በኢየሩሳሌም፣ በሊባኖስና በግዛቱ
ሁሉ ለመሥራት የፈለጋቸውን ነገሮች ሁሉ
ሠራ።
7እስራኤላውያን ያልሆኑ ግን ከኬጢ
ያውያን፣ ከአሞራውያን፣ ከፌርዜያውያን፣
ከኤዊያውያንና ከኢያቡሳውያን የቀሩት ሕዝ
ቦች ሁሉ፣ 8እስራኤላውያን ያላጠፏቸውን፣
በምድሪቱ የቀሩ ዘሮቻቸውን የጕልበት ሥራ
ይሠሩ ዘንድ ሰሎሞን መለመላቸው[*]፤ እስከ
ዛሬም ይሠራሉ። 9ይሁን እንጂ ሰሎሞን
ማንም እስራኤላዊ ባሪያ ሆኖ በግዳጅ ሥራ
ውን እንዲሠራ አላደረገም፤ እነርሱ ተዋጊ
ዎች፣ የሻምበል አዛዦች፣ የሠረገሎችና
የሠረገላ ነጂዎች አዛዦች ነበሩና። 10ከእነዚ
ህም ሁለት መቶ አምሳዎቹ የንጉሥ ሰሎሞን
ሹማምንት ሰዎቹን የሚቈጣጠሩ ነበሩ።
11ሰሎሞንም፣ “የእግዚአብሔር ታቦት የገ
ባበት ቦታ ሁሉ ቅዱስ ስለሆነ፣ ሚስቴ በእ
ስራኤል ንጉሥ በዳዊት ቤተ መንግሥት
መኖር አይገባትም” በማለት የፈርዖንን ልጅ
ከዳዊት ከተማ እርሱ ወደሠራላት ቤተ መንግ
ሥት አመጣት።

8፥1 2ሳሙ7፥2
8፥4 2ሳሙ8፥9
8፥5 ኢሱ10፥10
8፥6 ኢሱ19፥44
8፥7 ዘፍ10፥16፤ 15፥18-21፤ዕዝ9፥1
8፥8 2ዜና2፥18
8፥11 1ነገ3፥1
8፥12 1ነገ8፥64፤ 2ዜና15፥8
8፥13 ዘፀ12፥17፤ 23፥14:16፤29፥38፤ ዘኁ10፥10፤28፥9:16 -25፤29፥12- 38፤ነህ8፥17
8፥14 1ዜና9፥17፤ 23፥6፤24፥1፤25፥1፤ ነህ12፥24:36:45
8፥18 2ዜና9፥9

12ሰሎሞንም በቤተ መቅደሱ መመላለሻ
ፊት ለፊት ባሠራው የእግዚአብሔር መሠዊያ
ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት ለእግዚአብሔር
አቀረበ። 13ሙሴ ስለ መሥዋዕት አቀራረብ
ባዘዘው መሠረት በእያንዳንዱ የበዓል ቀን
ይኸውም በየሰንበቱ፣ በየወሩ መባቻና በሦ
ስቱ የዓመት በዓላት ማለትም በቂጣ በዓል፣
በመከር በዓልና በዳስ በዓል ጊዜ የሚቃጠ
ለውን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቀረበ።
14የአባቱን የዳዊትን ሥርዐት በመከተልም፣
ካህናቱን በየአገልግሎት ክፍላቸው ሌዋው
ያኑንም ምስጋናውን እንዲመሩና በየዕለቱ
ሥራቸው ካህናቱን እንዲረዱ መደባቸው።
ደግሞም የእግዚአብሔር ሰው ዳዊት ባዘዘው
መሠረት የቤተ መቅደሱን በር ጠባቂዎች
በልዩ ልዩ በሮች ጥበቃ ላይ በየክፍላቸው
መደባቸው። 15እነርሱም ንጉሡ ግምጃ ቤቱን
ጨምሮ ስለማናቸውም ነገር ለካህናቱና
ለሌዋውያኑ የሰጠውን ትእዛዝ አልተላለፉም
ነበር።
16የእግዚአብሔ ቤተ መቅደስ መሠረት
ከተጣለበት ዕለት አንሥቶ እስከ ፍጻሜው
ድረስ ያለው የሰሎሞን ሥራ ሁሉ ተከናወነለት፤
በዚሁ ሁኔታም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
ሥራ ከፍጻሜ ደረሰ።
17ከዚያም ሰሎሞን የኤዶም የባሕር ጠረፍ
ወደ ሆኑት ወደ ዔድዮንጋብርና ወደ ኤሎት
ሄደ። 18ኪራምም ባሕሩን በሚያውቁት በራሱ
መኰንኖች የሚታዘዙ መርከቦችን ላከለት፤
እነዚህም ከሰሎሞን ሰዎች ጋር በመሆን
ወደ ኦፊር ተጓዙ፤ ከዚያም አራት መቶ
አምሳ መክሊት[*] ወርቅ አምጥተው ለንጉሥ
ሰሎሞን ሰጡት።

[*]6 ወይም ሠረገለኞች ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
[*]8 ወይም ከሌቦ ሐማት ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
[*]18 ዐሥራ ስድስት ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።

የሚቀጥል መሆኑን ለማሳየትና ዳዊትን ከሙሴ ጋር ለማነጻጸር ጸሐፊው ያለውን ጽኑ ፍላጎት በአጽንዖት ይገልጻል (ከ1ዜና መግቢያ “ዓላማና መሪ ሐሳብ” የሚለውን ይመ)።

*8፥1-2፤* ሰሎሞን ከተሞቹን ለኪራም እንደሰጠ በ1ነገ9፥10-14 ላይ ተጽፎአል፤ በዚህ ክፍል የሚገኘው ግን ተገላቢጦሹ ነው። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ከሰለሞን የተሰጡት ከተሞች በኪራም ዘንድ ተቀባይነት አለማግኘታቸውን (1ነገ 9፥11-13) ያልጠቀሰው፣ ለንጉሥ ሰሎሞን ያለውን ታላቅ አክብሮት ለማሳየት ከሚያደርገው ጥረት የተነሣ ሳይሆን አይቀርም፤ ታሪኩንም በመቀጠል ከተሞቹ ለሰሎሞን መመለሳቸውንና ተሻሽለው መሠራታቸውን ይጠቅሳል። ኪራም ከተሞቹን በመያዣነት ይዞ ከቈየ በኋላ ሰሎሞን ዕዳውን እንደ ከፈለው ለቆለት ይሆናል (የ1ነገ9፥11 ማብ ይመ)። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ፈርዖን ጌዘርን ለሰሎሞን ስለ መስጠቱ አልተናገረም (1ነገ9፥16)።

*8፥3-4፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በመጽሐፈ ነገሥት ውስጥ ያልተጠቀሰውን ተጨማሪ ወታደራዊ ዘመቻ ወደ ሰሜን መደረጉን ጽፎአል። ዳዊትም እንደዚሁ ወደ ሰሜን ዘምቶ ሰባን መውጋቱ ይታወቃል (1ዜና18፥3-9፤19፥6፤2ሳሙ8፥3-12፤10፥6-8 ይመ፤ ከ1ነገ11፥23-24 ጋር ያነጻጽሩ)።

*8፥5* ሁለቱ የቤትሖሮን ከተሞች የተሠሩት ከባሕሩ የጠረፍ ሜዳ አንሥቶ ልክ ወደ ሰሜን ኢየሩሳሌም በሚወስደው መንገድ ላይ ጠላትን ለመከላከልም ሆነ ለማጥቃት በሚያመች ቍልፍ ቦታ ላይ ነው።

8፥7 *እስራኤላውያን ያልሆኑ፤* 2፥17፤ 1ዜና22፥2፤ 1ነገ9፥21 ይመ።

*8፥8፤* እስከ ዛሬም፤ የ5፥9 ማብ ይመ።

*8፥11፤ ቅዱስ፤* 1ነገ9፥24 እና ዜና መዋዕሉ የፈርዖን ልጅ ወደ ተለየ ስፍራ መዛወሯን ጽፈዋል፤ ምክንያቱን ያወሣው ግን ዜና መዋዕሉ ብቻ ነው፤ ይኸውም ቤተ መቅደሱ ብቻ ሳይሆን፣ የዳዊትም ቤተ መንግሥት እንደ አንድ ቅዱስ ቦታ ተቈጥሮአል፤ ታቦቱ ዐርፎበት ነበርና።

*8፥12-16፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ካለው ጥልቅ ስሜት የተነሣ ሰሎሞን ስላቀረበው መሥዋዕትና ለቤተ መቅደሱም ስላ ደረገው ስጦታ በሰፊት ጽፎአል። 1ነገ9፥25 የሚያወሣው በሦስቱ ዐበይት በዓላት ስለሚቀርበው መሥዋዕት ብቻ ሲሆን የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን ስጦታዎቹ ከሙሴ ሕግ ጋር እንዲጣጣሙ (ዘሌ23፥1-37፤ ዘኁ28-29) የሰንበትንና የወር መባቻ መሥዋዕቶች ይጨምራል ።

*8፥17-18፤* 1ነገ9፥26-28 ይመ። ሰሎሞንና ኪራም የዘረጉት የንግድ ልውውጥ ከሜድትራኒያን ባሕር እስከ ደቡብ ዐረብ ልሳነ ምድር ድረስ ለሁለቱም ነገሥታት ከፍተኛ ጥቅም አስገኝቶአል። በንግድ ልውውጡም ሥራ መካከለኛውና እንቅስቃሴውን የሚመራው ሰሎሞን ነበር።

8፥18፤ *ኪራምም...መርከቦችን ላከለት፤* ምናልባትም ለመርከቡ ሥራ የሚያስፈልገው ቍሳቍስ በፊንቄ ከተዘጋጀ በኋላ በየብስ ተጓጕዞ በዔጽዮንጋብር ወደብ ሳይገጣጠም አይቀርም (9፥21 ይመ)።

*9፥1-12፤* 1ነገ10፥1-13 እና ማብ ይመ። የሳባ ንግሥት ሰሎሞንን መጐብኘቷ እግዚአብሔር ጥበብና ብልጽግናን እንደሚሰጠው

## የሳባ ንግሥት ሰሎሞንን ጐበኘች

9፥1-12ተጓ ምብ— 1ነገ10፥1-13

9 የሳባ ንግሥት የሰሎሞንን ዝና በሰማች
ጊዜ አስቸጋሪ በሆኑ ጥያቄዎች ልትፈ
ትነው ወደ ኢየሩሳሌም መጣች:: ቅመማ
ቅመም፣ እጅግ ብዙ ወርቅና የከበሩ ድን
ጋዮችን በግመሎች አስጭና ከታላቅ ጓዝ
ጋር ደረሰች፤ ወደ ሰሎሞንም ቀርባ በልቧ
ያለውን ሁሉ አጫወተችው:: 2ሰሎሞንም
የጠየቀችውን ሁሉ መለሰላት፤ ሊመልስላት
የተሳነው አንዳች ነገር አልነበረም:: 3የሳባ
ንግሥት የሰሎሞንን ጥበብና የሠራውን
ቤተ መንግሥት፣ 4በገበታው ላይ የሚቀርበ
በውን መብል፣ የሹማምቱን አቀማመጥ፣
አስተናባሪዎቹንና አለባበሳቸውን፣ ጠጅ አሳ
ላፊዎቹንና አለባበሳቸውን እንዲሁም በእግ
ዚአብሔር ቤተ መቅደስ ያቀረባቸውን የሚ
ቃጠሉ መሥዋዕቶች[ሌ] ባየች ጊዜ እጅግ
ተደነቀች::
5ንጉሡንም እንዲህ አለችው፤ "ስለ ሥራ
ህና ስለ ጥበብህ በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት
ሁሉ እውነት ነው:: 6ነገር ግን መጥቼ በዓ
ይኔ እስካየሁ ጊዜ ድረስ የነገሩኝን አላመ
ንሁም ነበር፤ በእርግጥም የጥበብህ እኩሌታ
እንኳ አልተነገረኝም፤ እኔ ከሰማሁት ዝና
እጅግ ትልቃለህ:: 7ሰዎችህ ምንኛ ታድ
ለዋል! ዘወትር በፊትህ ቆመው ጥበብህን
የሚሰሙ ሹማምትህስ ምንኛ ታድለዋል!
8በአምላክህ ለእግዚአብሔር ንጉሥ ሆነህ እን
ድትገዛ፣ በአንተ ደስ የተሰኘውና በዙፋኑ ላይ
ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር ብሩክ
ይሁን፤ አምላክህ ለእስራኤል ካለው ፍቅርና
ለዘላለም ሊያጸናቸው ካለው ፍላጎት የተ
ነሣ፣ ፍትሕና ጽድቅ እንዲሰፍን ታደርግ
ዘንድ አንተን በላያቸው ላይ አንግሦሃልና ::"
9ከዚያም ለንጉሡ አንድ መቶ ሃያ መክሊት[ፐ]
ወርቅ፣ እጅግ ብዙ ቅመማ ቅመምና የከበሩ
ድንጋዮች ሰጠችው፤ የሳባ ንግሥት ለንጉሥ
ሰሎሞን እንደሰጠችው ዐይነት ቅመማቅመም
ያለ ከቶ አልነበረም::
10የኪራም ሰዎችና የሰሎሞን ሰዎች ወርቅ
ከኦፊር እንደዚሁም ሰንደልና[ሀ] የከበሩ ድን
ጋዮች አመጡ:: 11ንጉሡም የሰንደሉን
እንጨት ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና
ለቤተ መንግሥቱ ደረጃ መሥሪያ እንደዚሁም
ለመዘምራኑ የመሰንቆና የበገና መሥሪያ
አደረገው፤ ይህን የመሰለ ነገር በይሁዳ ምድር
ከቶ አልታየም::
12ንጉሥ ሰሎሞን ለሳባ ንግሥት የፈለገ
ችውንና የጠየቀችውን ሁሉ ሰጣት፤ ስጦ
ታውም እርስዋ ካመጣችለት በላይ ነበር::
ከዚያም ከአጃቢዎቿ ጋር ወደ አገሯ ተመለሰች::

9፥1 ዘፍ10፥7፤ ሕዝ23፥42፤ ማቴ12፥42፤ ሉቃ11፥31
9፥3 1ነገ5፥12
9፥6 2ዜና6፥32
9፥8 1ነገ2፥12፤ 1ዜና17፥14፤ 2ዜና2፥11፤13፥8
9፥9 2ዜና8፥18
9፥10 2ዜና8፥18
9፥14 2ዜና17፥11፤ ኢሳ21፥13፤ ኤር25፥24፤ ሕዝ27፥21፤30፥5
9፥16 1ነገ7፥2፤ 2ዜና12፥9
9፥17 1ነገ22፥39
9፥22 1ነገ3፥13፤ 2ዜና1፥12
9፥23 1ነገ4፥34
9፥24 2ዜና32፥23፤ መዝ45፥12፤68፥29፤ 72፥10፤ኢሳ18፥7

## የሰሎሞን ብልጽግና

9፥13-28ተጓ ምብ—1ነገ10፥14-29፤2ዜና1፥14-17

13ሰሎሞን በየዓመቱ የሚቀበለው ወርቅ
ክብደቱ ስድስት መቶ ሥልሳ ስድስት
መክሊት[ለ] ነበር:: 14ይህም ከታላላቅና ከተራ
ነጋዴዎች ከሚገባው ቀረጥ ሌላ ነበር፤ እንዲ
ሁም መላው የዐረብ ነገሥታትና የግዛ ምድሩ
አገረ ገዦች ለሰሎሞን ወርቅና ብር ያመጡ
ለት ነበር::
15ንጉሥ ሰሎሞን ሁለት መቶ ከጥፍጥፍ
ወርቅ የተሠራ ታላላቅ ጋሻዎች አበጀ፤ በእያ
ንዳንዱም ጋሻ የገባው ጥፍጥፍ ወርቅ ስድስት
መቶ ሰቅል[ሐ] ነበር:: 16እንዲሁም ሦስት መቶ
ትንንሽ ጋሻዎች በጥፍጥፍ ወርቅ ሠራ፤
በእነዚህም በእያንዳንዳቸው የገባው ጥፍጥፍ
ወርቅ ሦስት መቶ ሰቅል[መ] ነበር:: ንጉሡም
ጋሻዎቹን "የሊባኖስ ደን" በተባለው ቤተ
መንግሥት ውስጥ አኖራቸው::
17ከዚያም ንጉሡ በዝሆን ጥርስ ያጌጠና
በንጹሕ ወርቅ የተለበጠ ትልቅ ዙፋን ሠራ::
18ዙፋኑ ስድስት መውጫ መውረጃ ደረጃዎች
ሲኖሩት፣ ከዙፋኑ ጋር የተያያዘ ከወርቅ
የተሠራ የእግር መርገጫ ነበረው:: መቀመ
ጫውም ግራና ቀኙ መደገፊያ ያለው ሆኖም
ከመደገፊያዎቹም አጠገብ አንዳንድ አንበሳ
ቆሞ ነበር:: 19እንዲሁም በስድስቱ ደረ
ጃዎች ዳርና ዳር ላይ አንዳንድ አንበሳ፣ ባጠ
ቃላይ አሥራ ሁለት አንበሶች ቆመው ነበር፤
ይህን የመሰለ ዙፋን በየትኛውም አገር ተሠ
ርቶ አያውቅም:: 20ንጉሥ ሰሎሞን የሚጠ
ጣባቸው ዕቃዎች በሙሉ ከወርቅ የተሠሩ
ነበሩ፤ "የሊባኖስ ደን" ተብሎ በሚጠራው
ቤተ መንግሥት ውስጥ የነበሩትም ዕቃዎች
ሁሉ ከንጹሕ ወርቅ የተሠሩ ነበሩ፤ በሰ
ሎሞን ዘመን ብር ዋጋ እንደ ሌለው ስለ
ሚቈጠር ከብር የተሠራ አንድም ነገር አል
ነበረም:: 21ንጉሡ በኪራም ሰዎች የሚነዱ
የንግድ መርከቦች ነበሩት፤[ሠ] እነዚህም በየ
ሦስት ዓመቱ አንድ ጊዜ ወርቅ፣ ብር፣ የዝ
ሆን ጥርስ፣ ጦጣዎችና ዝንጀሮዎች እየያዙ
ይመለሱ ነበር::
22ንጉሥ ሰሎሞን በሀብትም ሆነ በጥበብ
ከምድር ነገሥታት ሁሉ የበለጠ ነበር::
23የምድር ነገሥታት ሁሉ እግዚአብሔር በልቡ
ያኖረውን ጥበብ ለመስማት ከሰሎሞን ጋር
መገናኘት ይፈልጉ ነበር:: 24በየዓመቱ ወደ
እርሱ የሚመጡትም ሁሉ የብርና

ሌ4 ወይም ወደላይ የሚመጣባቸውን ደረጃዎች ተብሎ መተርጐም ይቻላል::
ፐ9 4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው::
ሀ10 የአልሙግ እንጨት ሊሆን ይቻላል
ለ13 23 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው::
ሐ15 3.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው::
መ16 1.7 ኪሎ ግራም ይህል ነው
ሠ21 ዕብራይስጡ ወደ ተርሴስ ሊሄዱ የሚችሉ መርከቦች ይላል::

የገባለት የተስፋ ቃል መፈጸሙን ያሳያል (1፥12):: ሰሎሞን በጥበብና በሀብት መግነኑ ቅድሚያ የሚሰጠው ቢሆንም፣ ንግሥቲቱ ለጉብኝት የተነሣሣችበት ዋናው ምክንያት ወደ ደቡብ ዐረብ የሚመላለሱት የሰሎሞን የመርከቦች እንቅስቃሴ የንግድ ግንኙነት እንድትፈጥር ገፋፍቷት ይሆናል:: (8፥17-18)::

9፥1 *የሳባ፤* የ1ነገ10፥1 ማብ ይመ፤ እንዲሁም ኢዮ1፥15፤ 6፥19፤መዝ72፥10-11፡15፤ኢሳ60፥6፤ኤር6፥20፤ሕዝ27፥22፤ 38፥13፤ኢል3፥8 ይመ)::

9፥8 *በዙፋኑ፤* በ1ነገ10፥9 የተጻፈው የንግሥቲቱ ጉብኝት ታሪክ በዚህ ክፍል ለየት ባለ መንገድ ተጠቅሶአል፤ የንግሥቲቱ ንግግር ንጉሡ የሚቀመጥበት የእስራኤል ዙፋን የእግዚአብሔር ዙፋን መሆኑን እንዲያምን አድርጎታል (13፥18፤ እንዲሁም

የወርቅ ዕቃ፣ የልብስ፣ የጦር መሣሪያና የቅመማ
ቅመም እንደዚሁም የፈረስና የበቅሎ ግጻ በረከት
ያመጡለት ነበር::
[25]ሰሎሞን አራት ሺ የፈረሶችና የሠረገሎች[ሉ]
ጋጥ ነበረው፤ እንዲሁም በሚኖርበት በኢ
የሩሳሌምና በሰረገላ ከተሞች አሥራ ሁለት
ሺህ ፈረሶች ነበሩት:: [26]እርሱም ከኤፍራጥስ
ወንዝ[ሰ] እስከ ፍልስጥኤም ምድርና እስከ
ግብፅ ዳርቻ ድረስ ባሉት ነገሥታት ሁሉ
ላይ ገዛ:: [27]ንጉሡ በኢየሩሳሌም ብሩን እንደ
ማንኛውም ድንጋይ፣ የዝግባውንም ዕንጨት
ብዛት በየኰረብታው ግርጌ እንደሚበቅል
ሾላ አደረገው:: [28]ለሰሎሞን ከግብፅና[ኣ] ከሌ
ሎች አገሮች ሁሉ ፈረሶች ያመጡለት ነበር::

## የሰሎሞን መሞት

9፥29-31ተጓ ምብ—1ዜና11፥41-43

[29]ሰሎሞን በዘመነ መንግሥቱ የሠራው
ሌላው ነገር በነቢዩ በናታን ታሪክና በሴሎ
ናዊው በአሒያ ትንቢት እንዲሁም ባለ ራእዩ
አዶ ስለናባጥ ልጅ ስለ ኢዮርብዓም ባየው
ራእይ ውስጥ የተጻፈ አይደለምን? [30]ሰሎሞን
በኢየሩሳሌም ተቀምጦ በእስራኤል ሁሉ ላይ
አርባ ዓመት ነገሠ:: [31]ከዚያም እንደ አባቶቹ
አንቀላፋ፤ በአባቱም በዳዊት ከተማ ተቀበረ::
ልጁም ሮብዓም በእርሱ ፋንታ ነገሠ::

## እስራኤል በሮብዓም ላይ ዐመፀ

10፥1-11፥4ተጓ ምብ—1ዜና12፥1-24

10 እስራኤላውያን ሁሉ ሊያነግሡት
ወደዚያ ሄደው ስለነበር፣ ሮብዓም
ወደ ሴኬም ሄደ:: [2]ከንጉሥ ሰሎሞን ሸሽቶ
በግብፅ ይኖር የነበረው የናባጥ ልጅ ኢዮርብ
ዓም ይህን ሲሰማ፣ ከግብፅ ተመልሶ መጣ::
[3]እርሱንም ልከው አስጠሩት፤ ከዚያም እርሱና
እስራኤል ሁሉ ወደ ሮብዓም ሄደው እንዲህ
አሉት፤ [4]“አባትህ በላያችን ከባድ ቀንበር
ጫነብን፤ አንተ ግን አስጨናቂውን ሥራና
በላያችን የጫነብንን ከባድ ቀንበር አቅልልን፤
እኛም እንገዛልሃለን::”
[5]ሮብዓምም፣ “ከሦስት ቀን በኋላ ተመል
ሳችሁ ወደ እኔ ኑ” አላቸው፤ ስለዚህ ሰዎቹ
ወጥተው ሄዱ::
[6]ከዚያም ንጉሥ ሮብዓም፣ “ለዚህ ሕዝብ
ምን እንድመልስለት ትመክሩኛላችሁ?”
በማለት አባቱ ሰሎሞን በሕይወት ሳለ ያገ
ለገሉትን የእስራኤልን ሽማግሌዎች ጠየ
ቃቸው::
[7]እነርሱም፣ “ለእዚህ ሕዝብ ደግ ከሆንህለት፣
ደስ ካሰኘኸውና የሚስማማው መልስ ከሰጠ
ኸው ምን ጊዜም ይገዛልሃል” አሉት::
[8]ሮብዓም ግን ሽማግሌዎች የሰጡትን ምክር
ትቶ፣ አብሮ አደጎቹና አገልጋዮቹ ከሆኑት
ወጣቶች ምክር ጠየቀ፤ [9]እንዲህም አላቸው፤
“ ‘አባትህ የጫነብንን ቀንበር አቅልልልን’
ለሚሉኝ ለእነዚህ ሰዎች የምትሰጡኝ ምክር
ምንድነው? ምንስ ብለን እንመልስላቸው?”
[10]አብሮ አደጎቹም ወጣቶች እንዲህ ሲሉ
መለሱለት፤ “ለጠየቀህ ሕዝብ፤ ‘አባትህ በላ
ያችን ከባድ ቀንበር ጫነብን፤ አንተ ግን
ቀንበራችንን አቅልልልን’ ለሚሉህ እንዲህ
በላቸው፤ ‘ትንሿ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ይልቅ
ትወፍራለች፤ [11]አባቴ ከባድ ቀንበር ጫነባችሁ፤
እኔ ግን የባሰ አከብደዋለሁ፤ አባቴ በዐለንጋ
ገረፋችሁ፤ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ::”
[12]ንጉሡ፣ “ከሦስት ቀን በኋላ ተመል
ሳችሁ ኑ” ባላቸው መሠረት ኢዮርብዓምና
ሕዝቡ ሁሉ ከሦስት ቀን በኋላ ወደ ሮብዓም
ተመለሱ:: [13]ንጉሡም የሽማግሌዎችን ምክር
በመናቅ፣ አመናጭቆ መለሰላቸው፤ [14]እርሱም
የወጣቶቹን ምክር በመቀበል፣ “አባቴ ቀንበራ
ችሁን አከበደ፤ እኔ ደግሞ የባሰ አከብደዋለሁ፤
አባቴ በአለንጋ ገረፋችሁ፤ እኔ ደግሞ በጊንጥ
እገርፋችኋለሁ” አላቸው:: [15]እግዚአብሔር በሴሎ
ናዊው በአሒያ አማካይነት ለናባጥ ልጅ
ለኢዮርብዓም የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ፣
ወስኖ ስለነበር፣ ንጉሡ ሕዝቡን አላዳመጠም::

9፥25 1ሳሙ8፥11
9፥26 ዘፍ15፥18-21፤1ነገ4፥21፤ መዝ72፥8-9
9፥29 2ሳሙ7፥2፤ 1ነገ11፥29፤ 2ዜና10፥2
9፥31 1ነገ2፥10
10፥2 1ነገ11፥40፤ 2ዜና9፥29
10፥3 1ዜና9፥1
10፥4 2ዜና2፥2
10፥6 ኢዮ8፥8-9፤12፥12፤15፥10፤ 32፥7
10፥7 ምሳ15፥1
10፥8 2ሳሙ17፥14፤ ምሳ13፥20
10፥15 1ነገ11፥29፤ 2ዜና11፥4፤ 25፥16-20

ሉ 25 ወይም ሠረገለኞች ተብሎ መተርጐም ይቻላል::
ሰ 26 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው፤ ነገር ግን አንዳንድ ቅጅዎች ኤፍራጥስ የሚለውን ቃል አይጨምሩም
ኣ 28 በኪልቂያ የምትገኘው ሙዙር ነች::

የ1ዜና17፥14 ማብ ይመ)::

*9፥26፤* 7፥8 እና ማብ ይመ::

*9፥27፤* 1፥15 ይመ::

*9፥28፤* የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ስለ ሰሎሞን ሚስቶችም ሆነ በዘመነ መንግሥቱ ማብቂያ ገደማ ስለተነሣበት ዐመፅ የሚያወሣውን ታሪክ (1ነገ 11፥1-40)፣ እንዲሁ በዝምታ አልፎታል፤ ምክንያቱም ጸሐፊው ስለ ሰሎሞን በጎ ገጽታ በወጥነት ያቀረባቸውን ዘገባዎች ስለሚያጐድፉበት ነው:: *ከግብጽ…ፈረሶች፤* የ1፥16 ማብ ይመ::

*9፥29-31፤* 1ነገ11፥41-43 ይመ::

*10፥1-36፥23፤* በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ታሪክ ግማሹ ያህል በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ብቻ የሚገኝ ሲሆን፣ ይህም ያለ መጽሐፈ ነገሥት ድጋፍ ራሱን ችሎ መቆም እንደሚችል ያሳያል:: ለዚህም ግልጽ የሆነው ምክንያት የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በይሁዳ ምድር ስለገዛው የዳዊት ሥርወ መንግሥት የሚያወሣውን ታሪክ መጻፉ ነው፤ የሰሜኑን መንግሥት ታሪክ በተመለከተ ግን በይሁዳ ላይ ተጽዕኖ ስለማሳደሩ የሚናገረውን ክፍል ብቻ በማውሳት የቀረበው በዝምታ አልፎታል:: ስለ እስራኤል መንግስት መከፈል የሚናገረው ታሪክ ቢያንስ በሁለት መልክ ሊታይ ይችላል፣ ይህም፡ (1) በእስራኤል ዙፋን ላይ ሥርወ መንግስቱ እንደማይቋረጥ ለዳዊት ቃል የገባለት እግዚአብሔር ታማኝ መሆኑን ጸሐፊው በአጽንዖት መናገሩንና (2) የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በነበረበት ዘመን ከባቢሎን የተመለሰው ማኅበረሰብ ከይሁዳ መንግሥት ተማርኮ የሄደው ብቻ ቢሆንም፣ ሕዝቡ ከመላው የእስራኤል ነገድ የአንዱ ክፍል ቅሬታ መሆኑን ለመግለጽ ነው (ከ1ዜና መግቢያ “ዓላማና መሪ ሐሳብ” የሚለውን ይመ)::

*10፥1-19፤* 1ነገ 12፥1-20 እና ማብ ይመ:: የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ለሰሎሞን ካለው እጅግ ከፍ ያለ ግምትና አድናቆት የተነሣ ለመገንጠሉና ለመከፈሉ ምክንያት የሚያደርገው የኢዮርብዓምን ዐመፅ ነው (ከ13፥6-7 ጋር ያነጻጽሩ)::

10፥1 *ሮብዓም፤* ከ930-913 ዓ.ቅ.ክ. ገዝቶአል::

10፥2 *ኢዮርብዓም፤* በዜና መዋዕል መጽሐፍ ስሙ ሲጠቀስ ይህ ሁለተኛው ጊዜ ነው (9፥29 ይመ):: የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ አንባቢዎች በ1ነገ 11፥26-40 የተጻፈውን ታሪክ በሚገባ እንደሚያወቁት ይገምታል::

10፥15 *በአሒያ፤* አንባቢዎቹ በ1ነገ 11፥29-33 ላይ የሚገኘውን ታሪክ በሚገባ እንደሚያወቁት ይገምታል::

10፥18፤ *የገባሮች ኀላፊ… አዶራምን፤* ተገደው የጉልበት ሥራ በሚሠሩት ሰዎች ላይ ኀላፊ ሆኖ የተሾመ ነው፤ በሰሎሞንም

16መላው እስራኤልም ንጉሡ ሊሰማቸው
አለመፈለጉን በተረዱ ጊዜ፣ እንዲህ ሲሉ
መለሱለት፤ 1

"ከዳዊት ምን ድርሻ አለን? ከእሴይስ ልጅ
ምን ክፍል አለን? እስራኤል፣ ሆይ፤ ወደ
ድንኳንህ ተመለስ፤ ዳዊት ሆይ፤ አንተም
የገዛ ቤትህን ጠብቅ።"

ስለዚህ እስራኤላውያን ሁሉ ወደ የቤ
ታቸው ተመለሱ። 17ይሁን እንጂ በይሁዳ
ከተሞች የሚኖሩትን እስራኤላውያን አሁንም
የሚገዛቸው ሮብዓም ነበር።
18ንጉሥ ሮብዓም የገባሮች ኀላፊ የነበረውን
አዶራምን ላከው፤ እስራኤላውያን ግን በድን
ጋይ ወግረው ገደሉት። ንጉሥ ሮብዓም
ግን እንደምንም ብሎ ሰረገላው ላይ በመ
ውጣት ወደ ኢየሩሳሌም ሸሽቶ አመለጠ።
19ስለዚህ እስራኤል እስከ ዛሬ ድረስ በዳዊት
ቤት ላይ እንደ ዐመፀ ነው።

11 ሮብዓም ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ፣
እስራኤልን ወግተው መንግሥቱን
ወደ ሮብዓም እንዲመልሱ ከይሁዳና ከብንያም
ቤት አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ ወታደሮች
ሰበሰበ።
2ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ወደ እግ
ዚአብሔር ሰው ወደ ሸማያ እንዲህ ሲል መጣ፤
3"ለይሁዳ ንጉሥ ለሰሎሞን ልጅ ለሮብዓ
ምና በይሁዳና በብንያም ላሉ እስራኤላው
ያን ሁሉ እንዲህ በል፤ 4'እግዚአብሔር እን
ዲህ ይላል፤ ይህ ነገር ከእኔ ዘንድ ስለ ሆነ፣
ወንድሞቻችሁን ለመውጋት ወደዚያ አትውጡ፤
እያንዳንዳችሁም ወደ የቤታችሁ ሂዱ" አላ
ቸው። ስለዚህ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ
በኢዮርብዓም ላይ መዝመቱን ትተው ተመለሱ።

10፥16 2ሳሙ 20፥1፤ 1ዜና 9፥1
10፥18 2ሳሙ 20፥24፤ 1ነገ 5፥14
11፥1 1ነገ 12፥21
11፥2 1ነገ 12፥22፤ 2ዜና 12፥5-7፡15
11፥4 2ዜና 28፥8-11
11፥10 ኢሱ 10፥20፤ 2ዜና 12፥4፤17፥2፡19፤21፥3
11፥14 ዘኍ 35፥2-5፤1ዜና 6፥81
11፥15 ዘሌ 17፥7፤ 1ነገ 12፥28፡31፤13፥33፤2ዜና 13፥8
11፥16 2ዜና 15፥9
11፥17 2ዜና 12፥1

## ሮብዓም የይሁዳን ከተሞች መሸገ

5ሮብዓም መኖሪያውን በኢየሩሳሌም በማ
ድረግ ለመከላከያ የሚሆኑ ከተሞችን በይ
ሁዳ ሠራ፤ እነዚህም 6ቤተ ልሔም፣ ኤጣም፣
ቴቁሔ፣ 7ቤትጹር፣ ሦኮ፣ ዓዶላም፣ 8ጌት፣
መሪሳ፣ ዚፍ፣ 9አዶራይም፣ ለኪሶ፣ ዓዜቃ፣
10ጾርዓ፣ ኤሎን፣ ኬብሮን ናቸው። በይሁዳና
በብንያም ውስጥ የተመሸጉት ከተሞች እነዚህ
ነበሩ። 11እነዚህንም ምሽጎቻቸውን አጠንክሮ፣
አዛዦችን ሾመባቸው፤ ምግብ፣ ዘይትና የወይንጠጅ
አከማቸባቸው። 12በየከተሞቹም ሁሉ ጋሻና
ጦር አከማችቶ ይበልጥ አጠናከራቸው። በዚህ
ዓይነት ይሁዳንና ቢንያምን የራሱ አደረገ።
13በመላው እስራኤል ያሉት ካህናትና
ሌዋውያን ከየክልላቸው ሁሉ ወደ እርሱ
ተሰበሰቡ። 14ኢዮርብዓምና ልጆቹ ሌዋውያኑን
ከእግዚአብሔር የክህነት አገልግሎት ስላባረ
ሯቸው ሌዋውያኑ ማሰማሪያ ቦታቸውንና
ንብረታቸውን ሁሉ ትተው ወደ ይሁዳና ወደ
ኢየሩሳሌም መጡ፤ 15እርሱም ለየኰረብታው
መስገጃ እንዲሁም ለሠራቸው የፍየልና የጥጃ
ምስሎች የራሱን ካህናት ሾመ። 16ከእያ
ንዳንዱም የእስራኤል ነገድ ከልባቸው የእስ
ራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ሁሉ፣
ለአባቶቻቸው አምላክ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት
ያቀርቡ ዘንድ፣ ሌዋውያኑን ተከትለው ወደ
ኢየሩሳሌም ሄዱ። 17በዚሁ ሁኔታ የዳዊትንና
የሰሎሞንን መንገድ በመከተል፣ ለሦስት ዓመት
የይሁዳን መንግሥት አበረቱ፤ የሰሎሞንን
ልጅ ሮብዓምንም ረዱ።

## የሮብዓም ቤተሰብ

18ሮብዓም መሐላትን አገባ፤ አባቷ የዳዊት
ልጅ ኢያሪሙት ሲሆን፣ እናቷም አቢካኢል

---

ዘመን ሥራው ይኸው ነበር፤ (1ነገ 4፥6፤5፥14)።

10፥19 *እስከ ዛሬ ድረስ፤* የ5፥9 ማብ ይመ።

*11፥1-23፤* ከቍ 1-4 ያለው ከ1ነገ12፥21-24 ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ከቍ 5-23 ያለው ግን በአብዛኛው በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ብቻ የሚገኝ ነው። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ለእግዚአብሔር መታዘዝ በረከት እንደሚያመጣ፣ አለመታዘዝም የአጸፋ ቅጣት የሚያስከትል መሆኑን ለማሳየት የሮብዓምን ታሪክ በምሳሌነት ያቀርባል (ከ1 ዜና መግቢያ "ዓላማና መሪ ሐሳብ" የሚለውን ይመ)፡ ም11 ለእግዚ አብሔር ሕግ መታዘዝ ስለሚያስገኘው በረከት ይናገራል (ቍ 1-4)፤ ይኸውም፦ ሮብዓም እየበለጸገና እያየለ መሄዱ (ቍ5-12) የሕዝብ ድጋፍ ማግኘቱን (ቍ 13-17) እና ብዙ ልጆች መውለዱን (ቍ 18-23 ) የሚጠቀልም ሲሆን ም12 ግን በተቃራኒው ለእግዚ አብሔር ሕግ አለመታዘዝ ፍርድ እንደሚያስከትል ይናገራል።

11፥2 *ሸማያ፤* ነቢያት የእግዚአብሔርን ሕግ የመን ከባከብና የመጠበቅ ኀላፊነት የተሰጣቸው የእግዚአብሔር መን ግሥት ሞግዚቶች መሆናቸውን ዜና መዋዕሉ በጕልህ ያሳያል። ብዙዎቹ የይሁዳ ነገሥታት ከነቢያት ምክር ይቀበሉ እንደ ነበርም ተጠቅሶአል (ከ1ዜና መግቢያ "ዐላማና መሪ ሐሳብ" የሚ ለውን ይመ)።

11፥3 *በይሁዳና በብንያም ላሉ እስራኤላውያን፤* በዚህ ክፍል የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ትልቅ ግምት የሚሰጠው እስራኤላው ያን ሁሉ የሚለው ሐረግ በ1ነገ 12፥23 ላይ ለሚገኘው ተጓዳኙ ምንባብ የተለየ ነው።

11፥4 *ከእኔ ዘንድ ስለሆነ፤* 10፥15 ይመ።

*11፥5-10፤* እዚህ ላይ የተዘረዘሩት ከተሞች በመጽሐፈ ነገሥት ላይ አይገኙም። ሮብዓም በምሥራቅ፣ የምዕራብና በደቡብ በኩል ለድንበሮቹ ምሽግ ሲሠራላቸው፣ በስተ ሰሜን ግን አለመ ሥራቱ ሁለቱን መንግሥታት ለማዋሐድ ተስፋ ስለ ነበረው ወይም ግብፅ ብትወረው ለመሸሽ እንዲመቸው እስቦ ያደረገው ሊሆን ይችላል።

*11፥13-17፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ፣ አንባቢዎች በ1ነገ12፥26-33 የተጻፈውን ታሪክ በሚገባ እንደሚያውቁት ይገምታል። ይህ ክፍል በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ብቻ የሚገኝ ሲሆን ጸሓፊው ስለ ቤተ መቅደሱና ስለ አገልጋዮቹ እንዲሁም የይሁዳ መንግሥት የእስራኤል ሁሉ ቅሬታ ስለ መሆኑ የሰጠውን ትኵረት ያን ጸባርቃል።

11፥14 *ማሰማሪያ ቦታዎቻቸውንና ንብረታቸውን፤* 1ዜና 6፥54-80፤ ዘሌ25፥32-34፤ዘኍ35፥1-5 እንዲሁም ከ1ዜና መግቢያ "ዐላማና መሪ ሐሳብ" የሚለውን ይመ።

11፥15 *የፍየልና የጥጃ ምስሎች፤* መጽሐፈ ነገሥት የሚያ ወሣው ስለ ወርቅ ጥጃ ብቻ ነው (የፍየል ምስል ወይም ግማሽ አካሉ ፍየልና ግማሽ አካሉ ሰው የሆነ የጣዖት አምልኮን በተመ ለከተ ዘሌ17፥7 ይመ)።

11፥17 *ለሦስት ዓመት፤* የ12፥2 ማብ ይመ። *የዳዊትንና የሰሎሞንን መንገድ፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ስለ ሰሎሞን ያለውን ከፍተኛ አድናቆት ያመለክታል፤ በነገ11፥1-13 ስለ ሰሎሞን የተሰጠውን ገለጻ ከዚህ ክፍል ጋር ያነጻጽሩ።

*11፥18-22፤* ጸሓፊው በዚህ ክፍል የሮብዓምን ቤተ ሰብ ብዛት መጥቀሱ በመታዘዙ ምክንያት እግዚአብሔር ምን ያህል እንደባረከው ለማሳየት ፈልጎ ነው (የ11፥1-23 ማብ ይመ)። የታሪኩ አቀማመጥ ከዐውዱ አኳያ ሲታይ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ አይደለም፤ ይሁን እንጂ በዘመነ መንግሥቱ የተፈጸሙትን ድርጊቶች እጥር ምጥን አድርጎ ያቀርበዋል። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የዘር ወይም የትውልድ ብዛት የእግዚአብሔር በረከት መግለጫ እንደ ሆነ ያምናል (13፥21 እንዲሁም የ21፥2፤ የ1ዜና 25፥5 ማብ ይመ)።

*11፥20 የአቤሴሎምን ልጅ መዓካን፤* የ1ነገ15፥2 ማብ

የተባለች፣ የእሴይ የልጅ ልጅ የኤልያብ ልጅ ነበረች። 19እርስዋም የዑስ፣ ሰማርያና ዛሃም የተባሉ ወንዶች ልጆች ወለደችለት። 20ከዚያም የአቤሴሎምን ልጅ መዓካን አገባ፤ እርሷም አብያ፣ ዓታይ፣ ዚዛ፣ ሰሎሚት የተባሉትን ወለደችለት። 21ሮብዓም መዓካን ከሌሎቹ ሚስቶቹና ቁባቶቹ ይልቅ አብልጦ ወደዳት። ባጠቃላይ ዐሥራ ስምንት ሚስትና ስልሣ ቁባት፣ ሃያ ስምንት ወንድና ሥልሳ ሴት ልጆች ነበሩት።

22ሮብዓም የማዕካን ልጅ አቢያን ሊያነግሥ ስለ ፈለገ ከልዑላን ወንድሞቹ አልቆ ዋና አደረገው። 23ከወንዶች ልጆቹም ጥቂቱን በይሁዳና በብንያም አውራጃዎች እንዲሁም በተመሸጉት ከተሞች ስለ ሾማቸው፣ ዘዴኛነቱን አሳይቶአል። የሚያስፈልጋቸውን በብዛት ሰጣቸው፤ ብዙ ሚስቶችም አጋባቸው።

## ሺሻቅ በኢየሩሳሌም ላይ ዘመተ

12፥9-16ተን ምብ— 1ዜና14፥21፡25-31

**12** ሮብዓም መንግሥቱን ከመሠረተና ካጸና በኋላ እርሱና እስራኤል* ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕግ ተዉ። 2እግዚአብሔርን ከመበደላቸው የተነሣም፣ ሮብዓም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት የግብፅ ንጉሥ ሺሻቅ በኢየሩሳሌም ላይ ዘመተ። 3ከግብፅ አብረውት የመጡትን ዐሥራ ሁለት ሺህ ሠረገላዎች፣ ስድሳ ሺ ፈረሰኞችና ስፍር ቍጥር የሌላቸውን የሊብያ፣ የሱኪምና የኢትዮጲያ ወታደሮች ይዞ፣ 4የተመሸጉትን የይሁዳ ከተሞች በቁጥጥሩ ሥር በማድረግ እስከ ኢየሩሳሌም ዘለቀ።

5ከዚህ በኋላ ነቢዩ ሸማያ ወደ ሮብዓምና ሺሻቅን ፈርተው በኢየሩሳሌም ወደ ተሰበሰቡት ወደ እስራኤል መሪዎች መጥቶ፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ 'እናንተ ትታችሁኛል፤ ስለዚህ እኔም በሺሻቅ እጅ ትቼአችኋለሁ' " አላቸው።

6የእስራኤል መሪዎችና ንጉሡ ራሳቸውን በማዋረድ፣ "እግዚአብሔር ጻድቅ ነው" አሉ።

7እግዚአብሔርም ራሳቸውን እንዳዋረዱ ባየ ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ ሸማያ መጣ፤ "ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ስላዋረዱ እታደጋቸዋለሁ እንጂ አላጠፋቸውም፤ ቍጣዬም በሺሻቅ እጅ በኢየሩሳሌም ላይ አይፈስስም። 8ይሁን እንጂ እኔን በማገልገልና የሌሎችን አገሮች ነገሥታት በማገልገል መካከል ያለውን ልዩነት ያውቁ ዘንድ፣ ለእርሱ ይገዛሉ።"

9የግብፅ ንጉሥ ሺሻቅ ኢየሩሳሌምን በወረረ ጊዜ፣ የቤተ መቅደሱን ንብረትና የቤተ መንግሥቱን ንብረት ዘርፎ ወሰደ፤ ሰሎሞን ያሠራው የወርቅ ጋሻ ሳይቀር፣ እንዳለ ሁሉንም አጋዘው። 10ንጉሥ ሮብዓምም በተወሰዱት ፈንታ የናስ ጋሻዎች ሠርቶ፤ የቤተ መንግሥቱን ቅጥር በሮች ለሚጠብቁ የዘብ አለቆች በኀላፊነት ሰጠ። 11ንጉሡ ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በሚሄድበት ጊዜ ሁሉ፣ ዘበኞቹ ጋሻዎቹን አንግበው ያጅቡት ነበር፤ ከዚያም በኋላ ጋሻዎቹን ወደ ዘበኞች ክፍል ይመልሱ ነበር።

12ሮብዓም ራሱን ዝቅ አድርጎ ስላዋረደ የእግዚአብሔር ቍጣ ከእርሱ ተመለሰ፤ ፈጽሞም አላጠፋውም፤ በይሁዳም ደግሞ በጥቂቱም ቢሆን መልካም ነገር ተገኝቶ ነበር።

13ንጉሥ ሮብዓም በሚገባ ተደላድሎ በኢየሩሳሌም በንጉሥነቱ ቀጠለ፣ ሲነግሥ ዕድሜው አርባ አንድ ዓመት ነበር፤ እግዚአብሔር ስሙን በዚያ ለማኖር ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ በመረጣት በኢየሩሳሌም ከተማ ተቀምጦም፣ ዐሥራ ሰባት ዓመት ገዛ፤ እናቱም

11፥20 1ነገ15፥2፤ 2ዜና12፥16፤13፥2
11፥21 ዘዳ17፥17
11፥22 ዘዳ21፥15-17
11፥23 2ዜና21፥3
12፥1 ቍ13፤ 1ዜና9፥1፤2ዜና1፥1፤7፥19፤11፥17
12፥2 1ነገ11፥40፤14፥22-24፤ 1ዜና5፥25
12፥3 ዘፍ10፥6፤ 2ዜና14፥9፤16፥8፤ኢሳ18፥2፤ዳን11፥43፤አሞ9፥7፤ናሆ3፥9
12፥4 2ዜና11፥10
12፥5 ዘዳ28፥15፤ 2ዜና11፥2
12፥6 ዘፀ9፥27፤ ዘሌ26፥41፤2ዜና6፥37፤ዕዝ9፥15፤ መዝ11፥7፤116፥5፤ ዳን9፥14
12፥7 ዘዳ9፥19፤ መዝ69፥24፤78፥38፤ ኤር7፥20፤42፥18፤ ሕዝ5፥13
12፥8 ዘዳ8፥48
12፥9 2ዜና9፥16
12፥12 1ነገ14፥13፤ 2ዜና6፥37፤19፥3
12፥13 ቍ1፤ዘፀ20፥24፤ዘዳ12፥5፤ 1ነገ2፥12

*1ዜና ካልዕ መጽሐፍ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው ይህ የይሁዳ ክፍል ነው
°2ብዙ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች የሱርስቱ ቅጂ (እንዲሁም 2ዜና 11፥20 እና 1ነገ15፥2) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን ሚካያ ይላል።

ይመ። የልጁ ልጅ የትዕማር ልጅ ሳትሆን አትቀርም (2ሳሙ14፥27፤18፥18)፤ ትዕማር የዑሩኤል ሚስት ነበረች (2ዜና 13፥2)።

*11፥21-22፤* የሮብዓም የበኵር ልጁ ለምን በዙፋኑ እንዳልተተካ ከዚህ ክፍል መረዳት ይቻላል።

11፥23 *ስለ ሾማቸው፤* ሮብዓም አብያ በእርሱ ፋንታ እንዲነግሥ ስለ ፈለገ ሌሎች ልጆቹን በመሾም ሩቅ ወደ ሆኑ ግዛቶች መላኩ፣ አዶንያስና አቤሰሎም ሥልጣኑን ለመንጠቅ በአባታቸው በዳዊት ላይ ባመፁ ጊዜ የፈጠሩት ዐይነት ችግር በድጋሚ እንዳይከሰት አስቦ ያደረገው ሊሆን ይችላል።

*12፥1-14፤* የ11፥1-23 ማብ ይመ። ለትንቢቱ ቃል መታዘዝ በረከት የሚያመጣ ሲሆን 11፥1-4፣ በዚህ ስፍራ ግን ነቢዩ ለቃሉ አለመታዘዝ (14፥25-28) ፍርድ የሚያስከትል መሆኑን ይናገራል። የነገሥት ጸሐፊ የሺሻቅን ወረራ ሲዘግብ፣ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ግን የወረራው ምክንያት የእግዚአብሔርን ሕግ ከመተላለፍ የመነጨ መሆኑን በተጨማሪ ይገልጻል።

12፥1 *እስራኤል ሁሉ፤* ሐረጉ በዚህ መጽሐፍ የተለያዩ ነገሮችን ያመለክታል፤ ይኸውም፦ (1) የሰሜኑንና የደቡቡን መንግሥት (9፥30)፤ (2) የሰሜኑን መንግሥት ብቻ (10፥16፤ 11፥13) ወይም (3) የደቡቡን መንግሥት ብቻ (እዚህ ላይ እንደተጻፈው ማለት ነው፤ እንዲሁም (11፥3) ለማሳየት ገብቶአል። *ተዉ፤* "እግዚአብሔርን ፈለጉ" ከሚለው ቃል ጋር ተቃራኒ ነው (ቍ14፤) ቍ5 ይመ፤ እንዲሁም የ24፥18፡20፡24 ማብ ይመ።

*12፥2 ሺሻቅ፤* በግብፅ አገር የሀያ ሁለተኛው ሥርወ መንግሥት መሥራች ነው፤ የገዛውም ከ945-924 ዓ.ቅ.ክ. ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ይህ የሺሻቅ ወረራ ኢየሩሳሌምን እንደጐዳት ብቻ ይገልጻል፤ ነገር ግን ሺሻቅ፣ ካርናክ (ቴብስ) ባለው በአሞን ቤተ ጣዖት ግድግዳ ላይ ያስቀረጸው የራሱ ጽሑፍ እንደሚያመለክተው የእርሱ ሰራዊት በዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ ወደ ሰሜን ከኢይዝራኤል ሜዳ፣ እስከ መጊዶን ድረስ በመዝለቅ ወረራ አካሂዶአል። *በአምስተኛው ዓመት፤* 925 ዓ.ቅ.ክ. ማለት ነው። የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ አብዛኛውን ጊዜ በመጽሐፈ ነገሥት ተጽፎ የማይገኝ የዘመናት ቅደም ተከተል ያስተዋውቃል (ለምሳሌ 11፥17፤15፥10፡19፤16፥1፡12-13፤17፥7፤21፥20፤24፥15፡17፡23፤ 26፥16፤ 27፥5፡8፤ 29፥3፤34፥3፤36፥21)። ጸሐፊው የእያንዳንዱን ንጉሥ የግዛት ዘመን በመታዘዝ በረከት፣ ባለመታዘዝ ቅጣት በሚል ሁለት ቦታ ከፍሎ በማስቀመጥ፣ ነገሥታቱ ለእግዚአብሔር በታዘዙበት ጊዜ ወዲያውኑ ያገኙትን በረከት፣ ባልታዘዙበትም ጊዜ ወዲያውኑ የደረሰባቸውን ቅጣት አሳይቶአል። ይህም በሮብዓም ላይ ተራ በተራ ሲፈጸም ታይቶአል፤ ይኸውም ሦስት ዓመት ታዝዞ በረከት ካገኘ በኋላ (11፥17) በአራተኛው ዓመት ስላመፀ በአምስተኛው ዓመት (እዚህ ላይ እንደምናገኘው) ቅጣቱን ተቀብሎአል።

12፥3 *የሱኪምና፤* የግብፃውያን ጽሑፍ እንደሚያስረዳው የጥንት የዘር ግንዳቸው ከሊቢያ ሲሆን፣ እነርሱም በግብፃውያን ጐን የተሰለፉ ቅጥረኛ ወታደሮች ሳይሆኑ አይቀሩም።

*12፥5* የቍ1-14፤ ማብ እና ቍ1 ይመ ።

*12፥6-7፤* ቍ12 ይመ። እዚህ ላይ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በ7፥14 ላይ የሚገኘው የእግዚአብሔር ተስፋ ትዝ ብሎታል።

12፥13፤ *ዐሥራ ሰባት ዓመት፤* የ10፥1 ማብ ይመ።

*12፥15-16* 1ነገ 14፥29-31 ይመ።

ናዕማ የምትባል አሞናዊት ነበረች:: 14እግ
ዚአብሔርን ይሻ ዘንድ ልቡን ስላላዘጋጀ
ክፉ ነገር አደረገ::
15ሮብዓም በዘመነ መንግሥቱ ያከናወናቸው
ተግባሮች ሁሉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ
ድረስ ነቢዩ ሸማያ በጻፈው የታሪክ መዝገብና
በባለ ራእዩ አዶ በዘገበው የትውልድ ሐረግ
ታሪክ የሚገኝ አይደለምን? በሮብዓምና በኢ
ዮርብዓም መካከል የማያቋርጥ ጦርነት
ነበር:: 16ሮብዓም እንደ አባቶቹ ሁሉ አንቀላፋ፤
በዳዊትም ከተማ ተቀበረ፤ ልጁ አብያም በእርሱ
ፈንታ ነገሠ::

## የይሁዳ ንጉሥ አብያ

13፥1-2፡22-14፥1 ተጓ ምብ—1ዜና15፥1-2፡6-8

**13** ኢዮርብዓም በነገሠ በዐሥራ ስምን
ተኛው ዓመት አብያ በይሁዳ ነገሠ::
2በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ሦስት ዓመት ገዛ::
እናቱ ሚካያ[a] ትባላለች፤ እርስዋም የገብዓ
ተወላጅ የኡርኤል ልጅ ነበረች::
በአብያና በኢዮርብዓምም መካከል ጦርነት
ነበር:: 3አብያ አራት መቶ ሺህ ብርቱ
ተዋጊዎች ይዞ ዘመተ፤ ኢዮርብዓምም ስምንት
መቶ ሺህ ብርቱ ተዋጊዎች ይዞ በመውጣት
ጠበቀው::
4አብያ በኰረብታማው በኤፍሬም አገር
በጽማራይም ተራራ ላይ ቆሞ፣ እንዲህ አለ፤
"ኢዮርብዓምና እስራኤል ሁሉ አድምጡኝ!
5የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ዳዊትና
ዘሮቹ በእስራኤል ላይ ለዘላለም እንዲነግሡ
በጨው ኪዳን የሰጣቸው መሆኑን አታውቁ
ምን? 6የዳዊት ልጅ የሰሎሞን ባሪያ የነበረው
የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ግን በጌታው ላይ
ዐመፀ:: 7የሰሎሞን ልጅ ሮብዓም ገና ሕፃን
ሳለ፣ ምንም ማድረግ በማይችልበትና እነር
ሱንም ለመቋቋም አቅሙ በማይፈቅድለት
ጊዜ የማይረቡ ጥቂት ወሮበሎች በዙሪያው
ተሰበሰቡበት፣ በረቱበትም::
8"አሁንም እናንተ በዳዊት ዘርዐ-ትውልድ
እጅ ያለውን የእግዚአብሔርን መንግሥት
ልትቋቋሙ አስባችኋል:: በእርግጥም በሰራ
ዊት ረገድ እጅግ ብዙ ናችሁ፤ አማልክቶቻችሁ
ይሆኑ ዘንድ ኢዮርብዓም የሠራቸውንም የወ
ርቅ ጥጆች ይዛችኋል:: 9ደግሞስ የአሮን
ልጆች የሆኑትን ካህናትና ሌዋውያን አባር
ራችሁ፣ ሌሎች ሕዝቦች እንደሚያደርጉት
ሁሉ፣ እናንተም የራሳችሁን ካህናት አልሾ
ማችሁምን? አንድ ኮርማና ሰባት አውራ
በግ ይዞ ራሱን ለመቀደስ የሚመጣ ማናቸውም
ሰው አማልክት ላልሆኑ ለእነዚያ ጣዖታት
ካህን ይሆናል::
10"ለእኛ ግን አምላካችን እግዚአብሔር ነው፤
እርሱንም አልተውነም፤ እግዚአብሔርን በማ
ገልገል ላይ ያሉት ካህናት የአሮን ልጆች
ሲሆኑ፣ ረዳቶቻቸውም ሌዋውያኑ ናቸው::
11እነርሱም በየጧቱና በየማታው የሚቃጠል
መሥዋዕትና ሽታው ደስ የሚያሰኝ ዕጣን ለእግ
ዚአብሔር ያቀርባሉ፤ የገጹን ኅብስት በሥ
ርዐቱ መሠረት በንጻው ጠረጴዛ ላይ ያኖራሉ፤
በየማታውም በወርቁ መቅረዝ ላይ ያሉትን
ቀንዲሎች ያበራሉ፤ እኛም የአምላካችንን
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንፈጽማለን፤ እናንተ ግን
ትታችሁታል:: 12እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፤
መሪአችንም እርሱ ነው:: መለከት የያዙ
ካህናቱም የጦርነቱን ድምፅ በእናንተ ላይ
ያሰማሉ:: እናንተ የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤
አይቀናችሁምና፣ ከአባቶቻችሁ አምላክ ከእግዚ
አብሔር ጋር አትዋጉ::"
13በዚህ ጊዜ ኢዮርብዓም ከሰራዊቱ ከፊሉን
ከይሁዳ ሰራዊት በስተ ጀርባ እንዲያደፍጡ
ላከ፤ የቀረውም ሰራዊት ከእርሱ ጋር የይሁዳን
ሰራዊት ፊት ለፊት እንዲገጥሙ አደረገ፤ 14የይ
ሁዳም ሰዎች ዙሪያቸውን ሲመለከቱ ከፊትና
ከኋላ መከበባቸውን አዩ፤ ወደ እግዚአብሔርም
ጮኹ፤ ካህናቱም መለከታቸውን ነፉ:: 15የይ
ሁዳም ሰዎች በሩከራ የጦርነት ድምፅ አሰሙ፤
እግዚአብሔር ኢዮርብዓምንና እስራኤልን ሁሉ
በአብያና በይሁዳ ፊት ፈጽሞ መታቸው:: 16እስራ
ኤላውያን ከይሁዳ ፊት ሸሹ፤ እግዚአብሔርም
በእጃቸው አሳልፎ ሰጣቸው:: 17አብያና ሰዎቹም
ከባድ ጉዳት አደረሱባቸው፤ ከዚህ የተነሣም
ከእስራኤል ብርቱ ተዋጊዎች መካከል አምስት
መቶ ሺህ ሰዎች ተገደሉ:: 18በጦርነቱም
የእስራኤል ሰዎች ተዋረዱ፣ የይሁዳ ሰዎች ግን

12፥15 2ዜና11፥2
12፥16 1ዜና3፥10፤ 2ዜና11፥20
13፥2 1ነገ15፥6፤ 2ዜና11፥20፤15፥16
13፥4 ኢሱ18፥22፤ 1ዜና11፥1
13፥5 ዘሌ2፥13፤ 2ሳሙ7፥13፤ 1ዜና17፥12
13፥6 1ነገ11፥26
13፥7 መሳ9፥4፤ 1ዜና29፥1
13፥8 ዘፀ32፥4፤ 1ሳሙ4፥3፤2ዜና9፥8፤ 11፥15
13፥9 ዘፀ29፥31፡ 35-36፤1ነገ12፥31፤ 2ዜና11፥14-15፤ ኤር2፥11፤ገላ4፥8
13፥11 ዘፀ25፥6፡ 37፤29፥39፤1ዜና9፥3 2፤2ዜና2፥4
13፥12 ዘኍ10፥8-9፤መሳ2፥15፤ ኢዮ9፥4፤ ምሳ21፥30፤29፥1፤ ሐሥ5፥39
13፥13 ኢሱ8፥9፤ 2ዜና20፥22
13፥14 1ዜና5፥20፤ 2ዜና14፥11፤18፥31
13፥15 1ዜና9፥1
13፥16 2ዜና16፥8
13፥18 2ዜና14፥ 11፤ 16፥7፤ መዝ22፥5

*13፥1-14፥1፤* የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በዚህ ክፍል ስለ አብያ ዘመነ መንግሥት ያቀረበው ታሪክ በ1ነገ15፥1-8 ላይ ከተገለጸው ሦስት ዕጥፍ ይረዝማል፤ ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት አብያ ረጅም ንግግር ስላደረገ ነው (13፥4-12፤ እንዲሁም የ28፥1-27 ማብ ይመ):: የአብያን ዘመነ መንግሥት በተመለከተ በመጽሐፈ ነገሥቱና በዜና መዋዕሉ መካከል እጅግ የሚያስደንቀው ልዩነት፣ እያንዳንዳቸው የሰጡት አስተያየት ነው፤ የመጽሐፈ ነገሥቱ አስተያየት አፍራሽ ሲሆን (1ነገ15፥3)፣ ሰፋ ያለ ማስረጃ አያቀርብም፤ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ግን ስለ አብያ ያለውን አዎንታዊ አስተያየት በማስረጃ ያቀርባል:: የንጉሡ የአገዛዝ ዘመን እንደ ማናቸውም ተራ ሰው ሕይወት ሁሉ፣ መልካሙንም ክፉውንም ቀላቅሎ የያዘ ነው::

13፥2 *ሦስት ዓመት፤* ከ913-910 ዓ.ቅ.ክ. ማለት ነው:: *ሚካያ፤* የ11፥20፡ ማብ ይመ::

13፥3 *አራት መቶ ሺህ...... ስምንት መቶ ሺህ፤* እጅግ ከፍ ያለ ቍጥር ሲሆን፣ በ1ዜና 21፥5ማብ ይመ ላይ ከተጻፈው ጋር ማብ ይመ ተመሳሳይነት አለው:: ይህም ያለ የሌለ ኀይሉን ያሰለፈበት ጦርነት መሆኑን ያመለክታል::

13፥4 *በጽማራይም ተራራ፤* ትክክለኛ ቦታው አይታወቅም፤ ጽማራይም የተባለ ከተማ ግን በብንያም ግዛት ውስጥ ነበር (ኢሱ 18፥22)፤ ጦርነቱም የተካሄደው በብንያምና በእስራኤል የጋራ ወሰን ላይ ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል:: *እስራኤል ሁሉ፤* የ12፥1 ማብ ይመ:: ይህ ሐረግ በዚህና በቍ15 ላይ የሚያመለክተው የሰሜኑን መንግሥት ነው::

*13፥5፤7፥17-18፤* 1ዜና17፥13-14 ይመ:: *በጨው ኪዳን፤* የዘሌ 2፥13፤ የዘኍ18፥19፤የ2ነገ 2፥20 ማብ ይመ::

13፥6፤ የ10፥1-19 ማብ ይመ

*13፥7* ዘለፋው የሚያመለክተው በሰሜኑ መንግሥት ሥር ያሉትን ሁሉ ሳይሆን፣ መሪዎቹን ብቻ ነው፤ ይህም የዐመፁ ተካፋይ ሆነው ለጦርነት የተሰለፉትን የሰሜኑን ወታደሮች ልብ ለመስረቅ የተደረገውን ዘዴ ያመለክታል:: *የማይረቡ፤* የዘዳ 13፥13 ማብ ይመ:: *ገና ሕፃን ሳለ፤* ከ1ዜና 22፥5፤29፥1 ጋር ያነጻጽሩ::

13፥8 *የእግዚአብሔርን መንግሥት፤* የዳዊት ቤት የእግዚ አብሔርን መንግሥት ይወክላል (9፥8 እና ማብ ይመ)::

*13፥9፤* 1ነገ12፥25-33 ይመ:: *ራሱን ለመቀደስ፤* ከዘፀ29፥1 ጋር ያነጻጽሩ::

*13፥10-12፤* ከዜና መዋዕሉ ጸሐፊ እይታ አኳያ ተቀባይነት ያለው ሕጋዊ በሆኑ ካህናት የሚካሄድና በሥርዐቱ መሠረት

በአባቶቻቸው *አምላክ* በእግዚአብሔር ታምነዋልና
ድል ነሡ::
19አብያም ኢዮርብዓምን አሳድዶ የቤቴልን፣
የይሻናንና የዔፍሮንን ከተሞች ከነመ
ንደሮቻቸው ወሰደበት:: 20ኢዮርብዓም በአብያ
ዘመን እንደ ገና ሊያንሠራራ አልቻለም፤
ከዚያም *እግዚአብሔር* ስለ ቀሠፈው ሞተ::
21አብያ ግን ይበልጥ እየበረታ ሄደ፤ ዐሥራ
አራት ሚስቶች አግብቶም ሃያ ሁለት ወን
ዶችና ዐሥራ ስድስት ሴቶች ልጆች ነበሩት::
22በአብያ ዘመን የተከናወነው ተግባር፣
እርሱ የፈጸመውና የተናገረው ሁሉ በነቢዩ
በአዶ የታሪክ መዛግብት ተጽፎአል::

**14** አብያ እንደ አባቶቹ ሁሉ አንቀላፋ፤
በዳዊትም ከተማ ተቀበረ፤ ልጁም አሳ
በእርሱ ፈንታ ነገሠ፤ በዘመኑም በምድሪቱ ለዐ
ሥር ዓመት ሰላም ሆነ::

### የይሁዳ ንጉሥ አሳ

14፥2-3ተዳ ምብ—1ዜና15፥11-12

2አሳ *በአምላኩ* በእግዚአብሔር ፊት መልካ
ምና ቅን የሆነውን ነገር አደረገ፤ 3ባዕዳን
መሠዊያዎችንና ማምለኪያ ኰረብታዎችን
አስወገደ፤ ማምለኪያ ዐምዶችን አፈረሰ፤
አሼራ ለተባለች ጣዖት አምላክ የቆሙ የዕ
ንጨት ቅርጽ ምስሎችንም[+] ቈራረጠ፤
4የአባቶቻቸውን *አምላክ* እግዚአብሔርን እንዲ
ፈልጉ፣ ሕጉንና ትእዛዙንም እንዲፈጽሙ
የይሁዳን ሕዝብ አዘዘ:: 5ከእያንዳንዱም
የይሁዳ ከተሞች የየኰረብታውን መስገጃ
ስፍራዎችንና የዕጣን መሠዊያዎችን አስወገደ፤
መንግሥቱም በእርሱ አገዛዝ ዘመን ሰላም
አገኘች:: 6በምድሪቱ ሰላም ስለ ሰፈነ፣
በይሁዳ የተመሸጉ ከተሞችን ሠራ:: *እግዚ
አብሔር* ዕረፍት ስለ ሰጠውም፣ በዘመኑ የተ
ዋጋው ማንም አልነበረም::
7እርሱም ለይሁዳ ሕዝብ እንዲህ አላቸው፤
"እነዚህን ከተሞች እንሥራ፤ ማማ፣ መዝጊያና
መወርወሪያ ያላቸውን ቅጥሮች በዙሪያቸው
እናብጅ:: *አምላካችንን* እግዚአብሔርን ስለ
ፈለግነው ምድሪቱ አሁንም የኛው ናት፤
እኛ ፈለግነው፤ እርሱም በሁሉም አቅጣጫ
ዕረፍት ሰጠን" እነርሱም ሠሩ፤ ተከናወነላ
ቸውም::
8አሳ ታላላቅ ጋሻና ጦር የያዙ ሦስት
መቶ ሺህ የይሁዳ ሰዎች እንዲሁም ጋሻና
ቀስት የያዙ ሁለት መቶ ሰማንያ ሺህ የብን
ያም ሰዎች ነበሩት፤ እነዚህ ሁሉ ብርቱ
ተዋጊዎች ነበሩ::
9ኢትዮጲያዊው ዝሪ አንድ ሚሊዮን[*] ሰራ
ዊትና ሦስት መቶ ሠረገላ ይዞ በመውጣት
እስከ መሪሳ ድረስ መጣባቸው:: 10አሳም ሊገ
ጥመው ወጣ፤ መሪሳ አጠገብ ባለው በጽፋታ
ሸለቆም የውጊያ ቦታ ቦታቸውን ያዙ::
11በዚህ ጊዜ አሳ ወደ *አምላኩ* ወደ እግዚ
አብሔር እንዲህ ሲል ጮኸ፤ "*እግዚአብሔር*
ሆይ፤ ደካሞችን ከኀይለኞች የሚታደግ
እንደ አንተ ያለ ማንም የለም፤ አምላካችን
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ በአንተ ታምነናልና፣
ይህን ታላቅ ሰራዊት በስምህ እንነጥመዋለን፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ አምላካችን አንተ ነህ፤

+3 በሁለተኛው የዜና መዋዕል መጽሐፍ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው
ይህ አሼራ የምትባለው ጣዖት አምላክ ምስል ነው::
*9 ዕብራይስጡ *ለአፋፍ ወይም እልፍ ጊዜ እልፍ ይላል*::

14፥2 2ዜና21፥12
14፥3 ዘፀ23፥24፤ 34፥13፤መሳ2፥2
14፥4 1ዜና16፥11
14፥5 1ነገ15፥14፤ ኢሳ27፥9፤ሕዝ6፥4
14፥6 1ዜና22፥9
14፥7 1ዜና22፥9
14፥8 1ዜና21፥1
14፥9 ዘፍ10፥8-9፤2ዜና11፥8፤12፥3፤ 24፥24
14፥11 1ሳሙ17፥45፤ 1ነገ8፥44፤ 2ዜና13፥14፡18፤ 25፥8፤ መዝ9፥19፤60፥11-12፤79፥9

---

የሚከናወን አምልኮ ነው (ከ1ዜና23፥28-31 ጋር ያነጻጽሩ)::

13፥21፡ የ11፥18-22 ማብ ይመ::

14፥1 *ለዐሥር ዓመት ሰላም፤* ለዜና መዋዕሉ ጸሐፊ፣ ሰላምና ብልጽግና ከጽድቅ አገዛዝ ጋር የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው:: አሳ ከነገሠ ከዐሥር ዓመት በኋላ (910-900 ዓ.ቅ.ክ.) ዝሪ ወረራ አካሄደ (14፥9-15)፤ ከዚያ በኋላ ከዐሥራ አምስተኛው (15፥10) እስከ ሠላሳ አምስተኛው ዘመነ መንግስሥቱ ያለው የሃያ ዓመት ጊዜ (15፥19) ሰላም የሰፈነበት ነበር:: ይህን ክፍል በአሳና በባኦስ መካከል በዘመነ መንግሥታቸው ሁሉ ጦርነት እንደ ነበር ከሚያወሣው ታሪክ ጋር ያነጻጽሩ (1ነገ 15፥16 እና ማብ ይመ):: አሳ ምሽጎችን እንዲሠራ ምክንያት የሆነው በሁለቱ መንግሥታት መካከል የተፈጠረው ውጥረት ነው (14፥7-8)፤ ምንም እንኳ በሁለቱ መካከል አልፎ አልፎ ድንገተኛ ግጭትና ትንኮሳ ቢኖርም አሳ በነገሠ በ36ኛው ዓመት (16፥1) ላይ አሳ ሰራዊቱን እስካዘመተበት ጊዜ ድረስ ይህን ያህል ከቍጥር የሚገባ ጦርነት በመካከላቸው አልነበረም (15፥8 እና ማብ ይመ)::

14፥2-16፥14 እዚህ ላይ የአሳን ዘመነ መንግሥት (910-869 ዓ.ቅ.ክ) በተመለከተ የተወሣው ታሪክ በ1ነገ15፥9-24 ላይ ከተጻፈው ይልቅ ተስፋፍቶ የቀረበ ነው፤ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ታሪኩን አስፋፍቶ ያቀረበበትም ምክንያት መታዘዝ በሚያስገኘው በረከትና አለመታዘዝ በሚያስከትለው ቅጣት መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት ነው:: ጸሐፊው የአሳን ዘመነ መንግሥት ታሪክ በሚጽፍበት ጊዜ፣ ለመከፋፈል ያመቸው ዘንድ በቅደም ተከተል አስቀምጦታል (የ12፥2 ማብ ይመ):: አሳ ለዐሥር ዓመት ያህል በአካሄዱ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘ፤ ስለዚህም ያሰበው ተከናወነለት (14፥1-7)፤ ወደ እግዚአብሔር ስለ ጮኸም ኀይለኛው የኩሽ ሰራዊት ወረራ ሊደመሰስ ችሎአል (14፥8-15):: ከዚያም ተሐድሶው ይቀጥልና (15፥1-9)፤ በአሳ በ15ኛው ዓመት (15፥10-18) ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጽናት እንደገና ቃል ኪዳኑን አደሰ፤ አሳም እስከ ሠላሳ አምስተኛው ዘመነ መንግሥቱ ድረስ ደስ ብሎት በሰላም ኖረ:: በሠላሳ ስድስተኛው ዘመነ መንግሥቱ ላይ ግን የሰሜኑ መንግሥት ወረራ ባካሄደበት ጊዜ (16፥1) እንደ በፊቱ ሁሉ በአምላኩ በእግዚአብሔር በመታመን ፈንታ፣ የሶርያን ንጉሥ ርዳታ ጠየቀ (16፥2-6)፤ የገሠጸውንም ነቢይ አሰረው (16፥7-10)፤ በሠላሳ ዘጠነኛው ዘመነ መንግሥቱ ክፉኛ ታመመ (16፥12)፤ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር እንዲረዳው አልተማጠነውም፤ እርሱም በአርባ አንደኛው ዘመነ መንግሥቱ ሞተ (16፥13)::

14፥3፤ *ማምለኪያ ዐምዶችን፤* የ1ነገ14፥23 ማብ ይመ::

14፥5 *ማምለኪያ ኰረብታዎችን አስወገደ፤* 1ነገ 15፥14 የሚያወሣው አሳ እነዚህን የማምለኪያ ስፍራዎች እንዳላስወገደ ነው፤ ይህም ችግር ራሱ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በ15፥17 ላይ ባሰፈረው ጽሑፍ በሚገባ መልስ አግኝቶአል፤ ይህም ከ1ነገ 15፥14 ጋር ይስማማል:: አሳ በዘመነ መንግሥቱ መጀመሪያ ላይ ማምለኪያ ኰረብታዎችን ለማስወገድ ከፍተኛ ጥረት ቢያደርግም የጣዖት አምልኮ እጅግ ተንሰራፍቶ ስለ ነበር ጥረቱ ሊሳካ አልቻለም (15፥17) የማምለኪያ ስፍራዎችን ማስወገድ መቻልና አለመቻልን በኢዮሳፍጥም ዘመነ መንግሥት ታይቶአል (17፥6፤20፥33) እንዲሁም ከዘጸ12፥2-3 ጋር ያነጻጽሩ::

14፥7፤ *በሁሉም አቅጣጫ፤* የ20፥30 ማብ ይመ::

14፥9፤ *(ኢትዮጵያዊው) ዝሪ፤* ይህ ሰው በሃያ ሁለተኛው የግብፅ ሥርወ መንግሥት የነገሠው ሁለተኛው ፈርዖን ማለትም ቀዳማዊኦስርኮን ነው የሚሉ አሉ:: ይሁን እንጂ "ንጉሥ" ወይም "ፈርዖን" የሚል ማዕረግ ስላልተቀጸለለትና "ኢትዮጵያዊው" (ወይም) "ኑብያዊው" በመባል ስለሚታወቅ አንድ ማንነቱ ያልተለየ የፈርዖን የጦር መሪ ሳይሆን አይቀርም የሚሉ አሉ:: ወረራው ከሠላሳ ዓመት በፊት (12፥1-12) ሺሻቅ ካደረገው ጋር ተመሳሳይ ነው፤ በውጤቱ ግን የአሳ ፈጽሞ የተለየ ነበር::

14፥10 *በጽፋታ ሸለቆም፤* ወደ ተራራማው አገር ወደ ይሁዳና ወደ ኢየሩሳሌም የሚወስደው ዋናው መንገድ የሚያልፈው በዚሁ አቋርጦ ነው:: *መሪሳ፤* እዚህ ላይ የተጠቀሰውን መንገድ ለመከላከል ቀደም ብሎ በሮብዓም የተመሸገ ነው (11፥8)::

ሰውም አያሸንፍህም::"
12እግዚአብሔርም ኢትዮጲያውያንን በአሳና
በይሁዳ ፊት መታቸው፤ ኢትዮጲያውያኑም
ሸሹ፤ 13አሳና ሰራዊቱም እስከ ጌራራ ድረስ
አሳደዷቸው፤ እጅግ ብዙ ቊጥር ያላቸው
ኢትዮጲያውያን ስለወደቁም፣ ሊያንሰራሩ
አልቻሉም፤ በሰራዊቱም ፊት ተደመሰሱ::
የይሁዳም ሰዎች እጅግ ብዙ ምርኮ ወሰዱ::
14በጌራራ ዙሪያ ባሉት ከተሞች ሁሉ ላይ
ታላቅ ድንጋጤ *ከእግዚአብሔር* ዘንድ ስለ
ወደቀባቸው ከተሞቹን ሁሉ አጠፉቸው፤ እጅግ
ብዙ ምርኮም በዚያ ስለ ነበር፣ በዘበዟቸው::
15እንዲሁም በእረኞች ሰፈር ላይ አደጋ ጥለው
እጅግ ብዙ በጎች፣ ፍየሎችና ግመሎች
ማረኩ ወደ ኢየሩሳሌምም ተመለሱ::

## ንጉሥ አሳ ያደረገው ተሐድሶ

15፥16-19ተጓ ምብ—1ዜና15፥13-16

**15** የእግዚአብሔር መንፈስ በዖዴድ ልጅ
በአዛርያስ ላይ መጣ:: 2እርሱም አሳን
ሊገናኘው ወጣ፤ እንዲህም አለው፤ "አሳ፣
እናንተም ይሁዳና ብንያም ሁሉ ሆይ፤ አድ
ምጡኝ፤ እናንተ *ከእግዚአብሔር* ጋር ስትሆኑ፣
እርሱም ከእናንተ ጋር ይሆናል፤ ብትፈልጉት
ይገኝላችኋል፤ ብትተውት ግን፣ ይተዋችኋል::
3እስራኤል ያለ እውነተኛ አምላክ፣ ያለ
አስተማሪ ካህንና ያለ ሕግ ብዙ ዘመን አሳ
ልፈዋል:: 4በመከራቸው ጊዜ ግን፣ ወደ እስ
ራኤል *አምላክ* ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው
ፈለጉት፤ እርሱም ተገኘላቸው:: 5በዚያን
ዘመን በምድር ነዋሪዎች ሁሉ ዘንድ ታላቅ
ሁከት ስለ ነበር፣ በሰላም ወጥቶ መግባት
አስተማማኝ አልነበረም:: 6እግዚአብሔር በተለያየ
መከራ ያስጨንቃቸው ስለ ነበር፣ አንዱ
መንግሥት በሌላው መንግሥት፣ አንዱም
ከተማ በሌላው ከተማ ይደመሰስ ነበር::
7እናንተ ግን የድካማችሁን ዋጋ ስለምታገኙ
በርቱ፤ እጃችሁም አይላላ::"
8አሳ ይህን ቃልና የነቢዩን የዖዴድን ልጅ[ን]
የዓዛርያስን ትንቢት በሰማ ጊዜ በረታ::
ከመላው ይሁዳና ከብንያም ምድር፣ በኤፍ
ሬምም ኮረብታዎች ላይ ከያዛቸው ከተሞች
አስጸያፊዎቹን ባያታት አስወገደ:: *ከእግዚ
አብሔር* መቅደስ ሰበሰበ ፊት ለፊት የነበረ
ውንም *የእግዚአብሔር* መሠዊያ አደሰ::
9*አምላኩ* እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑን
ባዩ ጊዜ፣ ከእስራኤል ብዙ ሰዎች እርሱን
ተጠግተው ነበር፤ እርሱም ይሁዳንና ብንያምን
እንዲሁም ከኤፍሬም፣ ከምናሴና ከስምዖን
መጥተው ከእነርሱ ጋር የተቀመጡትን ሰበሰበ::
10እነርሱም በአሳ ዘመነ መንግሥት በዐሥራ
አምስተኛው ዓመት፣ በሦስተኛው ወር በኢ
የሩሳሌም ተሰበሰቡ:: 11በዚያን ጊዜ በምርኮ
ካመጡት ውስጥ ሰባት መቶ በሬ፣ ሰባት ሺ
በግና ፍየል *ለእግዚአብሔር* ሠዉ:: 12የአባ
ቶቻቸውንም *አምላክ* እግዚአብሔርን በፍጹም
ልባቸውና በፍጹም ነፍሳቸው ይሹ ዘንድ ቃል
ኪዳን አደረጉ:: 13የእስራኤልን *አምላክ* እግዚ
አብሔርን የማይፈልግ ሁሉ ግን፣ ትንሽም ሆነ
ትልቅ፣ ወንድም ሆነ ሴት እንዲገደል አደረጉ::
14ይህንንም በታላቅ ድምፅ፣ በእልልታ፣ በእምቢ
ልታና በመለከት ድምፅ *ለእግዚአብሔር*
ማሉ:: 15በፍጹም ልባቸው ስለማሉም የይ
ሁዳ ሕዝብ በመሐላው ደስ ተሰኙ:: እግዚአብሔ
ርን ከልብ ፈለጉት፤ እርሱም ተገኘላቸው፤
ስለዚህ *እግዚአብሔር* በሁሉም አቅጣጫ ዕረፍት
ሰጣቸው::
16እንዲሁም ንጉሥ አሳ አያቱን ማዓካን
ለአስጸያፊዋ የአሼራ ባዖት ዐምድ ስላቆመች
ከእቴጌነት ክብሯ ሻራት:: አሳም ዐምዱን
ቈርጦ በመሰባበር በቄድሮን ሸለቆ አቃጠ
ለው:: 17ምንም እንኳ ማምለኪያ ኮረብታ
ዎችን ሙሉ በሙሉ ከእስራኤል ባያስወግ
ድም፣ የአሳ ልብ በዘመኑ ሁሉ ፈጽሞ
*ለእግዚአብሔር* የተገዛ ነበር:: 18እርሱና
አባቱ የቀደሱትን ብሩን፣ ወርቁንና ልዩ
ልዩ ዕቃ ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
አገባ::
19እስከ ሠላሳ አምስተኛው የአሳ ዘመነ
መንግሥት ድረስ ምንም ዓይነት ጦርነት
አልነበረም::

[ን]8 የቡልጌትና የሱርስቱ ቅጅ (እንዲሁም ቊጥር1) ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን *የዖዴድን ልጅ* የሚለውን አይጨምርም::

14፥12 1ነገ8፥45
14፥13 ዘፍ10፥19፤ 2ሳሙ22፥38፤2ዜና1 5፥11፡18፤ነህ9፥24፤ መዝ44፥2፡19፤ 135፥10
14፥14 ዘፍ35፥5፤ ዘዳ2፥25፤11፥25
15፥1 ዘኍ11፥ 25፡26
15፥2 ዘዳ31፥17፤ 1ዜና28፥9፤2ዜና7፥1 4፤20፥17፤ መዝ78፥34፤ ኢሳ45፥19፤ 55፥6፤ኤር29፥13፤ ሆሴ3፥5፤ያዕ4፥8
15፥3 ዘሌ10፥11፤ ሰቆ2፥9፤አሞ8፥11
15፥4 ዘዳ4፥29
15፥5 መሳ5፥6፤ 19፥20፤ዘካ8፥10
15፥6 ኢሳ19፥2፤ ማቴ24፥7፤ ማር13፥8፤ ሉቃ21፥10
15፥7 ኢሱ1፥7፡ 9፤1ሳሙ24፥19፤ መዝ18፥20፤58፥11፤ ምሳ14፥14፤ ኤር31፥16
15፥8 1ነገ8፥64፤ 15፥12፤2ዜና8፥12፤ 17፥2
15፥9 2ዜና11፥ 16-17
15፥10 ዘሌ23፥ 15-21
15፥11 2ዜና 14፥13
15፥12 2ነገ11፥ 17፤1ዜና16፥11
15፥13 ዘፀ22፥20፤ ዘዳ13፥9-16
15፥15 ዘዳ4፥29፤ 1ዜና22፥9
15፥16 ዘፀ34፥13፤ 2ሳሙ15፥23፤1ነገ12 ፥19፤2ዜና13፥2
15፥18 2ዜና14፥ 13

14፥13 *ጌራራ፤* የዘፍ20፥1 ማብ ይመ:: *ምርኮ፤* ከተገኘው ምርኮ አብዛኛው (ቍ 14) ወደ ቤተ መቅደሱ ግምጃ ቤት ገብቶአል (15፥18 እንዲሁም የ1ዜና18፥1-20፥8 ማብ ይመ)::

14፥14 *ድንጋጤ ከእግዚአብሔር ዘንድ፤* የ1ዜና 14፥17 ማብ ይመ::

*15፥1-19፤* ይህ ምዕራፍ ከዝሪ መሸነፍ የተጀመረውንና በዓዛርያስ ስብከት የተበረታታውን (ቍ1) የአሳ ተሐድሶ ሁለተኛ ዙር የሚተርክ ይመስላል::

15፥3 *ያለ አስተማሪ ካህንና፤* ካህናት በመሠዊያው ላይ ማከናወን የሚገባቸውን አገልግሎት መፈጸም ብቻ ሳይሆን፣ ሕጉንም ማስተማር ነበረባቸው (17፥7-9፤ዘሌ10፥11 ይመ)::

15፥8 *በኤፍሬምም... ከያዛቸው ከተሞች፤* ከ36ኛው የአሳ ዘመነ መንግሥት በፊት (16፥1፤ እንዲሁም 17፥1ይመ) በእርሱና በባእስ መካከል አልፎ አልፎ መቈራቈስና ግጭት ሳይኖር እንዳልቀረ ያሳያል::

15፥9 *ብዙ ሰዎች እርሱን ተጠግተው፤* በሮብዓም ዘመን ከሰሜኑ መንግሥት ፈልሰው ወደ ይሁዳ ስለ ሄዱ ሰዎች ሁኔታ የሚናገረውን ክፍል ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ 11፥13-17::

15፥10 *በዐሥራ አምስተኛው ዓመት በሦስተኛው ወር፤* ወቅቱ የጸደይ ወራት ሲሆን ዘመኑም 895 ዓ.ቅ.ክ ነበር:: ይህም ከዝሪ ወረራ በኋላ ነበር (ቍ19):: በዓለአምሳ የዋለውም በሦስተኛው ወር ስለ ነበር (ዘሌ23፥15-21)፤ ለዚህ ጉባኤ መሰብሰብ ምክንያት የሆነውም ይህ ሳይሆን አይቀርም::

15፥12 *ቃል ኪዳን፤* በሲና የተደረገው የኪዳን ተሐድሶ በሞዓብ ሜዳ (ዘዳ29፥1)፤ በጌባል ተራራ (ኢሱ8፥30-35)፣ በሴኬም (ኢሱ 24፥25) እንዲሁም በጌልገላ (1ሳሙ11፥14 እና ማብ ይመ) ከተደረገው የኪዳን ተሐድሶ ጋር ተመሳሳይ ነው:: ቀጥሎም ካህኑ ዮዳሄ (23፥16)፤ ሕዝቅያስ (29፥10) እና ኢዮስያስ (34፥31) እንደዚሁ ቃል ኪዳን ሲገቡ እናገኛቸዋለን፤ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በመጽሐፉ ውስጥ ልዩ ትኩረት የሰጣቸው ቁም ነገሮች ናቸው::

15፥13 *እግዚአብሔን... የማይፈልግ፤* ወደ ሌሎች አማልክት የሚመለስ ማለት ነው:: *እንዲገደል፤* ይህ የሚፈጸመው በቃል ኪዳኑ ሕግ መሠረት ነው (ዘፀ22፥20፤ዘዳ13፥6-9)::

*15፥15 ዕረፍት፤* የ20፥30 ማብ ይመ::

15፥16 *የአሼራ ባዖት ዐምድ፤* የ 14፥3 አማራጭ ትርጉም ይመ::

15፥17 *ማምለኪያ ኮረብታዎችን ......ባያስወግድም፤* 15፥5 እና ማብ ይመ::

16፥1 *አሳ በነገሠ በሠላሳ ስድስተኛው ዓመት... ባእስ፤*

## የአሳ የመጨረሻ ዓመታት

16፥1-6ተጓ ምብ—ዜና15፥17-22
16፥11-17፥1ተጓ ምብ —1ዜና15፥23-24

**16** አሳ በነገሠ በሠላሳ ስድስተኛው
ዓመት፣ የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ
በይሁዳ ላይ ዘምቶ፣ ከእስራኤል ንጉሥ ከአሳ
ግዛት ማንም እንዳይወጣ፣ ወደዚያም ማንም
እንደይገባ ለመከልከል ራማን መሸገ::
2 አሳም *ከእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስና
ከራሱም ቤተ መንግሥት ግምጃ ቤቶች
ብርና ወርቅ ወስዶ በደማስቆ ተቀምጦ
ይገዛ ለነበረው ለሶርያ ንጉሥ ለወልደ አዴር
ላከ፤ 3 ከዚያም “ቀድሞ በአባቴና በአባትህ
መካከል እንደ ነበረው ሁሉ፣ ዛሬም በእኔና
በአንተ መካከል የስምምነት ውል ይኑረን፤
እነሆ፤ ብርና ወርቅ ልኬልሃለሁ፤ ከእኔ ተመልሶ
ይሄድ ዘንድ ከባኦስ ጋር ያደረግኸውን የስ
ምምነት ውል አፍርስ” አለው::
4 ወልደአዴር የንጉሥ አሳን ሐሳብ ተቀበለ፤
የጦር አዛዦቹንም በእስራኤል ከተሞች ላይ
አዘመተ:: እነርሱ ዒዮንን፣ ዳንን፣ አቤል
ማይምንና የንፍታሌምን የዕቃ ግምጃ ቤት
ከተሞች ሁሉ ድል አድርገው ያዙ:: 5 ባኦስ
ይህን በሰማ ጊዜ ራማን መገንባቱን አቆመ፤
ሥራውንም አቋረጠ:: 6 ንጉሥ አሳም የይሁዳን
ሰዎች ሁሉ አመጣቸው፤ እነርሱም ባኦስ ይሠ
ራበት የነበረውን ድንጋይና እንጨት ወሰዱ፤
አሳም ጌባንና ምጽጳን ሠራባት::
7 በዚያን ጊዜም ባለ ራእዩ አናኒ ወደ ይሁዳ
ንጉሥ ወደ አሳ መጥቶ እንዲህ አለው፤ “*በአ
ምላክህ* በእግዚአብሔር ሳይሆን በሶርያ ንጉሥ
ስለ ታመንህ፣ የሶርያ ንጉሥ ሰራዊት ከእጅህ
አምልጦአል:: 8 ኢትዮጵያውያንና ሊቢያውያን
ብዙ ቍጥር ካላቸው ሠረገላዎቻቸውና[1] ፈረ
ሶቻቸው ጋር ኀያል ሰራዊት አልነበሩምን?
ይሁን እንጂ *በእግዚአብሔር* ስለ ታመንህ በእ
ጅህ አሳልፎ ሰጠህ፤ 9 በፍጹም ልባቸው የሚ
*ታመኑበትን ለማበርታት የእግዚአብሔር ዐይ
ኖች* በምድር ሁሉ ላይ ይመለከታሉና:: የሞ
ኝነት ሥራ ስለ ሠራህ ከእንግዲህ ወዲያ
ጦርነት አይለይህም::
10 ከዚህ የተነሣም አሳ ባለ ራእዩን ተቈጣው፤
በጣም ስለ ተናደደም እስር ቤት አስገባው::
በዚያን ጊዜም አሳ አንዳንድ ሰዎችን ክፉኛ
አስጨነቃቸው::
11 በአሳ ዘመነ መንግሥት ከመጀመሪያ
እስከ መጨረሻ የተከናወነው ሥራ በይሁዳና
በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መዛግብት
ተጽፎአል:: 12 አሳ በነገሠ በሠላሳ ዘጠነኛው
ዓመት እግሮቹን ክፉኛ ታመመ፤ ሕመሙ
ቢጸናበትም እንኳ፣ በዚያ ሁሉ ሕመም የባለ
መድኃኒቶችን እንጂ *የእግዚአብሔርን* ርዳታ
አልፈለገም:: 13 አሳም በነገሠ በአርባ አንደ
ኛው ዓመት ሞተ፤ እንደ አባቶቹም ሁሉ
አንቀላፋ:: 14 በዳዊት ከተማ ከዐለት አስፈልፍሎ
ለራሱ ባሠራውም መቃብር ቀበሩት:: በቅ
መማ ቅመምና በልዩ ልዩ ጣፋጭ ሽቱዎች
በተሞላ ቃሬዛ ላይ አኖሩት፤ ስለ ክብሩም
ትልቅ እሳት አነደዱ::

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ

**17** ልጁ ኢዮሣፍጥ በእርሱ ፈንታ ነገሠ፤
በእስራኤል ላይ በረታ:: 2 እርሱም
በተመሸጉት የይሁዳ ከተሞች ሁሉ ውስጥ
ወታደር አኖረ፤ እንዲሁም በይሁዳ ምድርና
አባቱ አሳ በያዛቸው በኤፍሬም መንደሮች
ዘበኞች አስቀመጠ::
3 በለጋነት ዕድሜው አባቱ ዳዊት በሄደበት
መንገድ ስለሄደ፣ *እግዚአብሔር* ከኢዮሣፍጥ
ጋር ነበር፤ የበኣልንም አማልክት አልጠ
የቀም፤ 4 ነገር ግን ከእስራኤል ድርጊት ይልቅ፣
የአባቱን አምላክ ፈለገ፤ ትእዛዛቱንም ተከተለ::

[1] 8 *ወይም ሠረዝኞች*

16፥1 2ነገ9፥9፤ ኤር41፥9
16፥2 2ዜና19፥1-20:37፤22፥1-9
16፥3 2ዜና20፥35፤ 25፥7
16፥4 2ነገ15፥29
16፥6 ኤር41፥9
16፥7 1ነገ16፥1፤ 2ዜና13፥18
16፥8 ዘፍ10፥6:8-9፤2ዜና12፥3፤13፥16፤24፥24
16፥9 1ሳሙ13፥13፤ 1ነገ15፥6፤ 2ዜና19፥2፤25፥7፤28፥16-21፤ኢዮ24፥23፤ መዝ33፥13-15፤ ምሳ15፥3፤ኤር16፥17፤ዘካ3፥9፤4፥10
16፥10 1ነገ22፥27
16፥12 2ዜና7፥14፤ 21፥18፤26፥19፤ መዝ103፥3፤ኤር17፥5-6
16፥14 ዘፍ50፥2:5፤2ዜና21፥19፤ ኤር34፥5
17፥1 1ነገ2፥12
17፥2 2ዜና11፥10፤ 2ዜና15፥8
17፥3 1ነገ22፥43
17፥4 2ዜና22፥9

በመጽሐፈ ነገሥት መሠረት ባኦስ ሃያ አራት ዓመት ከገዛ በኋላ፣ በአሳ ዘመነ መንግሥት በሃያ ስድስተኛው ዓመት፣ ልጁ ኤላ በእርሱ ፋንታ ተተክቶአል (1ነገ15፥33፤16፥8):: ይህ መጽሐፍ እንደሚለው፣ በአሳ ዘመነ መንግሥት በሠላሳ ስድስተኛው ዓመት ባኦስ በሕይወተ ሥጋ ሊኖር እንደማይችል የታወቀ ነው፤ ከሞተ ዐሥር ዓመት ሆኖት ነበርና:: አንዳንዶች ለዚህ ችግር እንደ መፍትሔ አድርገው የሚያቀርቡት፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ እዚህም ሆነ በ15፥19 ላይ መነሻ አድርጎ የሚጠቅሰው የአሳን ዘመነ መንግሥት ሳይሆን፣ የእስራኤል መንግሥት ከሁለት የተከፈለበትን ዘመን ነው:: የገዙትም ሮብዓም ዐሥራ ሰባት፣ አብያ ሦስት በድምሩ ሃያ ዓመት ከሆነ፣ ይህ ቍጥር ሠላሳ አምስትና ሠላሳ ስድስት ከተባለው ላይ ሲቀነስ ትክክለኛ ዘመኑ ዐሥራ አምስተኛውና ዐሥራ ስድስተኛው የአሳ ዘመነ መንግሥት ሊሆን ይችላል:: ይህም ከሰሜኑ መንግሥት የፈለሱትን ሰዎች ለመከላከል ባኦስ አደጋ መጣሉን ያመለክታል (15፥9)፤ በመሠረቱ ይህ መፍትሔ ትክክል መስሎ ይታይ እንጂ፣ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነትን አላገኘም:: እዚህ ላይ የተገለጸው ድርጊት የተፈጸመበት ዘመን በ1ነገ15፥17 ላይ አልተመለከተም:: ምናልባትም እዚህና በ15፥19 ላይ የተገለጠው ዘመን መጽሐፉን የገለበጠው ሰው ስሕተት ባይፈጽም ኖሮ ትክክለኛው ቍጥር 25ኛ ወይም 26ኛ ሊሆን ይችል ነበር::

16፥2-9፤ አሳ ከውጭ መንግሥት ጋር የጦር ስምምነት በማ ድረግ ወታደሮችን በገንዘቡ መቅጠሩ በእግዚአብሔር ላይ እምነት ማጣቱን ያሳያል:: ሌሎች የተወገዙ የጦር ቃል ኪዳን ምሳሌዎች በኢዮሳፍጥ (20፥35-37)፣ በአካዝያስ (22፥1-9) እና በአካዝ (28፥16-21) ዘመነ መንግሥት ታይተዋል:: አሳ የሰሜኑን ንጉሥ ወልደ አዴርን በእጅ መንሻ ገዝቶ የጦር ስምምነት በማድረጉ በባኦስ ላይ ከሁለት አቅጣጫ ጦርነት ከፍቶ ወደ ኋላው እንዲመለስ አስገድዶታል::

16፥12 *እግሮቹን ታመመ፤* ለኀጢአት ቅጣት ስለሚላክ ሕመም ለመገንዘብ 21፥16-20፤ 26፥16-23፤ ሐሥ 12፥23 ይመ ከ2ነገ15፥5 ጋር ያነጻጽሩ::

*17፥1-21፥3፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ስለ ኢዮሣፍጥ ዘመነ መንግሥት የተረከው፣ በመጽሐፈ ነገሥት ከሚገኘው በእጥፍ ይበልጣል፤ ምክንያቱም የመጽሐፈ ነገሥቱ ጸሓፊ የኢዮሣፍጥ ታሪክ መያዝ የሚገባውን ሰፊ ክፍል፣ በይበልጥ ትኵረት ላሳደረበት ለአክአብና ለኤልያስ ታሪክ ስለ ሰጠው ነው (1ነገ22፥1-46):: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የኢዮሣፍጥን ዘመነ መንግሥት ታሪክ፣ ነገሥታት ለእግዚአብሔር ቢታዘዙ በረከቱን እምቢ ብለው ቢያምፁ ቅጣቱን ወዲያው ይቀበሉ እንደነበረ በአጽንዖት ለማሳየት ተጠቅሞበታል:: ይህ መሪ ሐሳብም በተለይ በ19፥10 ላይ በማስጠንቀቂያ መልክ የተነገረ ሲሆን፣ ኢዮሳፍጥ በታዘዘ ጊዜ በረከት ባመፀ ጊዜ ግን ተግሣጽ እንዳገኘው በተግባር ታይቶአል:: (19፥2-3፤20፥35-37):: ኢዮሣፍጥ ከ872-848 ዓ.ቅ.ክ. ገዝቶአል፤ ከዚህ ውስጥ ከ872-869 ባለው ዘመን ከአባቱ ከአሳ ጋር የገዛበት ነው (20፥31 ይመ)፤ በዘመነ መንግሥቱ የተፈጸመው ታሪክ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ አይመስልም፤ በ17፥7-9 የተገለጠው የማስተማሩ ተልእኮ ምናልባትም በ19፥4-11 የተጻፈው የተሐድሶው አንዱ ክፍል ሊሆን ይችላል::

17፥2 *የይሁዳ ከተሞች... በኤፍሬም መንደሮች፤* የ15፥8 ማብ ይመ:: አብያ (13፥19)፣አሳ (15፥8) እዚህም ላይ ኢዮሣፍጥ

5እግዚአብሔርም መንግሥቱን በእጁ አጸናለት፤
መላው ይሁዳም ስጦታ አመጣለት፤ ከዚህ
የተነሣም ታላቅ ብልጽግናና ክብር አገኘ።
6ልቡም *በእግዚአብሔር መንገድ* የጸና ነበር፤
እንደዚሁም ማምለኪያ ኰረብታዎችንና የአ
ሼራ ዐምዶችን ከይሁዳ አስወገደ።

7በነገሠ በሦስተኛው ዓመት በይሁዳ ከተ
ሞች ያስተምሩ ዘንድ ሹማምቱን ማለትም
ቤን ኀይልን፣ አብድያስን፣ ዘካርያስን፣ ናትና
ኤልንና ሚክያን ላካቸው። 8ከእነዚህም ጋር
ጥቂት ሌዋውያን ነበሩ፤ ስማቸውም፦ ሸማያ፣
ነታንያ፣ ዝባድያ፣ አሣሄል፣ ሰሚራሞት፣
ዮናታን፣ አዶንያስ፣ ጦብያና ጦባዶንያ
ነበር። ካህናቱ ደግሞ ኢሊሳማና ኢዮራም
ነበሩ። 9እነርሱም *የእግዚአብሔርን* የሕጉን
መጽሐፍ ይዘው በመሄድ በይሁዳ ሁሉ
ላለው ሕዝብ አስተማሩ፤ በይሁዳ ከተሞች
ሁሉ በመዘዋወርም ሕዝቡን አስተማሩ።

10በይሁዳ ዙሪያ ባሉ ነገሥታት ሁሉ ላይ
*ከእግዚአብሔር* ዘንድ ፍርሀት ስለወደቀባቸው
ኢዮሣፍጥን አልተዋጉትም። 11ከፍልስጥኤ
ማውያንም አንዳንዶቹ እጅ መንሻ አመጡለት፤
ጥሬ ብርም ገበሩለት፤ ዐረቦችም ሰባት ሺህ
ሰባት መቶ አውራ በግና ሰባት ሺህ ሰባት መቶ
አውራ ፍየል መንጋ አመጡለት።

12ኢዮሣፍጥም እያየለ ሄደ፤ በይሁዳም
ምሽጎችና የዕቃ ማከማቻ ከተሞች ሠራ።
13በይሁዳም ከተሞች እጅግ ብዙ ስንቅና ትጥቅ
ነበረው። ደግሞም በቂ ልምድ ያላቸውን
ተዋጊዎች በኢየሩሳሌም አስቀመጠ።
14እነርሱም በየቤተ ሰቦቻቸው ሲመዘገቡ
እንደሚከተለው ነው፤ ከይሁዳ የየሻለቃው
አዛዦች፣

አዛዡ ዓድና ከሦስት መቶ ሺ ተዋጊዎች ጋር፤
15ከእርሱ ቀጥሎም አዛዡ የሆሐናን ከሁለት
መቶ ሰማንያ ሺህ ጋር፤
16ከዚያ ቀጥሎም *ለእግዚአብሔር* አገልግሎት

17፥5 1ሳሙ10፥27፤ 2ዜና18፥1
17፥6 ዘዳ34፥13፤ 1ነገ 8፥61፤ 15፥14፤2ዜና19፥3፤20፥33፤21፥12
17፥7 ዘሌ10፥11፤ ዘዳ6፥4-9፤2ዜና 19፥4-11፤35፥3፤ ነህ8፥7፤ሚል2፥7
17፥8 2ዜና19፥8፤ ነህ8፥7-8፤ሆሴ4፥6
17፥9 ዘዳ28፥61
17፥10 ዘፍ35፥5፤ ዘዳ2፥25
17፥11 2ዜና9፥14፤ 21፥16
17፥14 2ሳሙ24፥2
17፥16 መሳ5፥9
17፥17 ዘኍ1፥36
17፥19 2ዜና11፥10 ፤25፥5
18፥1 2ዜና17፥5፤ 19፥1-3፤21፥6፤22፥3

በፈቃደኝነት ራሱን የሰጠው የዝክሪ ልጅ
ዓማስያ ከሁለት መቶ ሺህ ተዋጊዎች ጋር፤
17ከብንያምም ጀግናው ወታደር ኤሊዳሄ
ቀስትና ጋሻ ከያዙ ከሁለት መቶ ሺ ሰዎች ጋር፤
18ቀጥሎም የዛባት ለጦርነት ዝግጁ ከሆኑ
ከአንድ መቶ ሰማንያ ሺህ ሰዎች ጋር፤
19እነዚህ እንግዲህ በመላው ይሁዳ በተመሸጉት
ከተሞች ካስቀመጣቸው ሌላ፣ ንጉሡን ያገለግሉ
የነበሩ ሰዎች ናቸው።

## ሚክያ በአክዓብ ላይ ትንቢት ተናገረ

18፥1-27ተጓ ምብ—1ዜና22፥1-28

18ኢዮሣፍጥ ታላቅ ሀብትና ክብር
ባገኘ ጊዜ ከአክዓብ ጋር በጋብቻ
ተሳሰረ። 2ከጥቂት ዓመታት በኋላም አክዓ
ብን ሊጎበኝ ወደ ሰማርያ ወረደ። አክዓብም
ለእርሱና አብሮት ለነበረው ሕዝብ ብዙ በግና በሬ
ዐረደ፤ ከዚያም በሬማት ዘገለዓድ ላይ አደጋ
እንዲጥል አግባባው። 3የእስራኤል ንጉሥ አክዓብም
የይሁዳን ንጉሥ ኢዮሣፍጥን፣ “ሬማት ዘገለዓ
ድን ለመውጋት አብረኸኝ ትሄዳለህን?” ሲል
ጠየቀው።

ኢዮሣፍጥም፣ “እኔ እንደ አንተው ነኝ፤ ሕዝ
ቤም እንደ ሕዝብህ ነው፤ በጦርነቱ አብረ
ናችሁ እንሰለፋለን” ሲል መለሰለት። 4ደግሞም
ኢዮሣፍጥ የእስራኤልን ንጉሥ፣ “አስቀድመህ
ግን *የእግዚአብሔርን ፈቃድ* ጠይቅ” አለው።
5ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ አራት መቶ
ነቢያትን በአንድነት ሰብስቦ፣ “ሬማት ዘገለዓድን
ለመውጋት ልሂድን ወይስ ልቅር?” ሲል ጠየ
ቃቸው።

እነርሱም፣ “እግዚአብሔር በንጉሡ እጅ አሳልፎ
ይሰጣታልና ሂድ” ብለው መለሱለት።
6ኢዮሣፍጥ ግን፣ “እንጠይቀው ዘንድ ሌላ
*የእግዚአብሔር* ነቢይ እዚህ የለምን?” አለ።
7የእስራኤልም ንጉሥ ለኢዮሣፍጥ፣ “መኖሩ
ንማ በእርሱ አማካይነት *የእግዚአብሔርን ፈቃድ*

እነዚህን ከተሞች ይዘው ለመቈጣጠር ችለዋል፤ በኋላ ግን ከተሞቹ በአሜስያስ ዘመነ መንግሥት ከእጃቸው ወጡ (25፥17-24)።

17፥6 *ማምለኪያ ኰረብታዎችንና... አስወገደ፤* አባቱ አሳ ለማድረግ እንደሞከረውና እንዳልተሳካለት ሁሉ (14፥5፤15፥17)፣ ኢዮሳፍጥም እንደዚሁ በመጀመሪያ ሊያስወግዳቸው ሞክሮአል፤ ሙሉ በሙሉ ግን አላጠፋም። (20፥33 ይመ፤ ከ1ነገ22፥43 ጋርም ያነጻጽሩ)፤ ይሁን እንጂ የ1ነገ3፥2፤15፥4 ማብ ይመ። *የአሼራ ዐምዶችን፤* የ14 3 አግራጭ ትርጕም ይመ።

*17፥7-9፤* ይህ በ19፥4-11 ላይ በዝርዝር ለቀረበው የተሐድሶ ታሪክ አንዱ ክፍል ሳይሆን አይቀርም። በእግዚአብሔር አስተዳደር ሥርዐት፣ የእግዚአብሔር ሕግ የአገሪቱ ሕግ ዋና ክፍል ሆኖ ይቈጠራል፤ ከዚህ የተነሣም ንጉሡና ሹማምንቱ እንዲሁም ካህናቱና ነቢያቱ ለሕዝቡ የእውነተኛው ንጉሥ የእግዚአብሔር እንደራሲዎች ናቸው።

17፥7 *በሦስተኛው ዓመት፤* ከአባቱ ከአሳ ጋር ለሦስት ዓመት ከገዛ በኋላ (20፥31 እና ማብ ይመ) ብቻውን የገዛበትን የመጀ መሪያ ዓመት የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም።

*17፥10-11፤* የ1ዜና 18፥1-20፥8 ማብ ይመ።

17፥10 *ከእግዚአብሔር ዘንድ ፍርሀት፤* የ1ዜና14፥17 ማብ ይመ።

17፥14-18 *ከሦስት መቶ ሺህ... ከሁለት መቶ ሰማንያ ሺ ህ ከሁለት መቶ ሺህ... ከሁለት መቶ ሺህ...ከአንድ መቶ ሰማንያ ሺህ* ወይም “ከ300 ሰብስብ... ከ280 ሰብስብ...ከ200 ሰብስብ...ከ200 ሰብስብ... ከ180 ሰብስብ (የ1ዜና12፥23-37፤27፥1 ማብ ይመ) ማለት ነው።

18፥1-19፥3፤ 1ነገ22፥1-40 እና ማብ ይመ። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በደቡብ መንግሥትና በኢዮሣፍጥ ላይ አጽንዖት ማድረጉን ለማመልከት ስለ አክአብ ሞትና በፋንታው ስለሚተኩት ሰዎች ሳይጠቅስ አልፎአል (1ነገ22፥36-40)፣ እንዲሁም ኢዮሣፍጥ ከእስራ ኤል ንጉሥ ጋር በማበሩ ነቢዩ እንዴት እንደ ገሠጸው ጨምሮ ጽፎአል (19፥2-3)።

*18፥1፤* በ1ነገ 22 ላይ አይገኝም። ክፍሉ ኢዮሳፍጥ ታማኝ ሆኖ በመገኘቱ በሀብትም፣ በክብርም መባረኩን በመግለጽ ከፍ ከፍ ያደርገዋል፤ እንዲሁም ኢዮሣፍጥ ወጥመድ ውስጥ መግባቱን ይጠቍማል፤ በ19፥2-3 ላይ ነቢዩ ኢዩ ይህን አስመልክቶ ገሥ ጾታል። *ከአክአብ ጋር በጋብቻ ተሳሰረ፤* ኢዮሣፍጥ ከአክአብ ልጅ ከጎቶልያ ጋር ያደረገው የጋብቻ ትስስር የኋላ ኋላ የዳዊትን ሥርወ መንግሥት ለማጥፋት (22፥10-23፥21) ለተደገረው ሙከራ በር ከፋች ሆኖአል።

*18፥2፤* እዚህም ላይ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ አክአብ ብዙ እንስሳት ለክብሩ እንዳረደለት በመግለጽ የኢዮሣፍጥን ታልቅነት አጕልቶ ያሳያል፤ ይህ ግን በ1ነገ22 ላይ አይገኝም። *አግባባው፤* ይህም እንደዚሁ በተጓዳኝ ታሪክ ላይ አይገኝም፤ ለዚህ ቃል የገባው የዕብራይስጡ ትርጕም ለክፉ ሥራ ማነሣሣትን (1ዜና21፥1) ያመለክታል፤ ይህም የሚያሳየው ኢዮሣፍጥ ከአክአብ ጋር ማበሩን በሚመለከት የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የነበረውን ዝንባሌ ሳይሆን አይቀርም።

18፥4 *የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቅ፤* ይህ አባባል፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ባጠቃላይ ለኢዮሣፍጥ ያለው አመለካከት ቀና መሆኑን የሚያመለክት ነው።

18፥29 አክአብ ራሱ አልባሌ ሰው መስሎ ወደ ጦርነቱ ሲገባ፣

የምንጠይቅበት አንድ ሰው አሁንም አለ፤ ነገር
ግን ምን ጊዜም ቢሆን ስለ እኔ ክፉ እንጂ ደግ
ትንቢት ስለማይናገር እጠላዋለሁ፤ እርሱም
የይምላ ልጅ ሚካያ ነው” ሲል መለሰ።
ኢዮሳፍጥም፣ “ንጉሥ እንዲህ ማለት አይገ
ባውም” አለው።
[8]የእስራኤልም ንጉሥ ከሹማምንቱ አን
ዱን ጠርቶ “ሂድና የይምላን ልጅ ሚካያን
በፍጥነት አምጣው” አለው።
[9]የእስራኤል ንጉሥና የይሁዳ ንጉሥ ኢዮ
ሣፍጥ ልብሰ መንግሥታቸውን ለብሰው፣ በሰ
ማርያ ቅጥር በር መግቢያ አጠገብ ባለው ዐው
ድማ ላይ በየዙፋናቸው ተቀምጠው፣ ነቢያቱ ሁሉ
በፊታቸው ትንቢት ይናገሩ ነበር። [10]የክንዓና
ልጅ ሴዴቅያስም የብረት ቀንዶች ሠርቶ፣
“እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ‘ሶርያውያን እስኪጠፉ
ድረስ በእነዚህ ትወጋቸዋለህ” አለ።
[11]ሌሎቹ ነቢያት ሁሉ፣ “እግዚአብሔር በንጉሡ
እጅ አሳልፎ ይሰጣታልና፣ በሬማት ገለዓድ
ላይ አደጋ ጣልባት” በማለት ተመሳሳይ ትንቢት
ይናገሩ ነበር።
[12]ሚካያን ሊጠራ ሄዶ የነበረውም መልእክተኛ፣
‘እነሆ፣ ሌሎቹ ነቢያት በአንድ አፍ ሆነው፣
ንጉሡ ድል እንደሚያደርግ እየተነበዩ ነው፤
ያንተም ቃል እንደቃላቸው ይሁን፤ ንጉሡን
ደስ የሚያሰኘውን ተናገር” አለው።
[13]ሚካያ ግን፣ “ሕያው እግዚአብሔርን! አምላኬ
የሚለውን ብቻ እናገራለሁ” አለ።
[14]እዚያ በደረሰም ጊዜ ንጉሡ፣ “ሚካያ
ሆይ፤ ሬማት ዘገለዓድን ለመውጋት እንሂድ
ወይስ ልቅር?” ሲል ጠየቀው።
እርሱም መልሶ፣ “ሂዱና ድል አድርጉ፤ በእጃ
ችሁ አልፈው ይሰጣሉና” አለው።
[15]ንጉሡም፣ “ከእውነት በቀር ምንም ነገር
በእግዚአብሔር ስም እንዳትነግረኝ ስንት
ጊዜ አምልሃለሁ?” አለው።
[16]ከዚያም ሚካያ “እስራኤል ሁሉ እረኛ
እንደሌላቸው በጎች በተራሮች ላይ ተበታ
ትነው አየሁ፤ እግዚአብሔርም፣ ‘እነዚህ ሰዎች
ጌታ የላቸውም፤ እያንዳንዱም በሰላም ወደ
የቤቱ ይመለስ’ ብሎአል” ሲል መለሰ።
[17]የእስራኤልም ንጉሥ ኢዮሣፍጥን፣ “ስለ
እኔ ክፉ ብቻ እንጂ፣ ደግ ትንቢት እንደማይ
ናገር አልነገርሁህምን?” አለው።
[18]ሚካያም በመቀጠል እንዲህ አለ፤ “እን
ግዲህ የእግዚአብሔርን ቃል ስማ፤ እግዚአ
ብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ፣ የሰማይም ሰራዊት
ሁሉ በቀኙና በግራው ቆመው አየሁ። [19]እግዚ
አብሔርም፣ ‘የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ በሬ
ማት ገለዓድ ላይ ዘምቶ እዚያው እንዲሞት
ማን ያሳስተው?’ አለ።

18፥11 2ዜና22፥5
18፥13 ዘኍ22፥
18:20:35
18፥16 ዘኍ27፥17
1ዜና9፥1
18፥18 ዳን 7፥9
8፥21 1ዜና21፥1፤
ኢዮ1፥6፤ ዘካ3፥1፤
ዮሐ8፥44
18፥22 ኢዮ12፥
16፤ ሕዝ14፥9
18፥23 ሐሥ23፥2
18፥26 ዕብ11፥36
18፥29 1ሳሙ28፥8
18፥31 2ዜና13፥14

“አንዱ አንድ ሐሳብ፣ ሌላውም ሌላ ሐሳብ
አቀረበ። [20]በመጨረሻም አንድ መንፈስ ወደ
ፊት ወጥቶ፣ በእግዚአብሔር ፊት በመቆም፣
‘እኔ አሳስተዋለሁ’ አለ።
“እግዚአብሔርም፣ ‘እንዴት አድርገህ?’ ሲል
ጠየቀው።
[21]“እርሱም፣ ‘እሄድና በነቢያቱ ሁሉ አፍ
የሐሰት መንፈስ እሆናለሁ’ አለ።
“እግዚአብሔርም፣ ‘እንግዲያውስ ሂደህ
አሳስተው፤ ይሳካልሃልም’ አለው።
[22]“አሁንም እነሆ፣ እግዚአብሔር በእነዚህ ነቢ
ያትህ አፍ የሐሰት መንፈስ አኖረ፤ እግዚአ
ብሔርም ጥፋት አዞብሃል”።
[23]ከዚያም የክንዓናም ልጅ ሴዴቅያስ ወጥቶ
ሚካያን በጥፊ መታውና፣ “ለመሆኑ የእግ
ዚአብሔር መንፈስ አንተን ያነጋገረህ፣ በየት
በኩል አልፎኝ ነው?” አለው።
[24]ሚካያም፣ “ለመሸሸግ ወደ እልፍኝህ በምት
ሄድበት በዚያ ዕለት ታገኘዋለህ” አለው።
[25]ከዚያም የእስራኤል ንጉሥ እንዲህ ሲል
አዘዘ፤ “ሚካያን ይዛችሁ ወደ ከተማዪቱ ገዥ
ወደ አሞንና ወደ ንጉሡ ልጅ ወደ ኢዮአስ
መልሳችሁ ላኩት፤ [26]እነርሱንም፣ ‘ንጉሡ፣
ይህን ሰው እስር ቤት አስገቡት፤ በደህና እስክ
መለስም ድረስ ከደረቅ ቂጣና ከውሃ በስተቀር
ምንም አትስጡት ብሎአል’ በሏቸው።”
[27]ሚካያም፣ “አንተ በደህና ከተመለስክማ
እግዚአብሔር በእኔ አልተናገረም ማለት ነው!”
አለ፤ ቀጥሎም፣ “እናንተ ሕዝብ ሁላችሁ
ስሙኝ” አለ።

## አክዓብ በሬማት ገለዓድ ተገደለ

18፥28-34ተጓ ምብ—1ዜና22፥29-36

[28]ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥና የይሁዳ
ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ወደ ሬማት ገለዓድ ወጡ።
[29]የእስራኤልም ንጉሥ ኢዮሣፍጥን፣ “እኔ
ልብሴን ለውጬ ወደ ጦርነቱ እገባለሁ፤
አንተ ግን ልብሰ መንግሥትህን ልበስ”
አለው። ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ ልብሱን
ለውጦ ሌላ ሰው መስሎ ወደ ጦርነቱ ገባ።
[30]በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ የሠረገላ አዛ
ዦቹን፣ “ከእስራኤል ንጉሥ በቀር፣ ትንሽም
ሆነ ትልቅ ከሌላ ከማንም ጋር አትዋጉ” ብሎ
አዘዛቸው። [31]የሠረገላው አዛዦችም ኢዮሣፍጥን
ባዩ ጊዜ፣ “የእስራኤል ንጉሥ ይህ ነው”
ብለው አሰቡ፤ ሊወጉትም ከበቡት፣ ኢዮ
ሣፍጥ ግን ጮኸ፤ እግዚአብሔርም ረዳው፤
አምላክም ከእርሱ መለሳቸው፤ [32]የሠረገላ
አዛዦቹም የእስራኤል ንጉሥ አለመሆኑን
በተረዱ ጊዜ እርሱን ከማሳደድ ተመለሱ።
[33]ይሁን እንጂ ቀስቱን በነሲብ ቢያስፈ

ኢዮሣፍጥ ግን ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ እንዲገባ ማድረጉ ንጉሡ እርሱ ነው ተብሎ በጠላት ዒላማ ውስጥ በቀጥታ እንዲገባ ለማ ድረግ ነበር። ይህም በዚያ ዘመን በእስራኤል መሪዎች ተደጋግሞ ሲፈጸም የታየ ነው።

18፥31 *እግዚአብሔርም ረዳው፤ አምላክም ከእርሱ መለሳቸው፤* ይህ በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 22፥32 ላይ አይገኝም፤ ይሁን እንጂ በአንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም በመጽሐፈ ነገሥት ላይ “እግዚአብሔርም ረዳው” የሚለው ሐረግ ይገኛል፤ ይህም የሚያሳየው የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ እነዚህን ቃላት የያዘውን የመጽሐፈ ነገሥት የዕብራይስጡን ቅጅ መከተሉን ነው።

ነጥረው በጥሩሩ መጋጠሚያዎች መካከል
አልፎ የእስራኤልን ንጉሥ ወጋው። ንጉሡም
ሠረገላ ነጂውን "ተመለስና ከጦርነቱ
አውጣኝ፤ ቈስያለሁና" አለው። 34ጦርነቱ
ቀኑን ሙሉ እንደ ተፋፋመ ዋለ፤ የእስራኤልም
ንጉሥ በሶርያውያን ፊት ለፊት በሠረ
ገላው ላይ እስከ ምሽት ድረስ ተደግፎ
ነበር፤ ፀሓይ ስትጠልቅም ሞተ።

19 የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሳፍጥ ኢየሩሳሌም
ወዳለው ቤተ መንግሥቱ በደኅና በተ
መለሰ ጊዜ፣ 2ባለ ራእዩ የአናኒ ልጅ ኢዩ
ሊገናኘው ወጣ፤ እንዲህም አለው፣ "አንተ
ክፉውን መርዳትህና እግዚአብሔርን የሚጠ
ሉትን ማፍቀርህ[ሀ] ተገቢ ነውን? ስለዚህ የእግዚ
አብሔር ቍጣ ባንተ ላይ ነው፤ 3ይሁን እንጂ
የአሼራን ዐምዶች ከምድሪቱ ስላስወገድህና
እግዚአብሔርን ለመፈለግ ልብህን ስላዘጋጀህ፣
መልካም ነገር ተገኝቶብሃል"።

## ኢዮሣፍጥ ዳኞችን ሾመ

4ኢዮሣፍጥ በኢየሩሳሌም ተቀመጠ፤ ከቤር
ሳቤህ እስከ ኰረብታማው አገር እስከ ኤፍሬም
ድረስ እንደ ገና በመውጣት ወደ ሕዝቡ
መካከል ገብቶ ወደ አባቶቻቸው አምላክ
ወደ እግዚአብሔር መለሳቸው። 5በምድሪቱም
ላይ በተመሸጉት የይሁዳ ከተሞች ሁሉ
ዳኞችን ሾመ፤ 6እንዲህም አላቸው፤ "እናንተ
የምትፈርዱት ለሰው ሳይሆን፣ ፍርድ በምት
ሰጡበት ጊዜ ሁሉ ከእናንተ ጋር ለሆነው
ለእግዚአብሔር ስለሆነ፣ በምትሰጡት ውሳኔ
ሁሉ ብርቱ ጥንቃቄ አድርጉ፤ 7አሁንም
እግዚአብሔርን መፍራት በእናንተ ላይ
ይሁን፤ በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ
ፍርድ ማጣመም፣ አድልዎ ማድረግና መማለጃ
መቀበል ስለሌለ ተጠንቀቃችሁ ፍረዱ።"

18፥34 2ዜና22፥5
19፥2 1ነገ16፥1፤ 2ዜና16፥2-9፤ 24፥18፡32፥25፤ መዝ7፥11፤ 139፥21-22
19፥3 1ነገ14፥13፤ 2ዜና17፥6፡18፥1፡20፥35፡25፥7
19፥5 ዘፍ47፥6፤ ዘፀ18፥26
19፥6 ዘሌ19፥15፤ ዘዳ16፥18-20፤ 17፥8-13
19፥7 ዘፍ18፥25፤ ዘፀ18፥16፤ ዘዳ10፥17፤ኢዮ8፥3፤ 13፥10፡32፥21፤ 34፥19
19፥8 1ዜና23፥4፤ 2ዜና17፥8-9፤ ሕዝ44፥24
19፥10 ዘዳ17፥8-13
19፥11 1ዜና28፥20
20፥1 1ዜና4፥41፤ መዝ83፥6
20፥2 ዘፍ14፥7፤ 1ሳሙ23፥29፤2ዜና2 4፥24፤መኃ1፥14

8ኢዮሳፍጥም በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔ
ርን ሕግ እንዲያስፈጽሙና ለሚነሡ ክርክ
ሮችም እልባት እንዲሰጡ ከሌዋውያን፣ ከካህ
ናትና ከእስራኤል ቤት አለቆች ጥቂት ሰዎች
ሾመ፤ እነርሱም መኖሪያቸው በኢየሩሳሌም
ሆነ። 9እነርሱንም እንዲህ ብሎ አዘዛቸው፤
"እግዚአብሔርን በመፍራት፣ በታማኝነትና
በፍጹም ልብ አገልግሉ። 10በየከተማው ከሚ
ኖሩት ወገኖቻችሁ ስለ ደም መፋሰስ ወይም
ሕግን፣ ትእዛዛትን፣ ደንብንና ሥርዐትን ስለ
መተላለፍ በሚቀርብላችሁ በማናቸውም
ጉዳይ እግዚአብሔርን እንዳይበድሉ
አስጠንቅቋቸው፤ ያለዚያ ግን ቍጣው
በእናንተና በወንድሞቻችሁ ላይ ይመጣል፤
ይህን ብታደርጉ በደለኞች አትሆኑም።
11"የእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ ላይ
የካህናቱ አለቃ አማርያ፣ የንጉሡ በሆነው ነገር
ሁሉ ላይ የይሁዳ ነገድ መሪ የሆነው የእስ
ማኤል ልጅ ዝባድያ በላያችሁ ተሾመዋል፤
ሌዋውያኑ ደግሞ በፊታችሁ አለቆች ሆነው
ያገለግላሉ፤ በርትታችሁ ሥሩ፤ እግዚአብሔርም
መልካም ከሚያደርጉ ጋር ይሁን።"

## ኢዮሣፍጥ ሞዓብንና አሞንን ድል ማድረጉ

20 ከዚህ በኋላ ሞዓባውያንና አሞናውያን
ከጥቂት ምዑናውያን[ለ] ጋር ሆነው
ኢዮሣፍጥን ለመውጋት መጡ።
2ሰዎችም መጥተው ኢዮሣፍጥን፣ "ግዙፍ
ሰራዊት ሊወጋህ ከሙት[መ] ባሕር ወዲያ ካለው
ከኤዶም[ሐ] መጥቶብሃል፤ እነሆም፣ ሐሰሶን ታማር

[ሀ]2 ወይም፣ ከሚጠሉት ጋር መተባበርህ
[ለ]1 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉሞች ከዚህ ጋር ይስማ ማሉ፤ ነገር ግን ዕብራይስጡ ምዒያማውያን ይላል።
[ሐ]2 አንድ የዕብራይስጥ ቅጂ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን አራም ይላል።
[መ]2 ምንም እንኳ የሙት ባሕር መሆኑን ግልጽ ቢሆንም አንዳንድ ቅጆች ሙት የሚለውን ቃል አይጨምሩም ።

*19፥1-3* ይህ በ1ነገ22 ላይ አይገኝም።

19፥2 *ክፉውን መርዳትህና... ተገቢ ነውን?* ከዚህ በፊት የኢዩ አባት አናኒ ይህንኑ የመሰለ ማስጠንቀቂያ ለኢዮሣፍጥ አባት ለአሳ ሰጥቶት ነበር (16፥7-9 ይመ)። ኢዮሣፍጥም ያንኑ ዓይነት ኅጢአት ሠርቶ ተገቢውን ቅጣት ተቀብሎአል (20፥35-37)።

19፥3፤ የ14፥3 አማራጭ ትርጉም ይመ።

19፥4፤ *ኢዮሳፍጥ... በመውጣት ወደ ሕዝቡ መካከል፤* ንጉሥ ኢዮሣፍጥ፣ ሕዝቡ በፍጹም ልቡ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ ለማድረግ በግዛቱ ሁሉ ከዳር እስከ ዳር ተዘዋውሮአል።

19፥5 *ዳኞችን ሾመ፤* ኢዮሣፍጥ የሚለው ስም "እግዚአብሔር ይፈርዳል" ማለት ሲሆን፣ ይህም እንዲህ ያለውን ፍትሓዊ አስተዳደር ላሰፈነ ሰው ተገቢ ስያሜ ነው። ኢዮሣፍጥ በአዲስ መልክ ያደራጀው የዚህ ዓይነቱ የፍርድ ችሎት መኖሩ (ቍ 5-11)፣ ከምርኮ ለተመለሱት የዜና መዋዕሉ ተደራሲያን የተለየ ጠቀሜታ ነበረው፤ ማኅበረሰቡ ይህን በምሣሌነት ተቀብሎ በሥራ ለመተርጐም ይረዳዋልና።

*19፥6፤* ከዘዳ16፥18-20፤17፥8-13 ጋር ያነጻጽሩ።

19፥7 *እግዚአብሔርን መፍራት በእናንተ ላይ ይሁን፤* የህልዎተ እግዚአብሔር አስፈሪነት ማናቸውንም ዓይነት ኢ ፍትሐዊ ፍርድ እንዳትሰጡ ይጠብቃችሁ ማለት ነው (የ1ዜና 14፥7 ማብ ይመ)።

19፥8 *ሕግ እንዲያስፈጽሙ......ከሌዋውያን፣ ከካህናትና፤* የ1ዜና 26፥29-32 ማብ ይመ። በአዲስ መልክ የተደራጀው የዚህ ዓይነቱ የዳኝነት ሥርዐት እንዲያመጣ ከሚፈለገው ውጤት አንዱ ቀድሞ በቤተ መንግሥቱና በቤተ ክህነቱ የቅርብ ተመልካችነት በከተ ማዪቱ ሽማግሌዎች ይከናወን የነበረው ጥንታዊው የዳኝነት ሥርዐት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ ሳይሆን አይቀርም።

19፥11 *የእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ ላይ... የንጉሡ በሆነው ነገር ሁሉ ላይ፤* ይህ በሃይማኖት ጉዳዮችና በንጉሡ አስተዳደር መካከል ያለው ሁለት ቦታ የመከፈል ሁኔታ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ከምርኮ ቡኋላ የኖረበትን ዘመን የሚያንጸባርቅ ነው ። የሰሎሞንና የሳዶቅን መቀባት 1ዜና29፥22 እንዲሁም ከዳዊት ዘር የሆነው ዘሩባቤል ከምርኮ የተመለሰው ሕዝብ ማስተዳደሩና የታላቁን ካህን የኢያሱን አገልግሎት ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ዘካ 4፥14፤6፥9-15)።

20፥1-30፤ በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ሕዝቦች ዝርያዎች ከምርኮ የተመለሰውን ማኅበረሰብ ያሠቃዩ ስለ ነበር የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በዚህ ስፍራ ለቀረበው ታሪክ ልዩ ትኵረት ሰጥቶታል (ነህ2፥19፤4፥1-3፡7-9፤ 6፥1-4፤ 13 ይመ)፤ ከዳዊት ዘር የሆነው ኢዮሣፍጥ የሰጠውን ምክር መሠረት በማድረግ (ቍ 20) በዘመኑ የነበሩትን ሰዎች ለማበረታታት ጸሓፊው ይህን ታሪክ ተጠቅሞበታል። ትረካው ትርጕም በሚሰጥ ሁኔታ የተዋቀረ ነው። ሁኔታዎች መገልበጣቸው ከሚያሳዩት ከመጀመርያውና ከመጨረሻው ክፍሎች ውጭ (ቍ 1-4፡28-30) ዋናውን ታሪክ ሦስት ቦታ መክፈል ይቻላል፤ (1) የኢዮሣፍጥ ጸሎት (ቍ 5-13)፤ (2) የእግዚአብሔር መልስ (ቍ 14-19)፤ (3) የተገኘው ከፍተኛ ድል (ቍ 20-27)። ከእነዚህም በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ማእከላዊውን ስፍራ የያዙ ወሳኝ ዐረፍተ ነገሮች አሉ፤ እነርሱም ቍልፍ በሆነ በአንድ ቃል ተያይዘዋል፤ ይኸውም፦ "ከዚህ ቤተ መቅደስ ፊት ለፊት በፊትህ ቆመን (ቍ9)፣ "ጸንታችሁ ቁሙ፤ እግዚአብሔር የሚሰጣችሁንም ማዳን እዩ (ቍ 17)፣ "የአሞንና የሞዓብ ሰዎችም የሴይርን ተራራ ሰዎች.... ለማጥፋት ተነሡባቸው (ቍ 23)።

20፥1 *ምዑናውያን፤* በኤዶም ውስጥ በሴይር ተራራ የሚኖሩ ሕዝቦች ናቸው (26፥7፤1ዜና 4፥41፤ ከ2ዜና 20፥10፡22-23 ጋር ያነጻጽሩ)

20፥2 *ከኤዶም፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ። አረማውያን በስተሰሜን ስለ ነበሩና በቍ1 ላይ ከሚገኙት ተዋጊዎች ጋር ስላል ተጠቀሱ፣ ኤዶም የሚለው ስም የገባው አራም በሚለው ስም ምትክ

በተባለው በዓይንጋዲ ናቸው" አሉት:: 3ኢዮሣ
ፍጥም እጅግ ስለ ፈራ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ
ወሰነ፤ በይሁዳም ሁሉ ጾም ዐወጀ:: 4የይ
ሁዳ ሕዝብም የእግዚአብሔርን ርዳታ ይሻ
ዘንድ በአንድነት ተሰበሰበ፤ ከይሁዳ ከተ
ሞች ሁሉም እግዚአብሔርን ለመፈለግ መጡ::
5ኢዮሣፍጥም በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፣
ከአዲሱ አደባባይ ፊት ለፊት በይሁዳና በኢ
የሩሳሌም ጉባኤ መካከል ቆመ፤ 6እንዲህም
አለ፤
"የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ
በሰማይ የምትኖር አምላክ አይደለህምን?
የምድር ሕዝቦችን መንግሥታት ሁሉ
የምትገዛ አንተ ነህ፤ ኀይልና ሥልጣን በእጅህ
ነው፤ ሊቋቋምህም የሚችል ማንም የለም::
7አምላካችን ሆይ፤ የዚህችን ምድር ነዋ
ሪዎች ከሕዝብህ ከእስራኤል ፊት አሳድደህ
ያስወጣህና ለወዳጅህ ለአብርሃም ዘሮች
ለዘላለም የሰጠሃቸው አንተ አይደለህምን?
8እነርሱም ተቀመጡባት፤ ለስምህ መቅደስ
ሠሩባት፤ እንዲህም አሉ፤ 9'የፍርድ ሰይ
ፍም ሆነ የቸነፈር ወይም የራብ መከራ ቢደ
ርስብን ስምህ በተጠራበት በዚህ ቤተ
መቅደስ ፊት ለፊት፣ በፊትህ ቆመን
በጭንቀታችን ወደ አንተ እንጮሃለን፤ አን
ተም ትሰማናለህ፤ ታድነናለህም::'
10እስራኤል ከግብፅ በወጡ ጊዜ፣ ግዛታቸውን
እንዳይወርሩባቸው በማድረግህ ከእነርሱ
ተመልሰው ሳያጠፏቸው የቀሩት የአሞን፣
የሞዓብና የሴይር ተራራ ሰዎች እነሆ እዚህ
አሉ:: 11እነሆ፣ አንተ ርስት አድርገህ ከሰጠኸን
ምድር እኛን በማፈናቀል ወሮታ ሊመልሱልን
መጥተዋል:: 12አምላካችን ሆይ፤ አንተ አትፈርድ
ባቸውምን? የመጣብንን ይህን ታላቅ ሰራዊት
እንቋቋም ዘንድ አቅም የለንምና የምናደ
ርገውን አናውቅም ነገር ግን ዓይኖቻችን
ወዳንተ ናቸው::
13የይሁዳ ሰዎች ሁሉ ከሚስቶቻቸው፣ ከል
ጆቻቸውና ከሕፃኖቻቸው ጋር በእግዚአብሔር
ፊት ቆመው ነበር::
14በዚህ ጊዜ የአሳፍ ዘር በሆነው በሌዋዊው
በዘካሪያስ ልጅ፣ በየሕዚኤል ላይ የእግዚ
አብሔር መንፈስ መጣ:: ዘካርያስም የበናያስ
ልጅ ሲሆን፣ በናያስም የማታንን ልጅ የሆነው
የይዒኤል ልጅ ነው::

20፥3 1ሳሙ7፥6፤ ዕዝ8፥23፤ ነህ1፥4፤አስ4፥16፤ ኢሳ58፥6፤ ኤር36፥9፤ዳን9፥3፤ ኢዩ1፥14፤ 2፥15፤ዮና3፥5፡7
20፥4 ኤር36፥6
20፥6 ዘዳ4፥39፤ 1ዜና29፥11-12፤2ዜና25፥8፤ ኢዮ25፥2፤ 41፥10፤42፥2፤ ኢሳ14፥27፤ ኤር32፥27፤49፥19፤ ማቴ6፥9
20፥7 ዘፍ12፥7፤ ኢሳ41፥8፤ያዕ2፥23
20፥8 2ዜና6፥20
20፥9 2ዜና6፥28
20፥10 ዘኍ20፥14-21፤ዘዳ2፥4-6፡9፡18-19
20፥11 መዝ83፥1-12
20፥12 መሳ11፥27፤ መዝ25፥15፤ ኢሳ30፥15፤ 45፥22፤ሚክ7፥7
20፥14 1ዜና9፥15፤ 12፥18
20፥15 1ሳሙ17፥47፤ 2ዜና32፥7፤ መዝ91፥8
20፥17 ዘፀ14፥13
20፥18 ዘፍ24፥26፤ 2ዜና29፥29
20፥20 ዘፍ39፥3፤ ምሳ16፥3፤ኢሳ7፥9
20፥21 1ዜና16፥29፤ 2ዜና5፥13፤ መዝ136፥1
20፥22 2ዜና13፥13
20፥23 ዘፍ19፥38፤ መሳ7፥22፤1ሳሙ14፥20፤2ዜና21፥8፤ሕዝ38፥21

15እርሱም እንዲህ አለ፤ "ንጉሥ ኢዮሣፍጥ፣
እናንተም በይሁዳና በኢየሩሳሌም የምትኖሩ
ሁሉ አድምጡ! እግዚአብሔር እንዲህ ይላችኋል፤
'ውጊያው የእግዚአብሔር እንጂ የእናንተ
አይደለምና፣ ከዚህ ታላቅ ሰራዊት የተነሣ
አትፍሩ፣ አትደንግጡ፣ 16ነገ በእነርሱ ላይ
ውረዱ፤ እነርሱ በጺጽ መተላለፊያ ሽቅብ
ይወጣሉ፣ እናንተም በይሩኤል ምድረ በዳ
ውስጥ በሸለቆው መጨረሻ ላይ ታገኟቸዋላ
ችሁ:: 17ይህን ጦርነት የምትዋጉት እናንተ
አይደላችሁም፤ ይሁዳና ኢየሩሳሌም ሆይ፤
ቦታ ቦታችሁን ያዙ፤ ጸንታችሁ ቁሙ፤
እግዚአብሔር የሚሰጣችሁንም ማዳን
እዩ:: አትፍሩ፤ አትደንግጡም፤ ነገውኑ
ውጡና ግጠሙአቸው፤ እግዚአብሔርም
ከእና ንተ ጋር ይሆናል::' "
18ኢዮሣፍጥ በግምባሩ ወደ መሬት ተደፋ፤
የይሁዳና የኢየሩሳሌምም ሕዝብ ሁሉ በእግ
ዚአብሔር ፊት ወደቁ፤ ሰገዱም:: 19ከቀዓትና
ከቆሬ ወገኖች ጥቂት ሌዋውያንም ቆመው፣
እጅግ ከፍ ባለ ድምፅ የእስራኤልን አምላክ
እግዚአብሔርን አመሰገኑ::
20በማግሥቱ ጠዋት በማለዳ ተነሥተው
ወደ ቴቊሔ ምድረ በዳ ሄዱ:: መንገድ እንደ
ጀመሩም ኢዮሣፍጥ ቆሞ፣ "ይሁዳና የኢየሩ
ሳሌም ሕዝብ ሆይ፣ አድምጡኝ! በአምላካችሁ
በእግዚአብሔር እመኑ፤ ትጸናላችሁ:: በነቢያቱም
እመኑ፤ ይሳካላችሁማል" አላቸው:: 21ከሕዝ
ቡም ጋር ከተመካከረ በኋላ ከሠራዊቱ ፊት
ቀድመው በመሄድ፣
"እግዚአብሔርን አመስግኑ፣ ፍቅሩ ለዘላለም
ጸንቶ ይኖራልና' እያሉ ለእግዚአብሔር የሚዘምሩና
ስለ ቅድስናውም ክብር የሚያወድሱ ሰዎችን
መደበ::
22መዘመርና ማወደስ እንደ ጀመሩም፣ እግዚ
አብሔር ይሁዳን በወረሩት በአሞን፣ በሞዓ
ብና በሴይር ተራራ ሰዎች ላይ ድብቅ ጦር
አመጣባቸው፤ ተሸነፉም:: 23የአሞንና የሞዓብ
ሰዎችም የሴይርን ተራራ ሰዎች ለማጥፋትና
ለመደምሰስ ተነሡባቸው:: ከሴይር የመጡትን
ሰዎች ካጠፉ በኋላም፣ እርስ በርስ ተጠፋፉ::
24የይሁዳ ሰዎች ምድረ በዳውን ቍልቍል
ወደሚያሳየው ቦታ መጥተው ግዙፉን ሰራዊት
ሲመለከቱ፣ መሬቱ ሬሳ በሬሳ ሆኖ አዩ፤
አንድም ሰው አላመለጠም::

ነው የሚል ግምት አለ፤ በዕብራይስጡ "አራም" በሚለውና "ኤዶም" በሚለው ቃል መካከል ያለው ልዩነት የአንዲት ሆሄ ብቻ ነው ሆሄው እዚህም ሆነ እዚያ ቢገባ በቅርጽ አንድ ዐይነት ስለሆነ፣ ገልባጭን በቀላሉ ሊያደናግር የሚችል ነው::

*20፥5-12፤* የኢዮሣፍጥ ጸሎት እርሱ በእግዚአብሔር አገዛዝ ሕዝቡን ያስተዳደረ እውነተኛ ንጉሥ፣ እውነተኛው የዳዊት ልጅ፣ የሚጠበቀውም መሲሕ እውነተኛ አምሳያ መሆኑን ያሳያል (ከ1ዜና መግቢያ "ዐላማና መሪ ሐሳብ" የሚለውን ይመ)::

*20፥9፤* ከሰሎሞን ጸሎትና የመለኮታዊ መልስ ተስፋ ከተሰጠበት ክፍል ጋር የሚመሳሰል ነው (6፥14-42፤7፥12-22)::

*20፥15፤* ዘፀ14፥13-14 ይመ::

20፥16 *በጺጽ መተላለፊያ፤* ከዓይንጋዲ በስተ ሰሜን ዐሥራ አንድ ኪሎ ሜትር ላይ ይነሣና ተጠምዝዞ ቤተቊሔ በስተምዕራብ ብቅ ይላል:: *በይሩኤል፤* ከቴቊሔ ደቡብ ምሥራቅ ላይ ትገኛለች::

20፥19፤ *ሌዋውያንም፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በካህናትና በሌዋውያን ላይ ያለው አዎንታዊ አመለካከት በትረካው ሁሉ በግልጽ ይታያል (ቍ14፡21-22፡28)::

20፥20 *በአምላካችሁ በእግዚአብሔር እመኑ ... በነቢያቱም፤* ይህም የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በነበረበት ዘመን የኖሩት ሰዎች ከዚህ ከዳዊት ልጅ አንደበት ሊሰሙት የሚገባ ታላቅ ቁም ነገር ነበር፤ የወደፊቱ ተስፋቸው ማረፍ ያለበት በእግዚአብሔርና ይህንኑ በሚያጸኑላቸው በነቢያቱ ቃል ላይ ነውና::

20፥21 *ስለ ቅድስናውም ክብር፤* የመዝ29፥2 ማብ ይመ::

20፥22 *ድብቅ ጦር፤* የዚህ "የድብቅ ጦር" ምንነት በቍ 23 ላይ ተመልክቶአል፤ ጦርነቱም የእስራኤል ጠላቶች ግራ በመጋባት እርስ በርስ የተላለቁበት ነበር፤ የተገኘውም ድል በጌዴዎን ከተገኘው ድል ጋር ተመሳሳይ ነው (መሳ7፥22)::

20፥26 *እስከ ዛሬ ድረስ፤* የ5፥9 ማብ ይመ::

25ኢዮሣፍጥና ሰዎቹም ምርኮአቸውን ለማጋዝ
ሄዱ፤ በዚያም መካከል እጅግ ብዙ መሣሪያና
ልብስ፣ °ሊሸከሙ ከሚችሉትም በላይ
ውድ ዕቃዎችን አገኙ። ምርኮውም ከመብዛቱ
የተነሣ ለማሰባሰብ ሦስት ቀን ፈጀ። 26በአራ
ተኛውም ቀን እግዚአብሔርን ባመሰገኑበት
በበረከት° ሸለቆ ተሰበሰቡ፤ ያም ስፍራ እስከ
ዛሬ ድረስ የበረከት ሸለቆ ተብሎ የተጠራው
ከዚህ የተነሣ ነው።
27እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው ላይ እንዲ
ደሰቱ ስላደረጋቸው፣ የይሁዳና የኢየሩሳሌም
ሰዎች ሁሉ በኢዮሳፍጥ እየተመሩ፣ በታላቅ
ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። 28ወደ
ኢየሩሳሌም ከተማ እንደገቡም በበገና፣ በመ
ሰንቆና በመለከት ድምፅ ታጅበው ወደ እግ
ዚአብሔር ቤተ መቅደስ አመሩ።
29እግዚአብሔር የእስራኤልን ጠላቶች እንዴት
እንደተዋጋቸው በሰሙ መንግሥታት ሁሉ
ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ፍርሀት ወደቀባቸው።
30እግዚአብሔር በየአቅጣጫው ዕረፍት ስለ ሰጠው፣
የኢዮሣፍጥ መንግሥት ሰላም አግኝቶ ነበር።

## የኢዮሣፍጥ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ

20፥31-21፥1 ተጓ ምብ —1ዜና22፥41-50

31ኢዮሣፍጥ በይሁዳ ላይ ነገሠ። መንገሥ
በጀመረ ጊዜም ዕድሜው ሠላሳ አምስት ዓመት
ሲሆን፣ በኢየሩሳሌም ተቀምጦ ሃያ አምስት
ዓመት ገዛ። እናቱም የሺልሒ ልጅ ዓዙባ
ነበረች። 32እርሱም በአባቱ በአሳ መንገድ
ሄደ፤ ከዚያም ፈቀቅ አላለም፤ በእግዚአብሔ
ርም ፊት መልካም የሆነውን ነገር አደረገ።
33ያም ሆኖ ግን ማምለኪያ ኰረብታዎች
ሙሉ በሙሉ አልተወገዱም፤ ሕዝቡም ገና
ልቡን በአባቶቹ አምላክ ላይ አልጣለም ነበር።
34በኢዮሣፍጥ ዘመነ መንግሥት ከመጀመሪያ
እስከ፣ መጨረሻ የተከናወኑት ሌሎች ተግ
ባራት የአናኒ ልጅ ኢዩ በዘገበው የእስራ
ኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝ
ግቦአል።

20፥29 ዘፍ35፥5፤ ዘፀ14፥14፤ ዘጸ2፥25
20፥30 1ዜና22፥9
20፥33 2ዜና17፥6
20፥34 1ነገ16፥1
20፥35 2ዜና16፥3፤ 19፥1-3
20፥37 1ነገ9፥26
21፥1 1ዜና3፥11
21፥3 2ዜና11፥10፡ 23
21፥4 መሳ9፥5፤ 1ነገ2፥12
21፥6 1ነገ12፥28-

35ከዚህ በኋላ የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ
ሥራው እጅግ ክፉ ከሆነው ከእስራኤል ንጉሥ
ከአካዝያስ ጋር የስምምነት ውል አደረገ፤
36የንግድ መርከብ[n] ለመሥራትም ተስማሙ፤
መርከቦቹንም በዔጽዮንጋብር አሠሩ። 37የመ
ሪሳ ሰው የሆነው የዶዳያ ልጅ አልዓዛር በኢ
ዮሣፍጥ ላይ፣ "ከአካዝያስ ጋር የስምምነት ውል
ስለ አደረግህ፣ እግዚአብሔር ሥራህን ያፈር
ሰዋል" ሲል ትንቢት ተናገረበት፤ መርከቦቹም
ተሰበሩ፤ ለንግዱም ሥራ መንቀሳቀስ አልቻ
ሉም።[π]

21 ኢዮሣፍጥ እንደ አባቶቹ ሁሉ አንቀላፋ፤
እነርሱ በተቀበሩበትም በዳዊት ከተማ
ተቀበረ። ልጁ ኢዮራምም በእርሱ ፈንታ ነገሠ።
2የኢዮራም ወንድሞች የሆኑት የኢዮሣፍጥ
ልጆችም ዓዛርያስ፣ ይሒኤል፣ ዘካርያስ፣
ዔዛርያስ፣ ሚካኤልና ሰፋጥያስ ይባላሉ።
እነዚህ ሁሉ የእስራኤል[r] ንጉሥ የኢዮ
ሣፍጥ ልጆች ነበሩ። 3አባታቸውም ብዙ
የብርና የወርቅ፣ የውድ ዕቃዎችም ስጦታ
እንዲሁም በይሁዳ ያሉትን የተመሸጉ ከተሞች
ሰጣቸው፤ ነገር ግን መንግሥቱን ለኢዮራም
ሰጠ፤ የበኵር ልጁ ነበርና።

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮራም

21፥5-10፡20ተጓ ምብ —2ዜና8፥16-24

4ኢዮራም በአባቱ መንግሥት ላይ ተደላድሎ
ከተቀመጠ በኋላ ወንድሞቹን በሙሉ ከጥቂት
የእስራኤል አለቆች ጋር በሰይፍ ገደለ።
5ኢዮራም በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሰላሳ ሁለት
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ስም
ንት ዓመት ገዛ።

°25 አንዳንድ የዕብራይስጥና የቩልጌት ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማ ማሉ ፤ ነገር ግን አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ሬሳ ይላል።
°26 በዕብራይስጡ፣ በራካ ማለት በረከት ማለት ነው።
[n]36 ዕብራይስጡ፣ ወደ ተርሴስ ሊሄዱ የሚችሉ መርከቦች ይላል።
[π]37 ዕብራይስጡ፣ ወደ ተርሴስ መሄድ አልቻሉም ይላል።
[r]2 በሁለተኛው የዜና መዋዕል መጽሐፍ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው ይህ ይሁዳ ነው።

20፥29 *ከእግዚአብሔር ዘንድ ፍርሀት፤* የ1ዜና14፥17ማብ ይመ።

20፥30 *በየአቅጣጫው ዕረፍት፤* በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ መሠረት ከጠላት ዕረፍት ማግኘት ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ከሚገኙት በረከቶች አንዱ ነው (14፥5-7፤15፥15፤1ዜና22፥8-9፡18)። በእግዚአብሔር መንገድ የሄዱ ነገሥታት (አብያ፣ አሳ፣ ኢዮሣፍጥ፣ ዖዝያን፣ ሕዝቅያስ) በጦርነት ላይ ድልን ሲጐናጸፉ፣ ክፉዎቹ ነገሥታት (ኢዮራም፣ አካዝ፣ ኢዮአስ፣ሴዴቂያስ) ግን ተሸንፈዋል።

*20፥31 ሃያ አምስት ዓመት፤* በመጽሐፈ ነገሥት የተጻፈው ግን ሃያ ሁለት ዓመት ነው (አሥራ ስምንቱ በ2ነገ3፥1 ሲገኝ አራቱ ደግሞ 8፥16 ላይ ይገኛል)። ይህ የቍጥር ልዩነት የሚወገደው አባቱ አሳ ለሦስት ዓመት ክፉኛ በታመመ ጊዜ የአባቱን ሥልጣን በመጋራት ያስተዳደረበትንና በሩንታው የሚተካበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የፈጀበትን ጊዜ በማሰብ ሊሆን ይችላል(16፥10-14)። የመጽሐፈ ነገሥቱ ጸሓፊ የዘገበው ግን አባቱ አሳ ከሞተ በኋላ ብቻውን የገዛበትን ዘመን ነው።

20፥33 *ማምለኪያ ኰረብታዎች፡ አልተወገዱም፤* የ17፥6 ማብ ይመ።

20፥34 *የአናኒ ልጅ ኢዩ፤* የ19፥2 ማብ ይመ።

*20፥35-37፤* 1ነገ22፥48-49 ይመ።

በአካባ ባሕረ ሰላጤ ዕቃዎችን በመርከብ በማመላለስ ከሚካሄደው ንግድ የሚገኘው ትርፍ አላስፈላጊ ስምምነት እንዲፈጥር ኢዮሣፍጥን ሳይፈታተነው ኣልቀረም (19፥2እና ማብ ይመ) ሰሎሞንም ቀደም ሲል ለተመሳሳይ ዐላማ እስራኤላውያን ካልሆኑ ነገሥታት ጋር የቃል ኪዳን ውል ያደርግ ነበር (8፥17-28)

20፥35 *ከአካዝያስ፤* ዘመነ መንግሥቱ ከ853-852 ዓ.ቅ.ክ ነበር ስለ ዘመነ መንግሥቱ በ1ነገ22፥51-2ነገ1፥18 ይመ።

21፥2 *የኢዮሣፍጥ ልጆችም፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ስለ ኢዮሣፍጥ ቤተ ሰብ ብዛት በተለይም ስባቱን ወንዶች ልጆቹን በመጥቀስ (11፥8-22፤1ዜና25፥5እና ማብ ይመ)፣ ይህ ከእግዚአብሔር የመባረክ ምልክት መሆኑን ያሳያል። የኢዮሣፍጥ ወንዶች ልጆች ብዛት ከክፉው ሰው ከኢዮራም ልጆች ብዛት ጋር ሲነጻጸር፣ እርሱ የገዛ ወንድሞቹን ከገደለ በኋላ ከራሱ ቤተ ሰብ የተረፈ ቢኖር የመጨረሻ ልጁ ብቻ ነበር (ቍ17)። የአዮራም ሚስት ጎቶልያም ይህንኑ የመሰለ ግድያ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ስትፈጽም እናገኛታለን (22፥10)።

*21፥3፤* ሮብዓም የፈጸመውን ተመሳሳይ ድርጊት (ከ11፥23) ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

*21፥4-20፤* 2ነገ8፥16-24 ይመ።

*21፥4* ዙፋኑን ይቀናቀኑኛል በሚል ፍራቻና ጥርጣሬ ስለ ፈሰሰው ደም መጽሐፈ ነገሥት አይናገርም፤ ድርጊቱ ግን የሰሜኑ ክፍል ነገሥታት ከሚከተሉት መንገድ ጋር ተመሳሳይ ነበር (ቍ6)። በደቡብ ግዛት ዙፋን ላይ የሚቀመጠው ንጉሥ የአክአብን ልጅ ማግባት የለበትም ሲሉ ከተቃወሙት ወገኖች ግንባር ቀደሞቹ የእስራኤል መሳፍንት የተባሉት የይሁዳ መሪዎች ሳይሆኑ አልቀሩም እዚህ ላይ "እስራኤል" ለሚለው ቃል ስለተሰጠው ትርጕም የ12፥1 ማብ ይመ።

21፥5 *ስምንት ዓመት፤* ከ848-841 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው። ከ853-848 ዓ.ቅ.ክ ያለው ጊዜ ኢዮራም የአባቱን የኢዮሳፍጥን ሥልጣን በመጋራት የገዛበት ጊዜ ሳይሆን አይቀርም (ከ2ነገ 1፥17፤3፥1 ጋር ያነጻጽሩ)።

6እርሱም የአክዓብን ልጅ አግብቶ ስለ
ነበር የአክዓብ ቤት እንደ አደረገው ሁሉ
የእስራኤል ነገሥታት የሄዱበትን መንገድ
ተከተለ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ ድርጊት
ፈጸመ። 7ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከዳ
ዊት ጋር ካደረገው ኪዳን የተነሣ፣ የዳዊትን
ቤት ማጥፋት አልፈለገም፤ ለዳዊትና ለዘሩ
ለዘላለም የሚጸና መብራት እንዲኖር ለማ
ድረግ ተስፋ ሰጥቶ ነበርና።
8በኢዮራም ዘመነ መንግሥት ኤዶም በይሁዳ
ላይ ዐምፆ፣ የራሱን ንጉሥ አነገሠ። 9ስለዚህ
ኢዮራም የጦር ሹማምንቱንና ሰረገላዎቹን ሁሉ
ይዞ ወደዚያው ሄደ። ኤዶማውያንም እር
ሱንና የሰረገላ አዛዦቹን ሁሉ ከበቡ፤ እርሱ ግን
በሌሊት ተነሥቶ የከበቧቸውን መታ። 10ኤዶምም
እስከ ዛሬ ድረስ በይሁዳ ላይ እንደ ዐመፀ ነው።
ኢዮራም የአባቶቹን አምላክ እግዚአብሔርን ስለ
ተወ፣ የልብና ከተማ በዚያኑ ጊዜ ዐመፀችበት።
11ከዚህም በላይ በይሁዳ ኰረብቶች ላይ
መስገጃ ስፍራዎች ሠርቶ የኢየሩሳሌም ሕዝብ
በዚያ እንዲያመነዝር አደረገ፤ ይሁዳንም
አሳተ።
12ከነቢዩ ከኤልያስ እንዲህ የሚል ደብዳቤ
ለኢዮራም መጣ፤
"የአባትህ የዳዊት አምላክ እግዚአብሔር እን
ዲህ ይላል፤ 'አንተ በአባትህ በኢዮሣፍጥ ወይም
በይሁዳ ንጉሥ በአሳ መንገድ አልሄድህም፤
13ነገር ግን በእስራኤል ነገሥታት መንገድ
ሄደሃል፤ የአክዓብ ቤት የእስራኤልን ሕዝብ
እንዲያመነዝር እንዳደረገ ሁሉ፣ አንተም
ይሁዳና የኢየሩሳሌም ሕዝብ እንዲያመነዝሩ
አሳሳትሃቸው፤ እንዲሁም ካንተ የሚሻሉትን፣
የገዛ ወንድሞችህንና የአባትህን ቤተ ሰብ
አባላት ገደልሃቸው፤ 14ስለዚህ እነሆ፤ እግዚ
አብሔር ሕዝብህን፣ ልጆችህን፣ ሚስቶችህንና
ያለህን ሁሉ በታላቅ መቅሠፍት ይመታል።
15አንተም ራስህ በየዕለቱ እየባሰ በሚሄድ
የአንጀት በሽታ ክፉኛ ትታመማለህ፤ በመጨ
ረሻም ሕመሙ አንጀትህን ወደ ውጭ ያወጣዋል።'"
16እግዚአብሔርም ፍልስጥኤማውያንንና በኢ
ትዮጵያውያን አጠገብ የሚኖሩ ዐረቦችን በኢዮ
ራም ላይ በጠላትነት እንዲነሡ አደረገ።
17እነርሱም በይሁዳ ላይ ወጡ፤ ወረሯትም።
በንጉሡ ቤተ መንግሥት የሚገኘውን ዕቃ ሁሉ፣
ከወንዶች ልጆቹና ከሚስቶቹ ጋር ወሰዱ፤
ከመጨረሻ ልጁ ከአካዝያስ[a] በስተቀር አንድም
ልጅ አልቀረለትም።
18ከዚህ ሁሉ በኋላ እግዚአብሔር ሊድን
በማይችል የአንጀት በሽታ ኢዮራምን ቀሠ
ፈው። 19ሕመሙም ሲያሠቃየው ከቈየ በኋላ፣
በሁለተኛው ዓመት መጨረሻ ላይ በዚሁ ሳቢያ
አንጀቱ ወጥቶ በከባድ ሥቃይ ሞተ። ሕዝቡም
ለአባቶቹ ክብር እሳት ያነድዱ ነበር፤ ለእርሱ
ግን አላነደዱለትም።
20ኢዮራም ሲነግሥ ዕድሜው ሠላሳ ሁለት
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ስምንት
ዓመት ገዛ። በሞተ ጊዜም ማንም አላዘ
ነለትም፤ በዳዊትም ከተማ እንጂ በነገሥታቱ
መቃብር አልቀበሩትም።

## የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ

22፥1-6ተጓ ምብ —2ዜና8፥25-29
22፥7-9ተጓ ምብ —2ዜና9፥21-29

22 ከዐረቦች ጋር ወደ ሰፈር የመጡት
ወራሪዎች፣ ታላላቅ ወንድሞቹን ሁሉ
ገድለዋቸው ስለ ነበር፣ የኢየሩሳሌም ሕዝብ
የኢዮራምን የመጨረሻ ልጅ አካዝያስን በአባቱ
ምትክ አነገሡት። ስለዚህ የይሁዳ ንጉሥ

[a]17 በዕብራይስጥ *አካዝ* እና *ኢዮአስ* አንድ ናቸው።

30፤2ዜና18፥1፤22፥3
21፥7 2ሳሙ7፥13፡15፤21፥17፤23፥3
21፥8 2ዜና20፥22፥23
21፥10 ዘኍ33፥20
21፥12 2ነገ1፥16-17፤2ዜና14፥2፤17፥3-6
21፥13 1ነገ2፥32፤16፥29-33
21፥15 ዘኍ12፥10
21፥16 2ዜና17፥10-11፤22፥1፤26፥7
21፥17 2ነገ12፥18፤2ዜና22፥1፤ኢል3፥5
21፥19 2ዜና16፥14
21፥20 2ዜና24፥25፤ 28፥27፤33፥20
22፥1 2ዜና21፥16-17፤23፥20-21፤26፥1፤33፥25፤36፥1

21፥6 *የአክአብን ልጅ አግብቶ ስለ ነበር፤* በ18፥1 ላይ የተጠቀሰው ጋብቻ በኢዮሣፍጥና በአክአብ መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማጠናከር ሳይሆን አይቀርም፤ እንዲህ ያለ የፖለቲካ ጥቅም የሚገኝበት ጋብቻ የተለመደ ነበረ። አብዛኛው የሰሎሞን ጋብቻ እንደ አክአብና እንደ ኤልዛቤል ጋብቻ ሁሉ ዓለም አቀፍ ግንኙነትን የሚያጸና ነው።

*21፥8-10፤* የእግዚአብሔር ሰው የነበረው ኢዮሣፍጥ ኤዶምን ድል ያደረገ ሲሆን (20፥1-30)፣ ክፉው ኢዮራም ግን በመሸነፉ፣ ኤዶምን የይሁዳ ግዛት አድርጎ ለማቈየት ያደረገው ጥረት አልተሳካለትም (የ20፥30 ማብ ይመ)።

21፥10 *እስከ ዛሬ ድረስ፤* የ5፥9 ማብ ይመ። *የልብና፤* በይሁዳና በፍልስጥኤም መካከል የምትገኝ ከተማ ናት። *ኢዮራም… እግዚአብሔርን ስለ ተወ፤* በ2 ነገ 8፥22 ላይ፤ አይገኝም። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ይህን ፍርድ የዘገበው ነገሥታቱ ለእግዚአብሔር ቢታዘዙ ወዲያውኑ እንደሚባረኩ፣ ባይታዘዙ ግን ፍዳ የሚጠብቃቸው መሆኑን ለማመልከት ነው (የ12፥1-14፤12፥2 ማብ፣ እንዲሁም ከ1ዜና መዋዕል መጽሐፍ መግቢያ "ዓላማና መሪ ሐሳብ" የሚለውን ይመ)።

*21፥12-20* ሀ፤ በተጓዳኙ ክፍል (2ነገ8)ላይ አይገኝም።

*21፥12-15፤* ከኤልያስ ስለ ተላከው ደብዳቤ በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ላይ የተወሣው በዚህ ክፍል ብቻ ነው፤ መጽሐፈ ነገሥት ግን ልዩ ትኵረት ሰጥቶታል (1ነገ17-2ነገ2)። ይህ የኤልያስ ደብዳቤ፣ ኢዮራም ካለመታዘዙ የተነሣ ወዲያው የሚገጥመውን መከራ ማለት በጦርነት እንደሚሸነፍ ሚስቶቹና ልጆቹ በጦርነት እንደሚገደሉና ኢዮራም ራሱ ለሞት በሚያበቃ ሕመም እንደሚታመም ይናገራል (የ16፥12 ማብ ይመ)፣ ከአሳ የእግር ሕመምና (16፥12-14) ከዖዝያን ለምጽ (26፥16-23) ጋር ያነጻጽሩ። መጽሐፈ ነገሥት ኢዮራም የሞተበትን ምክንያት አይገልጽም። አንዳንድ ሰዎች "ይህ ደብዳቤ በትክክል ከኤልያስ የተጻፈ አይደለም፤ ምክንያቱም ኤልያስ ወደ ሰማይ የተወሰደው ኢዮራም ከመንገሡ በፊት ነው" የሚል ክርክር ያቀርባሉ፤ ይህ ግን ከድምዳሜ የሚያደርስ ነጥብ ሊሆን አይችልም (2ነገ1፥17፤ እንዲሁም የ2ነገ 3፥11 ማብ ይመ)። ኤልያስ የተነጠቀው ዘግየት ብሎ በ848 ዓ.ቅ.ክ. እንደሆን ይገመታል።

21፥20 *ስምንት ዓመት፤* የቍ5 ማብ ይመ። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የአንዱን ንጉሥ ዘመነ መንግሥት በተመለከተ ስለ ዝርዝር ጕዳዩ ለአንባቢዎቹ የታሪክ ምንጩን ያገኘበትን ቦታ ሳይጠቅስ ሲያልፍ ይህ የመጀመሪያው ነው። *በነገሥታቱ መቃብር አልቀበሩትም ፤* ኢዮራም በነገሥታቱ መካነ መቃብር በወጋቸው መሠረት በክብር እንዳይቀበር ሕዝቡ መቃወሙን የሚያወሣው የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ብቻ ነው (ከ24፥25 ጋር ያነጻጽሩ)።

*22፥1-9፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የአካዝያስን ዘመነ መንግሥት ታሪክ በተመለከተ ያቀረበው ዘገባ በ2ነገ8፥24-9፥29 ላይ ባለው ተጓዳኝ ምንባብ ከተጻፈው እጅግ ያነሰ ነው፤ ይህም የሆነበት ምክንያት የመጽሐፈ ነገሥቱ ተራኪ ልዩ ትኵረት የሰጠው በኢዩ ማመፅና በዖምሪ ሥርወ መንግሥት መውደቅ ላይ ሳይሆን አይቀርም (2ነገ8፥26 እንዲሁም 1ነገ16፥21-28 ይመ)። ይህ የሰሜኑን መንግሥት የሚመለከት ስለ ሆነ ጸሓፊው በሰፊው ሊዘግበው አልፈለገም። የዜና መዋዕሉ ትረካ ነገሥታቱ ቢታዘዙ በረከት፣ ባይታዘዙ ግን ፍዳ የሚጠብቃቸው መሆኑን እዚህም ላይ ያሳያል። አካዝያስ በተፈጥሮው ክፉ ሰው ስለ ሆነና ለእግዚአብሔር ከማይታዘዙ ወገኖች ጋር ኅብረት ስለ ፈጠረ፣ ፍዳው ውሉ ሳያድር እንደተከፈለው እናያለን፤ ዘመነ መንግሥቱም ከአንድ ዓመት ሊያልፍ አልቻለም (የ16፥2-9 ማብ እንዲሁም ከ1ዜና መግቢያ "ዓላማና መሪ ሐሳብ" የሚለውን ይመ)።

22፥1 *ታላላቅ ወንድሞቹን ሁሉ ገድለዋቸው ስለ ነበር፤* ለእግዚአብሔር ካለመታዘዝ የሚመጣውን የአጸፋ ቅጣት በአጽንዖት ያሳያል፤ ወንድሞቹን ሁሉ የገደለው ኢዮራም የገዛ ልጆቹ ሲገደሉ በዐይኑ ማየት ነበረበት (21፥4፡13፡16-17)።

የኢዮራም ልጅ አካዝያስ መግዛት ጀመረ።
2አካዝያስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሃያ ሁለት[ፘ]
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም አንድ
ዓመት ገዛ። እናቱም ጎቶልያ የተባለች የዘ
ንበሪ የልጅ ልጅ ነበረች።
3እናቱ ክፋትን እንዲያደርግ ትመክረው
ስለ ነበር፣ እርሱም በአክዓብ ቤት መንገድ
ሄደ። 4ከአባቱ ሞት በኋላ የአክዓብ ቤት አማ
ካሪዎቹ በመሆን ወደ ጥፋት ስለ መሩት፣
የአክዓብ ቤት እንዳደረገው ሁሉ እርሱም
*በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ነገር አደረገ። 5እንዲ
ሁም የእስራኤል ንጉሥ የአክዓብ ልጅ ኢዮ
ራም የሶርያን ንጉሥ አዛሄል ለመውጋት ወደ
ሬማት ገለዓድ በሄደ ጊዜ የእነዚህኑ ሰዎች
ምክር ተከትሎ ከኢዮራም ጋር አብሮት ሄደ፣
ሶርያውያንም ኢዮራምን አቈሰሉት።
6ስለዚህ ከሶርያ ንጉሥ ከአዛሄል ጋር ባደ
ረገው ጦርነት ሬማት[ገ] ላይ ከደረሰበት ቍስል
ለመዳን ወደ ኢይዝራኤል ተመለሰ።
የአክዓብ ልጅ ኢዮራም በመቍሰሉም የይ
ሁዳ ንጉሥ የኢዮራም ልጅ አካዝያስ ሊጠ
ይቀው ወደ ኢይዝራኤል ወረደ።
7አካዝያስ ኢዮራምን ለመጠየቅ መሄዱን፣
እግዚአብሔር ለአካዝያስ መውደቅ ምክንያት
አደረገው፤ አካዝያስ እንደ ደረሰም የናሜሲን
ልጅ ኢዩን ለመቀበል ከኢዮራም ጋር ወጣ፤
ኢዩም የአክዓብን ቤት እንዲያጠፋ *እግዚ
አብሔር* የቀባው ሰው ነበር። 8ኢዩ በአክዓብ
ቤት ላይ ፍርድ በሚፈጽምበት ጊዜ፣ አካዝ
ያስን ያጀቡ የነበሩትን የይሁዳን መሳፍንትና
የዘመዶቹን ወንዶች ልጆች አግኝቶ ገደላቸው።
9ከዚያም አካዝያስን ለመፈለግ ሄደ፤ የእርሱም

22፥3 2ዜና18፥11፤ 21፥6
22፥5 2ዜና18፥ 11፡ 34
22፥6 1ነገ19፥15፤ 2ነገ8፥13-15
22፥7 2ነገ9፥16
22፥8 2ነገ10፥13
22፥9 መሳ9፥5፤ 2ዜና17፥4

ሰዎች አካዝያስን በሰማርያ ከተደበቀበት
አግኝተው ያዙት፤ ወደ ኢዩም አምጥተው
ገደሉት። "*እግዚአብሔርን* በፍጹም ልቡ የፈለገው
የኢዮሣፍጥ ልጅ ነው" በማለት ቀበሩት።
ስለዚህ ከአካዝያስ ቤት የመንግሥቱን ሥል
ጣን ይይዝ ዘንድ የሚችል ሰው አልነበረም።

## ጎቶልያና ኢዮአስ

22፥10-23፥21 ተጓ ምብ—2ዜና11፥1-21

10የአካዝያስ እናት ጎቶልያ ልጇዋ መሞቱን
ባየች ጊዜ፣ የይሁዳን ንጉሣውያን ቤተ ሰብ
በሙሉ አጠፋች፤ 11የንጉሥ ኢዮራም ልጅ
ዮሳቤት ግን፣ ከሚገደሉት መሳፍንት መካከል
ኢዮአስን ደብቃ ወሰደችው፣ ከሞግዚቱም
ጋር በእልፍኝ ሸሸገችው። የኢዮራም ልጅ
የካህኑ የዮዳሄ ሚስት ዮሳቤት፣ የአካዝያስ
እኅት በመሆኗ፣ ሕፃኑን የደበቀችው ጎቶልያ
እንዳትገድለው ነበር። 12እርሱም ጎቶልያ
ምድሪቱን በገዛችበት ጊዜ ሁሉ፣ በእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ ተደብቆ ስድስት ዓመት
አብሮአቸው ኖረ።

23 በሰባተኛው ዓመት ዮዳሄ በረታ፤
የመቶ አለቆች ከሆኑት ከይሮሐም
ልጅ ከዓዛርያስ፣ ከይሆሐናን ልጅ ከይስማኤል፣
ከዖቤድ ልጅ ከዓዛርያስ፣ ከዓዳያ ልጅ ከማዕ
ሴያ፣ ከዝክሪ ልጅ ከኤሊሳፋጥ ጋር ቃል ኪዳን
አደረገ።

[ፘ]2 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስቱ ቅጆች (እንዲሁም 2ነገ8፥26 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን *አርባ አራት* ይላል።
[ገ]6 ጥቂት የዕብራይስጥ ቅጆች የሰብዓ ሊቃናት፣ የቩልጌትና የሱርስቱ ትርጕም (2ነገ8፥29) ከዚህ ጋር ይስማማሉ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን *ራማ* ይላሉ።

22፥2 *ሃያ ሁለት፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ። ለዚህ ቍጥር የገባው የዕብራይስጡ ትርጕም "አርባ ሁለት" ይላል፤ ይህም የአካዝያስን ዕድሜ ከአባቱ ዕድሜ በላይ ያደርገዋል (21፥20)። *አንድ ዓመት* 841 ዓ.ቅ..ክ. ለማለት ነው።

*22፥3-4፤* በይሁዳ ምድር የየምሪ ሥርወ መንግሥት ተጽዕኖ የቱን ያህል አይሎ እንደ ነበር፣ በጎቶልያ ኀይልና ከሰሜኑ መንግሥት ግዛት የመጡ አማካሪዎች እዚያ በመኖራቸው ይታወቃል።

22፥5 *ለመውጋት....ከኢዮራም ጋር....ሄደ፤* በኢዮሣፍጥ ላይ ከደረሰው ተሞክሮ ጋር ተመሳሳይ ነው (19፥2 እና ማብ ይመ)። *አዛሄልን፤* የተቀባው በኤልሳዕ ሲሆን፣ በኋላም ዙፋኑን ለመያዝ ሲል ያልታሰበ ርምጃ በመውሰድ ንጉሡን ገደለው (2ነገ8፥13-15 ይመ፤ እንዲሁም ከ1ነገ19፥15 እና ማብ ጋር ያነጻጽሩ)። *ሬማት ገለዓድ፤* ከዮርዳኖስ ማዶ በእስራኤልና በአራም ወሰን ላይ የምትገኝ ከተማ ናት። ከዐሥር ዓመት በፊት ኢዮሣፍጥ ከአክአብ ጋር በመሰለፍ በዚህ ስፍራ በተደረገው ጦርነት ተካፍሎ ነበር፤ አክአብ የሞተውም በዚሁ ስፍራ ነበር (ም18፤1ነገ22)።

22፥6፤ *ወደ ኢይዝራኤል ተመለሰ፤* ኢዮራም ሬማት ዘገለዓድን መልሶ ከያዘ በኋላ ኢዩን ኀላፊ አድርጎ ሾመባት (2ነገ8፥28-9፥28)።

22፥7 *እግዚአብሔር ለአካዝያስ መውደቅ ምክንያት አደረገው፤* ኢዩ እንዴት እንደተቀባ ከዚህም በቀር የኢዮራምንና የአካዝያስን ሞት ያስከተለውን የዐመፅ ርምጃ እንዴት እንዳካሄደ ዝርዝር ሁኔታዎቹን በዘመኑ የነበረው የዚህ ታሪክ አንባቢ አሳምሮ እንደ ሚያውቅ ጸሓፊው ይገምታል (2ነገ8፥28-9፥28)። የመጽሐፈ ነገሥቱ ጸሓፊ የየምሪ ሥርወ መንግሥት ዕድሜው ያጠረው ከእግዚ አብሔር ፍርድ የተነሣ መሆኑን ሲገልጽ (1ነገ21፥20-29፤ 2ነገ 9፥24-10፥17)፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ደግሞ አካዝያስ በሰው እጅ የተገደለው እግዚአብሔር ፈርዶበት መሆኑን አሳይቶአል።

22፥9 በዜና መዋዕሉና በመጽሐፈ ነገሥቱ የተጻፈው የአካዝያስ አሟሟት ልዩነት ያለው ይመስላል፤ (ከ2ነገ9፥21-27፤ከ10፥12-14 ጋር ያነጻጽሩ)። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ እዚህ ላይ ሳይጻፍ የታለፈውን ታሪክ አንባቢው በሚገባ ያውቀዋል ብሎ ስለሚያስብ (የቍ7 ማብ ይመ)፣ ትክክለኛውን ቅደም ተከተልና ድርጊቶቹ የተፈ ጸሙባቸውን ቦታዎች በትክክል አላቀረበም፤ ስለዚህ የዜና መዋዕሉን መጽሐፍ ዝርዝር ነገሮች ለመጽሐፈ ነገሥቱ ተጨማሪ አድርጎ መውሰድ ይመረጣል፤ በዚህ ሁኔታ ከታየም ታሪኩ አይፋለስም። የአካዝያስ ሥርዐተ ቀብር፣ በክብር መፈጸሙ ከእርሱ ደግነት የተነሣ ሳይሆን፣ አባቱ እግዚአብሔርን ይፈራ ስለ ነበር ነው፤ ከዜና መዋዕሉ ሌላ፣ በሁለቱ ታሪኮች መካከል ያለው ልዩነት በትምህርተ መለኮት አንጻር ሲታይ፣ የሚጋጭ አይደለም። የአካዝያስን ዘመን መንግሥት በተመለከተ በሁለቱም ታሪኮች የተሰጠ ማጠቃለያ ሐሣብ የለም።

*22፥10-12፤* 2ነገ11፥1-3 ይመ። በይሁዳ ታሪክ፣ በዳዊት ሥርወ መንግሥት ጣልቃ በመግባት የነገሠ ሰው ቢኖር ጎቶልያ ብቻ ናት፤ እርሷም በይሁዳ ምድር በራሷ ስም የገዛች ብቸኛ ንግሥት ናት (ዘመኑም ከ841-835 ዓ.ቅ.ክ. ነው)። የዳዊትን ሥርወ መንግሥት ትውልድ ከምድር ገጽ ለማጥፋት ያደረገችውም ጥረት ቀድሞ ባሏ ኢዮራም ሞክሮ ሳይሳካለት የቀረውን የሚደግም ነው። (21፥4)፤ ይህም የዳዊትን ሥርወ መንግሥት ሕልውና ክፉኛ የተፈታተነ ሲሆን፣ እንዳሰበችው ተሳክቶላት ቢሆን ኖሮ በሰሜን ያለው የየምሪ ሥርወ መንግሥት የይሁዳን ምድር የራሱ ግዛት አድርጎ እስከ ማወጅ በደረሰም ነበር፤ ምክንያቱም ጎቶልያ ከዚሁ ሥርወ መንግሥት የምትወለድ ስትሆን፣ በሕይወት ያለ ዙፋኑን የሚወርስ ልጅ ስላልነበራት ጠቅላላ ልትገዛ ነበር ማለት ይቻላል።

22፥11 *የካህኑ የዮዳሄ ሚስት፤* በመጽሐፈ ነገሥት ውስጥ አይገኝም።

*23፥1-24፥27፤* 2ነገ 11፥4-12፥21 እና ማብ ይመ። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ከ835-769 ዓ.ቅ.ክ. ያለውን የኢዮአስን ዘመነ መንግሥት በሦስት ቦታ ይከፍለዋል፤ (1) ዙፋኑ ለዳዊት ቤት መመለሱ (ም23)፣(2) ኢዮአስና ዮዳሄ የነበሩበት መልካሙ ዘመን (24፥1-16)፣(3) ኢዮአስ ከእግዚአብሔር ጋር የተቃቃረበት ክፉው ዘመን (24፥17-27)። የመጨረሻው ክፍል በአብዛኛው በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ላይ ብቻ የተጻፈና ነገሥታቱ ለእግዚአብሔር ቢታዘዙ

2እነርሱም ወደ መላው ይሁዳ ሄደው፣ ሌዋ
ውያንንና የእስራኤል ቤት አለቆችን ከየከተ
ማው ሁሉ ሰበሰቡ:: ወደ ኢየሩሳሌም በመጡ
ጊዜም፣ 3ጉባኤው ሁሉ በእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ውስጥ ከንጉሡ ጋር ቃል ኪዳን አደረጉ።
ዮዳሄም እንዲህ አላቸው፤ "*እግዚአብሔር*
ለዳዊት ዘር በሰጠው ተስፋ መሠረት እነሆ፣
የንጉሡ ልጅ ይነግሣል:: 4እንግዲህ እናንተ
የምታደርጉት ይህ ነው፤ በሰንበት ዕለት
ተረኛ ከሆናችሁት ከእናንተ ከካህናቱና
ከሌዋውያኑ አንድ ሦስተኛው በሮቹን ጠብቁ፤
5አንድ ሦስተኛው ቤተ መንግሥቱን፣ አንድ
ሦስተኛው "የመሠረት ቅጽር በር" የተባለ
ውን ጠብቁ፤ የቀሩት ሰዎች በሙሉ *በእግ
ዚአብሔር* ቤተ መቅደስ አደባባይ ይሁኑ::
6ተረኛ ከሆኑት ካህናትና ሌዋውያን በቀር
ማንም ሰው ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ
አይግባ፤ እነርሱ የተቀደሱ ስለሆኑ ይግቡ፤
የቀሩት ሰዎች በሙሉ ግን፣ ወደ ቤተ
መቅደሱ እንዳይገቡ *እግዚአብሔር* ያዘዘውን
ይጠብቁ[ጣ]:: 7ሌዋውያኑም የጦር መሣሪያቸውን
በእጃቸው ይዘው በንጉሡ ዙሪያ ይቁሙ፤
ወደ ቤተ መቅደሱ የሚገባ ማንኛውም ሰው
ይገደል፤ ንጉሡ በሚሄድበትም ቦታ ሁሉ
አብረውት ይሁኑ::"
8ሌዋውያኑና ይሁዳ ሁሉ ልክ ካህኑ ዮዳሄ
እንዳዘዘው አደረጉ፤ ካህኑ ዮዳሄ ከጥበቃ ክፍ
ሎች የትኛውንም አላሰናበተም ነበርና፣ እያን
ዳንዱ በሰንበት ቀን በሥራ ላይ የሚሰማሩትንና
ከሥራ የሚወጡትን የራሱን ሰዎች ወሰደ፤
9ከዚያም በቤተ መቅደሱ የነበሩትን የንጉሥ
ዳዊት ጦሮች፣ ታላላቅና ታናናሽ ጋሻዎች
ለመቶ አለቆቹ ሰጣቸው:: 10ሰዎቹም ሁሉ
እያንዳንዳቸው መሣሪያቸውን በእጃቸው እንደ
ያዙ ከቤተ መቅደሱ ደቡብ አንሥቶ እስከ
ሰሜን ድረስ በመሠዊያውና በቤተ መቅደሱ
አጠገብ በንጉሡ ዙሪያ እንዲቆሙ አደረገ::
11ዮዳሄና ወንዶች ልጆቹ የንጉሡን ልጅ
አምጥተው ዘውድ ጫኑለት፤ የኪዳኑንም
መጽሐፍ ሰጥተውት አነገሡት፤ ቀቡትውትም፣
"ንጉሡ ለዘላለም ይኑር!" እያሉ ጮኹ::
12ጎቶልያም የሚሯሯጠውንና ደስታውን
ለንጉሡ የሚገልጠውን ሕዝብ ሁካታ ስትሰማ፣
ሕዝቡ ወዳለበት ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ ሄደች:: 13ንጉሡ በመግቢያው ላይ
ባለው በዐምዱ አጠገብ ቆሞ አየች፣ የጦር
መኰንኖችና መለከት ነፊዎችም በንጉሡ
አጠገቡ ነበሩ፤ የምድሪቱ ሕዝብ ሁሉ
ይደሰቱ፣ መለከትም ይነፉ ነበር፤ መዘምራ
ንም በዜማ ዕቃ ታጅበው የበዓሉን ዝማሬ
ይመሩ ነበር፤ ጎቶልያም ልብሷን ቀድዳ፣
ይህ ዐመፅ ነው! ይህ ዐመፅ ነው!" ብላ ጮኸች::
14ካህኑ ዮዳሄም የወታደር አዛዥ ወደ ሆኑት
ወደ መቶ አለቆቹ፣ "በሰልፉ መካከል አውጥ
ታችሁ አምጧት[ጨ]፤ የሚከተላት ካለም በሰይፍ
ግደሉት' ሲል ላከባቸው:: ካህኑም፣ "*በእግ
ዚአብሔር* ቤተ መቅደስ አትግደሏት" ብሎ
ነበርና:: 15እርሷም በቤተ መንግሥቱ ግቢ የፈረስ
መግቢያ በር ወደ ተባለው ቦታ እንደ ደረ
ሰች ያዟት፤ በዚያም ገደሏት::
16ዮዳሄም ራሱ፣ ሕዝቡና ንጉሡ *የእግዚ
አብሔር* ሕዝብ እንደሚሆኑ ቃል ኪዳን ገቡ[ሐ]::
17ከዚህ በኋላ ሕዝቡ በሙሉ ሄዶ የበአልን
ቤተ ጣዖት አፈረሰው፤ መሠዊያዎቹንና ጣዖታ
ቱን አደቀቀ፤ የበአልን ካህን ማታንንም
በመሠዊያዎቹ ፊት ለፊት ገደሉት:: 18ዮዳሄ
በሙሴ ሕግ እንደተጻፈውና ዳዊትም እንዳዘዘው፣
በደስታና በመዝሙር የሚቃጠለውን *የእግዚ
አብሔርን* መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ዳዊት
ለመደባቸው ካህናትና ሌዋውያን *የእግዚአብሔ
ርን* ቤተ መቅደስ ኀላፊነት ሰጣቸው:: 19እን
ዲሁም በማንኛውም ነገር የረከሰ ሰው እን
ዳይገባ፣ በቤተ መቅደሱ ቅጥር በሮች ላይ
ጠባቆች አቆመ::

23፥2 ዘኍ35፥2-5
23፥3 2ሳሙ7፥12፤ 1ነገ2፥4፤2ነገ11፥17፤ 2ዜና6፥16፤7፥18፤ 21፥7
23፥6 ዘካ3፥7
23፥8 2ነገ11፥9፤ 1ዜና24፥1
3፥11 ዘዳ17፥18
23፥13 1ነገ1፥41፤ 7፥15
23፥15 ኤር31፥40
23፥16 ዜና29፥10፤ 34፥31፤ነህ9፥38
23፥17 ዘዳ13፥6-9
23፥18 1ዜና23፥6፡ 28-32፤25፥6
23፥19 1ዜና9፥22

[ጣ]6 ወይም *አይግባ የሚለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ይጠብቁ*
[ጨ]14 ወይም *ከቅጥሩ ውስጥ አውጥታችሁ አምጡአት ተብሎ*
[ሐ]16 ወይም *በእግዚአብሔር በሕዝቡና በንጉሡ መካከል የተደረገው ቃል ኪዳን ...*

በረከት ባይታዘዙ ግን መከራ ያገኛቸዋል የሚለውን መሪ ሐሳብ ያጉላል:: እዚህም ላይ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ የመታዘዝና ያለመታዘዝ ታሪክ ተዋቅሮአል (24፥15-17፡23 እንዲሁም የ12፥2፤ 14፥2-16፥14 ማብ ይመ)::

*23፥1-21፤* 2ነገ 11፥4-20 *ይመ*:: የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ፣ ከሌላው ይልቅ፣ የታሪኩ ምንጭ አድርጎ በቅርብ የተከተለው የራሱን ነው፤ ይሁን እንጂ እንዲያንጸባርቅለት የፈለገውን ቁም ነገር በሦስት መንገድ ያቀርባል፤ (1) መጽሐፈ ነገሥቱ የወታደሩ ክፍል በመፈንቅለ መንግሥቱ ዐመፅ እንደ ተካፈለ ሰፋ አድርጎ ሲተርክ፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን በዐመፁ የቤተ መቅደሱ ሹማምት እጅ እንዳለበትና የተጫወቱትንም ሚና በማከል በአጽንዖት ያሳያል:: (ቍ2፡6፡8፡13፡18-19):: (2) የዜና መዋዕሉ "ሕዝቡ በሙሉ" ወይም "ጉባኤው ሁሉ" (ቍ3፡5-6፡8፡10፡16-17) የሚሉትን ሐረጎች ደጋግሞ በማውሣት የመፈንቅለ መንግሥቱ ዐመፅ ዳር እስከ ዳር የሕዝብን ድጋፍ ማግኘቱን በአጽንዖት ያሳያል (3)የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ የተቀደሰ መሆኑ እንዲታወቅ ያለውን ጽኑ ፍላጎት ባጭሩ በመግለጽ ወደዚያ መግባት የሚችሉት ለዚሁ ተገቢ ሆነው የተገኙት ብቻ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሲል ደረጃ በደረጃ የተከናወነውን ተግባር ያሳያል (ቍ5-6፡19)::

23፥1 *ከዓዛርያስ... ኤሊሳፋጥ፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በመጽሐፈ ነገሥት ላይ ያልተወሱትን የጦር አዛዦች ስም ያነሣል፤ ይሁን እንጂ ለቤተ መንግሥቱ ጥበቃ ተመድበው የሚያገለግሉትንና ከውጭ በገንዘብ የተቀጠሩትን ዘበኞች በዝምታ አልፎአቸዋል (ቍ20፤ከ2ነገ11፥19 ጋር ያነጻጽሩ የ2ነገ11፥4ማብ ይመ):: እዚህም ላይ ቅጥር ዘበኞቹን ሳያወሣ ያለፈው፣ ምናልባትም ወደ ቤተ መቅደሱ ቅጥር-ግቢ መግባት ያለባቸው ሥልጣን የተሰጣቸው ብቻ መሆኑን ለማሳየት ይሆናል::

23፥2 *ሌዋውያኑንና የእስራኤል ቤት አለቆችን፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ስለ ቤተ መቅደሱ ሹማምትና ሕዝቡ ከዳር እስከ ዳር ተንቀሳቅሶ በጎቶልያ ላይ ስለ መነሣቱ የሚያንጸባርቅ ክፍል ነው::

23፥3 *እግዚአብሔር... በሰጠው ተስፋ መሠረት፤* 2ሳሙ 7፥11-16 ይመ::

23፥11 *የኪዳኑንም መጽሐፍ፤* ጉባኤውን በመሐላ ቃል የገባበት ሰነድ (1፥3፤ ከቍ16 ጋር ያነጻጽሩ) ወይም ንጉሡ ሕዝቡን የሚያስተዳድርበት የእግዚአብሔር ሕግ መጽሐፍ ሊሆን ይችላል (ዘዳ17፥18-20 ይመ)፤ እንዲሁም የ2ነገ11፥12 ማብ ይመ::

23፥13 *መዘምራንም በዜማ ዕቃ፤* ይህ በ2ነገ 11፥14 ላይ አይገኝም:: ዝማሬውን በዜማ ዕቃ የሚመሩ ሌዋውያን መኖራቸውን የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በተጨማሪ ገልጸአል (የ1ዜና.6፥31-48 ማብ ይመ)::

*23፥18-19፤* የመሥዋዕት አቀራረቡን ሥርዓትና ቤተ መቅደሱን የሚጠብቁትን ዘበኞች የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ የቀረበውም በዚሁ መጽሐፍ ብቻ ነው (የቍ1-21 ማብ ይመ)::

[20]የመቶ አለቆቹን፣ መኳንንቱን፣ የሕዝ
ቡን ገዦችና የአገሩን ሕዝብ ሁሉ ይዞ ንጉ
ሡን ከላይ ከቤተ መቅደሱ ወደ ታች አመጣው::
በላይኛውም መግቢያ በኩል ወደ ቤተ መን
ግሥቱ ገብተው ንጉሡን በመንግሥቱ ዙፋን
ላይ አስቀመጡት:: [21]መላውም የአገሩ ሕዝብ
ተደሰተ፤ ጎቶልያ ስለ ተገደለችም ከተማ
ዪቱ ሰላም አግኝታ ነበር::

## ኢዮአስ ቤተ መቅደሱን ማደሱ

24፥1-14-ተጓ ምብ 2ነገ ዜና —12፥1-16
24፥23-27ተጓ ምብ —2ነገ12፥17-21

**24** ኢዮአስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሰባት
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀ
ምጦም አርባ ዓመት ገዛ:: እናቱ ሳብያ
የተባለች የቤርሳቤህ ሴት ነበረች:: [2]ካህኑ
ዮዳሄ በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ፣ ኢዮ
አስ *እግዚአብሔርን* ደስ የሚያሰኝ ነገር
አደረገ:: [3]ዮዳሄ ሁለት ሚስቶች መረጠለት፤
ወንዶችና ሴቶች ልጆችም ወለደ::
[4]ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኢዮአስ *የእግዚአብሔርን*
ቤተ መቅደስ ለማደስ ወሰነ:: [5]ካህናቱንና
ሌዋውያኑን ሰብስቦም፣ “ወደ ይሁዳ ከተሞች
ሂዱና የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በየዓ
መቱ ለማደስ የሚሆን ገንዘብ ከእስራኤል
ሁሉ ሰብስቡ፤ ይህንንም አሁኑኑ አድርጉት”
አላቸው ሌዋውያኑ ግን ቸል አሉ::
[6]ስለዚህ ንጉሡ ሊቀ ካህኑን ዮዳሄን ጠርቶ፣
“*የእግዚአብሔር* ባሪያ ሙሴና የእስራኤል
ጉባኤ ለምስክሩ ድንኳን እንዲወጣ የወሰ
ኑትን ግብር ከይሁዳና ከኢየሩሳሌም እንዲ
ያመጡ ሌዋውያኑን ያላተጋሃቸው ለምንድን
ነው?” አለው::
[7]በዚህ ጊዜ የዚያች ክፉ የጎቶልያ ልጆች
የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሰብረው በመ
ግባት የተቀደሱ ዕቃዎች እንኳ ሳይቀሩ፣ ለበ
ኣል ጣዖታት አገልግሎት እንዲውሉ አድርገው
ነበር::
[8]በንጉሡም ትእዛዝ የገንዘብ መሰብሰቢያ
ሣጥን ሠርተው *በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ
መግቢያ በር አጠገብ በውጭ በኩል አኖሩት::

23፥20 2ነገ11፥15፥35
23፥21 2ዜና22፥1
24፥2 2ዜና25፥2፤ 26፥5
24፥5 ዘፀ30፥16፤ 1ዜና11፥1፤26፥20፤ ነህ10፥32-33፤ ማቴ17፥24
24፥6 ዘፀ38፥21
24፥10 ዘፀ25፥2፤ 1ዜና29፥3:6:9
24፥12 2ዜና34፥11

[9]ከዚህ በኋላ እስራኤል በምድረ በዳ ሳሉ
*የእግዚአብሔር* ባሪያ ሙሴ ያዘዘውን ግብር
ለእግዚአብሔር እንዲያመጡ በይሁዳና በኢየሩ
ሳሌም ዐዋጅ ተነገረ:: [10]ሹማምንቱ ሁሉ፣
ሕዝቡም ሁሉ ግብሩን በደስታ አመጡ፤
እስኪሞላም ድረስ በሣጥኑ ውስጥ ጨመሩ::
[11]ሣጥኑ በሌዋውያኑ እጅ ወደ ንጉሡ ሹማ
ምንት በሚደርስበት ጊዜ፣ እነርሱም በውስጡ
ብዙ ገንዘብ መኖሩን በሚያዩበት ጊዜ ሁሉ፣
የቤተ መንግሥቱ ጸሓፊና የሊቀ ካህናቱ ሹም
ይመጡና ሣጥኑን አጋብተው ወደ ቦታው
ይመልሱት ነበር:: ይህን በየቀኑ በማድረግ
እጅግ ብዙ ገንዘብ ሰበሰቡ:: [12]ንጉሡና ዮዳሄም
*የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ ሥራ እንዲያ
ሠሩ ለተመደቡት ሰዎች ገንዘቡን አስረከ
ቧቸው፤ እነርሱም *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ
ለማደስ ድንጋይ ጠራቢዎችንና ዐናጢዎችን
እንዲሁም ቤተ መቅደሱን ለመጠገን የብረትና
የናስ ሠራተኞችን ቀጠሩ::
[13]በሥራው ላይ የተሰማሩት ሰዎች ትጉሃን
ስለ ነበሩ፣ ሥራው በእጃቸው ተከናወነ፤ የእግዚ
አብሔርንም ቤተ መቅደስ ቀደም ሲል በነበ
ረው ዓይነት መሠረት አደሱት፤ አጠናከሩ
ትም:: [14]ከጨረሱም በኋላ ቀሪውን ገንዘብ
ወደ ንጉሡና ወደ ዮዳሄ አመጡ፤ በገንዘቡም
*የእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ዕቃዎች ማለትም
ለአገልግሎትና ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚ
ውሉ ዕቃዎች እንደዚሁም ጭልፋዎችና
ሌሎች የወርቅና የብር ዕቃዎችም ተሠሩ::
ዮዳሄ በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ
*በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ የሚቃጠል
መሥዋዕት ዘወትር ይቀርብ ነበር::
[15]ዮዳሄ ሸምግሎ ዕድሜ ከጠገበ በኋላ በመቶ
ሠላሳ ዓመቱ ሞተ:: [16]እርሱም በእስራኤል
ውስጥ ለእግዚአብሔርና ለቤተ መቅደሱ መልካም
ሠርቶአልና በዳዊት ከተማ በነገሥታቱ መቃብር
ተቀበረ::

## የኢዮአስ ክፋት

[17]ከዮዳሄ ሞት በኋላ የይሁዳ ሹማምንት
መጥተው ለንጉሡ ታማኝነታቸውን ገለጡ፤

*23፥20፤* የቍ1 ማብ ይመ::
*24፥1-14፤* 2 ነገ12÷1-17 ይመ::
24፥1 *አርባ ዓመት፤* 835-769 ዓ.ቅ.ክ. ለማለት ነው::
*24፥2፤* ዮዳሄ በነበረበት በዚያ በደጉ ዘመን የኢዮአስ ሕይወት ምን ይመስል እንደ ነበር (ቍ1-16)፣ ከእርሱ ሞት በኋላ ደግሞ ኢዮአስ ወደ ክፋት እንዴት እንዳመራ (ቍ17-27) ጸሓፊው መሪ ሐሳቡን ያቀርባል፤ የ25÷2 ማብ ይመ::
*24፥3* ብዙ ልጆች መውለድ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ በረከት ነው የሚለውን የዜና መዋዕሉን ጸሓፊ ጽኑ እምነት የሚያሳይ ሌላ ዓይነት አቀራረብ ነው (ቍ27):: እንዲሁም የ1ዜና 25÷5 ማብ ይመ)::
24፥4 *ቤተ መቅደስ ለማደስ፤* የጎቶልያ ክፋትና ቅርሶችን የማጥፋት ድርጊት (ቍ7) ለቤተ መቅደሱ መታደስ ምክንያት ሆኖአል::
*24፥5፤* የ2ኛ ነገሥት ጸሓፊ ለዚህ ሥራ እንዲውል የተፈለገው ገንዘብ ከሦስት ምንጮች የሚገኝ መሆኑን ሲያወሣ (2ነገ12÷4-5) የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን የቈጠራውን ግብር ብቻ ይጠቅሳል (ዘፀ 30÷14፤38÷26፤ ማቴ17÷24 ይመ):: ካህናቱ ለምን ሥራ ውን እንዳዘገዩት ግን የተገለጠ ነገር የለም (2ነገ 12÷6-8):: የመ ጽሐፈ ነገሥቱ ጸሓፊ ሕዝቡ ከካህናቱ ጋር ወደ ንጉሡ የቀረቡት ኢዮአስ በነገሠ በሃያ ሦስተኛው ዓመት መሆኑን ያመለክታል:: ይህ ጊዜም ንጉሡ በዮዳሄ አመራር ሥር መሆኑ ካከተመ በኋላ ሳይሆን አይቀርም:: ካህናቱ የመጠገኛውን ገንዘብ እንዲሰበስቡ እንደገና በተመደቡበት ጊዜ ፈቃደኛ ሆነው አለመገኘታቸው ራሱን የቻለ ምክንያት ሊሆን ይችላል::
24፥8 *የገንዘብ መሰብሰቢያ ሳጥን፤* የጥንት ቤተ ጣዖታት በዚህ ክፍል ከተጠቀሰው የገንዘብ መሰብሰቢያ ጋር የሚመሳሰል ሣጥን እንደነበራቸው መስጴጦምያ ጽሑፎች ይገልጻሉ፤ ገንዘብ የመሰብሰቡን ተግባር በጋራ እንዲወጡ የተመደቡት የንጉሡና የቤተ መቅደሱ ሹማምንት ነበሩ (የ1ዜና 26÷20 ማብ ይመ)::
*24፥14፤* 2ነገ12÷13-14 ይመ:: ***ዮዳሄ በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ፤*** የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዮዳሄ ከሞተ በኋላ (ቍ15-16) በኢዮአስ ዘመነ መንግሥት ክፋት እየበዛ መሄዱን ለመግለጽ የተጠቀመበት ተጨማሪ መግለጫ ነው::
*24፥15-22፤* ይህ ክፍል በዜና መዋዕል መጽሐፍ ብቻ የሚገኝ ሲሆን፣ ባለመታዘዛቸውም ምክንያት መቀጣታቸውን በአጽንዖት ያሳያል (የ23÷1-24÷27 ማብ ይመ):: ዮዳሄ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ የነበረው የኢዮአስ ዘመነ መንግሥት ጽድቅ የሰፈነበት ነበር፤ ዮዳሄ ከሞተ በኋላ ግን ኢዮአስ ወደ ጣዖት አምልኮ ዞረ፤ የዮዳሄንም ልጅ ገደለው:: በቀጣዩም ዓመት በአራም መንግሥት ተወሮ ድል ሆነ፤ በእርሱ አመራር ይሁዳ እግዚአብሔርን ትቶ ነበርና (ቍ24)::

ንጉሡም አዳመጣቸው:: 18እነርሱም የአባቶ
ቻቸውን አምላክ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ
ትተው፣ የአሼራን ዐምዶችና ጣዖታትን
አመለኩ፤ በበደላቸውም ምክንያት የእግዚ
አብሔር ቍጣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ መጣ።
19ወደ እግዚአብሔር ይመልሷቸው ዘንድ እርሱ
ነቢያቱን ወደ ሕዝቡ ሰደደ፤ ነቢያቱም
መሰከሩባቸው፤ እነርሱ ግን አላዳመጡም::
20የእግዚአብሔርም መንፈስ በካህኑ በዮዳሄ ልጅ
በዘካርያስ ላይ መጣ፤ እርሱም በሕዝቡ ፊት
ቆሞ፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ የእግዚ
አብሔርን ትእዛዝ ለምን ትተላለፋላችሁ?
አይሳካላችሁም፤ እናንተ እግዚአብሔርን ስለ
ተዋችሁት እርሱም ትቶአችኋል" አላቸው::
21እነርሱ ግን አሤሩበት፤ በንጉሡም ትእዛዝ
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አደባባይ ላይ
በድንጋይ ወግረው ገደሉት::
22ንጉሥ ኢዮአስ የዘካርያስ አባት ዮዳሄ
ያደረገለትን ቸርነት አላሰበም፤ በዚህ ፈንታ
ልጁን ገደለው፤ በሚሞትበትም ጊዜ፣ "እግዚ
አብሔር ይየው፤ እርሱው ይበቀልህ" አለ::
23በዓመቱም መጨረሻ፣ የሶርያ ሰራዊት በኢ
ዮአስ ላይ ዘመተ፤ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን
ወሮም የሕዝቡን መሪዎች ሁሉ ደመሰሰ፤
ምርኮውንም ሁሉ ወደ ንጉሡ ወደ ደማስቆ
ላከ:: 24የሶርያ ሰራዊት ሰዎች ጥቂት ቢሆኑም
እንኳ እግዚአብሔር በጣም የሚበልጠውን
ሰራዊት በእጃቸው አሳልፎ ሰጠ፤ ይሁዳ የአ
ባቶቹን አምላክ እግዚአብሔርን ስለ ተወ፣ በኢ
ዮአስ ላይ ተፈረደበት:: 25ሶርያ ውያንም በወጡ
ጊዜ ኢዮአስን ክፉኛ አቍስለው፣ ጥለውት
ሄዱ፤ የካህናቱ የዮዳሄን ልጅ ስለ ገደለም፣
ሹማምንቱ አሢረውበት በዐልጋው ላይ እንዳለ
ገደሉት:: በዚህ ሁኔታም ሞቶ በዳዊት ከተማ
ተቀበረ እንጂ በነገሥታቱ መቃብር አልተቀበረም።
26በእርሱ ላይ ያሤሩትም የአሞናዊቱ የሰ
ምዓት ልጅ ዛባድና የሞዓባዊቱ የሰማሪት

24፥18 ዘፀ34፥13፤ ኢሱ24፥20፤ 2ዜና7፥19፤19፥2፤33፥3፤ኤር17፥2
24፥19 ዘኍ11፥29፤ ኤር7፥25፤ዘካ1፥4
24፥20 ዘኍ14፥41፤ ዘዳ31፥17፤ መሳ3፥10፤1ዜና12፥18፤ማቴ23፥35፤ ሉቃ11፥51
24፥21 ኢሱ7፥25፤ ኤር20፥2፤26፥21
24፥22 ዘፍ9፥5
24፥23 2ነገ12፥17-18
24፥24 ዘሌ26፥23-25፤ዘዳ28፥25፤2ዜና14፥9፤16፥8፤20፥2፡12
24፥25 2ዜና21፥20
24፥26 ሩት1፥4፤ 2ነገ12፥21
25፥2 1ነገ8፥61፤ 2ዜና24፥2
25፥4 ዘኍ26፥11፤ ዘዳ28፥61
25፥5 ዘፀ30፥14፤ 2ሳሙ24፥2፤1ዜና21፥1፤2ዜና17፥14-19
25፥7 2ዜና16፥2-9፤19፥1-3

ልጅ ዮዛባት ነበሩ:: 27የወንዶች ልጆቹ
ታሪክ፣ ስለ እርሱ የተነገሩት ብዙ ትንቢ
ቶችና የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መታደስ
በነገሥታቱ የታሪክ መዛግብት ተጽፏል::
ልጁ አሜስያስም በእርሱ ፈንታ ነገሠ::

## የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ

25፥1-4 ተጓ ምብ —2ዜና14፥1-6
25፥11-12 ተጓ ምብ —14፥7
25፥17-28 ተጓ ምብ—2ዜና14፥8-20

25 አሜስያስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሃያ
አምስት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም
ተቀምጦም ሃያ ዘጠኝ ዓመት ገዛ:: እናቱም
ዮዓዳን የተባለች የኢየሩሳሌም ሴት ነበረች::
2እርሱም በእግዚአብሔር ፊት መል ካም
ነገር አደረገ፤ ነገር ግን በፍጹም ልቡ
አልነበረም:: 3መንግሥቱን በቍጥጥር ሥር
ካጸና በኋላ፣ ንጉሥ የነበረውን አባቱን የገደ
ሉትን ሹማምንት በሞት ቀጣቸው:: 4እግዚአ
ብሔር በሙሴ መጽሐፍ በተጻፈው ሕግ "ሰው
ሁሉ በገዛ ኀጢአቱ ይሙት እንጂ ወላጆች ስለ
ልጆቻቸው አይገደሉ፤ ልጆችም ስለ ወላጆቻቸው
አይገደሉ"[°] ብሎ ባዘዘው መሠረት አደረገ እንጂ
ልጆቻቸውን አልገደለም::
5አሜስያስ የይሁዳን ሕዝብ በአንድነት
ሰብስቦ፣ እንደየቤተሰቡ በሻለቆችና በመቶ
አለቆች በመደልደል በመላው ይሁዳና በብ
ንያም መደባቸው:: ከዚያም ዕድሜያቸው
ሃያና ከሃያ በላይ የሆናቸውን ሰብስቦ፣ ለው
ትድርና አገልግሎት ብቁ ሆነው ጋሻና ጦር
መያዝ የሚችሉ ሦስት መቶ ሺህ ሰዎች አገኘ።
6እንዲሁም በመቶ መክሊት[^] ጥሬ ብር አንድ
መቶ ሺህ ተዋጊዎች ከእስራኤል ቀጠረ::
7ነገር ግን አንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ
እርሱ መጥቶ እንዲህ አለው፤ "ንጉሥ ሆይ፤

*23 ምናልባት መስከረም፣ ጥቅምትና ኅዳር
°4 ዘዳ 24፥16
^6 በዚህና በቍጥር 9 ላይ 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው

24፥18፡20፡24 *ትተው... ተዋችሁት...ትቶአችኋል...* ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል:: ጸሐፊው እነዚህን ቃላት የተጠቀመው መለኮታዊውን ቅጣት ለማመልከት ነው (የ12፥1 ማብ፤ እንዲሁም 7፥19፡22፤12፥5፤13፥10-11፤15፥2፤ 21፥10፤ 24፥18፡20፡24፤ 28፥6፤29፥6፤ 34፥25፤ 1ዜና 28፥9፡ 20ይመ )::

*24፥19 እርሱ ነቢያቱን ወደ ሕዝቡ ሰደደ፤* እስራኤል የእግዚአብሔርን ነቢያት አለማድመጧ በመጨረሻ ወደ ጥፋት መርቶአታል (36፥16ይመ፤ ከ20፥20 ጋር ያነጻጽሩ):: በተጨማሪም ከ1ዜና መግቢያ "ዓላማና መሪ ሐሳብ" የሚለውን ይመ::

24፥20 *በዘካርያስ፤* የማቴ 23፥35 ማብ ይመ::

24፥24 *... ሰዎች ጥቂት ቢሆኑም፤* ንጉሡና ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው በተገኙበት ጊዜ፣ ጥቂቱ የይሁዳ ሰራዊት ስፍር ቍጥር የሌለውን የጠላት ወገን በእግዚአብሔር ርዳታ አሸንፎአል (14፥8-9፤20፥2፡12)፤ ባሁኑ ጊዜ ደግሞ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው ባለመገኘታቸው ፣ በቍጥር ከእነርሱ እጅግ ባነሱ ወራሪዎች ተሸነፉ (የ20፥30 ማብ ይመ)::

24፥25 *ስለ ገደለም፤... ገደሉት፤* ግድያው የዘካርያስን ደም ለመበቀል የተደረገ መሆኑን የሚገልጽልን የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ብቻ ነው:: *በነገሥታቱ መቃብር አልተቀበረም፤* ዮዳሄ በነገሥታቱ መቃብር እንዲቀበር መደረጉ፣ ለእርሱ የተሰጠውን ክብር ያሳያል (ቍ16)፣ ኢዮአስ ግን ለዚህ አልታደለም (የ21፥20 ማብ ይመ)::

24፥26 *የአሞናዊቱ... የሞዓባዊቱ፤* በመጽሐፈ ነገሥት አልተወሣም፤ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ግን አጽንዖት ሰጥቶታል፤ (የ20፥1-30 ማብ ይመ)::

25፥1-28፤ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ፣ የአሜስያስን ዘመነ መንግሥት በሁለት ከፍሎታል፤ አንዱ መታዘዝ መለኮታዊ በረከት፣ ድል የታየበት መልካም ዘመን (ቍ1-13) ሲሆን ሌላው የጣዖት አምልኮ ሽንፈት፣ የነገሥታት መገደል የሰፈነበት ክፉ ዘመን (ቍ14-28) ነው:: 2ነገ 14፥1-20 እና ማብ ይመ::

25፥1 *ሃያ ዘጠኝ ዓመት፤* ከ796-769 ዓ.ቅ.ክ. ለማለት ነው::

*25፥2፤* የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ አሜስያስ ሕዝቡ ያለማቋረጥ መሥዋዕት ያሚያቀርብባቸውን የማምለኪያ ኰረብታዎች አለማስወገዱን (2ነገ14፥4) አልጠቀሰም፤ 24፥2ን ከ2ነገ12፥4 ጋር 26፥4ን ከ2ነገ15፥4 ጋር ያነጻጽሩ::

*25፥5-16፤* በ2ነገ14፥7 ላይ የተጻፈውን አስፋፍቶ የሚያቀርብ ነው:: አሜስያስ ኤዶምያስን ድል ማድረጉ ብቻ በኢዮአካዝ ላይ እንዲደነፋ የልብ ልብ የሰጠው መሆኑን የነገሥታቱ ጸሐፊ ሲተርክ፣ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ግን አሜስያስ ከጦርነቱ በኋላ ክፉ ድርጊት ስለፈጸመ አጸፋ ቅጣት የደረሰበት መሆኑን ለማሳየት እንደሚከተለው በአጽንዖት አስቀምጦታል፤ አሜስያስ በመታዘዙ በኤዶምያስ ላይ ድል መጎናጸፉን፣ ከዚያ በኋላ ግን ጣዖት በማምለኩ (ቍ14-16) በእስራኤል ላይ ያደረገው ዘመቻ በሽንፈት የተደመደመ መሆኑን፣ ይህንም ታሪክ ሰፋ አድርጎ በማቅረብ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በኤዶምያስ ላይ የተገኘው ድል ከሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ጋር በተደረገው ጦርነት ለምን እንዳልተደገመ ሥነመለኮታዊ ምክንያት አቅርቦአል::

25፥7፤ *እነዚህ የእስራኤል ወታደሮች ከአንተ ጋር አይዝመቱ፤* የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በእግዚአብሔር አለመታመንን (የ16፥2-9፤22፥5 ማብ ይመ) ያሳያሉ ብሎ ካወገዛቸው የጦር ስምምነቶች

*እግዚአብሔር* ከእስራኤልም ሆነ ከማናቸ
ውም የኤፍሬም ሕዝብ ጋር አይደለምና፣
እነዚህ የእስራኤል ወታደሮች ከአንተ ጋር
አይዝመቱ:: 8ሄደህ ጦርነቱን በቈራጥነት
ብትዋጋም እንኳ፣ የመርዳትና የመጣል ኀይል
ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለ ሆነ እግዚአብሔር በጠ
ላቶችህ ፊት ይጥልሃል::"
9አሜስያስም የእግዚአብሔርን ሰው፣ "*ታዲያ*
ለእነዚህ ለእስራኤል ወታደሮች የከፈልኩት
መቶ መክሊት እንዴት ይሁን?" ሲል ጠየቀው
የእግዚአብሔርም ሰው፣ "*እግዚአብሔር* ከዚህ
አብልጦ ሊሰጥህ ይችላል" ሲል መለሰለት::
10ስለዚህ አሜስያስ ከኤፍሬም ወደ እርሱ
የመጡትን ወታደሮች ወደየመኖሪያ ስፍራ
ቸው አሰናበታቸው:: እነርሱም በይሁዳ ላይ
ክፉኛ ተበሳጭተው ነበርና በታላቅ ቊጣ ወደ
መኖሪያ ስፍራቸው ተመለሱ::
11አሜስያስም ኃይሉን በሚገባ አደራጅቶ
ሰራዊቱን ወደ ጨው ሸለቆ መራ፤ በዚያም
ዐሥር ሺህ የሴይር ወታደሮችን ገደለ:: 12የይሁዳ
ሰራዊት ሌሎች ዐሥር ሺህ ሰዎች ማረኩ፤
ወደ አንድ ዓለት ዐናት ላይም አውጥተው
ቍልቍል ለቀቁአቸው፤ ሁሉም ተፈጠፈጡ::
13በዚያኑ ጊዜ አሜስያስ ያሰናበታቸውና
በጦርነቱ እንዳይካፈሉ የከለከላቸው ወታደሮች፤
ከሰማርያ እስከ ቤትሖሮን ያሉትን የይሁዳ
ከተሞች ወረሩ፤ ሦስት ሺህ ሰው ገደሉ፤
እጅግ ብዙ ምርኮም ወሰዱ::
14አሜስያስም ኤዶማያውያንን ደምስሶ በተ
መለሰ ጊዜ፣ የሴይርን ሕዝብ አማልክት
ይዞ መጣ፤ ለራሱም አማልክት አድርጎ በማ
ቆም ሰገደላቸው፤ መሥዋዕትም አቀረበላቸው::
15*የእግዚአብሔርም* ቍጣ በአሜስያስ ላይ
ነደደ፤ ነቢይንም ላከበት፤ ነቢዩም፣ "የገዛ
ሕዝባቸውን ከእጅህ ማዳን ያልቻሉትን የአሕ
ዛብን አማልክት ርዳታ የጠየቅኸው ለምን
ድን ነው?" አለው::
16እርሱም በመናገር ላይ ሳለ፣ ንጉሡ፣
"ለመሆኑ አንተን የንጉሥ አማካሪ አድርገን
ሾመንሃልን? ዝም አትልም እንዴ! መሞት
ትፈልጋለህ?" አለው::
ነቢዩም ዝም አለ፤ ሆኖም፣ "ይህን አድር
ገሃልና ምክሬንም አልሰማህምና፤ እግዚአብሔር
ሊያጠፋህ እንደወሰነ ዐውቃለሁ" አለ::
17የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ አማካሪዎቹን
ካማከረ በኋላ፣ የእስራኤል ንጉሥ የኢዩ የልጅ
ልጅ፣ የኢዮአካዝ ልጅ ወደ ሆነው ወደ
ኢዮአስ፣ "እስቲ ናና ፊት ለፊት እንጋጠም"
ሲል ላከበት::
18የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአስ ግን፣ ለይሁዳ
ንጉሥ ለአሜስያስ እንዲህ ሲል መለሰለት፤
"አንድ የሊባኖስ ኵርንችት፣ 'ሚስት እንድ
ትሆነው ሴት ልጅህን ለልጄ ስጠው' ሲል
ወደ ሊባኖስ ዝግባ ላከበት:: ከዚያም የዱር
አውሬ ከሊባኖስ ወጥቶ ኵርንችቱን ረገጠው::
19ኤዶምን አሸንፌአለሁ ብለህ ራስህን በትዕ
ቢት ክበሃዋል፤ ኰርተሃልም፤ ግን ዐርፈህ
እቤትህ ተቀመጥ! በራስህና በይሁዳ ላይ
ውድቀት *ታመጣ* ዘንድ ችግር የምትጠራው
ስለምንድን ነው?"
20የኤዶምን አማልክት ማምለክ በመፈ
ለጋቸው፣ እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው እጅ
አሳልፎ ሊሰጣቸው ወስኖአልና፣ አሜስያስ
አላዳመጣቸውም:: 21ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ
ኢዮአስ አደጋ ጣለ:: እርሱና የይሁዳ ንጉሥ
አሜስያስ በይሁዳ ውስጥ ቤትሳሚስ በተባለ
ስፍራ ፊት ለፊት ተጋጠሙ:: 22ይሁዳ በእስ
ራኤል ክፉኛ ተመታ፤ እያንዳንዱም ሰው
ወደየመኖሪያው ሸሸ:: 23የእስራስል ንጉሥ
ኢዮአስም የአካዝያስን የልጅ ልጅ የኢዮአስን
ልጅ አሜስያስን ቤትሳሚስ ላይ ማርኮ ወደ
ኢየሩሳሌም አመጣው፤ ከኤፍሬም በር እስከ
ማዕዘኑ በር ድረስ አንድ መቶ ሰማንያ ሜትር[ᵀ]
ያህል ርዝመት ያለውንም የኢየሩሳሌምን
ቅጥር አፈረሰ:: 24እርሱም በዖቤድኤዶም ጥበቃ
ሥር የነበረውንና በቤተ መቅደሱ የተገኘውን
ወርቅ፣ ጥሬ ብርና ዕቃ በሙሉ፣ ከቤተ መንግ
ሥቱም ንብረትና በመያዣ ከያዛቸው ሰዎች
ጭምር ወስዶ ወደ ሰማርያ ተመለሰ::
25የይሁዳ ንጉሥ የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ፣
የእስራኤል ንጉሥ የኢዮአካዝ ልጅ ኢዮአስ
ከሞተ በኋላ አሥራ አምስት ዓመት ኖረ::
26በአሜስያስ ዘመነ መንግሥት ከመጀመሪያው
እስከ መጨረሻው የተከናወነው ሌላው
ተግባር ሁሉ በይሁዳና በእስራኤል ነገሥታት
የተጻፈ አይደለምን? 27አሜስያስ *እግዚ
አብሔርን* መከተል ከተወ በኋላ፣ በኢየሩ
ሳሌም ሰላመፁበት ወደ ለኪሶ ሸሸ፤ ነገር ግን
የሚከታተሉትን ሰዎች ከኋላው ልከው በዚ
ያው በለኪሶ ገደሉት:: 28በፈረስ ተጭኖ
ከመጣ በኋላም፣ እንደ አባቶቹ ሁሉ በይሁዳ

[ᵀ]23 *ዕብራይስጡ፣ 80 ሜትር ያህል ነው ይላል፤ አንዳንድ ቅጂዎች ግን ስድስት መቶ ጫማ ይላሉ::*

25፥8 2ዜና14፥11፤ 20፥6
25፥9 ዘጸ8፥18፤ ምሳ10፥22
25፥10 ቍ13
25፥12 መዝ141፥6፤ አብ1፥3
25፥14 ዘፀ20፥3፤ 2ዜና28፥23፤ ኢሳ44፥15
25፥15 ኢሳ36፥20
25፥18 መሳ9፥8-15
25፥20 2ዜና10፥15
25፥23 2ነገ14፥13፤ 2ዜና26፥9፤ነህ8፥16፤ 12፥39፤ኤር31፥38
25፥24 1ዜና26፥15
25፥27 ኢሱ10፥3

አንዱ ነው፤ ሕዝቡ በእግዚአብሔር እንዲታመን ከሚጋብዙት የትንቢት ቃሎች ጋር ያነጻጽሩ (20፥15-17:20፤ 32፥7-8)::

25፥13፤ ከሰሜኑ መንግሥት ክፍል ጋር ለመዋጋት ምክ ንያት የሆነውን ነገር የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም:: *ከሰ ማርያ፤* በደቡቡ መንግሥት እንዲህ ባለ ስም የሚጠራ ከተማ የለም:: ይህም መጽሐፉ ከአንዱ ቅጅ ወደ ሌላው ሲገለበጥ በስሕ ተት የተጻፈ ስም ሊሆን ይችላል::

*25፥14-25፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ከሰሜኑ መንግሥት ጋር ስለተደረገው ጦርነት የሚያውሣው ታሪክ ስለ አጸፋ ቅጣት መሪ ሐሳብ መግለጫ ከመጨመሩ በስተቀር ከ2ነገ14፥8-14 ላይ ከሚገኘው ተጓዳኝ ምንባብ ጋር ተመሳሳይ ነው:: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ፣ አሜስያስ የተከተለውን የጣዖት አምልኮና በነቢዩ አንደበት የተነገ ረውን የእግዚአብሔር ፍርድ ይገልጻል፤ ከእነዚህ ታሪኮች አንዱም በመጽሐፈ ነገሥቱ አይገኝም:: ጸሓፊው የአሜስያስ የጣዖት አምልኮ ስለ መቀጣቱ አጽንዖት የሚሰጡ ነጥቦችን በ ቍ 20:27 ላይ ጨምሮአል::

*25፥18፤* በመሳ9፥7-15 ከተጻፈው ምሳሌ ጋር ያነጻጽሩ::

25፥23 *ከኤፍሬም በር እስከ ማዕዘኑ በር ድረስ፤* ሁለቱም በሮች በከተማዪቱ ሰሜናዊ ቅጥር ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ የኤፍሬም በር በሰሜን ምዕራብ፣ የማዕዘኑ በር ደግሞ በሰሜን ምሥራቅ በኩል ነበሩ::

*25፥24፤* የዖቤድኤዶም ቤተ ሰብ ከሌዊ ነገድ ሲሆን፣ የቤተ መቅደሱን ሀብትና ንብረት የመጠበቅ ኀላፊነት የተሰጠ ውም ለዚሁ ቤተ ሰብ ነበር (1ዜና 26፥15)::

*25፥27፤* የቍ14-25 ማብ ይሙ::

*26፥1-23፤* 2ነገ15፥1-7 እና ማብ ይሙ:: የዜና መዋዕሉ

ከተማ ተቀበረ።

## የይሁዳ ንጉሥ ዖዝያን

26፥1-4ተጓ ምብ —2ዜና14፥21-22፤15፥1-3
26፥1-23ተጓ ምብ —2ዜና15፥5-7

**26** ከዚህ በኋላ የይሁዳ ሕዝብ በሙሉ
ዕድሜው ዐሥራ ስድስት ዓመት
የነበረውን ዖዝያንን ወስደው በአባቱ በአሜ
ስያስ ፈንታ አነገሡት። [2]አሜስያስ እንደ
አባቶቹ ሁሉ ካንቀላፋ በኋላ፣ ኤላትን እንደገና
የሠራት፣ ወደ ይሁዳም የመለሳት ዖዝያን
ነበር።
[3]ዖዝያን በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ዐሥራ
ስድስት ዓመት ሲሆን፣ በኢየሩሳሌም ተቀምጦ
አምሳ ሁለት ዓመት ገዛ። እናቱ ይኮልያ
የተባለች የኢየሩሳሌም ሴት ነበረች። [4]እርሱም
አባቱ አሜስያስ እንደ አደረገው ሁሉ *በእግ
ዚአብሔር* ፊት ቅን ነገር አደረገ። [5]እግዚ
አብሔርን *መፍራት* ባስተማረው በዘካርያስ ዘመን
እግዚአብሔርን ፈለገ፤ *እግዚአብሔርን* በፈለገ መጠ
ንም ስምሳክ ነገሮችን አከናወነለት።
[6]በፍልስጥኤማውያን ላይ ዘምቶ የጌትን፣
የየብናንና የአዛጦንን ቅጥሮች አፈረሰ። ከዚ
ያም በአዛጦን አጠገብና በቀሩትም የፍል
ስጥኤም ግዛቶች ውስጥ ከተሞችን እንደገና
ሠራ። [7]እግዚአብሔርም በፍልስጥኤማውያን፣ በጉ
ርበኣል በሚኖሩ ዐረቦችና በምዑናውያን ላይ
ድልን አቀዳጀው። [8]አሞናውያን ለዖዝያን ግብር
ገበሩለት፤ ኀይሉ ስለ ገነነም ዝናው እስከ ግብፅ
ዳርቻ ወጣ።
[9]ዖዝያንም በኢየሩሳሌም በማዕዘኑ በር፣
በሸለቆው በርና በቅጥሩ ማዕዘን ማማዎች ሠርቶ
መሸጋቸው። [10]እንዲሁም በየኰረብታው ግርጌና
በየሜዳው ላይ ብዙ የቀንድ ከብት ስለ ነበረው፣
በምድረ በዳ የግንብ ማማዎች ሠራ፤ ብዙ የውሃ
ጉድጓዶችም ቈፈረ። ግብርና ይወድድ ስለ ነበ
ረም በኰረብታዎችና ለም በሆኑ መሬቶች
ላይ ዕርሻ የሚያርሱና ወይን የሚተክሉ ሰራ
ተኞች ነበሩት።
[11]ዖዝያን ከንጉሡ ሹማምንት አንዱ በሆነው
በሐናንያ መሪነት፣ በጸሓፊው በይዒኤልና
በአለቃው በመዕሤያ አማካይነት ተሰብስቦ
በተቈጠረው መሠረት በየምድቡ ለጦርነት
ዝግጁ ሆኖ የሚወጣ፣ በሚገባ የሠለጠነ ሰራ
ዊት ነበረው። [12]በተዋጊዎቹ ላይ የተሾሙት
የየቤተሰቡ መሪዎች ጠቅላላ ቍጥር ሁለት
ሺህ ስድስት መቶ ነበር። [13]በእነዚህም የሚመራ
ሦስት መቶ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰው ያለው
ሰራዊት አለ፤ ይህም ንጉሡ በጠላቶቹ ላይ
በሚያደርገው ዘመቻ ለመሰለፍ የሚበቃ ጠን
ካራ ኃይል ነበር። [14]ዖዝያን ለሰራዊቱ ሁሉ
ጋሻ፣ ጦር፣ የራስ ቁር፣ ጥሩር፣ የቀስት
ማስፈንጠሪያ ደጋንና የሚወነጨፍ ድንጋይ
አደለ። [15]በኢየሩሳሌምም፣ ንድፎቻቸው በባለ
ሙያዎች የተዘጋጁ፣ በመጠበቂያ የግንብ
ማማዎችና በየማዕዘኑ መከላከያዎች ላይ
ፍላጻ የሚስፈነጠርባቸውንና ትልልቅ ድንጋዮች
የሚወረወርባቸውን መሣሪያዎች አሠራ። እስ
ኪበረታም ድረስ በሚያስደንቅ ሁኔታ ስለታገዘ፣
ዝናው በርቀትና በስፋት ተሰማ።
[16]ዖዝያን ከበረታ በኋላ ግን ዕብሪቱ ለው
ድቀት ዳረገው። በዕጣን መሠዊያው ላይ ዕጣን
ለማጠን ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ
በመግባቱ እግዚአብሔርን በደለ፤ [17]ካህኑም ዓዛ
ርያስ ቈራጥ ከሆኑ ከሌሎች ሰማንያ *የእግዚ
አብሔር* ካህናት ጋር ተከትሎት ገባ።

[u]5 ብዙ የዕብራይስጥ ትርጕሞች፣ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ እንዳንድ የዕብራስጥ ቅጆች ግን *እንደ እግዚአብሔር ራእይ ባስተማረው*

26፥1 2ዜና22፥1
26፥5 2ዜና24፥2፤ 27፥6
26፥6 ኢሳ2፥6፤ 11፥14፤14፥29፤ኤር2 5፥20፤አሞ1፥8፤3፥9
26፥7 2ዜና20፥1፤ 21፥16
26፥8 ዘፍ19፥38
26፥9 2ነገ14፥13፤ 2ዜና25፥23፤ነህ2፥13 ፤3፥13
26፥14 ኤር46፥4
26፥16 ዘዳ32፥5፤ 2ነገ14፥10፤16፥12፤1 ዜና5፥25
26፥17 1ነገ4፥2

ጸሓፊ የዖዝያንን ዘመነ መንግሥት መልካምና ክፉ ዘመን በማለት በሁለት ከፍሎታል፤ ስለ ዖዝያን አባት ስለ አሜስያስ ስለ አያቱ ስለ ኢዮአስ የተዘገበውን (የ24፥2፤25፥1-8) ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ። ዖዝያን ለእግዚአብሔር ታዛዥና ታማኝ ሆኖ በመገኘቱ ያገኘውን በረከትና አምላካዊ ርዳታ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በስፋት ጽፎታል። የመጽሐፈ ነገሥቱ ጸሓፊ ግን የጠቈመው ታማኝ መሆኑን ብቻ ነው (2ነገ15፥3)። መጽሐፈ ነገሥቱ ዖዝያን ለምጽ የወጣበት መሆኑን ብቻ ሲያወሣ (2ነገ፡15፥5) የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ደዌው በዖዝያን ላይ ሊወጣ የቻለው ለእግዚአብሔር ካለመታመኑ የተነሣ መሆኑን ለማሳየት ተጨማሪ ዝርዝር አቅርቦአል (ቍ16-21)። ዖዝያን በደቡብ ክፍል፣ ዳግማዊ ኢዮርብዓም ደግሞ በሰሜኑ ክፍል በነገሡ ጊዜ በስተሰሜንና በስተደቡብ ያለው የእስራኤልና የይሁዳ መንግሥታት ድንበር በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን ወደ ነበረው ተመልሶአል (ቍ6-8፤ 2ነገ14፥25)። የእነዚህ ሁለት መንግሥታት መስፋፋት በከፊልም ቢሆን ሊመቻች የቻለው በአሦሩ ንጉሥ በሣልሳዊ አዳድኒራሪ መሪነት (802 ዓ.ቅ.ክ) የሶሪያ አስጊነት በመወገዱና ቀጥሎም አሦር ራሷ በመዳከሟ ነው።

26፥1 *ዖዝያንን* አንዳንድ ትርጉሞች 2ነ 15፥6-7፤ 1ዜና3፥12 ይመ፦ ዓዛርያስ መደበኛ ስሙ፣ ዖዝያን ደግሞ የዙፋን ስሙ ሳይሆን አይቀር ም።

26፥3 *አምሳ ሁለት ዓመት፤* 792-740 ዓ.ቅ.ክ ለማለት ነው፤ ይህም ከአሜስያስ ጋር ሥልጣን ተጋርቶ የገዛበትን (ከ792-767 ዓመት ዓ.ቅ.ክ.) ጊዜ የሚያካትት ነው።

*26፥4፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የዖዝያንን ዘመነ መንግሥት ታሪክ ፍሬ ሐሳቦች ያቀነባበረው፣ ከአሜስያስና ከኢዮአስ ዘመነ መንግሥት ታሪክ ጋር በሚመሳሰል መልኩ ነው (የቍ1-23 ማብ ይመ)። እንዲሁም ይህንኑ ታሪክ በተመሳሳይ ሁኔታ ያቀረበው መጽሐፈ ነገሥት፣ ንጉሡ ማምለኪያ ኰረብታዎችን ስላለማስወገዱ የዘገበውን፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ሳያወሣ አልፎታል (2ነገ15፥4)። እንደዚሁም የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የሁለት ነገሥታትን ታሪክ ሳይጠቅስ አልፎአል (25፥2 ማብ ይመ)።

26፥5 *በዘካርያስ ዘመን፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ እዚህም ላይ ነገሥታቱ ቢታዘዙ በረከት፣ ባይታዘዙ ግን ፍርድ እንደሚጠብቃቸው በቅደም ተከተል ያሳያል (የ12፥2 ማብ ይመ)።

26፥6-8፤ ዖዝያን ድል አድርጎ የያዛቸው ቦታዎች በደቡብ ምሥራቅና በደቡብ ምዕራብ በኩል ያሉትን ሲሆን፣ ኀያሉ የእስራኤል ንጉሥ ዳግማዊ ኢዮርብዓም የያዛቸው ቦታዎች ደግሞ ከይሁዳ በስተሰሜን ያሉትን ነበር።

26፥7 *በምዑናውያን፤* የ20፥1 ማብ ይመ።

26፥9 *በማዕዘኑ በር፣ በሸለቆው በርና፤* እነዚህ በሮች የሚገኙት በሰሜን ምሥራቅና በደቡብ ምዕራብ በኩል ባሉት ቅጥሮች ላይ ነው። *መሸጋቸው፤* በኢየሩሳሌም ቅጥር ላይ የተከናወነው ይህ የግንቢታ ሥራ በአሜሲያስ ዘመነ መንግሥት ኢዮአስ ያፈረሰው ቅጥር በከፊል መጠገኑን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም (25፥23)።

26፥10፤ *የግንብ ማማዎች... የውሃ ጉድጓዶችም፤* የግንብ ማማዎችና የውሃ ጉድጓዶች በሥነ ቅርስ ቍፋሮ (ከቍምራን፣ ከገባዖን፣ ከቤርሴባህ) ተገኝተዋል። የዖዝያን ስም የተቀረጸበት ማንተምም ቴል ቤይት ሚርሲም በተባለ ቦታ በሚገኝ የውሃ ጉድጓድ ላይ ተገኝቶአል።

26፥11፤ *ዖዝያን... በሚገባ የሰለጠነ፤ ሰራዊት ነበረው፤* (በ743 ዓ.ቅ.ክ) የሶርያ ንጉሥ ሣልሳዊው ቴልጌልቴልፌልሶርን በምዕራብ በኩል ያደረገው ወረራ "ብያውዲው ንጉሥ በአዝሪያው" ምናልባትም በይሁዳው አዛርያስ (ዖዝያን)" መሪነት የተባበረው ሰራዊት ወደፊት እንዳይገፋ ማድረጉን ገልጾአል።

26፥15 *ፍላጻ የሚስፈነጠርባቸውንና ትልልቅ ድንጋዮች የሚወረወሩባቸውን መሣሪያዎች ፤* ማስፈንጠሪያ መሣሪያ በዚያ ወቅት በነበረው በወታደራዊ ቴክኖሎጂ ስለማይታወቅ የቀስት መወርወርያ መሣሪያዎችም በሚቀጥሉት ሦስት መቶ ዓመታት ያህል በተግባር ላይ ስላልዋሉ በዚህ ክፍል የተጠቀሱት መሣሪያዎች ከቅጥር ላይ ወደ ታች የሚስፈነጠሩ ፍላጻችንና የሚወረወሩ ድንጋዮችን ለመከላከል የሚያገለግሉትን መሣሪያዎች ሊያመለክቱ ይችላሉ።

18እነርሱም ፊት ለፊት በመጋፈጥ፣ "ዖዝያን
ሆይ፤ ለእግዚአብሔር ማጠን ለተለዩትና የአሮን
ዘሮች ለሆኑት ለካህናቱ እንጂ ለአንተ የተገባ
አይደለም፤ እግዚአብሔርን በድለሃልና ከመ
ቅደሱ ውጣ፤ ከእግዚአብሔር አምላክ ዘንድም
ክብር አይሆንልህምና" አሉት።

19ጥና በእጁ ይዞ ዕጣን ለማጠን ዝግጁ
የነበረው ዖዝያን ተቈጣ፤ በእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ውስጥ በዕጣን መሠዊያው ፊት ሆኖ
ካህናቱ ላይ እየተቈጣ ሳለ፣ በግንባሩ ላይ ለምጽ^
ወጣበት። 20ሊቀ ካህናቱ ዓዛርያስና ሌሎቹ
ካህናት ሁሉ በተመለከቱት ጊዜ፣ በግንባሩ
ላይ ለምጽ እንደ ወጣበት አዩ። ስለዚህ
አጣድፈው አስወጡት፤ በእርግጥ እርሱም
ራሱ ለመውጣት ቸኵሎ ነበር፤ እግዚአብሔር
አስጨንቆታልና።

21ንጉሥ ዖዝያን እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ
ለምጻም ነበረ። ለምጻም በመሆኑም ከቤተ
መቅደስ ተወግዶ ነበርና በተለየ ቤት ተቀ
መጠ"። ከዚያም ልጁ ኢዮአታም የቤተ
መንግሥቱን አስተዳደር በኀላፊነት ተረክቦ
የአገሩን ሕዝብ ይመራ ጀመር።

22በዖዝያን ዘመነ መንግሥት ከመጀመሪያው
እስከ መጨረሻው የተከናወነውን ሌላውን
ተግባር ሁሉ የአሞጽ ልጅ ነቢዩ ኢሳይያስ
ጽፎታል። 23ዖዝያንም እንደ አባቶቹ ሁሉ
አንቀላፋ። ሕዝቡም "ለምጽ አለበት" ብለው
የነገሥታቱ በሆነው መቃብር አጠገብ ባለው
ቦታ ቀበሩት፤ ልጁም ኢዮአታም በእርሱ
ፈንታ ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአታም

27፥1-4፡7-9ተጓ ምብ —2ዜና15፥33-38

**27** ኢዮአታም በነገሠ ጊዜ ዕድሜው
ሃያ አምስት ዓመት ሲሆን፣ በኢየሩ
ሳሌም ተቀምጦ ዐሥራ ስድስት ዓመት ገዛ።
እናቱም ኢየሩሳ የተባለች የሳዶቅ ልጅ
ነበረች። 2አባቱ ዖዝያን እንዳደረገው ሁሉ
በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገር አደረገ፤ ይሁን
እንጂ እንደ አባቱ ወደ እግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ አልገባም። ሕዝቡም በበደሉ እንደ
ገፉበት ነበር። 3ኢዮአታም የእግዚአብሔርን
ቤተ መቅደስ የላይኛውን በር እንደገና ሠራው፤
በዖፌልም በኩል ባለው ቅጥር ላይ፣ አያሌ
የማሻሻል ተግባር አከናወነ። 4በይሁዳ ኰረ
ብታዎች ላይ ከተሞችን፣ ደን በለበሱ ስፍ
ራዎችም ምሽጎችንና ማማዎችን ሠራ።

5ኢዮአታም የአሞናውያንን ንጉሥ ወግቶ
ድል አደረጋቸው። በዚያው ዓመትም አሞና
ውያን አንድ መቶ መክሊት" ጥሬ ብር፣ ዐሥር
ሺህ ቆሮስ" ስንዴና ዐሥር ሺህ ቆሮስ ገብስ
ገበሩለት። አሞናውያን በሁለተኛውና በሦስ
ተኛው ዓመት ይህንኑ ግብር አመጡለት።

6ኢዮአታም በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት
በታማኝነት ስለተመላለሰ፣ እየበረታ ሄደ።

7በኢዮአታም ዘመነ መንግሥት የተከናወነው
ሌላው ተግባር፣ ያደረጋቸው ጦርነቶችና የሠ
ራቸው ነገሮች በሙሉ በእስራኤልና በይሁዳ
ነገሥታት መጽሐፍ ተጽፎአል። 8እርሱም
በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት ነበር፤
በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ዐሥራ ስድስት
ዓመት ገዛ። 9ኢዮአታም እንደ አባቶቹ ሁሉ
አንቀላፋ፤ በዳዊት ከተማ ተቀበረ፤ ልጁ አካዝም
በእርሱ ፈንታ ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ አካዝ

28፥1-27ተጓ ምብ 2ዜና16፥10-20

**28** አካዝ መንገሥ በጀመረ ጊዜ ዕድሜው
ሃያ ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀም
ጦም ዐሥራ ስድስት ዓመት ገዛ። እርሱም
በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገር እንዳደረገው
እንደ አባቱ እንደ ዳዊት አላደረገም። 2በእ
ስራኤል ነገሥታት መንገድ ሄደ፤ በኣሊምን
ለማምለክም የተቀረጹ ጣዖታትን ሠራ። 3እግ
ዚአብሔር ከእስራኤላውያን ፊት ያስወገዳ
ቸውን አሕዛብ ልማድ በመከተል፣ በሄኖም
ልጅ ሸለቆ ዐጠነ፤ ወንዶች ልጆቹንም የሚቃጠል

26፥18 ዘፀ30፥7፤ ዘኍ16፥39፤18፥1-7፤1ዜና6፥49
26፥19 ዘኍ12፥10
26፥21 ዘፀ4፥6፤ ዘሌ13፥46፤14፥8፤ ዘኍ5፥2፤19፥12
26፥22 2ነገ15፥1፤ ኢሳ1፥1፤6፥1
26፥23 2ነገ14፥21፤ ኢሳ1፥1፤6፥1፤ አሞ1፥1
27፥1 2ነገ15፥5፡32፤1ዜና3፥12
27፥3 2ዜና33፥14፤ ነህ3፥26
27፥5 ዘፍ19፥38
27፥6 2ዜና26፥5
28፥1 1ዜና3፥13፤ ኢሳ1፥1
28፥2 ዘፀ34፥17
28፥3 ዘሌ18፥21፤ ዘዳ18፥9፤ኢሱ15፥8፤ 2ነገ3፥27፤2ዜና33፥2፤ሕዝ20፥26

^19 የዕብራይስጡ ቃል በዚህም ሆነ በቍጥር 20:21 እና 23 ላይ ማንኛውንም ዐይነት የቈዳ በሽታ የሚያመለክት ነው።
"21 ወይም ከኃላፊነቱ በሚርቅበት ቤት ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
'"5 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።
‴5 2, 200 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።

26፥16፤ *ዖዝያን ከበረታ በኋላ፤* የቍ 5 ማብ ይመ።

26፥19 *ለምጽ፤* ደዌ በኀጢአት ምክንያት የሚመጣ ቅጣት ስለመሆኑ የ16፥12፤21፥12-15 ማብ ይመ።

26፥21 *ዖዝያን ......ሞቱ ፤* ኢሳ 6፥1 እና ማብ ይመ።

26፥22 *ኢሳይያስ ጽፎታል፤* ይህ በትንቢተ ኢሳይያስ መጽሐፍ ላይ ሳይሆን፣ በሌላ መጽሐፉ የተጻፈ ነው፤ መጽሐፉም ባሁኑ ጊዜ የማይገኝ ነው።

26፥23፤ *የነገሥታቱ.....ቦታ ቀበሩት፤* ከ2ነገ15፥7 ጋር ያነጻጽሩ። ዖዝያን ለምጻም ስለ ሆነ በነገሥታት መካከ መቃብር ሳይሆን በመቃ ብሩ አጠገብ ባለው ቦታ ተቀበረ።

*27፥1-9፤* 2ነገ15፥32-38እና ማብ ይመ።

27፥1፤ *ዐሥራ ስድስት ዓመት፤* 750-735 ዓ.ቅ.ክ ለማለት ነው፤ ይህም ከዖዝያን ጋር ሥልጣን ተጋርቶ የገዛበትን (750-740) ጊዜ ይጨምራል። የኢዮአታም ዘመነ መንግሥት ከ735-732 ዓ.ቅ.ክ. የነበረውን የወራሹን የአካዝን ዘመነ መንግሥት ደርቦ ይይዛል።

27፥2፤ *ወደ ቤተ መቅደሰ አልገባም፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ፣ ኢዮአታም አባቱ ዖዝያን የፈጸመውን ስሕተት (26፥16) ባለመድገሙ የተለየ ግምት ይሰጠዋል። *በበደሉ፤* ማምለኪያ ኰረብታዎች እየበዙ መሄዳቸውን ያመለክታል (2ነገ15፥35)

*27፥3-6፤* ይህ ክፍል ተጽፎ የሚገኘው በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ላይ ብቻ ነው። ኢዮአታም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በሚገባ በመጠበቁ፣ እግዚአብሔር ስለ ባረከው፣ የግንባታው ሥራ የተከናወነለት መሆኑን፣ በጠላቶቹ ላይ ድልን መጐናጸፉንና መበልጸጉን፣ ይህ ሁሉ ሊሳካለት የቻለውም በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅ ጸንቶ በመኖሩ መሆኑን ጸሓፊው አስፋፍቶ ጽፎለታል (ቍ6)። ይሁዳ ከአሞናውያን ጋር ስላለው ግንኙነት የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ልዩ ትኩረት ሰጥቶታል (የ20፥1-30፤24፥26 ማብ ይመ)።

27፥7 *ያደረጋቸው ጦርነቶችና፤* ለምሳሌ 2ነገ15፥37 ይመ።

*28፥1-27* እጅግ የሚመሳሰሉት የ2ኛ ነገሥትና የ2ኛ ዜና መግቢያና መደምደሚያ ብቻ ቢሆኑም 2ነገ16፥1-20እና ማብ ይመ። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ቅንጣት ታህል በጎ ነገር ያልጻፈለት ንጉሥ ቢኖር አካዝ ብቻ ነው። የደቡብ መንግሥት በአካዝ መሪነት የተዘፈቀበትን ክህደት በግልጽ ለማሳየት ሲል፣ አብያ የሰሜኑን መንግሥት ለማጥላላትና ለማውገዝ የተጠቀመበትን ንግግር (ም13) ጸሓፊው እዚህ ላይ የደገመው ይመስላል። አብያ ይመካበት የነበረው የይሁዳ ሃይማኖታዊ ታማኝነት፣ በአካዝ ዘመን ድራሹ ጠፍቶአል።

28፥1 *ዐሥራ ስድስት ዓመት፤* ከ732-715 ዓ.ቅ.ክ. ነው፤ ይህም ከኢዮአታም ጋር ሥልጣን ተጋርቶ የገዛበትን 735-732 ያለውን ጊዜ አይጨምርም።

28፥2፤ *የተቀረጹ ጣዖታትን ሠራ፤* ከ13፥8 ጋር ያነጻጽሩ።

28፥3 *በሄኖም ልጅ ሸለቆ፤* ከ33፥6 ጋር ያነጻጽሩ በዚህ ቦታ ይደረግ የነበረውን የአሕዛብ አምልኮ ልማድና ሥርዓት ያስወገደው ኢዮስያስ ነው (2ነገ23፥10)። *ልጆቹንም የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ፤* ዘሌ20፥1-5፤ ኤር7፥31-32፤ ይመ። በ2ነገ16፥3

መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። 4በኩረብታ መስ
ገጃዎችና በተራሮች አናት ላይ፣ በየዛፉም ጥላ
ሥር መሥዋዕት አቀረበ፤ ዕጣንም ዐጠነ።
5ስለዚህ አምላኩ እግዚአብሔር ለሶርያ ንጉሥ
አሳልፎ ሰጠው፤ ሶርያውያንም ድል አደረጉት፤
ከሕዝቡም ብዙዎቹን ምርኮኞች አድርገው
ወደ ደማስቆ ወሰዷቸው።
ደግሞም ለእስራኤል ንጉሥ አልፎ ተሰጠ፤
እርሱም ከባድ ጕዳት አደረሰበት። 6ይሁዳ
የአባቶቹን አምላክ እግዚአብሔርን ስለ ተወ፣
የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ በአንድ ቀን ከይሁዳ
መቶ ሃያ ሺህ ወታደሮች ገደለ። 7ጦረኛው
ኤፍሬማዊ ዝክሪም የንጉሡን ልጅ መዕሤ
ያን፣ የቤተ መንግሥቱ ኀላፊ የሆነውን
ዓዝሪቃምንና ለንጉሡ በማዕረግ ሁለተኛ
ሰው የሆነውን ሕልቃናን ገደለ። 8እስራኤላ
ውያንም ከገዛ ወገኖቻቸው ሁለት መቶ ሺ
ባለ ትዳር ሴቶችን፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን
ማረኩ፤ እንዲሁም እጅግ ብዙ ምርኮ ይዘው
ወደ ሰማርያ ተመለሱ።
9ዖዴድ የተባለ የእግዚአብሔር ነቢይ በዚያ
ስለ ነበር፣ ሰራዊቱ ወደ ሰማርያ በተመለሰ ጊዜ
ለመቀበል ወጣ፤ እንዲህም አላቸው፤ "የአባቶ
ቻችሁ አምላክ እግዚአብሔር ይሁዳን ስለ ተቈጣ
በእጃችሁ አሳልፎ ሰጣችሁ፤ እናንተ ግን እስከ
ሰማይ በሚደርስ ቍጣ ፈጃችኋቸው። 10አሁንም
የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ወንዶችና ሴቶች፣
ባሪያዎቻችሁ ልታደርጓቸው ትፈልጋላችሁ፤ እናን
ተስ ብትሆኑ ኀጢአት ሠርታችሁ አምላካችሁን
እግዚአብሔርን አልበደላችሁምን? 11እንግዲህ ስሙኝ፤
የእግዚአብሔር አስፈሪ ቍጣ በእናንተ ላይ
ነዶአልና፣ በምርኮ ያመጣችኋቸውን ወገኖቻ
ችሁን መልሷቸው።"
12ከዚያም ከኤፍሬም መሪዎች ጥቂቶቹ
የዮሐናን ልጅ ዓዛርያስ፣ የምሺሌሞት ልጅ
በራክያ፣ የሰሎም ልጅ ይሒዝቅያ፣ የሐድላይ
ልጅ ዓሜሳይ ከጦርነቱ የተመለሱትን በመ
ቃወም፣ 13"እነዚህን ምርኮኞች እዚህ ማምጣት
አልነበረባችሁም፤ ያለዚያ እኛ በእግዚአብሔር
ፊት በደለኞች እንሆናለን፤ በኀጢአታችንና
በበደላችን ላይ ሌላ ልትጨምሩ ታስባላችሁን?
በደላችንማ ቀድሞውኑ በዝቶአል፤ ቍጣውም
በእስራኤል ላይ ነውና" አሉ።
14ስለዚህ ወታደሮቹ በሹማምንቱና በጉባኤው
ሁሉ ፊት ምርኮኞቹን ለቀቁ፤ የተማረከ
ውንም ዕቃ መለሱ። 15በስም የተጠቀሱ ሰዎችም
ምርኮኞቹን ተረክበው ዕራቁታቸውን ለቀሩት
ሁሉ ከምርኮው አለበሷቸው፤ ልብስና ጫማ፣
ምግብና መጠጥ ሰጧቸው፣ በቅባትም ቀቧቸው፤
የደከሙትንም ሁሉ በአህያ ላይ አስቀመጧቸው።
ከዚያም ወገኖቻቸው ወደ ሚገኙባት የዘንባባ
ከተማ ተብላ ወደምትጠራው ወደ ኢያሪኮ
ወስደዋቸው፣ ወደ ሰማርያ ተመለሱ።
16በዚያን ጊዜ ንጉሡ አካዝ ወደ አሦር
ንጉሥ[ሀ] ልኮ ርዳታ ጠየቀ፤ 17ኤዶማውያን እንደ
ገና መጥተው በይሁዳ ላይ አደጋ በመጣል
ምርኮኞችን ወስደው ነበርና። 18ፍልስጥኤማውያን
ደግሞ በየኰረብታው ግርጌና በይሁዳ ደቡብ
ያሉትን ከተሞች በመውረር ቤት ሳሚስን፣
ኤሎንን፣ ግዴሮትን፣ ሦኮን፣ ተምናን፣ ጊምዞንና
በአካባቢአቸው የሚገኙትን መንደሮች ሁሉ ያዙ፤
ተቀመጡባቸውም። 19የእስራኤል[ለ] ንጉሥ አካዝ
ክፋትን በይሁዳ ምድር ስላስፋፋና ለእግዚ
አብሔርም የነበረውን ታማኝነት በከፍተኛ
ደረጃ ስላጓደለ፣ እግዚአብሔር ይሁዳን አዋረደ።
20የአሦር ንጉሥ ቴልጌልቴልፌልሶር ወደ እርሱ
መጥቶ ነበር፤ ሆኖም ችግር ፈጠረበት እንጂ
አልረዳውም። 21አካዝ ከእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ፣ ከቤተ መንግሥቱና ከመሳፍንቱ
ጥቂት ዕቃዎች ወስዶ ለአሦር ንጉሥ ሰጥቶ
ነበር፤ ይህም አልረዳው።
22ንጉሥ አካዝ በተጨነቀ ጊዜም፣ ለእግ
ዚአብሔር የነበረውን ታማኝነቱን ከምን ጊዜውም
ይበልጥ አጓደለ፤ 23እርሱም "የሶርያ ነገሥታት
አማልክት እነርሱን ስለ ረዷቸው፣ እኔንም ይረዱኝ
ዘንድ እሠዋላቸዋለሁ" ሲል እርሱን ላሸነፉት

28፥5 ኢሳ7፥1
28፥6 ቍ8፤ 2ነገ15፥25፡27፤ ኢሳ9፥21፤11፥13
28፥8 ዘዳ28፥25-41፤2ዜና29፥9
28፥9 ዕዝ9፥6፤ ኢሳ10፥6፤ 47፥6፤ዘካ1፥15፤ ራእ18፥5
28፥10 ዘሌ25፥39-46
28፥11 2ዜና11፥4
28፥15 ዘዳ34፥3፤ መሳ1፥16፤2ነገ6፥22፤ ምሳ25፥21-22፤ሉቃ10፥25-37
28፥16 2ነገ16፥7፤ሕዝ23፥12
28፥17 2ዜና29፥9፤ መዝ137፥7፤ ኢሳ34፥5፤ 63፥1፤ ኤር25፥21፤ ሕዝ16፥57፤ 25፥12፤ አሞ1፥11
28፥18 ዘፍ38፥12፤ ኢሱ10፥12፤ 15፥41፤1ሳሙ17፥1፤ ኢሳ9፥12፤11፥14፤ ኤር25፥20፤ ሕዝ 16፥27፡ 57፤25፥15
28፥19 1ዜና5፥25
28፥20 2ነገ15፥29፤ 16፥7፤1ዜና5፥6፤ኢሳ7፥17፤8፥7፤10፥5-6፡20፤36፥1
28፥21 2ዜና16፥2-9፤ኤር2፥36
28፥22 ኤር5፥3፤ 15፥7፤17፥23
28፥23 1ዜና11፥1፤ 2ዜና25፥14፤ ኢሳ10፥20፤ ኤር18፥5፤44፥17-18

ሀ16 አንድ የዕብራይስጥ ቅጅ፣ የሰብዓ ሊቃናትና የቡርስቱ ቅጅ እንዲሁም (2ነገ16፥7) ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ትርጕሞች ግን ነገሥታት ይላሉ።
ለ19 በዜና ካልዕ መጽሐፍ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው ይህ ይሁዳ ነው።

ላይ የተጠቀሰው አንድ ወንድ ልጅ ብቻ ነው፤ አንዳንዶች ግን የልጆቹ ቍጥር የበዛው፣ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ የአካዝን ክፋት ለማጕላት ካለው ፍላጎት የተነሣ ነው የሚል ግምት አላቸው። ይሁን እንጂ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች በ2ነገ16፥3 ላይ ልጆቹ ብዙ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፤ ይህም ጸሐፊው ቀደም ሲል ከነበረው ቅጅ ላይ እንዳለ ሳይገለብጥ እንደማይቀር ተገምቶአል።

*28፥5፤* ከ13፥16-17 ጋር ያነጻጽሩ። *እግዚአብሔር... አሳልፎ ሰጠው፤* ጸሐፊው መታዘዝ በረከትን አለመታዘዝ ግን የአጸፋ ቅጣት እንደሚያስከትል ባለው እምነት መሠረት በጦርነት መሸነፍም ያለመታዘዝ ውጤት ነው (የ20፥30 ማብ ይመ)። *ደግሞም ለእስራኤል ንጉሥ አልፎ ተሰጠ፤* 2ነገ16፥5-6 እና ኢሳ 7 ፋቍሔና የሶርያው ንጉሥ ረአሶን ግንባር ፈጥረው በይሁዳ ላይ እንደተነሡ በግልጽ አስቀምጦአል።

*28፥6፤ ፋቁሔ፤* ከ752-732 ዓ.ቅ.ክ. ሰሜኑን የእስራኤል መንግሥት የገዛ ንጉሥ ነው (2ነገ15፥27-31)። *እግዚአብሔርን ስለተወ፤* አብያ በሰሜኑ መንግሥት ላይ ከተናገረው ጋር የሚመሳሰል ነው (13፥11)።

*28፥9-15፤* የሰሜኑ ሰዎች ከደቡቡ መንግሥት ለማረኳቸው ምርኮኞች ያደረጉት ርኅራኄ (ከቍ14-15) ኢየሱስ ስለ ደጉ ሳምራዊ (ሉቃ10፥25-37) ለተናገረው ምሳሌ መሠረት ሳይሆን አይቀርም። ዖዴድ "ወገኖቻችሁን" የሚል ቃል መናገሩ በሰሜኑ ክፍል ለሚኖሩት እስራኤላውያን ያለውን በጎ አመለካከት የሚገልጽ ነው (ቍ11)።

*28፥17-18 ኤዶማውያን...በይሁዳ ላይ አደጋ በመጣል ... ፍልስጥኤማውያን... በመውረር፤* እነዚህ የተባበሩ የውጭ ጠላቶች (ቍ16) ለአካዝ መውደቅ ምክንያቶች ናቸው (የ16፥2-9 ማብ ይመ)።

28፥19 *አካዝ... ስላጓደለ እግዚአብሔር ይሁዳን አዋረደ፤* በዚህ ክፍል በአካዝ መሪነት ሽንፈት የደረሰበት ይሁዳ ቢሆንም፣ በ(13፥18)፣ ላይ በሰሜኑ ነገዶች መሸነፋቸውን ለመግለጽ ተመሳሳይ አባባል ተጠቅሞአል።

28፥20 *ቴልጌልቴልፌልሶር፤* 745-727 የነበረ የአሦር ንጉሥ ነው (1ዜና5፥26 እና ማብ ይመ)። *ችግር ፈጠረበት እንጂ አልረዳውም፤* ነገሩ ላይ ላዩን ሲታይ ኀልሳዊው ቴልጌልቴልፌልሶር የአካዝን ጥያቄ ተቀብሎ በመዝመት ደማስቆን መያዙን፣ ሕዝቡን በምርኮ መውሰዱንና ረአሶንን መግደሉን ከሚተርከው ከ2ነገ 16፥9 ጋር የሚቃረን ይመስላል። የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ግን ይህን ሲጽፍ አንባቢው ሌላ ቦታ የተጻፈውን ታሪክ እንደሚያውቅ ይገ ምታል፤ እንዲሁም አሦር ጣልቃ ገብቶ የደማስቆንና የሰሜኑን መንግ ሥት በመውጋቱ፣ ይሁዳ ለጊዜው ፋታ እንዳገኘ ያውቃል። እዚህ ላይ የጸሐፊው ትኵረት ግን ይሁዳ ከጊዜ በኋላ የአሦር መንግሥት አንድ አውራጃ መሆኗ እንደማይቀር መግለጹ ነው።

*28፥22-23፤* አካዝ ወደ ደማስቆ ሄዶ በዚያ ያለውን የመሠዊያ አሠራርና የአምልኮ ሥርዐቶችን መኰረጁን ተደራሲያኑ እንደሚያ ውቁ ጸሐፊው ይገምታል (2ነገ16፥10-16)።

*28፥24-25፤* አካዝ ያደረጋቸው ተጨማሪ ለውጦችም በ2ነገ

የደማስቆ አማልክት መሥዋዕት አቀረበ::
24አካዝ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ዕቃዎች
ሁሉ አንድ ላይ ሰብስቦ ወሰደ[ᄀ]፤ የእግዚአብሔ
ርን ቤተ መቅደስ በሮች ዘጋ፤ በኢየሩሳሌምም
በየአውራ ጎዳናው ማዕዘን ላይ መሠዊያ አቆመ::
25በይሁዳ ከተሞች ሁሉ ለሌሎች አማልክት
መሥዋዕት የሚያቃጥልባቸውን የኰረብታ
መስገጃዎች ሠራ፤ በዚህም የአባቶቹን አምላክ
እግዚአብሔርን ለቍጣ አነሣሣው::
26በአካዝ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው
ሌላው ተግባርና አካሄዱ ሁሉ ከመጀመሪያው
እስከ መጨረሻው በይሁዳና በእስራኤል ነገ
ሥታት መጽሐፍ ተጽፎአል:: 27አካዝ እንደ
አባቶቹ ሁሉ አንቀላፋ፤ በኢየሩሳሌምም ከተማ
ተቀበረ፤ የተቀበረው ግን በእስራኤል ነገሥታት
መካከ መቃብር አልነበረም:: ልጁ ሕዝቅያስም
በእርሱ ፈንታ ነገሠ::

## ሕዝቅያስ ቤተ መቅደሱን አነጸ

29፥1-2 ተጓ ምብ —1ዜና18፥2-3

**29** ሕዝቅያስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሃያ
አምስት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም
ተቀምጦም ሃያ ዘጠኝ ዓመት ገዛ:: እናቱም
አቡ የተባለች፤ የዘካርያስ ልጅ ነበረች::
2አባቱ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ፣ እርሱም
በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገር አደረገ::
3በዘመነ መንግሥቱ በመጀመሪያው ዓመት፣
በመጀመሪያው ወር የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስ በሮች ከፈተ፤ አደሳቸው:: 4ካህናቱንና
ሌዋውያኑን አስጉብቶ በምሥራቅ በኩል ባለው
አደባባይ ላይ በመሰብሰብ፣ 5እንዲህ አላቸው፤
"እናንት ሌዋውያን፤ ስሙኝ! ራሳችሁን አሁኑኑ

28፥24 2ነገ16፥18፤ 2ዜና29፥19፤30፥14፤ ሚል1፥10
28፥27 2ዜና21፥20፤ ኢሳ14፥28-32
29፥1 1ዜና3፥13
29፥2 2ዜና34፥2
29፥3 2ነገ18፥16
29፥5 ዘሌ11፥44፤ ነህ13፥9
29፥6 1ዜና5፥25፤ ዕዝ9፥7፤መዝ106፥6-47፤ኤር2፥27፤18፥17፤ሕዝ23፥35፤ዳን9፥5-6
29፥7 ዘፀ30፥7
29፥8 ዘሌ26፥32፤ ዘዳ28፥25፤ኤር18፥16፤19፥8፤25፥9፡18
29፥9 2ዜና28፥5-8፡17
29፥10 ዘኍ25፥4፤ 2ነገ11፥17፤2ዜና23፥16፤30፥8፤ዕዝ10፥14
29፥11 ዘኍ3፥6፤ 8፥6፡14፤1ዜና15፥2
29፥12 ዘኍ3፥17-20፤2ዜና31፥15

ቀድሱ፤ የአባቶቻችሁን አምላክ የእግዚአብሔ
ርንም ቤተ መቅደስ ቀድሱ:: ርኩስ ነገርንም
ሁሉ ከመቅደሱ አስወግዱ:: 6አባቶቻችን
ታማኞች አልነበሩም፣ በአምላካችን በእግዚአብሔር
ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤ ተዉትም:: ከእግዚ
አብሔር ማደሪያ ፊታቸውን መለሱ፤ ጀርባቸ
ውንም አዞሩበት:: 7የሰበሰቡንም በሮች ዘጉ፤
መብራቶቹንም አጠፉ:: ለእስራኤል አምላክ
ለእግዚአብሔር ዕጣን አላጠኑም፤ በመቅደሱም
የሚቃጠል መሥዋዕት አላቀረቡም:: 8ስለዚህ
የእግዚአብሔር ቍጣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም
ላይ ወርዶአል፤ እናንተ በገዛ ዓይናችሁ እንደ
ምታዩት ለድንጋጤ፣ ለመደነቂያና ለማዘብቻ
አሳልፎ ሰጣቸው:: 9በዚህ ምክንያት አባቶ
ቻችን በሰይፍ ወደቁ፣ ወንዶችና ሴቶች
ልጆቻችን፣ ሚስቶቻችንም ተማረኩ:: 10አሁንም
አስፈሪ ቍጣው ከእኛ እንዲመለስ፣ ከእስራ
ኤል አምላክ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ለመ
ግባት አስቤአለሁ:: 11ልጆቼ ሆይ፤ እንግዲህ
ቸል አትበሉ፤ በፊቱ እንድትቆሙና እንድ
ታገለግሉት፣ በፊቱም አገልጋዮቹ እንድት
ሆኑና ዕጣን እንድታጥኑለት እግዚአብሔር
መርጦአችኋልና::"
12ከዚያም እነዚሁ ሌዋውያን በሥራው
ላይ ተሰማሩ፤ ከቀዓት ዘሮች የአማሢ ልጅ
መሐትና የዓዛርያስ ልጅ ኢዩኤል፤
ከሜራሪ ዘሮች፣
የአብዲ ልጅ ቂስና የይሃሌልኤል
ልጅ ዓዛርያስ፤
ከጌድሶን ዘሮች፣
የዛማት ልጅ ዮአክና የዮአክ ልጅ ዔድን፤

[ᄀ]24 ወይም ሰበረ ተብሎ መተርጐም ይቻላል::

16፥17-18 ላይ በዝርዝር ተጽፎዋል:: እንደዚሁም የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ አካዝ የፈጸመውን ስሕተት ለማካካስ ሲል ሕዝቅያስ ያደረገውን ተሐድሶ በሰፊው ጽፎአል፤ ይኸውም:- አካዝ የቤተ መቅደሱን በሮች መዝጋቱ ብቻ ሳይበቃው መብራቶቹ እንዳይበሩ፣ በቅድስተ ቅዱሳኑም መሥዋዕት እንዳይቀርብ አድርጎአል (29፥7)፤ መሠዊያውንና የቀሩትን ንዋያተ ቅድሳት አርክሶአል፤ የተቀደሰው ገጸ ኅብስት የሚቀመጥበት ጠረጴዛ ከቦታው እንዲነሣ አድርጎአል (29፥18-19):: አብያ የይሁዳን ታማኝነት ከሰሜኑ መንግሥት ጋር እያነጻጸረ ይመካ የነበረው እነዚህ የተቀደሱ የቤተ መቅደሱ ዕቃዎች የሚሰጡትን ግልጋሎት በማውሣት ነበር (13፥11):: አካዝ ግን እነዚህ የተከበሩ የቤተ መቅደሱ ዕቃዎች ተገቢ ክብራቸውን እንዲያጡ ደቡብም ልክ እንደ ሰሜኑ ክፍል ከአምልኮተ እግዚአብሔር እንዲርቅ አደረገ (የቍ 1-27 ማብ ይመ)::

28፥27 *የተቀበረው ... በነገሥታት መካነ መቃብር አልነበረም፤* አካዝ ከክፉ ሥራው የተነሣ በክብር ለመቀበር ያልታደለ ሦስተኛው ንጉሥ ነው:: ሌሎቹ ሁለቱ ኢዮራም (21፥20) እና ኢዮአስ (24፥25) ናቸው:: ምንም እንኳ እንደዚህ ተገልጾ ባይጻፍም፣ የዖዝያን ኀጢአትና ለምጽ ተመሳሳይ ውጤት አስከትሎአል (26፥23):: የምናሴንም መጨረሻ ከዚሁ ጋር ያነጻጽሩ(33፥20)

*29፥1-32፥33፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ከሰሎሞን በኋላ ከተነሡት ነገሥታት ሁሉ ይልቅ ለሕዝቅያስ የሰጠው ትኵረት በጣም የተለየ ነው፤ ተጓዳኙ ምንባብ (2ነገ18-20) ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ሐሳብ ቢኖረውም፣ በቀጥታ ተመሳሳይነት ያለው ከአራት እጅ አንዱ ብቻ ነው፤ በሥነ ጽሑፋዊ ይዘታቸው ከዚህ ክፍል ጋር የሚቀራረቡት እጅግ ጥቂት ቍጥሮች ናቸው (29፥1-2፤32፥32-33):: በመጽሐፈ ነገሥት ከሰሎሞን በኋላ ከተነሡት ነገሥታት ሁሉ ይልቅ በክብር ደረጃ ቅድሚያ የተሰጠው ለኢዮስያስ ነው (2ነገ22-23፤ ከ1ነገ፤13፥2 ጋር ያነጻጽሩ):: የሕዝቅያስን ታሪክ በተመለከተ ከአሦሩ ንጉሥ ከሰናክሬም ጋር ላካሄደው ጦርነት ትኵረት ሰጥቶአል:: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን ሕዝቅያስ ለሃይማኖታዊ ተሐድሶ፣ ለበዓላት አከባበርና ለአምልኮ ሥርዐት የሰጠውን ከፍተኛ ግምት አጒልቶ ያሳያል፤ በ2ነገ18፥1-6 ላይ የሚገኘው ተጓዳኙ ምንባብ ለሃይማኖታዊው ተሐድሶ የሰጠው ትኵረት አነስተኛ ነው:: ከሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ጋር በተያያዘ መልኩ በዚህ ክፍል የሚገኘው አብዛኛው ታሪክ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ሕዝቅያስን ዳግማዊ ሰሎሞን አድርጎ እንደሚያቀርበው ይጠቍማል፤ ለዚህም፣ የፋሲካ በዓል አከባበሩን (30፥2፡5፡23፡25-26) ብልጽግናውን (32፥27-29) የአምልኮ ሥርዐት አደረጃጀቱን (29፥7፡18፡35፤ 31፥2-3) ከአሕዛብ ያገኘውን ክብር (32፥23) እንዲሁም የግዛቱን ስፋት አስመልክቶ የጻፈውን ማስተያየቱ በቂ ነው::

29፥1 *ሃያ ዘጠኝ ዓመት፤* ዘመኑ 715-686 ዓ.ቅ.ክ. ለማለት ነው (ሆኖም የኢሳ 36፥1 ማብ ይመ):: ይህም እግዚአብሔር የጨመረለትን የዐሥራ አምስት ዓመት ዕድሜ የሚጨምር ሲሆን (2ነገ 20፥6) የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን ይህን አላወሣውም::

*29፥3-30፥27፤* ይህ ክፍል በመጽሐፈ ነገሥት አይገኝም::

29፥3 *በመጀመሪያው ዓመት፤* ዘመኑ 715 ዓ.ቅ.ክ. ነው፤ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በታሪኩ ውስጥ የጊዜን ቅደም ተከተል ለማሳየት የሞከረበት ሌላው ምሳሌ ነው:: (የ12፥2 ማብ ይመ):: *ቤተ መቅደስ በሮች ከፈተ፤* ከአካዝ እኵይ ድርጊት በኋላ (28፥24) ይህን ማድረጉ አስፈላጊ ነገር ነበር:: *አደሳቸው፤* የመዝጊያዎቹ ጥገና በወርቅ የመለበጡንም ሥራ የሚጨምር ነበር (2ነገ18፥16)::

*29፥5-11፤* የሕዝቅያስ ንግግር ድርጊትና አጸፋን ያካተተ በመሆኑ፣ ያለፈው ኀጢአት መከራና ፍርድን ሲያስከትል፣ ታማኝነትን አድሶ መገኘትም ከመከራና ከችግር የሚገላግል መሆኑን ማመልከቱ በዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ላይ ያሳደረበትን ጽኑ እምነት እንደገና ያሳያል::

*29፥7፤* ሕዝቅያስ የሰሎሞንን ፈለግ በመከተል፣ ቤተ መቅደሱን እንደገና አደራጀ (2፥4፤4፥7)::

29፥8 *ለድንጋጤ፣ ለመደነቂያና ለመዘበቻ፤* ይህ አባባል የነቢያቱን በተለይም የኤርምያስን ንግግር የሚያስተጋባ ነው (ኤር 19፥8፤25፥9፡18፤29፥18፤51፥37 ይመ):: ይህም የሚያመለክተው አሦር የሰሜኑን መንግሥትና አብዛኛውን ይሁዳን ማጥፋቱን ነው::

29፥12 *ከቀዓት ዘሮች.... ከሜራሪ ዘሮች... ከጌድሶን ዘሮች፤* ከሌዊ ወገን የሆኑ ሦስቱ ጐሣዎች ናቸው (1ዜና6፥1)::

29፥13-14 *ከአሳፍ ...ከኤማን...ከኤዶታም፤* ሦስቱ የሌዋውያን

13ከኤሊጻፋን ዘሮች፣
ሺምሪና ይዒኤል፤
ከአሳፍ ዘሮች፣
ዘካርያስና መታንያ፤
14ከኤማን ዘሮች፣
ይሒኤልና ሰሜኢ፣
ከኤዶታም ዘሮች፣
ሸማያና ዑዝኤል።
15ወንድሞቻቸውን ከሰበሰቡና ራሳቸውን
ከቀደሱ በኋላ፣ ንጉሡ የእግዚአብሔርን ቃል
ተከትሎ ባዘዘው መሠረት የእግዚአብሔርን
ቤተ መቅደስ ለማንጻት ገቡ። 16ካህናቱ የእግዚ
አብሔርን መቅደስ ለማንጻት ወደ ውስጡ
ገቡ። በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ
ያገኙትንም ማናቸውንም የረከሰ ነገር ወደ
እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አደባባይ አወጡት።
ሌዋውያኑም ተሸክመው በመውሰድ በቄድሮን
ሸለቆ ውስጥ ጣሉት። 17ማንጻቱንም በመጀ
መሪያው ወር፣ በጀመሪያው ቀን ጀምረው
በዚያኑ ወር በስምንተኛው ቀን እስከ መቅደስ
ሰበሰብ ደረሱ፤ በሚቀጥሉትም ስምንት ቀናት
የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቀደሱ፤ የመ
ቀደሱም ሥራ በመጀመሪያው ወር በዐሥራ
ስድስተኛው ቀን ተጠናቀቀ።
18ከዚያም ወደ ንጉሡ ወደ ሕዝቅያስ ገብተው
እንዲህ አሉ፤ "የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ
በሙሉ፣ የሚቃጠል መሥዋዕት የሚቀርብ
በትን መሠዊያ ከነዕቃዎቹ ሁሉ፣ ገጸ ኅብስቱ
የሚቀመጥበትን ጠረጴዛ፣ ከነዕቃዎቹ አን
ጽተናል። 19ንጉሥ አካዝ ነግሦ ሳለ ታማኝነቱን
ትቶ፣ ከቦታቸው ያነሣቸውን ዕቃዎች ሁሉ
አዘጋጅተን ቀድሰናቸዋል፤ እነሆ፤ ዕቃዎቹ
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሠዊያ ፊት
ለፊት ናቸው።"
20በማግስቱም ማለዳ በማለዳ፣ ንጉሥ ሕዝቅያስ
የከተማዪቱን ሹማምንት በአንድነት ሰብስቦ፣
ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ወጣ፤ 21እነር
ሱም ስለ መንግሥቱ፣ ስለ መቅደሱና ስለ
ይሁዳ ሰባት ወይፈኖች፣ ሰባት አውራ በጎች፣
ሰባት ተባዕት የበግ ጠቦቶችና ሰባት ተባዕት
የፍየል ጠቦቶች ለኀጢአት መሥዋዕት አቀረ
ቧቸው፤ ንጉሡም እነዚህን በእግዚአብሔር መሠ
ዊያ ላይ እንዲያቀርቡ የአሮንን ዘሮች ካህናቱን
አዘዘ። 22ካህናቱም ወይፈኖቹን ዐርደው ደሙን
በመውሰድ በመሠዊያው ላይ ረጩት፤ አውራ
በጎቹንም ዐርደው ደሙን በመሠዊያው ላይ
ረጩት፤ እንደዚሁም ጠቦቶቹን ዐርደው ደሙን
በመሠዊያው ላይ ረጩት። 23ለኀጢአት መሥዋዕት
የሚሆኑትን ፍየሎች በንጉሡና በጉባኤው

29፥13 ዘፀ6፥22፤ 1ዜና6፥39
29፥15 1ዜና23፥28፤ ኢሳ1፥25
29፥16 2ሳሙ15፥23
29፥19 2ዜና28፥24
29፥21 ዘሌ4፥13-14፤ዕዝ6፥17፤8፥35
29፥22 ዘሌ4፥18፤ ዘኍ18፥17
29፥23 ዘሌ4፥15፤ 16፥5
29፥24 ዘፀ29፥36፤ ዘሌ4፥26፤1ዜና11፥1 ፤ዕዝ8፥35
29፥25 1ሳሙ22፥5፤ 1ዜና25፥6፤ 28፥19
29፥26 1ዜና15፥16፡24
29፥27 1ሳሙ16፥16
29፥28 2ዜና2፥4
29፥29 2ዜና20፥18
29፥31 ዘፀ25፥2፤ 35፥22፤ ዕብ13፥15-16
29፥32 ዘሌ1፥1-17
29፥34 2ዜና30፥3፡ 15፤ሕዝ44፥11

ፊት አቀረቡ፤ እነርሱም እጆቻቸውን ጫኑባቸው።
24ንጉሡ የሚቃጠል መሥዋዕትና የኀጢአት
መሥዋዕት ስለ እስራኤል ሁሉ እንዲቀርብ
አዞ ስለ ነበር፣ ካህናቱ ፍየሎቹን ዐርደው
ስለ እስራኤል ሁሉ ማስተስረያ እንዲሆን
የኀጢአት መሥዋዕት በማድረግ ደሙን በመ
ሠዊያው ላይ አቀረቡ።
25ንጉሥ ሕዝቅያስም በዳዊት፣ በንጉሡ
ባለ ራእይ በጋድና በነቢዩ በናታን በተሰጠው
መመሪያ መሠረት ሌዋውያኑን ጸናጽል፣
በገናና መሰንቆ አስይዞ በእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ መደባቸው፤ ይህም በነቢያት አማ
ካይነት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትእዛዝ ነበር።
26ስለዚህ ሌዋውያኑ የዳዊትን የዜማ ዕቃዎች፣
ካህናቱም መለከቶቻቸውን ይዘው ዝግጁ
በመሆን ቆሙ።
27ከዚህ በኋላ ሕዝቅያስ የሚቃጠለው መሥ
ዋዕት በመሠዊያው ላይ እንዲቀርብ አዘዘ።
መሥዋዕቱ ማረግ በጀመረ ጊዜም፣ በእስራ
ኤል ንጉሥ በዳዊት የዜማ ዕቃዎችና በመለከት
የታጀበ ዝማሬም ጀመረ። 28መዘምራኑ
በሚዘምሩበትና መለከተኞቹም በሚነፉበት
ጊዜም መላው ጉባኤ አጎንብሰው ሰገዱ፤
የሚቃጠለው መሥዋዕት እስኪጠናቀቅ
ድረስም ይህ ሁሉ ቀጠለ።
29መሥዋዕቱ ሁሉ ቀርቦ ካበቃ በኋላ፣
ንጉሡና አብረውት የነበሩት ሁሉ ተንበ
ርክከው ሰገዱ። 30ንጉሥ ሕዝቅያስና ሹማ
ምንቱ፣ ሌዋውያኑ በዳዊትና በባለ ራእዩ
በአሳፍ ቃል እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ
አዘዙ። እነርሱም ውዳሴውን በደስታ ዘመሩ፤
ራሳቸውንም አጎንብሰው ሰገዱ።
31ከዚያም ሕዝቅያስ፣ "እነሆ፤ ራሳችሁን
ለእግዚአብሔር ቀድሳችኋል፤ አሁንም ቅረቡ፤
መሥዋዕትና የምስጋና ስጦታ ወደ እግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ አምጡ" አላቸው።
ስለዚህ ጉባኤው መሥዋዕትና የምስጋና ስጦታ
አመጡ፤ ልባቸው የፈቀደ ሁሉም የሚቃጠል
መሥዋዕት አመጡ።
32ጉባኤውም ያመጣው የሚቃጠለው መሥ
ዋዕት ብዛት ሰባ ወይፈኖች፣ መቶ አውራ
በጎችና ሁለት መቶ ተባዕት የበግ ጠቦቶች
ናቸው፤ ሁሉም የሚቃጠል መሥዋዕት ሆነው
ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ ነበሩ። 33ለመሥዋዕት
የተቀደሱት እንስሳት ባጠቃላይ ስድስት
መቶ ወይፈን፣ ሦስት ሺህ በጎችና ፍየሎች
ነበሩ። 34ይሁን እንጂ ካህናቱ የሚቃጠለውን
መሥዋዕት ቈዳ ሁሉ ለመገፈፍ ቍጥራቸው
እጅግ ጥቂት ነበር፤ ስለዚህ ወገኖቻቸው

መዘምራን ቤተ ሰብ መሥራቾች ናቸው (1ዜና6፥31-48፤25፥1-31)።

29፥13 *ከኤሊጻፋን፤* የቀዓታውያን መሪ ሲሆን (ዘኍ3፥30)፣ ቤተ ሰቡም ራሱን ችሎ እንደ ንዑስ ጐሣ ለመቈጠር የበቃ ነበር (1ዜና15፥8፤ እና የ1ዜና15፥4-10 ማብ ይመ)።

29፥16 *በቄድሮን ሸለቆ ውስጥ ጣሉት፤* አሳም እንደዚሁ የአረማውያንን የጣዖት ማምለኪያ ዕቃዎች በዚሁ ቦታ አቃጥሎአል (15፥16፤ከ30፥14 ጋር ያነጻጽሩ)።

*29፥18፤* በሕዝቅያስ ዘመን የተፈጸመው ይህ የማንጻት ተግባር በሰሎሞን ጊዜ የተፈጸመውን የሚያሳይ ነው።

29፥21 *ለኀጢአት መሥዋዕት፤* ዘሌ4፥1-5፥13 ይመ።

29፥22 *ደሙን... ረጩት፤* ዘሌ17፥6፤ ዘኍ18፥17 ይመ።

29፥23 *እጆቻቸውን ጫኑባቸው፤* ዘሌ4፥13-15፤8፥14-15፤ ዘኍ8፥12 ይመ።

29፥25፤ *በዳዊት ...ጋድ...በናታን በነቢያት፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ፣ ዳዊትን የሚመለከተው ከነቢያት እንደ አንዱ አድርጎ ነው (የ1፥7፤ የ1ዜና28፥19 ማብ ይመ)።

29፥26 *የዳዊትን የዜማ ዕቃዎች፤* 1ዜና 23፥5 ይመ።

29፥35 *የኅብረት መሥዋዕት... የመጠጡን ቍርባን...*

የሆኑት ሌዋውያን ሥራው እስኪያልቅና ሌሎች
ካህናት እስኪቀደሱ ድረስ ረዷቸው፤ ሌዋው
ያኑም ራሳቸውን ለመቀደስ ከካህናቱ ይልቅ
ጠንቃቆች ነበሩና:: 35ከሚቃጠለው መሥዋዕት
ጋር የሚቀርበውን የኅብረት መሥዋዕት*
ስብና የመጠጡን ቍርባን ጨምሮ የሚቃጠ
ለው መሥዋዕት እጅግ ብዙ ነበር:: በዚህ
ሁኔታም *የእግዚአብሔር* ቤት አገልግሎት
እንደገና ተደራጀ:: 36ሕዝቅያስና ሕዝቡ ነገሩ
ሁሉ እንዲህ በተፋጠነ ሁኔታ እንዲከናወን
እግዚአብሔር ስለረዳቸው ሐሴት አደረጉ::

## ሕዝቅያስ ፋሲካን ማክበሩ

30 ሕዝቅያስ የእስራኤልን *አምላክ* የእግዚ
አብሔርን ፋሲካ ለማክበር በኢየሩሳሌም
ወዳለው ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ
እንዲመጡ፣ ለመላው እስራኤልና ለይሁዳ
መልእክት ላከ፤ ለኤፍሬምና ለምናሴም ደብዳቤ
ጻፈ:: 2ንጉሡ፣ ሹማምንቱና መላው የኢየሩ
ሳሌም ጉባኤ የፋሲካውን በዓል በሁለ
ተኛው ወር ለማክበር ተስማሙ:: 3በቂ
ካህናት ራሳቸውን ስላልቀደሱና ሕዝቡም
ገና በኢየሩሳሌም ስላልተሰበሰቡ፣ በዓሉን
በወቅቱ ለማክበር አልቻሉም ነበር::
4ንጉሡና መላው ጉባኤም ዕቅዱ ትክ
ክል ሆኖ አገኙት:: 5ስለዚህ የእስራኤልን
*አምላክ* የእግዚአብሔን ፋሲካ ለማክበር ሕዝቡ
እንዲመጣ፣ ከባርሳቤህ እስከ ዳን ድረስ
ዐዋጅ እንዲነገር ወሰኑ፤ በተጻፈው መሠ
ረት በዓሉ ብዛት ባለው ሕዝብ ተከብሮ
አያውቅም ነበርና::
6መልእክተኞችም በንጉሡ ትእዛዝ፣ የንጉ
ሡንና የሹማምንቱን ደብዳቤ ይዘው ወደ
እስራኤልና ወደ ይሁዳ ሁሉ ሄዱ፤ ደብ

29፥35 ዘፍ4፥4፤ 35፥14፤ዘፀ29፥13፤ ዘሌ7፥11-21
29፥36 2ዜና35፥8
30፥1 ዘፍ41፥52፤ ዘፀ12፥11፤ ዘኍ28፥16፤1ዜና9፥1
30፥2 ዘኍ9፥10
30፥3 ዘኍ9፥6-13፤2ዜና29፥34
30፥5 መሳ20፥1
30፥7 ዘዳ28፥25፤ 1ዜና5፥25፤መዝ78፥8:57፤106፥6፤ ኢር11፥10፤ ሕዝ20፥18
30፥8 ዘፀ32፥9፤ ዘኍ25፥4፤ 2ዜና29፥10
30፥9 ዘፀ3፥21፤ 22፥27፤ዘዳ4፥31፤ 30፥2-5፤ 1ነገ8፥50፤2ዜና6፥39፤ ኢሳ1፥16 55፥7፤ኤር25፥5፤ሕዝ33፥11፤ሚክ7፥18
30፥10 2ዜና36፥16
30፥11 ቍ25፤ 2ዜና6፥37
30፥12 ኤር32፥39፤ሕዝ11፥19
30፥13 ዘኍ28፥16

ዳቤውም እንዲህ የሚል ነበር፤
"የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፤ እርሱ ወደ
ተረፋችሁት፣ ከአሦር ነገሥታትም እጅ
ወዳመለጣችሁት ወደ እናንተ እንዲመለስ፣
እናንተም የአብርሃም፣ የይስሐቅና የእስ
ራኤል *አምላክ* ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር
ተመለሱ:: 7እንደምታዩት ሁሉ መሣለቂያ
እንስኪያደርጋቸው ድረስ፣ ለአባቶቻቸው
*አምላክ* ለእግዚአብሔር እንዳልታመኑ እንደ
አባቶቻችሁና እንደ ወንድሞቻችሁ አትሁኑ::
8እንደ አባቶቻችሁም አንገተ ደንዳኖች አትሁኑ፤
*ለእግዚአብሔር* ተገዙ፤ እርሱ ለዘላለም
ወደ ቀደሰውም መቅደስ ኑ:: አስፈሪ
ቍጣው ከእናንተ እንዲመለስም፣ *እግዚአ
ብሔር* አምላካችሁን አገልግሉ:: 9እናንተ ወደ
*እግዚአብሔር* ብትመለሱ *አምላካችሁ* እግዚ
አብሔር ቸርና ርኅሩኅ ስለሆነ ወንድሞቻችሁና
ልጆቻችሁን በማረኳቸው ዘንድ ምሕረትን
ያገኛሉ፤ ወደዚህች ምድር ይመለሳሉ:: እናንተ
ወደእርሱ ብትመለሱ፣ እርሱም ፊቱን
ከእናንተ አይመልስም::
10መልእክተኞቹም በኤፍሬምና በምናሴ ምድር
ካንዱ ከተማ ወደ ሌላው ከተማ በመዘዋወር
እስከ ዛብሎን ድረስ ሄዱ፤ ሕዝቡ ግን አንቋሸ
ሻቸው፤ ተሣለቀባቸውም:: 11ሆኖም ከአሴር፣
ከምናሴና ከዛብሎን ጥቂት ሰዎች ራሳቸውን
ዝቅ አድርገው ወደ ኢየሩሳሌም መጡ::
12እንዲሁም ንጉሡና ሹማምንቱ በእግዚአብሔር
ቃል መሠረት ያዘዙትን እንዲፈጽሙ አንድ
ልብ ይሰጣቸው ዘንድ *የእግዚአብሔር* እጅ
በይሁዳ ላይ ነበር::
13በሁለተኛው ወር የቂጣን በዓል ለማክበር
እጅግ ብዙ ሕዝብ በኢየሩሳሌም ተሰበሰበ::

*35 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል::

***የሚቃጠለው መሥዋዕት እጅግ ብዙ ነበር፤*** ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን በመረቀበት ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ያሳስባል (7፥4-6):: የኅብረት መሥዋዕትን በተመለከተ ዘሌ3፤7፥11-21፤ የመጠጥ ቍርባንን በተመለከተ ዘኍ15፥1-12ይመ:: ***የእግዚአብሔር ቤት አገል ግሎት እንደገና ተደራጀ፤*** የሰሎሞንን ሥራ በተመለከተ 8፥13 ላይ ከተጻፈው ጋር ተመሳሳይ ነው::

*30፥1-27፤* በዜና መዋዕሉ ብቻ የሚገኝ ታሪክ ነው:: በኢዮስያስ ዘመን ከተደረገው ታልቅ የፋሲካ በዓል አከባበር ጋር ያነጻጽሩ (35፥1-19፤2ነገ23፥21-23):: በዚህ ጊዜም ሕዝቅያስ የበዓሉ አከባበር በሁለት መንገድ በሕጉ ከታዘዘው ዘፀ12፤ዘዳ16፥1-8 ሥርዐቱ እንዲለይ ፈቀደ፤ ይኸውም: (1)የፋሲካ በዓል በሁለተኛው ወር እንዲከበር (ቍ2) እና (2) ሥርዐተ አምልኮው የሚጠይቃቸው አንዳንድ ነገሮች እንዲቀሩ ማድረጉ ነበር (ቍ18-19)::

30፥1 ***ለመላው እስራኤልና ለይሁዳ፤*** ከ1ዜና መግቢያ "ዓላማና መሪ ሐሳብ" የሚለውን ይመ:: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በአሦር ተወሮና ተማርኮ የተደመሰሰውን የሰሜኑን መንግሥት "መላው እስራ ኤል" ሲል በዳዊት መንግሥትና በቤተመቅደሱ ጥላ ሥር እንደገና መዋቀሩን ለማሳየት ነው (ቍ5:18-19:25 ይመ)::

30፥2 ***በሁለተኛው ወር፤*** አንድ የነበረው የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ከተከፈለ በኋላ፣ ኢዮርብዓም የተቀደሰውን የዘመን አቈጣጠር በአንድ ወር በማበላለጥ የሰሜኑ መንግሥት እንዲጠቀምበት አድርጎአል (1ነገ12፥32)፤ ይህን ያደረገውም በሰሜን ያለው ሕዝብ ልቡ ከኢየሩሳሌም እንዲርቅ ለማድረግ ሊሆን ይችላል:: ሕዝቅያስ የፋሲካን በዓል በአንድ ወር በማዘግየቱ፣ ካህናቱ ራሳቸውን እንዲቀድሱ (ቍ3)፣ ሕዝቡም እንዲሰበሰብ (ቍ3: 13) በቂ ጊዜ እንዲገኝ ከማድረጉም በላይ ከሁለት መቶ ዓመት በላይ ተለያይተው የነበሩት የደቡቡና የሰሜኑ ሕዝቦች ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ ቀን እንዲያከብሩ ለማድረግ አስችሎአል:: የተለመደው የበዓል ማክበሪያ ጊዜ እንዲዘገይ መደረጉም ሕዝቅያስ "መላው እስራኤል" በበዓሉ ዕለት እንዲገኝ ያለውን በጎ ምኞት ያንጸባርቃል:: ከሰሎሞን ዘመን ወዲህ መላው የእስራኤል ሕዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ የፋሲካን በዓል በአንድነት ማክበሩ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ሕዝቅያስን፣ "ዳግማዊ ሰሎሞን" ትክክለኛ አባባል እንደሆነ አድርጎ ያቀረበውን ያጠናክራል:: የፋሲካ በዓል እንዲከበር የታዘዘው በመጀመሪያው ወር በዐሥራ አራተኛው ቀን ነው (ዘፀ 12፥2:6፤ ዘዳ16፥1-8)፤ ይሁን እንጂ በዚያ ጊዜ ቤተ መቅደሱ ስለረከሰና የማንጻቱም ሥርዐት በመከናወን ላይ ስለ ነበር (29፥3:17) በተለ መደው ጊዜ ሊከበር አልቻለም:: ከምርኮ የተመለሰው ማኅበረሰብ፣ ቤተ መቅደሱ እንደገና ተሠርቶ ከተመረቀ በኋላ የፋሲካን በዓል ስለማክበሩ ለመገንዘብ ዕዝ6፥16-22 ይመ::

30፥5 ***ብዛት ባለው፤*** ከሰሎሞን ዘመን ጋር ለማነጻጸር የገባ ሌላው ሐረግ ነው (ቍ26 ይመ):: ሕጉ በመጀመሪያ በተሰጠበት ጊዜ የፋሲካ በዓል የሚከበረው በቤተሰብ ደረጃ ነበር (ዘፀ12)፤ በኋላ ግን በአገር ዐቀፍ ደረጃ በቤተ መቅደስ የሚከበር በዓል ሆነ (ቍ8፤ዘዳ16፥1-8 ይመ)::

30፥8 ***ወደ... መቅደስ ኑ፤*** በዓመት ሦስት ጊዜ መንፈሳዊ ጕዞ እየተደረገ በቤተ መቅደሱ እንዲከበሩ ከታዘዙት ሦስት ዐበይት በዓላት ፋሲካ አንዱ ነበር (ዘኍ28፥9-29፥39 ይመ)::

30፥9 ***በማረኳቸው.... ምሕረትን ያገኛሉ፤*** ማራኪዎቻቸው "ምሕረት ያደርጉላችኋል" ተብሎ በተጓዳኙ ምንባብ ላይ (1ነገ8፥50) የተጻፈውን ዐረፍተ ነገር የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በ6፥39 ላይ በዘገበው የሰሎሞን ጸሎት ውስጥ አልጠቀሰውም፤ ዐረፍተ ነገሩ በዚህ ክፍል በሕዝቅያስ ንግግር ውስጥ መጠቀሱ ጸሓፊው ሕዝቅያስን ዳግማዊ ሰሎሞን እንደሆነ አድርጎ ማቅረቡን በድጋሚ ያሳያል (ዘሌ 26፥40-42ይመ):: ***ወደዚህችም ምድር ይመለሳል፤*** ወደ አሦር የተማረኩትም እንኳ ቢሆኑ ንስሓ የገቡት ሁሉ የመመለስ ተስፋ አላቸው::

14በኢየሩሳሌም የነበሩትን መሠዊያዎች ነቃ
ቅለው፣ የዕጣን መሠዊያዎችንም ከስፍራው
አንሥተው ወደ ቄድሮን ሸለቆ ጣሉ።
15በሁለተኛው ወር በዐሥራ አራተኛው
ቀን የፋሲካውን በግ ዐረዱ። ካህናቱና ሌዋውያኑ
አፍረው ስለ ነበር ራሳቸውን ቀደሱ፤ የሚ
ቃጠል መሥዋዕትንም ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ አመጡ። 16ከዚያም በእግዚአብሔር
ሰው በሙሴ ሕግ እንደ ታዘዘው መደበኛ
በታቸውን ያዙ። ካህናቱም ከሌዋውያኑ እጅ
የተቀበሉትን ደም ረጩ። 17ከጉባኤው መካከል
አብዛኞዎቹ ራሳቸውን ያልቀደሱ ስለ ነበሩ፣
ሌዋውያኑ በሥርዐቱ መሠረት ራሳቸውን
ላላነጹትና ጠቦቶቻቸውን *ለእግዚአብሔር* መቀደስ
ላልቻሉት ሁሉ የፋሲካውን በጎች ማረድ
ነበረባቸው። 18ምንም እንኳ ከኤፍሬም፣
ከምናሴ፣ ከይሳኮርና ከዛብሎን ከመጡት
አብዛኞዎቹ ራሳቸውን ያላነጹ ቢሆንም ከተጻፈው
ትእዛዝ ውጭ ፋሲካውን በሉ። ሕዝቅያስ ግን
እንዲህ ሲል ጸለየ፤ "ቸሩ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ይቅር
በላቸው፤ 19ምንም እንኳ በመቅደሱ ሥርዐት
መሠረት የነጹ ሆነው ባይገኙም የአባቶቻቸው
አምላክ የሆነውን እግዚአብሔር *አምላካቸውን* ለመ
ፈለግ ልባቸውን የሚያዘጋጁትን ሁሉ ይቅር
በላቸው።" 20*እግዚአብሔርም* ሕዝቅያስን ሰማው፤
ሕዝቡንም ፈወሰ።
21ሌዋውያኑና ካህናቱ *በእግዚአብሔር* የዜማ
ዕቃ ታጅበው፣ በየዕለቱ *ለእግዚአብሔር* እየዘ
መሩ[a]፣ በኢየሩሳሌም የነበሩት እስራኤላው
ያን የቂጣን በዓል በታላቅ ደስታ ለሰባት ቀን
አከበሩ፤
22ሕዝቅያስም *በእግዚአብሔር* አገልግሎት
አስተዋዮች የነበሩትን ሌዋውያን ሁሉ በን
ግግሩ አበረታታ። ሰባቱንም ቀን የተወሰነ
ላቸውን ድርሻ እየበሉና የኅብረት መሥዋዕቱ
ንም+ እያቀረቡ የአባቶቻቸውን *አምላክ* እግዚ
አብሔርን አመሰገኑ።
23ጉባዔውም ሁሉ በተከታዩ ሰባት ቀን
በዓሉን እንደገና ለማክበር ተስማሙ፣ ስለዚህ
በዓሉን ለሰባት ተጨማሪ ቀን በታላቅ ደስታ
አከበሩ። 24የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ አንድ
ሺህ ወይፈን፣ ሰባት ሺህ በግና ፍየል ለጉ
ባኤው ሰጠ፤ ሹማምንቱም እንደዚሁ አንድ
ሺህ ወይፈን፣ ዐሥር ሺህ በግና ፍየል ሰጡ።
እጅግ ብዙ ካህናትም ራሳቸውን ቀደሱ።
25መላው የይሁዳ ጉባኤ፣ ካህናቱና ሌዋውያኑ፣
ከእስራኤል የተሰበሰበው ጉባኤ ሁሉ፣ እንዲ
ሁም ከእስራኤል የመጡ መጻተኞችና በይሁዳ
የሚኖሩ መጻተኞች ደስ አላቸው። 26ከእስ
ራኤል ንጉሥ ከዳዊት ልጅ ከሰሎሞን ጊዜ
አንሥቶ በኢየሩሳሌም እንዲህ ያለ በዓል
ተደርጎ ስለማያውቅ፣ በኢየሩሳሌም ታላቅ
ደስታ ሆነ። 27ከዚያም ካህናቱና ሌዋውያኑ
ተነሥተው ሕዝቡን ባረኩ፤ እግዚአብሔርም
ሰማቸው፤ ጸሎታቸውም ወደ ሰማይ ወደ
ቅዱሱ ማደሪያው ደረሰ።

**31** ይህ ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ፣ በዚያ
የነበሩት እስራኤላውያን ወደ ይሁዳ
ከተሞች ወጥተው፣ የማምለኪያ ድንጋዮችን
ሰባበሩ፤ የአሼራ ምስል ዐምዶች ቈረጡ፤
እንዲሁም በመላው ይሁዳና ብንያም፣ በኤፍ
ሬምና በምናሴ የነበሩትን የኰረብታ መስገ
ጃዎችና መሠዊያዎች አጠፉ፤ እስራኤላውያን
እነዚህን ሁሉ ካጠፉ በኋላ ወደየከተሞቻቸውና
ወደ የርስታቸው ተመለሱ።

### ለካህናት የተደረገ ስጦታ

31፥20-21 ተጓ ምብ —1ዜና18፥5-7

2ሕዝቅያስ ካህናቱና ሌዋውያኑ የሚቃጠል
መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት* እንዲ
ያቀርቡ፣ እንዲያገለግሉና እንዲያመሰግኑ እንዲ
ሁም *በእግዚአብሔር* ማደሪያ ደጆች ውዳ
ሴውን እንዲዘምሩ፣ ካህናትንም ሆኑ ሌዋ
ውያንን እያንዳንዳቸውን እንደየተግባራቸው
በየክፍሉ መደባቸው። 3*በእግዚአብሔር* ሕግ
እንደተጻፈው ንጉሡ ጠዋትና ማታ እንደዚ
ሁም በየሰንበቱ፣ በየወሩ መባቻውና በተወሰኑ

30፥14 2ሳሙ15፥23፤ 2ዜና28፥24
30፥15 2ዜና29፥34
30፥16 2ዜና 35፥10
30፥17 2ዜና35፥11፤ ዕዝ6፥20
30፥18 ዘፀ12፥43-49፤ዘኍ9፥6-10
30፥20 2ዜና6፥20፤7፥14፤ሚል4፥2፤ ያዕ5፥16
30፥21 ዘፀ12፥15፡17፤13፥6
30፥23 2ዜና7፥9
30፥24 1ነገ8፥5፤ 2ዜና35፥7፤ ዕዝ6፥17፤8፥35
30፥25 ቍ11
30፥26 2ዜና7፥8
30፥27 ዘፀ39፥43
31፥1 2ነገ18፥4፤ 2ዜና32፥12፤ ኢሳ36፥7
31፥2 1ዜና15፥2፤ 23፥28-32፤24፥1፤ 2ዜና29፥9፤መዝ7፥1 7፤9፥2፤47፥6፤71፥22
31፥3 ዘኍ28፥1-29፥40፤1ዜና29፥3፤2 ዜና35፥7፤ሕዝ45፥17

[a]21 ወይም *ሌዋውያንና ካህናቱ በእግዚአብሔር የዜማ ዕቃ ታጅበው በየዕለቱ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር*
+ 22 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል።
* 2 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል።

30፥14 *ወደ ቄድሮን ሸለቆ ጣሉ፤* 29፥16 እና ማብ ይመ።
30፥15 *ካህናቱና ሌዋውያኑ… ራሳቸውን ቀደሱ፤* ቀደም ሲል በካህናቱ ላይ የተሰነዘረው ወቀሳ (ቍ3፤29፥34)፣ እዚህ ላይ ሌዋውያኑንም ይጨምራል። ይህም ከምርኮ የተመለሰው ማኅበረ ሰብ ካህናትና ሌዋውያን ታማኞች መሆን እንደሚገባቸው ለመምከር ነው።
30፥17፤ *ሌዋውያኑ…. የፋሲካውን በጎች ማረድ ነበረባቸው፤* (ዘፀ12፥6፤ ዘዳ16፥6 ይመ)። በሕጉ መሠረት የፋሲካውን መሥዋዕት ማረድ የነበረበት የቤተ ሰቡ አባ ወራ ነው። ሌዋውያኑ በጎቹን እንዲያርዱ የተደረገበት ምክንያት በቅርቡ ከሰሜኑ መንግሥት የመጡና በሥርዐቱ መሠረት ያልነጹ ሰዎች በዚያ ስለነበሩ ሳይሆን አይቀርም፤ ከ11፥55 ጋር ያነጻጽሩ።
*30፥18-19፤* ማመንና መታዘዝ ከሥርዐተ አምልኮ ሁሉ ይልቅ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነገር ነው (ማር7፡1-23፤ ዮሐ7፥22-23፤9፥14-16ይመ)።
*30፥20፤* ለሕዝቅያስ ጸሎት የተሰጠው መልስ ለሰሎሞን ጸሎት የተሰጠውን መልስ የሚያሳስብ ነው (7፥14)።
30፥23 *ለሰባት ተጨማሪ ቀን፤* በዓሉ የተከበረው ለሁለት ሳምንት ነው፤ ይህም የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ምረቃ ከወሰደው ጊዜ ጋር ተመሣሣይ ነበር (7፥8-9)።
30፥26 *ከሰሎሞን ጊዜ አንሥቶ፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት የሰሎሞንን ዘመነ መንግሥት ፈለግ የተከተለ መሆኑን ለማሳየት የተጠቀመበት ሐረግ ነው።
30፥27 *ጸሎታቸውም ወደ ሰማይ ወደ ቅዱሱ ማደሪያው ደረሰ፤* ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሲመርቅ የጸለየውን የሚያስተጋባ ነው (6፥21፡30፡33፡39)።
*31፥1-21፤* ከ2ነገ18፥4 ጋር ከሚመሳሰለው ከቍ1 በስተቀር፣ ይህ ምዕራፍ የሚገኘው በዚሁ መጽሐፍ ብቻ ነው፤ እዚህ ላይ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ስለ ሌዋውያኑና ስለ ቤተ መቅደሱ ያለውን ከፍተኛ ግምት መረዳት ይቻላል። በኑሮ ረገድ ለሌዋውያኑ ሊደረግ ስለሚገባው ርዳታ (ቍ4) ሕዝቅያስ ትኩረት ሰጥቶ የሚያሳስበው የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ለጻፈላቸው ከምርኮ ለተመለሱት ወገኖች ሳይሆን አይቀርም።
31፥1፤ *እስራኤላውያን… እስራኤላውያን፤* በቍሙ "እስራ ኤል ሁሉ" እንደ ማለት ነው፤ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ "እስራኤል ሁሉ" በሕዝቅያስ አመራር አንድ እንዲሆኑ ያለውን ፍላጎት በድጋሚ የሚያሳይ ነው። *የማምለኪያ ድንጋዮችን፤* የ1ነገ14፥23 ማብ ይመ። *የአሼራ ምስል ዐምዶች ቈረጡ፤* የ14፥3 አግራጭ ተርጉም ይመ።
*31፥2፤* በ8፥14 ላይ የሚገኘውን የሚያስተጋባ ነው። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ እዚህም ላይ የሚያንጸባርቀው ሕዝቅያስ "ዳግማዊ ሰሎሞን" መሆኑን ነው (የ29፥7፡18 ማብ ይመ)።
*31፡3፤ ንጉሡ…. ከራሱ ንብረት ሰጠ፤* ንጉሡ ከግል ንብረቱ መስጠቱ፣ በዳዊት ዘመን እንደተደረገው ዓይነት ሕዝቡ በልግሥና

በዓላት፣ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ከራሱ
ንብረት ሰጠ። 4ካህናቱና ሌዋውያኑም ሙሉ
ጊዜአቸውን *ለእግዚአብሔር* ሕግ አገልግሎት
ማዋል ይችሉ ዘንድ፣ በኢየሩሳሌም የሚኖ
ረው ሕዝብ ተገቢውን ድርሻ እንዲሰጣቸው
አዘዘ። 5ትእዛዙ እንደ ወጣ እስራኤላውያን
ወዲያውኑ የእህሉንና የአዲሱን ወይን ጠጅ፣
የዘይቱንና የማሩን እንዲሁም የዕርሻውን
ፍሬ ሁሉ በኩራት በልግሥና ሰጡ፤ ካላቸው
ከማንኛውም ነገር ሁሉ ላይ እጅግ ብዙ የሆነ
ዐሥራት አውጥተው አመጡ። 6በይሁዳ ከተ
ሞች ይኖሩ የነበሩት የእስራኤልና የይሁዳ
ሰዎችም ከከብቶቻቸው፣ ከበግና ከፍየል መን
ጎቻቸውና *ለአምላካቸው* ለእግዚአብሔር ከለ
ዩአቸው የተቀደሱ ነገሮች ዐሥራት አውጥተው
አመጡ ፤ ከመሩትም። 7ይህንም በሦስተኛው
ወር ጀምረው፣ በሰባተኛው ወር አጠናቀቁ።
8ሕዝቅያስና ሹማምቱም መጥተው ክምሩን ባዩ
ጊዜ *እግዚአብሔርን* አመሰገኑ፤ ሕዝቡን እስ
ራኤልንም ባረኩ።

9ሕዝቅያስም ካህናቱንና ሌዋውያኑን ስለ
ክምሩ ጠየቃቸው፤ 10ከሳዶቅ ቤተሰብ የሆነው
ሊቀ ካህናቱ ዓዛርያስም፣ "ሕዝቡ ስጦታውን
ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ማምጣት
ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ በቂ ምግብ አግኝ
ተናል፤ ብዙም ተርፎናል፤ *እግዚአብሔር* ሕዝ
ቡን ስለባረከም ይህን ያህል ብዛት ያለው
ሊተርፍ ችሎአል" አለ።

11ሕዝቅያስም *በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ
ውስጥ ጎተራ እንዲያዘጋጅ አዘዛቸው፤ እነ
ርሱም አዘጋጁ። 12ከዚያም ስጦታውን፣ ዐሥራ
ቱንና የተቀደሱ ስጦታዎቹን በታማኝነት
አምጥተው አስገቡ። ሌዋዊው ኮናንያ የእነ
ዚሁ ዕቃዎች ኀላፊ ሲሆን ወንድሙ ስሜኢ
ደግሞ በማዕረግ ሁለተኛ ነበር። 13ይሒኤል፣
ዓዛዝያ፣ ናሖት፣ አሣሄል፣ ይሬሞት፣ ዮዛባት፣
ኤሊኤል፣ ስማኪያ፣ መሐትና በናያስ በንጉሡ
ሕዝቅያስና በእግዚአብሔር ቤት ኀላፊ በዓዛርያስ
ተሹመው በኮናንያና በወንድሙ በስሜኢ
ሥር ሆነው ተቈጣጣሪዎች ነበሩ።

14የምሥራቁ በር ጠባቂ የሆነው የሌዋዊው
የይምና ልጅ፣ ቆሬ ደግሞ በበጎ ፈቃድ፣
ለእግዚአብሔር በቀረበው ስጦታ ላይ *የእግዚ
አብሔርን* መባና የተቀደሱትንም ነገሮች

31፥4 ዘኍ18፥8፤ ዘዳ18፥8፤ነህ13፥10
31፥5 ዘኍ18፥12፡ 24፤ዘዳ12፥17፤ነህ13፥ 12፤ሕዝ44፥30
31፥6 ዘሌ27፥30 ፤ ሩት3፥7፤ ነህ13፥10-12
31፥7 ዘፀ23፥16
31፥8 መዝ144፥ 13-15
31፥10 ዘፀ36፥5፤ 2ሳሙ8፥17፤ ሕዝ44፥30፤ ሚል3፥10-12
31፥12 2ዜና35፥9
31፥13 2ዜና35፥9
31፥15 ኢሱ21፥9- 19፤2ዜና29፥12
31፥16 1ዜና23፥3
31፥19 ዘኍ35፥2-5
31፥20 2ነገ20፥3
31፥21 ዘዳ29፥9
32፥1 ኢሳ36፥1፤ 37፥9፡17፡37

ለማከፋፈል፣ ኀላፊ ነበረ። 15ዔድን፣ ሚንያ
ሚን፣ ኢያሱ፣ ሸማያ፣ አማርያና ሴኬንያ በካህ
ናቱ ከተሞች ተገኝተው፣ ለካህናት ወገኖቻ
ቸው ለታላላቆቹም ሆነ ለታናናሾቹ፣ እን
ደየምድባቸው፣ በማከፋፈሉ ረገድ በታማ
ኝነት ረዱት።

16በተጨማሪም፣ ስማቸው በትውልድ መዝገቡ
ውስጥ የነበረና የየዕለቱ ልዩ ልዩ ተግባራ
ቸውን እንደየኀላፊነታቸው መጠንና እንደ
የምድብ ሥራቸው ለማከናወን ወደ *እግዚ
አብሔር* ቤተ መቅደስ መግባት ለሚችሉት፣
ዕድሜአቸው ሦስት ዓመትና ከዚያም በላይ
ለሆናቸው ወንዶች ልጆች እንደዚሁ አከፋ
ፈሉ። 17በትውልድ መዝገብ በየቤተሰባቸው
ተቈጥረው ለገቡት ካህናት፣ ዕድሜአቸው
ሃያ ዓመትና ከዚያም በላይ ለሆናቸው ሌዋ
ውያን እንደየኀላፊነታቸው መጠንና እንደየ
ምድብ ሥራቸው አካፈሏቸው። 18በዚህ የት
ውልድ መዝገብ ላይ የተዘረዘሩትን መላውን
የማኅበረሰቡን ሕፃናት፣ ሚስቶችን፣ ወንዶችና
ሴቶች ልጆች ጨመሯቸው፤ ራሳቸውን በመ
ቀደስ ታማኞች ነበሩና።

19በከተሞቻቸው ዙሪያ ባሉት የዕርሻ
ቦታዎች፣ ወይም በሌሎች ከተሞች ሁሉ
ለሚኖሩት ለካህናቱ ለአሮን ዘሮች፣
በመካከላቸው ላሉት ወንዶችና በሌዋውያን
የትውልድ መዝገብ ለተመዘገቡት ሁሉ
እንዲያከፋፍሉ በየስማቸው የተጻፉ ሰዎች
ነበሩ።

20ሕዝቅያስ በአምላኩ *በእግዚአብሔር* ፊት
መልካም፣ ቅንና ታማኝ ሆኖ በመገኘት በመላው
ይሁዳ የፈጸመው ተግባር ይህ ነው። 21የእግዚ
አብሔርን ቤተ መቅደስ በማገልገልም ሆነ፣ ለእግዚ
አብሔር ሕግና ትእዛዝ በመገዛት አንጻር ያደ
ረገውን ሁሉ በፍጹም ልቡ አምላኩን በመፈለግ
አከናወነ፤ ተሳካለትም።

## ሰናክሬም በኢየሩሳሌም ላይ ዛተ

32፥9-19ተጓ ምብ —2ዜና18፥17-35፤ኢሳ36፥2-20
32፥20-21ተጓ ምብ -2ዜና19፥35፤ኢሳ37፥36-38

32 ሕዝቅያስ እንዲህ ባለ ታማኝነት
ነገሮችን ሁሉ ካከናወነ በኋላ፣ የአሦር
ንጉሥ ሰናክሬም መጥቶ ይሁዳን ወረረ። ድል
አድርጎ የራሱ ሊያደርጋቸው በማሰብም የተመ
ሸጉትን ከተሞች ከበበ።

---

እንዲሰጥ አነሣሥቶታል (1ዜና29፥3-9)።

*31፥5-6፤* ዘዳ12፥5-19፤14፤22-27 ይመ። እህል አዲስ የወይን ጠጅና ዘይት ወደ ቤተ መቅደስ ማምጣት እንዳለባቸው ታዝዋል (ዘዳ12፥17)። ከሩቅ የሚመጡት ግን መገንዘባቸው ለቍርባን የሚሆነውን ነገር ከዚያው መግዛት ይችላሉ (ዘዳ14፥24) ከቀንድ ከብቶች፣ ከበጉና ከፍየሉ የሚወጣውን ዐሥራት ማምጣት የሚችሉት በይሁዳ የሚኖሩት ብቻ ናቸው፤ ይህ ደግሞ ከሩቅ ለሚመጡት እጅግ አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው ግልጽ ነው። ከምርኮ የተመለሰው ማኅበረሰብ ከምድሩ ፍሬም ሆነ ከሌሎች ነገሮች ስለሚወጣው ዐሥራት፣ በኩራትና ልዩ ልዩ ቍርባን ለመስጠት የገባውን ቃል በተመለከተ ነህ10፥35-39 ይመ፤ ይህ ቃል ስላለመከበሩ ነህ13፥10-13፤ ሚኪ3፥8-10 ይመ።

31፥7 *በሦስተኛው ወር፤* ወቅቱ በግንቦትና በሰኔ መካከል የሚገኝ ሲሆን፣ በዓለ አምሳ የሚከበርበትና እህል የሚሰበሰብበት ጊዜ ነው። *በሰባተኛው ወር፤* በመስከረምና በጥቅምት መካከል የሚገኝ ጊዜ ነው። ይህም የዳስ በዓል የሚከበርበት፣ አዝመራ የሚሰበሰብበትና፣ ወይን የሚቈረጥበት ወቅት ነው (ዘፀ23፥16 ይመ)።

*31፥16 ሦስት ዓመት፤* ምንም እንኳ ከዚህ ክፍል ጋር የማይስማሙ ትርጕሞች ወይም ቅጆች ባይኖሩም መጽሐፉን የገለበጠው ሰው ሠላሳ ዓመት የሚለውን ሦስት ዓመት ብሎ በስሕተት ሳይጽፍ እንዳልቀረ ይገመታል፤ በቤተ መቅደስ ለማገልገል መነሻው ዕድሜ ሠላሳ ዓመት ነበር (1 ዜና23፥3)።

*31፥20-21፤* ማንም ሰው የእጁን ወዲያውኑ እንደሚያገኝ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ አጽንዖት የሰጠበት ሌላኛው ክፍል ነው፤ አለመታዘዝ የአጸፋ ቅጣት እንደሚያስከትል ብቻ ሳይሆን መታዘዝና እግዚአብሔርን ማገልገል በረከት እንደሚያስገኝ የሚያመለክት ነው።

*32፥1-23፤* የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ያደረገው ወረራ ከዚህ ክፍል ይልቅ በሁለተኛ ነገሥትና በኢሳይያስ ላይ በስፋት ተጽፎአል (የ29፥1-32፥33)።

*32፥1፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ወረራው የተካሄደበትን ዘመን አልገለጸም (701 ዓ.ቅ.ክ የሕዝቅያስ ዐሥራ አራተኛው ዘመነ መንግሥት ነበር (2ነገ 18፥13፤ ኢሳ 36፥1 ይመ)።

2ሕዝቅያስም ሰናክሬም መምጣቱንና ኢየሩ
ሳሌምንም ለመውጋት ማሰቡን ባወቀ ጊዜ፣
3ከከተማዪቱ ውጭ ያሉት የውሃ ምንጮች
እንዲዘጉ ከሹማምንቱና ከጦር አለቆቹ ጋር
ተማከረ፤ እነርሱም ረዱት። 4ብዙ ሰዎችም
ተሰብስበው "የአሦር ነገሥታት[ን] መጥተው
ለምን ብዙ ውሃ ያግኙ?" በማለት ምንጮቹን
ሁሉና በምድር ውስጥ ለውስጥ ይተላለፍ
የነበረውን ውሃ ዘጉ። 5ከዚህ በኋላም
ንጉሡ ጠንክሮ በመሥራት፣ ከቅጥሩ የፈራ
ረሱትን ሁሉ ጠገነ፤ በላዩም ማማ ሠራበት፤
በውጭ በኩልም ሌላ ቅጥር በመገንባት የዳዊትን
ከተማ ድጋፍ እርከን አጠናከረ፤ እንደዚሁም
ብዙ የጦር መሣሪያዎችንና ጋሻዎችን ሠራ።
6የጦር መኮንኖችንም በሕዝቡ ላይ ሾሞ
በከተማዪቱ በር አደባባይ ላይ በፊቱ ከሰበሰበ
በኋላ እንዲህ ሲል አበረታታቸው፤ 7"በርቱ፤
ጠንክሩ፤ ከእኛ ጋር ያለው ከእርሱ ጋር ካለው
ስለሚበልጥ፣ የአሦርን ንጉሥና አብሮት ያለውን
ብዙ ሰራዊት አትፍሩ፤ አትደንግጡም።
8ከእነርሱ ጋር ያለው የሥጋ ክንድ ሲሆን፣
ከእኛ ጋር ያለው ግን የሚረዳንና ጦላታ
ችንን የሚዋጋልን አምላካችን እግዚአብሔር
ነው።" ሕዝቡም የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ
በተናገረው ቃል ተበረታታ።
9ከዚህ በኋላ ሰናክሬም ከሰራዊቱ ሁሉ
ጋር ለኪሶን ከቦ ሳለ፣ የሚከተለውን መልእክት
በጦር መኮንኖቹ አማካይነት፣ ለሕዝቅያስና
ከእርሱ ጋር በኢየሩሳሌም ለነበሩት ለይሁዳ
ሕዝብ ላከ፤
10"የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም የሚለው ይህ
ነው፤ በተከበበችው በኢየሩሳሌም እስከዚህ
የቈያችሁት በማን ተማምናችሁ ነው?
11ሕዝቅያስ፣ 'አምላካችን እግዚአብሔር ከአሦር
ንጉሥ እጅ ያድነናል' ማለቱስ በራብና በጥ
ማት እንድትሞቱ ሊያስታችሁ አይደለምን?
12ለይሁዳና ለኢየሩሳሌም፣ 'በአንድ መሠዊያ
ፊት ስገዱ፤ በላዩም መሥዋዕት አቃጥሉ'
በማለት የራሱን አምላክ የኰረብታ መስገጃ
ስፍራዎችንና መሠዊያዎችን ያስወገደስ
ሕዝቅያስ አይደለምን?
13"እኔና አባቶቼ በሌሎች አገሮች ሕዝቦች
ሁሉ ላይ ያደረግነውን አታውቁምን? ታዲያ
የእነዚያ መንግሥታት አማልክት ምድራ
ቸውን ከእጄ ለማዳን ችለዋልን? 14አባቶቼ
ካጠፏቸው ከእነዚህ የመንግሥታት አማል
ክት ሁሉ፣ ሕዝቡን ከእጄ ሊያድን የቻለ
ከእነዚህ አምላክ የትኛው ነው? ታዲያ
አምላካችሁ እንዴት ከእጄ ሊያድናችሁ
ይችላል? 15አሁንም ሕዝቅያስ በዚህ ዐይነት
አያታልላችሁ፤ አያስታችሁም። የየትኛውም
አገር ሕዝብ ወይም መንግሥት አምላክ
ሕዝቡን ከእጄ ወይም ከአባቶቼ እጅ መታደግ
የቻለ ስለሌለ አትመኑት። የእናንተ አምላክማ
ከእጄ ያድናችሁ ዘንድ ምንኛ ያንስ!"
16የሰናክሬም ሹማምንትም በእግዚአብሔር
አምላክና በባሪያው በሕዝቅያስ ላይ ከዚህ የከፋ
ብዙ ነገር ተናገሩ። 17ንጉሡም እንደዚሁ
የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን በመሳደብ፣
"የሌሎቹ አገሮች ሕዝቦች አማልክት፣ ከእጄ
እንዳልታደጉ ሁሉ፣ የሕዝቅያስም አምላክ
ሕዝቡን ከእጄ ሊታደግ አይችልም" ሲል በእ
ርሱ ላይ ደብዳቤ ጻፈ። 18ከዚያም በማስደን
ገጥና በማስፈራራት ከተማዪቱን ለመያዝ
ሲሉ በቅጥሩ ላይ ወደተቀመጠው ወደ ኢየሩ
ሳሌም ሕዝብ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በዕ
ብራይስጥ ቋንቋ ጮኹ፤ 19የሰው እጅ በሠራ
ቸው በሌሎች የምድር አሕዛብ አማልክት ላይ
እንደ ተናገሩት ሁሉ፣ በኢየሩሳሌም አምላክ
ላይም ተናገሩ።
20ንጉሥ ሕዝቅያስና የአሞጽ ልጅ ነቢዩ
ኢሳይያስም ስለዚህ ጒዳይ በጸሎት ወደ ሰማይ
ጮኹ። 21እግዚአብሔርም መልአክ ልኮ በአሦር
ንጉሥ ሰፈር ተዋጊዎችን፣ መሪዎችንና የጦር
መኮንኖችን እንዲያጠፋቸው አደረገ። ስለዚህ
ንጉሡ በውርደት ወደ ገዛ አገሩ ተመለሰ።
ወደ አምላኩ ቤተ ጣዖት እንደገባም፣ የገዛ
ወንዶች ልጆቹ በሰይፍ ገደሉት።
22እግዚአብሔርም ሕዝቅያስንና የኢየሩ
ሳሌምን ሕዝብ ከአሦር ንጉሥ ከሰናክሬምና
ከሌሎችም እጅ ሁሉ አዳናቸው፤ በዙሪያቸው
ካሉትም ሁሉ ጠበቃቸው[a]፤ 23ብዙዎችም ለእግ
ዚአብሔር መባ ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፤
ለይሁዳ ንጉሥ ለሕዝቅያስም ውድ የሆኑ
ገጸ በረከቶች አመጡለት፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም

[a]4 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስቱ ትርጒም ግን ንጉሥ ይላል።
[a]22 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል የሰብዓ ሊቃናት የቩልጌት ቅጆች ግን አሳረፋቸው ይላል።

32፥2 ኢሳ22፥7፤ ኤር1፥15
32፥4 2ነገ18፥17፤ ኢሳ22፥9፡11፤ናሆ 3፥14
32፥5 1ዜና11፥8፤ ኢሳ22፥8፡10
32፥7 ዘኍ14፥9፤ ዘዳ31፥6፤2ነገ6፥16፤2 ዜና20፥15
32፥8 ዘዳ3፥22፤1 ሳሙ17፥45፤1ዜና5፥ 22፤ኢዮ40፥9፤ መዝ20፥7፤ ኢሳ28፥6፤52፥10 ኤር17፥5፤32፥21
32፥9 ኢሱ10፥3፡ 31
32፥10 ሕዝ29፥16
32፥11 ኢሳ37፥10
32፥12 2ዜና31፥1
32፥13 ቀ፥15
2፥15 ዘፀ5፥2፤ኢ ሳ37፥10፤ዳን3፥15
32፥17 2ነገ19፥ 12፤ መዝ74፥22፤ ኢሳ37፥4፡14፡17
32፥19 መዝ11 5፥4- 8፤ኢሳ2፥8፤17፥8፤ 37፥19፤ኤር1፥16
32፥20 ኢሳ1፥15፤ 37፥15
32፥21 ዘፍ19፥13፤ 2ነገ19፥7፤ኢሳ37፥7፡ 38፤ኤር41፥2
32፥23 1ሳሙ10፥ 27፤2ዜና9፥24፤ መዝ68፥18፡29፤76፥ 11፤ኢሳ16፥1፤ 18፥7፤ 45፥14፤ ሶፎ3፥10፤ ዘካ14፥ 16-17

*32፥2-8፤* በዜና መዋዕሉ ብቻ የሚገኝ ነው፤ ይሁን እንጂ ወረራ ለማድረግ በሚፈለግበት ጊዜ የሚደረገውን የተለመደ ዝግጅት ያመለክታል።

*32፥3-4* ቍ30 ይመ።

*32፥9፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በ2ነገ18፥14-16 እንደ ተጻፈው በመካከላቸው ሰላም እንዲመሠረት ለመለማመጥ የቤተ መቅደሱን ሀብት ጒቦ አድርጎ ለሰናክሬም መላኩን በዝምታ አልፎታል፤ ይህን ያደረገውም ለሕዝቅያስ ካለው ከፍተኛ አክብሮት የተነሣ ነው እንዲሁም (በ2ነገ18፥17-18 ያለውን ክፍል ሳይጠቅስ አልፎአል።

*32፥10፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በ2ነገ18፥20-21 (እንዲሁም በኢሳ36፥5-6) ላይ የአሦር ሰራዊት አዛዥ፣ ሕዝቅያስና የኢየሩ ሳሌም ከተማ ነዋሪዎች ግብፅንና ፈርዖንን በመተማመናቸው እያንቋሸሸና እያናናቀ የተናገረውን አልጻፈም። ይህም ጸሓፊው ከውጭ ነገሥታት ጋር የጦር ስምምነት ማድርግን በሚመለከት ያለው ግንዛቤ በትምህርተ መለኮት የተደገፈ መሆኑን ያሳያል (የ16፥2-9 ማብ ይመ)። በ2ነገ 18፥23-27 እንዲሁም በኢሳ36፥8-12 ላይ የሚገኘውንና ግብፅ ጣልቃ እንድትገባ የቲርሐቅን ድንገተኛ ወረራ በተመለከተ (2ነገ19፥9 ይመ) በድጋሚ ተስፋ መደረጉን የሚያመለክተውን ክፍል ሳይጠቅስ ማለፉም በተመሳሳይ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ።

32፥16 *ከዚህ የከፋ ብዙ ነገር ተናገሩ፤* ጸሓፊው ተደራ ስያኑ የአሦርን ዛቻና ማስፈራራት በተመለከተ በመጽሐፈ ነገሥትና በኢሳይያስ በሰፈው የተጻፈውን እንደሚያውቁት ይገምታል።

32፥18፤ *በዕብራይስጥ ቋንቋ ጮኹ፤* ታሪኩን በሚገባ እንደሚያውቅ ይጠቁማል (2ነገ18፥26-28፤ኢሳ36፥11-13)።

*32፥20፤* የሕዝቅያስና የኢሳይያስ ጸሎት በ2ነገ19፥1-34 (እና በኢሳ37፥1-35) ላይ በስፋት የተዘገበውን ታሪክ በአጭሩ ያቀርባል።

*32፥21፤* 2ነገ19፥35-37፤ኢሳ37፥36-38 ይመ። የዜና መዋዕሉ መጽሐፍና ተጓዳኝ ምንባቡ ሰናክሬም ይሁዳን የወረረው በ710 ዓ.ቅ.ክ በልጆቹ እጅ የተገደለው ደግሞ በ681 ዓ.ቅ.ክ እንደሆነ ተርከዋል።

32፥23 *በአሕዛብ ሁሉ ፊት ከፍ ከፍ አለ፤* ሕዝቅያስ ከሰሎሞን ጋር የሚያነጻጽር ሌላው ክፍል ነው (9፥23-24ይመ)።

በአሕዛብ ሁሉ ፊት ከፍ ከፍ አለ::

**የሕዝቅያስ ዕብሪት፣ ያከናወናቸው ተግባሮ ችና ሞቱ**

32፥24-33 ተጓ ምብ —2ዜና20፥1-21፤ኢሳ37፥21-38፤38፥1-8

24በዚያ ጊዜ ሕዝቅያስ ታሞ ሊሞት ተቃ
ርቦ ነበር፤ ወደ *እግዚአብሔርም* ጸለየ፤
እርሱም መለሰለት፤ ምልክትም ሰጠው::
25የሕዝቅያስ ልብ ግን ታበየ እንጂ ስለ ተደረ
ገለት በጎ ነገር ተገቢ ምላሽ አልሰጠም፤ በዚህ
ምክንያት *የእግዚአብሔር* ቊጣ በእርሱ፣ በይሁዳና
በኢየሩሳሌም ላይ ወረደ:: 26ይሁን እንጂ ሕዝ
ቅያስና የኢየሩሳሌም ሕዝብ ስለ ልባቸው ትዕ
ቢት ራሳቸውን አዋረዱ፤ ስለዚህ *የእግዚአብሔር*
ቊጣ በዘመነ መንግሥቱ አልመጣባቸውም::
27ሕዝቅያስ እጅግ ብዙ ሀብትና ክብር
ነበረው፤ ከዚህ የተነሣም ለብሩ፣ ለወርቁ፣
ለከበሩት ዕንቊዎቹ፣ ለቅመማ ቅመሞቹ፣
ለጋሻዎቹና ለተለያዩ ውድ ዕቃዎቹ ሁሉ
ግምጃ ቤቶችን ሠራ:: 28እንደዚሁም ለእህሉ፣
ለወይን ጠጁና ለዘይቱ ማከማቻ የሚሆኑ
ግምጃ ቤቶች ለተለያዩ እንስሳት በረት ለበግና
ለፍየል መንጋም በረት ሠራ:: 29እግዚአብሔር
ታላቅ ብልጽግና ስለ ሰጠው፤ ብዙ የበግና
የፍየል፣ የእንስሳትም መንጋ ሰበሰበ፤ መን
ደሮችንም ሠራ::
30የላይኛውን የግዮንን ምንጭ መውጫ
ገድቦ፣ ውሃውን በቦይ ቊልቊል ወደ ምዕራቡ
የዳዊት ከተማ እንዲወርድ ያደረገም ይኸው
ሕዝቅያስ ነበር፤ ሥራውም ሁሉ ተከናወነለ
ት:: 31ነገር ግን በምድሪቱ ላይ ስለ ተፈ
ጸመው ታምራዊ ምልክት እንዲጠይቁት፣
የባቢሎን ገዦች መልእክተኞችን በላኩ ጊዜ፣
እግዚአብሔር ሊፈትነውና በልቡ ያለውን ሁሉ
ሊያውቅ ስለፈለገ ተወው::
32በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት የተከና
ወነው ሌላው ሥራና ቸርነቱ በአሞጽ ልጅ
በነቢዩ በኢሳይያስ ራእይ፣ በይሁዳና በእስራ
ኤል ነገሥታት መጽሐፍ ተጽፎአል:: 33ሕዝ
ቅያስም እንደ አባቶቹ ሁሉ አንቀላፋ፤ የዳዊት
ዘሮች መካነ መቃብር በሆነው ኰረብታም
ተቀበረ:: በሞተም ጊዜ ይሁዳ ሁሉና የኢየሩ
ሳሌም ሕዝብ በሙሉ አከበሩት:: ልጁ ምና
ሴም በእርሱ ፈንታ ነገሠ::

**የይሁዳ ንጉሥ ምናሴ**

33፥1-10 ተጓ ምብ —2ዜና21፥1-10
33፥18-20 ተጓ ምብ 2ዜና21፥17-18

33 ምናሴ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ዐሥራ
ሁለት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም
ተቀምጦም አምሳ አምስት ዓመት ገዛ:: 2*እግዚ
አብሔር* ከእስራኤላውያን ፊት አሳዶ ያስ
ወጣቸውን ሕዝቦች አስጸያፊ ልማድ በመ
ከተልም *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ድርጊት
ፈጸመ:: 3አባቱ ሕዝቅያስ ያጠፋቸውን የኰረብታ
መስገጃ ስፍራዎች መልሶ ሠራ፤ ለበአሊም
መሠዊያዎችን አቆመ፤ የአሼራንም ዐምዶች
ሠራ፤ ለሰማይ ከዋክብት ሰራዊትም ሰገደ፤
አመለካቸውም:: 4*እግዚአብሔር*፣ "ስሜ ለዘላለም
በኢየሩሳሌም ይኖራል" ባለበት *በእግዚአብሔር*
ቤተ መቀደስ መሠዊያዎችን ሠራ:: 5በሁለቱም
የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አደባባዮች
ላይ፣ ለሁሉም የሰማይ ከዋክብት ሰራዊት
መሠዊያዎችን ሠራ:: 6በሄኖም ልጅ ሸለቆ ወን
ዶች ልጆቹን በእሳት ሠዋ[†]፤ አስማት፣ መተ
ትና ጥንቈላ አደረገ፤ ሙታን ጠሪዎችንና መና
ፍስት ሳቢዎችን ጠየቀ:: ለቊጣ ያነሣሣው
ዘንድ *በእግዚአብሔር* ፊት እጅግ ክፉ ነገር አደረገ::
7ያበጀውን የተጠረበ ምስል ወስዶም በእግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ አኖረ፤ ስለዚህም ቤተ
መቅደስ እግዚአብሔር ለዳዊትና ለልጁ ለሰሎሞን
እንዲህ ብሎ ነበር፤ "በዚህ ቤተ መቅደስና
ከእስራኤል ነገድ ሁሉ በመረጥኋት በኢየሩ
ሳሌም ስሜን ለዘላለም አኖራለሁ፤ 8በሙሴ
አማካይነት ያዘዝኋቸውን ሕግጋቴን፣ ደንቦቼንና
ሥርዓቶቼን ሁሉ በጥንቃቄ ይፈጽሙ እንጂ፣
ለቀድሞ አባቶቻችሁ ከሰጠኋቸው ምድር

[†]6 *ወይም ወንዶች ልጆቹን ገደለ*

32፥24 ቊ31
32፥25 2ነገ 14፥10፤ 2ዜና19፥2
32፥26 2ዜና34፥27:28፤ኢሳ39፥8፤ ኤር26፥18-19
32፥27 1ዜና 29፥12፤2ዜና9፥24
32፥29 ኢሳ39፥2
32፥30 2ሳሙ5፥8፤ 1ነገ1፥33፤2ነገ18፥17
32፥31 ቊ24፤ዘፍ 22፥1፤ዘዳ8፥16፤ኢሳ 13፥1፤ 38፥7፤39፥1
33፥1 1ዜና3፥13
33፥2 ዘዳ18፥9፤ ኤር15፥4
33፥3 ዘዳ16፥21-22፤17፥3፤2ዜና24፥18
33፥4 2ዜና7፥16
33፥5 2ዜና4፥9
33፥6 ዘፀ22፥18፤ ዘሌ18፥21፤19፥31፤ ዘዳ18፥10፤ 1ሳሙ28፥13
33፥7 2ዜና7፥16
33፥8 2ሳሙ7፥10

*32፥24፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የኢሳያስን ሚና እና ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ ስለ ተመለሰው ጥላ ታምር ተደራሲያኑ እንደ ሚያውቁ በመገመት በ2ነገ20፥1-11 እና በኢሳ38፥1-8 ላይ የሚገኘውን ታሪክ በአጭሩ አቅርቦአል ይህን በሚጽፍበት ጊዜ ታሪኩን ያሳጠረው አን ባቢው ያደረገውን የጥላውን ተአምራዊ ክስተት ዐሥር እርከን ወደኋላ መመለስን የሚያሠሙውን ታሪክ አንባቢው በሚገባ እንደሚያውቅ አድርጎ በማሰብ ነው::

*32፥25-30፤* ይህ ክፍል በተጓዳኝ ምንባቦቹ ውስጥ አይገኝም ::

32፥25-26 *ታበየ...ትዕቢት፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ሕዝቅያስ ከምን የተነሣ እንደታበየ የገለጸው ነገር የለም (ይሁን እንጂ ቊ31፤2ነገ20፥12-13፤ ኢሳ39፥1-2 ይመ):: "ዳግማዊ ሰሎሞን" የሚል የሙገሳ ስም የተሰጠው ሕዝቅያስም ቢሆን፣ አልታዘዘም ካለ ከእግዚአብሔር ቊጣ አያመልጥም::

*32፥27-29፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የሕዝቅያስን ሀብት ብዛት በመቊጠር፣ ከሰሎሞን ሀብት ጋር ሊያመሳስለው ይፈልጋል (9፥13-14)::

*32፥30፤* ቊ2-4፤2ነገ20፥20 ይመ::

*32፥31፤* ቊ25 ይመ:: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ተደራስያኑ በ2ነገ20፥12-19 እንዲሁም በኢሳ39፥18 ላይ ያለውን ታሪክ በሚገባ እንደሚያውቁ ተገንዝቦአል:: ከባቢሎን ንጉሥ ተልከው የመጡት ሰዎች ዋናው ፍላጎታቸው፣ ኀይላቸውን በማቀናጀት በአሦራ ያውያን ላይ በአንድ ጊዜ ከሁለት ግንባሮች ጦርነት መክፈት ነበር::

*33፥1-20፤* 2ነገ21፥1-18 እና ማብ ይመ:: ምናሴ ከሌሎቹ የይሁዳ ነገሥታት ይልቅ ብዙ ዘመን የገዛ ንጉሥ ነበር፤ ባጠቃላይ አምሳ አምስት ዓመት ገዝቶአል (ቊ1):: በነገሥቱም ሆነ በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ልዩ ትኵረት የተሰጣቸው ነገሮች የተለያዩ ናቸው፤ ይኸውም በምናሴ ዘመነ መንግሥት የተፈጸሙት ክፉ ሥራዎች በሁለቱም መጻሕፍት ሰፊ ቦታ የተሰጣቸው ሲሆን፣ ተማ ርኮ ወደ ባቢሎን መወሰዱ፣ ስለሠራው በደል ንስሓ መግባቱ እንዲሁም የአስተዳደር ተሐድሶ ማድረጉን የሚገልጸው የዜና መዋዕሉ ብቻ ነው:: የነገሥቱ ጸሓፊ የጻፈው የምናሴ እኩይ ሥራዎች ሲሆን፣ ይህም ወደ ምርኮ ለመጋዛቸው ዋነኛ ምክንያት ነው:: (2ነገ21፥10-15፤23፥6):: አንዳንድ ሊቃውንት፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ለምናሴ ንስሓ መግባት ልዩ ትኵረት የሰጠው እግዚ አብሔር የእጅን እንደሚከፍል ለማሳየት ካለው ፍላጎት የተነሣ ነው የሚል እምነት አላቸው፤ ይኸውም ረጅም ዘመን በሥልጣን ላይ ለመቆየት የመታዘዝ በረከት እንደሆነና ምናሴም ብዙ ዘመን መግዛት የቻለው ከዚህ የተነሣ መሆኑን ለመግለጽ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ እንደዘገበው ይናገራሉ:: ይሁን እንጂ ረጅም ዘመን መግዛት የእግዚአብሔር በረከት መሆኑን ጸሓፊው በሌላ ቦታ ላይ አልጠቀሰም:: አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔር በረከት ተብለው በጸሐፊው ተደጋግመው የተጠቀሱት ሰላምና ብልጽግና፣ መሠ ረታዊ ተቋማት መገንባት፣ በጦርነት ድልን መቀዳጀትና ብዙ ቤተ ሰብ ማፍራት ናቸው::

33፥1 *አምሳ አምስት ዓመት፤* ዘመኑ 697-642 ዓ.ቅ.ክ ነው::

33፥3 *የአሼራ ምስል ዐምዶች፤* የ14፥3 እግርጌ ትርጉም ይመ::

33፥6፤ *ወንዶች ልጆቹን በእሳት ሠዋ፤* 28፥3-4 ይመ::

የእስራኤላውያን እግር ከእንግዲህ ለቆ እን
ዲወጣ አላደርግም::” 9ምናሴ ግን *እግዚአብሔር*
በእስራኤላውያን ፊት ካጠፋቸው አሕዛብ የባሰ
ክፉ ድርጊት ይፈጽሙ ዘንድ፣ የይሁዳንና
የኢየሩሳሌምን ሕዝብ አሳተ::
10*እግዚአብሔር* ለምናሴና ለሕዝቡ ተናገረ፤
እነርሱ ግን መስማት አልፈለጉም:: 11ስለዚህ
*እግዚአብሔር* የአሦርን ንጉሥ ሰራዊት አዛዦች
አመጣባቸው፤ እነርሱም በምናሴ አፍንጫ
መንጠቆ አገቡበት፤ በናስ ሰንሰለት አስረውም
ወደ ባቢሎን ወሰዱት:: 12በተጨነቀም ጊዜ
*የአምላኩን* የእግዚአብሔርን በጎነት ፈለገ፤ በአ
ባቶቹም አምላክ ፊት ራሱን እጅግ አዋረደ። 13ወደ
እርሱም በጸለየ ጊዜ፣ በጭንቀት ልመናው
ራርቶለት *እግዚአብሔር* ጸሎቱን ሰማው::
ስለዚህ ወደ ኢየሩሳሌም፣ ወደ መንግሥቱም
መለሰው፤ ምናሴም *እግዚአብሔር* አምላክ መሆኑን
ዐወቀ::
14ከዚህ በኋላ በሸለቆው ውስጥ ከሚገኘው
ከግዮን ምንጭ ምዕራብ አንሥቶ እስከ ዓሣ
በር መግቢያ ድረስ ያለውን የዳዊትን ከተማ
የውጭውን ቅጥር፣ የዖፌልን ኰረብታ እንዲከብበ
በማድረግ፣ ይበልጥ ከፍ አድርጎ እንደ ገና
ሠራው:: በተመሸጉትም የይሁዳ ከተሞች
ሁሉ የጦር አዛዦችን አኖረ::
15እንግዶች አማልክትንና ጣዖታቱን *ከእግዚአ
ብሔር* ቤተ መቅደስ አስወገደ፤ በቤተ መቅ
ደሱ ኰረብታና በኢየሩሳሌም የሠራቸውንም
መሠዊያዎች ሁሉ አራቀ፤ ከከተማዪቱም
ውጭ ጣላቸው:: 16ከዚያም *የእግዚአብሔርን*
መሠዊያ አደሰ፤ በላዩም የኅብረት መሥዋዕ
ትና የምስጋና መሥዋዕት አቀረበ፤ ይሁዳም
የእስራኤልን *አምላክ* እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ
አዘዘ:: 17ሕዝቡ ግን በኰረብታ መስገጃ

33፥9 ኤር15፥4፤ ሕዝ5፥7
33፥11 ዘዳ28፥36፤ 2ነገ19፥28፤ መዝ149፥8፤ ኢሳ37፥29፤ ሕዝ29፥4፤38፥4፤ አሞ4፥2
33፥12 2ዜና6፥37
33፥14 1ነገ1፥33፤ 2ዜና27፥3፤ ነህ3፥3፡26፤12፥39፤ ሶፎ1፥10
33፥15 2ነገ23፥12
33፥16 ዘሌ7፥11-18
33፥19 2ነገ21፥2 1፥17፤ 2ዜና6፥37
33፥20 2ነገ21፥18፤ 2ዜና21፥20
33፥21 1ዜና3፥14
33፥23 ዘፀ10፥3፤ 2ዜና7፥14፤ መዝ18፥27፤147፥6፤ ምሳ3፥34
33፥25 2ዜና22፥1

ስፍራዎች መሠዋቱን ቢቀጥልም፣ የሚሠዋው
ግን ለአንዱ *አምላክ* ለእግዚአብሔር ብቻ ነበር::
18በምናሴ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው
ሌላው ተግባር፣ ወደ አምላኩ ያቀረበው ጸሎ
ቱና ባለራእዮች በእስራኤል *አምላክ* በእግዚ
አብሔር ስም የነገሩት ቃል በእስራኤል[ሀ] ነገ
ሥታት ታሪክ ተጽፎአል:: 19ጸሎቱና እግዚአብሔር
ራርቶ ልመናውን እንዴት እንደ ተቀበ
ለው፣ ኀጢአቱ ሁሉና ታማኝነቱን ማጕደሉ፣
እንደዚሁም ራሱን ከማዋረዱ በፊት ያሠራ
ቸው የኰረብታ መስገጃ ስፍራዎች፣ ያቆ
ማቸው የአሼራ ምስል ዐምዶችና ጣዖታት
ሁሉ በባለ ራእዮች መዛግብት ተጽፈዋል::
20ምናሴም እንደ አባቶቹ ሁሉ አንቀላፋ፤
በቤተ መንግሥቱም ተቀበረ:: ልጁም አሞጽ
በእርሱ ፈንታ ነገሠ::

### የይሁዳ ንጉሥ አሞጽ

21አሞጽ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሃያ ሁለት
ዓመት ነበር፤ እርሱም በኢየሩሳሌም ተቀምጦ
ሁለት ዓመት ገዛ:: 22አባቱ ምናሴ እንዳደረገው
ሁሉ እርሱም *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ
ድርጊት ፈጸመ፤ አሞጽም ምናሴ ያሠራቸውን
ጣዖታት ሁሉ አመለከ፤ መሥዋዕትም አቀረበ
ላቸው:: 23አሞጽ *በእግዚአብሔር* ፊት ራሱን
እንዳዋረደ እንደ አባቱ እንደ ምናሴ ራሱን
አላዋረደም፤ ነገር ግን በበደል ላይ በደል
እየጨመረ ሄደ::
24የአሞጽ ሹማምንት በእርሱ ላይ አሢረው
በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ገደሉት:: 25ከዚ
ያም ያገሩ ሕዝብ በንጉሡ አሞጽ ላይ ያሤሩ
ትን ሁሉ ገደሉ፤ ልጁን ኢዮስያስንም በእርሱ
ፈንታ አነገሡት::

[ሀ] 18 በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው ይህ ይሁዳ ነው::

*33፥10፤* የ1-20 ማብ ይመ:: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት ለምናሴና እና ለሕዝቡ የተናገረውን እዚህ ላይ ባጭሩ አቅርቦታል፤ ሙሉ ታሪኩ በ2ነገ21፥10-15 ላይ ይገኛል::

*33፥11-17፤* በዜና መዋዕሉ ብቻ የሚገኝ ታሪክ ነው:: ይህም ለሚታዘዙ በረከት ለማይታዘዙ የአጸፋ ቅጣት መኖሩን ለሚገልጸው ሐሳቡ አጽንዖት በመስጠት የምናሴ ክፋት ወረራና ሽንፈት እንዳመጣበት ሁሉ ንስሓ መግባቱ ደግሞ ወደ ሥልጣን እንዲመለስ እንደረዳው ያሳያል::

33፥11 *ወደ ባቢሎን ወሰዱት፤* እስካሁን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጭ ምናሴ በአሦር ንጉሥ ተማርኮ ወደ ባቢሎን ስለ መወሰዱ የሚናገሩ የታሪክ መዛግብት አልተገኙም፤ ከ681-669 ዓ.ቅ.ክ የነበረው አስራዶን ለሕንጻ ግንባታው ሥራ የተለያዩ ዕቃዎች ከሚያቀርቡለት ሃያ ሁለት ነገሥታት ውስጥ አንዱ ምናሴ መሆኑን ጠቅሶታል፤ ከ669-627 ዓ.ቅ.ክ. የነበረው አሹርባኒፓል ግብፅን በወረረ ጊዜ ከረዱት ነገሥታት መካከል አንዱ ምናሴ መሆኑን ገልጾአል፤ ይህ የአሦር ንጉሥ ምናሴን ማርኮ ወደ ባቢሎን የወሰደውም፣ የገዛ ወንድሙና የበታቹ ባለሥልጣን የነበረው ሻማሽ-ሹም-ዑኪን ዐምፆ በነበረበት ጊዜ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አለ:: ዐመፁ የቈየው ለአራት ዓመት ያህል (652-648 ዓ.ቅ.ክ) ሲሆን፣ ምናልባትም ምናሴ የዐመፁ ተባባሪ ወይም ባቢሎን ከአሦር መንግሥት ለማፈንገጥ ባደረገው ሙከራ ተካፋይ ሳይሆን አይቀርም:: ምናሴም ታማኝ ለመሆን እንደገና ቃል በመግባቱ፣ ይቅርታ ተደርጎለት ይሆናል፤ ወይም ጥፋት ያልተገኘበት ሆኖ ሊሆን ይችላል:: ግብፅም በበኩሏ በሃያ ስድስተኛው ሥርወ መንግሥት ከአሦር እጅ አፈንግጣ ለመውጣት የተነሣችበት ጊዜ ስለ ነበር፣ ምናሴን መልሶ በዙፋኑ ላይ እንዲቀመጥ ማድረጉ አሦራውያን የሚያግዛቸውን ኀይል በግብፅ ወሰን ላይ የማስቀመጥ ፍላጎት እንደነበራቸው ያሳያል::

*33፥12፤* ቃልቶቹ የሰልሞንን ጸሎት የሚያስታውስ ክፍል ነው (7፥14)::

33፥14 *የውጭውን ቅጥር... እንደገና ሠራው፤* ለዜና መዋዕሉ ጸሓፊ እንዲህ ያለው የግንባታ ሥራ በእግዚአብሔር የመባረክ ምልክት ነው (8፥1-6፤11፥5-12፤14፥6-7፤ 26፥9-10፡ 14-15፤32፥1-5፡27-30፤ 1ዜና፡11፥7-9፤15፥1)

*33፥15-16፤* ምናሴ ያመጣው ተሐድሶ ምን እንደ ሆነ በትክክል ባይታወቅም፣ ኢዮስያስ በኋለኛው ዘመን “ምናሴም በሁለት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አደባባዮች ላይ የሠራቸው መሠዊያዎች” እንዳፈረሰ ተጽፎአል (2ነገ23፥12)

33፥20 *በቤተ መንግሥቱም ተቀበረ፤* ከ2ነገ21፥18 ጋር ያነጻጽሩ:: በዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዘገባ መሠረት ምናሴ በቤተ መንግሥቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ መቀበሩ፣ በነገሥታቱ መካነ መቃብር ካልተቀበሩት ነገሥታት መካከል አምስተኛው ንጉሥ ያደርገዋል (የ28፥27 ማብ ይመ)::

*33፥21-25፤* 2ነገ21፥19-26 ይመ፤ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የዘገበው የአሞን ዘመነ መንግሥት ታሪክ (ከ642-640 ዓ.ቅ.ክ) በመጽሐፈ ነገሥት ከተጻፈው ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ነው፤ የሚለይበት ነገር ቢኖር (1) አባቱ ምናሴ ንስሓ መግባቱንና ልጁ አሞን ግን ንስሓ አለመግባቱን ጨምሮ የገለጸው የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ብቻ መሆኑ ከቍ12-13፣ (2) ሥርዐተ ቀብሩ እንዴት እንደተፈጸመ አለመናገሩ ናቸው::

*34፥1-36፥1፤* 2ነገ22፥1-23፥30 እና ማብ ይመ:: የኢዮስያስን ዘመነ መንግሥት አስመልክቶ፣ ሁለቱም መጻሕፍት በተመሳሳይ መጠንና ዐይነት፣ በተመሳሳይ ርእሰ ጕዳይ ላይ ያተኵሩ ቢሆኑም እንኳ፣ በአጽንዖታቸው ግን በመጠኑ ይለያያሉ:: ሁለቱም መጻሕፍ ኢዮስያስ ተሐድሶን ለማምጣት ያደረጋቸውን ሦስት መሠረታዊ ነገሮችን ዘርዝረዋል፤ እነዚህም (1) ባዕድ አምልኮን ማስወገድ፣ (2) የሕጉ መጽሐፍ መገኘትና ይህንን አስከትሎ የተደረገውን የኪዳን

## ኢዮስያስ ያደረገው ተሐድሶ

34፥1-2ተጓ ምብ —2ዜና22፥1-2
34፥3-7ተጓ ምብ —2ዜና23፥4-20
34፥8-13ተጓ ምብ —2ዜና22፥3-7

**34** ኢዮስያስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው
ስምንት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም
ተቀምጦም ሠላሳ አንድ ዓመት ገዛ። 2እርሱም
*በእግዚአብሔር* ፊት መልካም የሆነውን ነገር
አደረገ፤ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ሳይል፣ በአባቱ
በዳዊት መንገድ ሄደ።
3በዘመነ መንግሥቱ በስምንተኛው ዓመት
ገና ወጣት ሳለ፣ የአባቱን የዳዊትን አምላክ
መፈለግ ጀመረ፤ በዐሥራ ሁለተኛውም
ዓመት ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን ከኰረብታ
መስገጃ ስፍራዎች፣ ከአሼራ፣ ምስል ዐም
ዶች፣ ከተቀረጹ ባዕድ አማልክትና ቀልጠው
ከተሠሩ ምስሎች አነጻ። 4በእርሱም
ትእዛዝ የበኣሊም መሠዊያዎችን አፈራረሱ፤
እርሱም ከበላያቸው የነበሩትን የዕጣን
መሠዊያዎችን አደቀቀ፤ የአሼራን ምስል ዓም
ዶችን፣ ባዕድ አማልክቱንና ምስሎቹን ሰባብሮ
ከፈጫቸው በኋላ ይሠዉ ላቸው በነበሩት ሰዎች
መቃብር ላይ በተነ። 5የካህናቱን ዐጥንት
በመሠዊያዎቻቸው ላይ አቃጠለ፤ በዚህ
ዐይነትም ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን አነጻ። 6እስከ
ንፍታሌም ባሉ በምናሴ፣ በኤፍሬምና በስ
ምዖን ከተሞች እንዲሁም በዙሪያቸው ባሉ
የፈራረሱ አካባቢዎች፣ 7መሠዊያዎችንና የአ
ሼራ ምስል ዐምዶችን አፈራረሰ፤ ባዕድ አማልክቱን
እንደ ዱቄት አደቀቀ፤ በመላው እስራኤል
የሚገኙትንም የዕጣን መሠዊያዎች አንኰታኰተ፤
ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።
8ኢዮስያስ በነገሠ በዐሥራ ስምንተኛው
ዓመት፣ ምድሪቱንና ቤተ መቅደሱን ካነጻ
በኋላ፣ የኤዜልያስን ልጅ ሳፋንን፣ የከተማ

34፥1 1ዜና3፥14፤ ሶፎ1፥1
34፥2 2ዜና29፥2
34፥3 1ዜና16፥11
34፥4 ዘፀ32፥20፤
34፥13፤ዘሌ26፥30፤2 ነገ23፥11፤ሚክ1፥5
34፥5 1ነገ13፥2
34፥7 ዘፀ32፥20
34፥9 1ዜና6፥13
34፥11 2ዜና24፥12፤33፥4-7
34፥12 2ነገ12፥15፤ 1ዜና25፥1
34፥13 1ዜና23፥4

ዪቱን ገዥ መዕሤያንና የጸሓፊውን የኢዮ
አካዝን ልጅ ኢዮአክን *የአምላኩን* የእግዚአ
ብሔርን ቤተ መቅደስ ይጠግኑ ዘንድ ላካቸው።
9እነርሱም ወደ ሊቀ ካህኑ ወደ ኬልቅያስ
ሄደው፣ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የመጣውን
ገንዘብ ሰጡት፤ ገንዘቡም በር ጠባቂዎች የነ
በሩት ሌዋውያን፣ ከምናሴ፣ ከኤፍሬምና
ከመላው የእስራኤል ቅሬታዎች እንደዚሁም
ከመላው ይሁዳና ከብንያም፣ ከኢየሩሳሌምም
ነዋሪዎች የሰበሰቡት ነበር። 10እነርሱም *የእግ
ዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ ሥራ እየተቈጣጠሩ
እንዲያሠሩ ለተሾሙት ሰዎች ዐደራ ሰጡ፤
እነዚህም ሰዎች ገንዘቡን ቤተ መቅደሱን ለጠ
ገኑትና ላደሱት ሰዎች ከፈሉ። 11እንዲሁም
የይሁዳ ነገሥታት እንዲፈርሱ ላደረጓቸው
ሕንጻዎች ጥርብ ድንጋዮችን፣ ሠረገላዎችንና
ማገጣጠሚያ ዕንጨቶችን እንዲገዙ ለዐናጢ
ዎችና ለግንበኞች ገንዘብ ሰጡ።
12ሰዎቹም ሥራውን በታማኝነት አከናወኑ።
የበላይ ሆነው አመራር የሚሰጧቸውም ከሜራሪ
ጐሣ የሆኑት ሌዋውያን፣ ኢኤትና አብድዩ፣
ከቀዓት ጐሣ ዘካርያስና ሜሱላም ነበሩ። በዜማ
ዕቃ የላቀ ችሎታ የነበራቸው ሌዋውያን
ሁሉ፣ 13የጕልበት ሠራተኞች ኀላፊ በመሆን፣
በየሥራው ላይ የተመደቡትን ሠራተኞች ይቈጣጠሩ
ነበር። ጥቂቶቹ ሌዋውያን ደግሞ ኀላፊዎች፣
ጸሓፊዎችና በር ጠባቂዎች ነበሩ።

## የሙሴ ሕግ መጽሐፍ መገኘት

34፥14-28ተጓ ምብ —2ዜና22፥8-20
34፥29-32ተጓ ምብ —2ዜና23፥1-3

14ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ የገባውን
ገንዘብ በሚያወጡበት ጊዜ፣ ካህኑ ኬልቅያስ
በሙሴ አማካይነት የተሰጠውን *የእግዚአ
ብሔርን* ሕግ መጽሐፍ አገኘ። 15ኬልቅያስም

መታደስ፣ (3) የፋሲካ በዓል መከበር ናቸው። በሁለተኛው ተራ ቍጥር ላይ የተጠቀሰውም ሐሳብ በተመለከተ ሁለቱም መጻሕፍት ተመሳሳይ የሆነ ዘገባ አቅርበዋል። በአንደኛው ተራ ቍጥር ላይ የተገለጸውን ሐሳብ በተመለከተ ግን የነገሥቱ ጸሓፊ በዝርዝር ሲጽፍ (2ነገ23፥4-20)፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን በአጭሩ አቅርቦታል 34፥3-7:33። እንደዚሁም የፋሲካን በዓል በተመለከተ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በዝርዝር ሲጽፍ (35፥1-19)፣ የነገሥቱ ጸሓፊ ግን ጠቀስ አድርጎት ብቻ አልፎአል (23፥21-23)። ታሪኩን አንዱ በዝርዝር፣ ሌላው ደግሞ በአጭሩ በመጻፉ ብቻ ሳይሆን፣ በቅደም ተከተልም ረገድ እንዲሁ ልዩነት አላቸው። በነገሥት መጽሐፍ ኢዮስያስ በነገሠ ዐሥራ ስምንተኛው ዓመት የሕጉ መጽሐፍ በቤተ መቅደስ የመገኘቱ ጕዳይ፣ ቅድሚያ ተሰጥቶት ተዘግቦአል። የነገሥቱ ጸሓፊ መልክዐ ምድራዊ ይዘት ባለው መንገድ መጀመሪያ ስለ ቤተ መቅደሱ፣ ቀጥሎም ስለ ከተማዪቱ ይጽፍና በመጨረሻም ስለተቀረው ሕዝብ ጽፎአል። በሌላ መልኩ ደግሞ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዘገባውን ያቀረበው የድርጊቶችን ቅደም ተከተል በጠበቀ ሁኔታ ነው (34፥3 ፤ 34፥8 ፤ 2ነገ 22፥3 ፤35፥19፤2ነገ 23፥23 ይመ፤ እንዲሁም የ2ዜና 12፥2 ማብ ይመ)። የዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ተሐድሶ የተጀመረው ኢዮስያስ በነገሠ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት (34፥3) መሆኑን ዘግቦአል፣ ይህም የሕጉ መጽሐፍ ከመገኘቱ ከስድስት ዓመት በፊት ማለት ነው።

*34፥1-2፤* 2ነገ22፥1-2 ይመ።

*34፥1፤ ሠላሳ አንድ ዓመት፤* 640-609 ዓ.ክ.ቅ. ማለት ነው።

*34፥3-7፤* የነገሥቱ ጸሓፊ ይህን የኢዮስያስን ተሐድሶ በተመለከተ ያቀረበው ዘገባ፣ ሰፋና ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚዳስስ ነው (2ነገ23፥4-20)። የባዕድ አምልኮ የመወገዱን ጕዳይ የዘገበው ስለ ሕጉ መጽሐፍ መገኘት ከዘገበ በኋላ ሲሆን፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን ቅድሚያ የሰጠው የባዕድ አምልኮ ስለመወገዱ ጕዳይ ነው።

*34፥3፤* አንዳንድ ሊቃውንት በ8ኛው (ቍ3)፣በ12ኛው (ቍ3)፣ በ18ኛው (ቍ8) የኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት የተፈጸሙትን ድርጊቶች፣ ለሁለት መቶ ዓመት በአካባቢው ሲገዛ ከቈየው፣ አሁን ግን ቀስ በቀስ ከተዳከመ በኋላ በወደቀው የአሦራውያን ግዛት ዐይ ጋር ለማያያዝ ሞክረዋል። የአራምንና የፍልስጥኤምን ምድር ጠቅልሎ በቍጥጥሩ ሥር በማድረግ ለዘመናት ገኖ የነበረው የአሦር መንግሥት መውደቁ፣ ቀድሞ በይዞታው ሥር የነበሩትን አውራጃዎች እንደ ጥንቱ የዳዊትና የሰሎሞን ዘመን፣ ግዛቱ ለማ ድረግ ሁኔታዎችን ለኢዮስያስ ያመቻቸለት ለመሆኑ ጥርጥር የለውም (ቍ6-7)።

34፥6 *እስከ ንፍታሌም ባሉ በምናሴ፣ በኤፍሬምና በስምዖን፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ "እስራኤል ሁሉ" ለሚለው ሐረግ ልዩ ትኵረት የሰጠው (በ1ዜና መጽሐፍ መግቢያ ሥር፣ 'ዐዮቹና መሪ ሐሳብ' የሚለውን ይመ)፣ ኢዮስያስ ባደረገው ተሐድሶ የሰሜኑ ነገዶች ተካፋይ እንደነበሩ ለማመልከት ፈልጎ መሆኑ ግልጽ ነው ቍ9:21:33 ይመ)። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ልክ በሕዝቅያስ ዘመን እንደ ሆነው እስራኤል ሁሉ በዳዊት ሥርወ መንግሥት ተጠቃ ለው አንድ እንደሆኑ ያሳያል (የ30፥1 ማብ ይመ)። *በስምዖን፤* ምናልባትም አንዳንድ የስምዖን ነገድ ሰዎች ከይሁዳ ወደ ሰሜኑ ክፍል ፈልሰው ሊሆን ይችላል።

34፥7 *በመላው እስራኤል፤* የነገድ ዝርዝራቸው በቍ6 ላይ ተገልጾአል።

*34፥8-21፤* 2ነገ 22፥3-13 እና ማብ ይመ።

34፥9 *ከምናሴ፣ ከኤፍሬምና ከመላው የእስራኤል ቅሬታዎች፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ "እስራኤል ሁሉ" ለሚለው ሐረግ ከሚሰጠው ልዩ ትኵረት የተነሣ፣ እዚህም ላይ የሰሜኑ ክፍል ሰዎች ለቤተ መቅደሱ ስጦታ ማምጣታቸውን ዘግቦአል (ይህ ግን በ2ነገ22፥4 ላይ በግልጽ አልተጠቀሰም)።

*34፥10-13፤* ከ24፥8-12 ጋር ያነጻጽሩ።

*34፥22-28፤* 2ነገ22፥14-20 እና ማብ ይመ።

ጸሓፊውን ሳፋንን፣ "የሕጉን መጽሐፍ በእግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ አገኘሁት"
አለው፤ ከዚያም መጽሐፉን ለሳፋን ሰጠው።
16ሳፋንም መጽሐፉን ወደ ንጉሡ ወስዶ
እንዲህ አለው፤ "ሹማምንትህ የታዘዙትን ሁሉ
በመፈጸም ላይ ናቸው፤ 17በእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ የነበረውንም ገንዘብ አውጥተው ለተቈ
ጣጣሪዎቹና ለሠራተኞቹ አስረክበዋል።"
18ከዚያም ጸሓፊው ሳፋን ንጉሡን፣ "ካህኑ
ኬልቅያስ መጽሐፍ ሰጥቶኛል" አለው። ሳፋ
ንም መጽሐፉን ለንጉሡ አነበበለት።
19ንጉሡም የሕጉን ቃል በሰማ ጊዜ ልብሱን
ቀደደ። 20እርሱም ለኬልቅያስ፣ ለሳፋን ልጅ
ለአኪቃም፣ ለሚክያስ ልጅ ለዓብዶን፣
ለጸሓፊው ለሳፋንና ለንጉሡ የቅርብ አገል
ጋይ ለዓሳያ ይህን ትእዛዝ ሰጠ፤ 21"ሂዱችሁ
ስለ እኔ እንደዚሁም በእስራኤልና በይሁዳ
ስላሉት ቅሬታዎች በተገኘው መጽሐፍ ውስጥ
ስለ ተጻፈው ነገር እግዚአብሔርን ጠይቁ።
አባቶቻችን የእግዚአብሔርን ቃል ስላልጠ
በቁ በላያችን ላይ ታላቅ የእግዚአብሔርን
ቍጣ ፈስሶአል፤ በዚህ መጽሐፍ በተጻፈው
መሠረት አልተመላለሱምና።"
22ኬልቅያስና ንጉሡ ከእርሱ ጋር የላካቸው[ሀ]
ሰዎች የአልባሳት ጠባቂ የነበረው የሐስራ
ልጅ፣ የቲቁዋ ልጅ የሴሌም ሚስት ወደ
ሆነችው ወደ ነቢይቱ ወደ ሕልዳና ሄደው
ነገሯት። እርሷም በኢየሩሳሌም ውስጥ በሁለ
ተኛው ክፍለ ከተማ ትኖር ነበር።
23ነቢይቱም እንዲህ አለቻቸው፤ "የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ወደ እኔ
ለላካችሁ ሰው እንዲህ ብላችሁ ንገሩት፤
24'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በይሁዳ ንጉሥ
ፊት በተነበበው መጽሐፍ በተጻፈው ርግማን
ሁሉ መሠረት፣ በዚህ ስፍራና በሕዝቡ ላይ
ጥፋትን አመጣለሁ። 25እኔን ትተውኝ
ለሌሎች አማልክት ዕጣን ስላጠኑና እጃቸው
በሠራው ነገር ሁሉ[ሁ] ለቍጣ ስላነሣሡኝ፣ ቍጣዬ
በዚህ ስፍራ ይነድዳል፤ አይጠፋምም።' 26እግዚ
አብሔርን ለመጠየቅ የላካችሁን የይሁዳን
ንጉሥ እንዲህ በሉት፤ 'ስለ ሰማኸው ቃል
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
27በዚህ ስፍራና በሕዝቡ ላይ የተናገረውን በሰ
ማህ ጊዜ፣ ልብህ ስለ ተነካና በእግዚአብሔርም
ፊት ራስህን ስለ አዋረድህ፣ እንዲሁም በእኔ
ፊት ራስህን ዝቅ ስላደረግህ፣ ልብስህንም በመ
ቅደድ በፊቴ ስለ አለቀስህ፣ ሰምቼሃለሁ ይላል
እግዚአብሔር። 28እነሆ፤ ወደ አባቶችህ እሰበ
ስብሃለሁ፤ በሰላምም ትቀበራለህ፤ በዚህ ቦታና
በነዋሪዎቹ ላይ የማመጣውን መከራ ሁሉ በዓ
ይንህ አታይም።'" መልሷንም ይዘው ወደ
ንጉሡ ሄዱ።

29ከዚያም ንጉሡ የይሁዳንና የኢየሩ
ሳሌምን ሽማግሌዎች ሁሉ በአንድ ላይ ሰበ
ሰበ። 30እርሱም ከትንሽ እስከ ትልቅ ካሉት
ከይሁዳ ሰዎች፣ ከኢየሩሳሌም ሕዝብ፣ ከካህ
ናትና ከሌዋውያን ጋር ወደ እግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ወጣ። በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
የተገኘውንም የኪዳኑን መጽሐፍ ቃል ሁሉ
ለሕዝቡ አነበበላቸው 31ንጉሡም በዐምዱ አጠ
ገብ ቆሞ፣ እግዚአብሔርን ይከተል ዘንድ
በፍጹም ልቡና በፍጹም ነፍሱ ትእዛዛቱን፣
ሕግጋቱንና ሥርዐቱን ለመጠበቅ፣ በዚህ
መጽሐፍ ለተጻፈውም የኪዳን ቃል ለመታዘዝ
በእግዚአብሔር ፊት ኪዳኑን አደሰ።
32ከዚህ በኋላ በኢየሩሳሌምና በብንያም የሚ
ኖረው ሁሉ በዚህ ነገር ቃል እንዲገባ አደረገ፤
የኢየሩሳሌምም ሕዝብ የአባቶቹ አምላክ በዘዘው
የአምላክ ቃል ኪዳን መሠረት ፈጸሙ።
33ኢዮስያስም አስጸያፊ ጣዖታትን ሁሉ
ከመላው የእስራኤል ግዛት አስወገደ፤ በእስ
ራኤል የነበሩትም ሁሉ አምላካቸውን እግዚአ
ብሔርን እንዲያመልኩ አደረገ፤ እርሱ በሕ
ይወት እያለም የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚ
አብሔርን ከመከተል ወደ ኋላ አላሉም።

## ኢዮስያስ ፋሲካን ማክበሩ

35፥1፡18-19ተጓ ምብ— 2ዜና 23፥21-23

35 ኢዮስያስ በኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር
ፋሲካን አደረገ፤ በመጀመሪያውም
ወር በዐሥራ አራተኛው ቀን የፋሲካው በግ
ታረደ። 2ካህናቱን በየአገልግሎታቸው መደበ፤
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገልግሎትም
እንዲተጉ አበረታታቸው። 3እስራኤልን ሁሉ
ያስተምሩ ለነበሩትና ራሳቸውን ለእግዚአብሔር
ለቀደሱት ሌዋውያን እንዲህ አላቸው፤ "የእግዚ
አብሔርን ታቦት የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ባሠራው
ቤተ መቅደስ አኑሩ፤ በእናንተ ትከሻ አት
ሸከሙት፤ አሁንም አምላካችሁን እግዚአብሔርንና
ሕዝቡን እስራኤልን አገልግሉ። 4በእስራኤል
ንጉሥ በዳዊትና በልጁ በሰሎሞን በተጻፈው

34፥15 2ነገ22፥8፤ ዕዝ7፥6፤ ነህ8፥1
34፥19 ዘዳ28፥3-68፤ ኢሳ36፥22፤37፥1
34፥20 2ነገ22፥3
34፥21 ሰቆ2፥4፤ 4፥11፤ ሕዝ36፥18
34፥22 ዘፀ15፥20፤ ነህ6፥14
34፥24 ዘዳ28፥15-68፤ 2ዜና36፥14-20፤ ምሳ16፥4፤ ኢሳ3፥9፤ ኤር40፥2፤42፥10፤44፥2፡11
34፥25 2ዜና33፥3-6፤ ኤር22፥9
34፥27 ዘፀ10፥3፤ 2ዜና6፥37፤32፥26
34፥28 2ዜና32፥26፤ 35፥20-35
34፥30 2ነገ23፥2
34፥31 ዘጸ13፥4፤ 1ነገ7፥15፤ 2ነገ11፥17፤ 2ዜና23፥16
34፥33 ዘጸ18፥9
35፥1 ዘፀ12፥1-30፤ ዘኍ28፥16
35፥3 2ዜና17፥7
35፥4 ቍ10፤ 1ዜና24፥1፤ ዕዝ6፥18

[ሀ]22 አንድ የዕብራይስጥ ቅጅ እንዲሁም ቡልጌትና የሱርስት ትርጕሞች በዚህ ሲስማሙ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን *ከእርሱ ጋር የላካቸው* የሚለውን አይጨምሩም።
[ሁ]25 *ወይም ባደረጉት ነገር ሁሉ*

34፥28 *በሰላምም ትቀበራለህ፤* አሟሟቱንና ሥርዐተ ቀብሩን በተመለከተ 35፥20-25 ይመ።

*34፥29-31፤* 2ነገ23፥1-3 ይመ።

34፥30 *ከካህናትና ከሌዋውያን፤* "ካህናቱና ነቢያቱ" ከሚለው ከ2ነገ23፥2 ጋር ያነጻጽሩ።

34፥33 *ከመላው እስራኤል ግዛት.. በእስራኤል የነበሩትም ሁሉ፤* የቍ6 ማብ ይመ።

*35፥1-19፤* ኢዮስያስ የፋሲካን በዓል እንዴት እንዳከበረ በመጽሐፈ ነገሥት ላይ ባጭሩ ከቀረበው ይልቅ (2ነገ23፥21-23) የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በዝርዝር ጽፎአል።

35፥1 *በመጀመሪያውም ወር፤* የፋሲካ በዓል የሚከበርበት ወር ነው፤ ከሕዝቅያስ የፋሲካ በዓል አከባበር ጋር ያነጻጽሩ (የ30፥2 ማብ ይመ)።

35፥3 *የእግዚአብሔርን ታቦት ... በቤተ መቅደስ አኑሩ።* ቀድሞውኑ ታቦቱ ለምን ከዚያ እንደወጣ የሚገልጽ ጽሑፍ በነገሥቱም ሆነ በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ተጽፎ አይገኝም፤ ምናልባት ከኢዮስያስ በፊት በነበሩት በክፉዎቹ ነገሥታት በምናሴና በአሞጽ ዘመነ መንግሥት፣ ለጥንቃቄ ሲባል ወደ ሌላ ቦታ ሳያዛውሩት እንዳልቀረ ይገመታል።

35፥4 *በዳዊትና ...በሰሎሞን፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዳዊትንና ሰሎሞንን በሦስት ነገሮች ያመሳስላቸዋል፤ (1) 7፥10 (ዳዊት ብቻ ከተጠቀሰበት ከ1ነገ 8-66 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (2) 11፥17 እና (3) እዚሁ ላይ ነው፤ ጸሓፊው የፈለገው ለዳዊትና ለሰሎሞን ያለውን ከፍተኛ አክብሮትና አድናቆት ለመግለጽ ነው (የ1ዜናን መግቢያ የዳዊትና

መመሪያ መሠረት፣ እንደየቤተሰባችሁ በክፍል
በክፍላችሁ ራሳችሁን አዘጋጁ።
[5]“ሌዋውያን ባልሆኑ ወንድሞቻችሁ አንጻር
እንደየቤተሰቡ ምድብ በተቀደሰው ስፍራ ቁሙ፤
ለእያንዳንዱም የቤተሰብ ምድብ ሌዋውያን
ይኑሩት። [6]ከዚያም የፋሲካውን በጎች እረዱ፤
ራሳችሁን ቀድሱ፤ እግዚአብሔር በሙሴ አማ
ካይነት ባዘዘውም መሠረት ዕርዶቹን ለወንድሞ
ቻችሁ አዘጋጁ።”
[7]ኢዮስያስም እዚያ ለነበሩት ሕዝብ ሁሉ
ለፋሲካው መሥዋዕት እንዲሆኑ ባጠቃላይ
ሠላሳ ሺህ በግና ፍየል እንዲሁም ሦስት ሺህ
ወይፈን ከራሱ ሃብት ሰጠ።
[8]ሹማምንቱም ለሕዝቡ፣ ለካህናቱና ለሌዋ
ውያኑ በገዛ ፈቃዳቸው አዋጥተው ሰጡ።
የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አለቆች የሆኑት ኬል
ቅያስ፣ ዘካርያስና ይሒኤልም ለፋሲካ መሥ
ዋዕት የሚቀርቡ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ
በግ እንዲሁም ሦስት መቶ ወይፈን ሰጡ።
[9]ደግሞም ኮናንያ፣ ወንድሞቹ ሸማያና ናትናኤል
እንደዚሁም የሌዋውያኑ መሪዎች ሐሸቢያ፣
ይዒኤልና ዮዛባት ለፋሲካ መሥዋዕት እንዲ
ሆኑ አምስት ሺህ በግና ፍየል አምስት መቶም
በሬ ለሌዋውያኑ ሰጧቸው።
[10]የአገልግሎቱ ዝግጅት በተጠናቀቀ ጊዜ፣
ንጉሡ ባዘዘው መሠረት ካህናቱ በየክፍላቸው
ከተመደቡት ሌዋውያን ጋር ቦታ ቦታቸውን
ይዘው ቆሙ። [11]የፋሲካው በጎች ታረዱ፤ ካህ
ናቱ የተቀበሉትን ደም ረጩ፤ ሌዋውያኑም
የበጎቹን ቈዳ ገፈፉ። [12]በሙሴ ሕግ እንደ
ተጻፈው ለእግዚአብሔር እንዲያቀርቡም፣ እንደ
የቤተሰቡና እንደየምድቡ ለሕዝቡ ለመስጠት
የሚቃጠለውን መሥዋዕት ለዩ፤ ወይፈኖቹ
ንም እንደዚሁ አደረጉ። [13]እነርሱም የፋሲካውን
መሥዋዕት በሥርዐቱ መሠረት ጠበሱ፤ የተ
ቀደሰውንም ቍርባን በምንቸት፣ በሰታቴና
በድስት ቀቀሉ፤ ወዲያውኑም ለሕዝቡ አደሉ።
[14]ከዚህ በኋላ ለራሳቸውና ለካህናቱ ዝግጅት
አደረጉ፤ ምክንያቱም ካህናቱ የአሮን ልጆች
የሚቃጠለውን መሥዋዕትና ስቡን እስከ ሌሊት
ድረስ ያቀርቡ ስለ ነበር ነው። ስለዚህ ሌዋ
ውያኑ ለራሳቸውና ለካህናቱ ለአሮን ልጆች
ዝግጅት አደረጉ።
[15]መዘምራኑ የአሳፍ ዘሮች በዳዊት፣ በአሳፍ፣
በኤማንና በንጉሡ ባለ ራእይ በኤዶታም በተ
ሰጠው መመሪያ መሠረት በቦታቸው ነበሩ።
በእያንዳንዱ በር ላይ የነበሩት በር ጠባቂዎችም
ሌዋውያን ወገኖቻቸው ስላዘጋጁላቸው፣
ከጥበቃ ቦታቸው መለየት አያስፈልጋቸውም
ነበር።
[16]በዚህ ዓይነት የፋሲካን በዓል በማክበርና
የሚቃጠል መሥዋዕት በእግዚአብሔር መሠዊያ
ላይ በማቅረብ የእግዚአብሔር አግልግሎት
ሁሉ ንጉሥ ኢዮስያስ ባዘዘው መሠረት በዚያኑ
ቀን ተከናወነ። [17]በዚያን ጊዜ በስፍራው የተገኙ
እስራኤላውያን የፋሲካን በዓል አከበሩ፤ የቂ
ጣንም በዓል እንደዚሁ ሰባት ቀን አከበሩ።
[18]ከነቢዩ ከሳሙኤል ዘመን ወዲህ እንዲህ
ያለ ፋሲካ በእስራኤል ዘንድ ተከብሮ አያ
ውቅም፤ ኢዮስያስ ከካህናቱ፣ ከሌዋውያኑ፣
ከመላው ይሁዳና ከእስራኤል፣ በዚያ ከነበሩ
ትም ከኢየሩሳሌም ሰዎች ጋር እንዳከበረው
አድርጎ ያከበረ አንድም የእስራኤል ንጉሥ
የለም። [19]ይህ ፋሲካ የተከበረው በኢዮስያስ
ዘመነ መንግሥት በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት
ነበር።

## የኢዮስያስ መሞት

35፥20-36፥1ተጓ ምብ —2ዜና23፥28-30

[20]ከዚህ ሁሉ በኋላ ኢዮስያስ ቤተ መቅደሱን
አደራጅቶ ባጠናቀቀ ጊዜ፣ የግብፅ ንጉሥ
ኒካዑ በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ፣ በከር
ከሚሽ ላይ ለመዋጋት ወጣ፤ ኢዮስያስም ጦር
ነት ሊገጥመው ወጣ። [21]ኒካዑ ግን፣ “የይሁዳ
ንጉሥ ሆይ፤ አንተንና እኔን የሚያጣላን ምን
ድነው? ጦርነት ከገጠምሁት ቤት ጋር እንጂ
በአሁኑ ጊዜ አንተን የምወጋህ አይደለሁም፤
እግዚአብሔር እንድፈጥን አዞኛል፤ ስለዚህ ከእኔ
ጋር ያለውን እግዚአብሔርን መቃወምህን ተው፤
ያለዚያ ያጠፋሃል” አለው።
[22]ኢዮስያስ ግን ሌላ ሰው መስሎ በጦርነት
ሊገጥመው ወጣ እንጂ ወደ ኋላ አልተመለሰም፤
በመጊዶ ሜዳ ላይ ሊዋጋው ሄደ እንጂ ኒካዑ
ከእግዚአብሔር ታዞ የነገረውን ሊሰማ አልፈ
ለገም።
[23]ቀስተኞች ንጉሥ ኢዮስያስን ወጉት፤
እርሱም የጦር መኰንኖቹን፣ “ክፉኛ ቈስያለሁና
ከዚህ አውጡኝ” አላቸው። [24]ስለዚህ ከሠረገላው
አውርደው በራሱ ሠረገላ ላይ አስቀምጠውት

35፥6 ዘሌ11፥44
35፥7 2ዜና30፥24፤ 31፥3
35፥8 1ዜና6፥13፤ 29፥3፤2ዜና29፥31-36
35፥9 2ዜና31፥12፡ 13
35፥10 ቍ-4፤ 2ዜና30፥16
35፥11 2ዜና30፥17
35፥13 ዘፀ12፥2-11
35፥14 ዘፀ29፥13
35፥15 1ዜና25፥1፤ 26፥12-19፤2ዜና2 9፥30፤ነህ1 2፥46፤መዝ6 8፥25
35፥20 ዘፍ2፥14፤ ኢሳ10፥9፤ኤር46፥2
35፥21 1ነገ13፥18፤ 2ነገ18፥25
35፥22 1ሳሙ28፥8
35፥23 1ነገ22፥34

የሰሎሞን ገጸ ባሕርይ አሣሣል የሚለውን ይመ)።

*35፥7-9፤* በዜና መዋዕሉ መጽሐፍት በፈቃደኝነትና በደስታ መስጠት ትልቅ ትኵረት ተሰጥቶታል (24፥8-14፤ 29፥31-36፤ 31፥3-21፤ 1ዜና29፥3-9)፤ ይህም በድኅረ ምርኮ ለነበሩት ለመጽሐፉ ተደራሲያን ትልቅ ጠቀሜታ እንደ ነበረው ይገመታል።

35፥18 ***ከነቢዩ ከሳሙኤል ዘመን ወዲህ*** በመጽሐፈ ነገሥት የተጻፈው ግን፣ “ከመሳፍንት ዘመን ጀምሮ” (2ነገ23፥22) ተብሎ ነው ።

35፥19 ***በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት፤*** የሕጉ መጽሐፍ ከተገኘበት ዓመት ጋር አንድ ነው (34፥8፡14)።

*35፥20-27፤* 2ነገ23፥28-30 ይመ። በ609 ዓ.ቅ.ክ ላይ “የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን ኒካዑ” ከባቢሎናውያን ጋር ለመዋጋት፣ “የአሦርን ንጉሥ ለመርዳት ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ወጥቶ ነበር” (2ነገ 23-29)።

35፥20፤ ***በከርከሚሽ፤*** ይህ ቦታ በመጽሐፈ ነገሥት ላይ አልተጠቀሰም።

*35፥21-22፤* በዜና መዋዕሉ ላይ ብቻ ተጽፎ የሚገኝ ነው፤ ይኸውም ቢታዘዙ በረከት ባይታዘዙ ደግሞ ቅጣት መኖሩን ለማ ሳየት ጸሓፊው ደጋግሞ የሚያሳየው ጕዳይ ነው። ኢዮስያስ በጦርነቱ ሊገደል የቻለው፣ ፈርዖን ምንም እንኳን አሕዛብ ቢሆ ንም በእርሱ አፍ የተናገረውን የእግዚአብሔርን ቃል ስላ ልታዘዘው ነው።

35፥21 ***ጦርነት ከገጠምሁት ቤት ጋር፤*** ከባቢሎናውያን ጋር ማለት ነው። በጊዜው በዙፋን ላይ የነበረው ንጉሥ ናቦፖላሳር ሲሆን፣ በጦርነቱ ላይ ሰራዊቱን ይመራ የነበረው ግን ልጁ ናቡከደነፆር ነበር። 605 ዓ.ቅ.ክ ላይ በከርከሚሽ ከግብፅ ጋር ከተደረገው ሌላ ጦርነት በኋላ፣ ናቡከደናፆር በአባቱ እግር ተተካ። ምናልባት ኢዮ ስያስ ሊረዳው የመጣው የባቢሎንን ንጉሥ ሳይሆን አይቀርም 32፥31፤33፥11 እና ማብ ይመ)።

35፥22 ***ሌላ ሰው መስሎ፤*** ከአክአብና ከኢዮሣፍጥ ጋር ያነጻጽሩ (18፥29 እና ማብ ይመ)። ***በመጊዶ ሜዳ፤*** የመሳ. 5፥19 ማብ ይመ።

*35፥24-25፤* በዜና መዋዕሉ ላይ ብቻ ተጽፎ የሚገኝ ነው።

35፥25 ***ኤርምያስ ለኢዮስያስ የሐዘን ግጥም ጻፈለት፤***

ወደ ኢየሩሳሌም ወሰዱት፤ እዚያም ሞተ፤
በአባቶቹ መካነ መቃብር ተቀበረ፤ የይሁዳና
የኢየሩሳሌም ሕዝብ ሁሉ አለቀሱለት::
25ኤርምያስ ለኢዮስያስ የሐዘን እንጕርጕሮ
ግጥም ጻፈለት፤ ወንዶችና ሴቶች ሙሾ
አውራጆች ሁሉ እስከ ዛሬ ድረስ በዚህ
ግጥም ኢዮስያስን ያስታውሱታል፤ ይህም
በእስራኤል የተለመደ ሆኖ በልቅሶ ግጥም
መጽሐፍ ተጽፎአል::
26በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት የተከና
ወነው ሌላው ድርጊትና *በእግዚአብሔር*
የሕግ መጽሐፍ በተጻፈው መሠረት ያከናወነው
መንፈሳዊ ተግባር፣ 27ከመጀመሪያው እስከ
መጨረሻው ያደረገው ሁሉ በይሁዳና በእስ
ራኤል ነገሥታት መጽሐፍ ተጽፎአል::

**36** የአገሩም ሰዎች የኢዮስያስን ልጅ
ኢዮአሐዝን ወስደው በአባቱ ፈንታ
በኢየሩሳሌም አነገሡት::

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአሐዝ

36፥2-4ተን ምብ —2ዜና23፥31-34

2ኢዮአሐዝ በነገሠ ጊዜ፣ ዕድሜው ሃያ
ሦስት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም
ሦስት ወር ገዛ:: 3ከዚያም የግብፅ ንጉሥ
በኢየሩሳሌም ካለው ዙፋኑ አወረደው፣ በአገሩም
ላይ አንድ መቶ መክሊት[ሀ] ብርና አንድ መክ
ሊት[ለ] ወርቅ ግብር ጣለበት:: 4የግብፅም ንጉሥ
የኢዮአሐዝን ወንድም ኤልያቄምን በይሁ
ዳና በኢየሩሳሌም ላይ አነገሠው፤ ስሙንም
ለውጦ ኢዮአቄም አለው:: ኒካዑም የኤል
ያቄምን ወንድም ኢዮአሐዝን ይዞ ወደ ግብፅ
ወሰደው::

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም

36፥5-8ተን ምብ —2ዜና23፥36-24፥6

5ኢዮአቄም በነገሠ ጊዜ፣ ዕድሜው ሃያ
አምስት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀም
ጦም ዐሥራ አንድ ዓመት ገዛ:: *በአምላኩም*
*በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ:: 6የባቢ
ሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር በእርሱ ላይ ዘመተ፤ ወደ
ባቢሎንም ይወስደው ዘንድ በናስ ሰንሰለት
አሰረው:: 7እንደዚሁም ናቡ ከደነፆር *የእግዚ*
*አብሔርን* ቤተ መቅደስ ዕቃ ወስዶ፣ ባቢ
ሎን ባለው በራሱ ቤተ ጣዖት[ሐ] አኖረው::
8በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት የተከና
ወነው ሌላው ተግባሩ የፈጸመው አስጸያፊ
ድርጊትና በእርሱ ላይ የተገኘበት ሁሉ በእስ
ራኤልና በይሁዳ ነገሥታት መጽሐፍ ተጽፎ
አል:: ልጁ ዮአኪንም በእርሱ ፈንታ ነገሠ::

## የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን

36፥9-10ተን ምብ —2ዜና24፥8-17

9ዮአኪን በነገሠ ጊዜ፣ ዕድሜው ዐሥራ
ስምንት[መ] ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም
ሦስት ወር ከዐሥር ቀን ገዛ፤ እርሱም *በእግ*
*ዚአብሔር* ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ:: 10በጸደይም
ወራት ንጉሡ ናቡከደነፆር ልኮ *በእግዚአ*
*ብሔር* ቤተ መቅደስ ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ
ካላቸው ዕቃዎች ጋር ወደ ባቢሎን ወሰደው::
የዮአኪንንም አጎት[ሠ] ሴዴቅያስን በይሁዳና
በኢየሩሳሌም ላይ አነገሠው::

## የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ

36፥11-16ተን ምብ—2ዜና24፥18፤ኤር52፥1-3

11ሴዴቅያስ በነገሠ ጊዜ፣ ዕድሜው ሃያ
አንድ ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም
ዐሥራ አንድ ዓመት ገዛ:: 12እርሱም በአምላኩ
*በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ፤
የእግዚአብሔርን ቃል በተናገረው በነቢዩ በኤርምያስ
ፊትም ራሱን ዝቅ አላደረገም:: 13እንደዚ
ሁም በእግዚአብሔር ስም አምሎት በነበረው
በንጉሥ ናቡከደነፆር ላይ ዐመፀ፤ አንገቱን
አደነደነ፤ ልቡንም አጠነከረ እንጂ ወደ እስ
ራኤል አምላክ ወደ *እግዚአብሔር* አልተመ
ለሰም:: 14ከዚህም በላይ የካህናቱና የሕዝቡ
መሪዎች ሁሉ፣ አስጸያፊ የሆኑትን የአሕዛብን
ልማዶች በመከተልና በኢየሩሳሌም የተቀ
ደሰውን *እግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ

35፥25 ዘፍ50፥10፤ 2ዜና34፥28፤ኤር22፥10:15:16
36፥1 2ዜና22፥1
36፥4 ኤር22፥10-12፤ሕዝ19፥4
36፥5 ኤር22፥18፤ 25፥1፤26፥1፤35፥1፤36፥1፤45፥1፤46፥2
36፥6 ኤር25፥9፤ 27፥6፤ሕዝ19፥9፤ 29፥18፤ዳን1፥1
36፥7 ቍ18፤ዕዝ 1፥7፤ ኤር27፥16፤ ዳን1፥2
36፥9 ኤር22፥24-28፤24፥1፤27፥20፤29፥21፤52፥31
36፥10 ቍ18፤ 2ነገ20፥17፤ ዕዝ1፥7፤ኢሳ52፥11፤ ኤር14፥18፤21፥7፤22፥25፤24፥1፤ 27፥16:20:22፤29፥1፤34፥21፤40፥1፤ሕዝ17፥12፤ዳን5፥2
36፥11 2ነገ24፥17፤ ኤር27፥1፤28፥1፤34፥2፤37፥1፤39፥1
36፥12 ዘዳ8፥3፤ 2ዜና7፥14፤ኤር37፥1፤39፥18፤44፥10
36፥13 ዘፀ32፥9፤ ዘዳ9፥27፤ሕዝ17፥13
36፥14 1ዜና5፥25

[ሀ]3 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው::
[ለ]3 34 ኪሎ ግራም ይህል ነው::
[ሐ]7 ወይም *ቤተ መንግሥት* ተብሎ መተርጐም ይቻላል::
[መ]9 አንድ የዕብራይስጥ ቅጂ ጥቂት የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስት ትርጒሞች (እንዲሁም 2ነገ24፥8) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆዎች ግን *ስምንት* ይላሉ::
[ሠ]10 ዕብራይስጡ *ወንድም* ይላል (እንዲሁም 2ነገ24፥17 ይመ) ::

ኤርምያስ ኢዮስያስን የሚመለከተው እጅግ ከፍ ባለ አክብሮት ነበር (ኤር22፥15-16):: የጻፈለት የሐዘን እንጕርጕሮ አሁን አይገኝም:: የሰቆቃውን መጽሐፍ የጻፈው ኤርምያስ ነው ተብሎ በትውፊት የሚነገረው ከዚህ የተነሣ ነው:: *እስከ ዛሬ ድረስ፤* የ5፥9 ማብ ይመ ::

*36፥2-14፤* ከእርሱ በኋል በተከታታይ ሦስት ልጆቹ የነገሡለት የይሁዳ ንጉሥ ኢዮስያስ ብቻ ነው (ኢዮአሐዝ፣ ኢዮአቄም፣ ሴዴቅያስ):: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ስለተቀሩት የይሁዳ ነገሥታት ታሪክ የጻፈው አሳጥሮ ነው::

*36፥2፤* 2ነገ23፥31-35 ይመ:: ኢዮስያስ በፈርዖን ኒካዑ እጅ ከተገደለ በኋላ፣ የይሁዳ ምድር ለተወሰነ ጊዜ በግብፅ አገዛዝ ሥር ወድቃለች (ቍ3-4):: *ሦስት ወር፤* 609 ዓ.ቅ.ክ. ማለት ነው:: ኒካዑ ሥልጣኑን አደላድሎ ይሁዳን በቍጥጥሩ ሥር ሲያደርግ በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ሰፍኖ የነበረው የሃያ ዓመት ነጻነት አከተመ:: ይህን አጭር የአገዛዝ ዘመን አስመልክቶ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ምንም ዐይነት ግብረገባዊ ፍርድ አልሰጠም፤ ነገር ግን የነገሥቱ ጸሓፊ ስለዚህ ነገር ብዙ ብሎአል (2ነገ23፥32)::

*36፥4፤* ኒካዑ ኢዮአሐዝን ወደ ምርኮ በመውሰድ፣ ለኤልያቄም ኢዮአቄም ብሎ ስም በማውጣት እንዳነገሠው ሁሉ፣ ናቡከደነፆር ኢዮአቄምን ወደ ባቢሎን በምርኮ በመውሰድ ለሴዴቅያስ ማታንያን የሚል ስም በመስጠት በምትኩ አንግሦታል (2ነገ 24፥15-17):: ድል አድራጊዎቹ ግብፅና ባቢሎን የየራሳቸውን ሰዎች በዙፋን ላይ አስቀምጠዋል፤ የስም ለውጡም ባስቀመጡት ሰው ላይ ሥልጣን እንዳላቸው የሚያመልክት ነው::

*36፥5-8፤* 2ነገ23፥36-24፥7 ይመ:: ኢዮአቄም ነቢያትን ያሠቃዩ ንጉሥ ስለ ነበር፣ ኤርምያስ በከፍተኛ ሁኔታ አውግዞታል (ኤር 25-26፤36):: በ605 ዓ.ቅ.ክ. ላይ ግብፅ በከርከሚሽ ድል ስትደረግ (ኤር46፥2)፣ ኢዮአቄም ከባቢሎን ንጉሥ ከናቡከደነፆር ጋር ኅብረትን ፈጠረ:: በኋላ ደግሞ ከባቢሎን ጋር የነበረውን ኅብረት በማቋረጥ ከግብፅ ንጉሥ ጋር በማበሩ የባቢሎን ንጉሥ የበቀል ቅጣት የሚወስዱ ሰራዊት ሰደደበት:: ይሁን እንጂ ይህ ሰራዊት ገና እዚያ ከመድረሱ በፊት ኢዮአቄም ሞተ፤ ስለዚህም ልጁን ዮአኪንን ምርኮኛ በማድረግ ወደ ባቢሎን ወሰዱት::

36፥5 *ዐሥራ አንድ ዓመት፤* 609-598 ዓ.ቅ.ክ. ማለት ነው::

*36፥9-10፤* 2ነገ24፥8-17፤ እንዲሁም ኤር22፥24-28፤ 24፥1፤29፥2፤52፥31 ይመ:: ምንም እንኳ ዮአኪን ንግሥት ከሆነችው ከእናቱና ከሹማምንቱ እንዲሁም ከብዙ ሕዝብ ጋር ቢወሰድም (597 ዓ.ቅ.ክ)፣ በምትኩ ሴዴቅያስ ነግሦአል፤ በሴዴቅያስም የንግሥና ዘመን ሁሉ ዮአኪን ምርኮኛ ነበር (ኤር52፥31፤ ሕዝ 1፥2፤ እንዲሁም ከኢስ.2፥5-6 ጋር ያነጻጽሩ)::

36፥9 *ሦስት ወር ከዐሥር ቀን፤* 598-597 ዓ.ቅ.ክ. ማለት ነው::

*36፥11-14፤* 2ነገ 24፥18-20፤ ኤር 52፥1-3 ይመ፤ ከቍ 13-14 ያለው ክፍል በዚህ መጽሐፍ ላይ ብቻ የሚገኝ ነው (ከኤር 1፥3፤ 21፥1-7፤ 24፥8፤27፥1-15፤ 32፥1-5፣34፥1-7:21፤37፥1-39፥7 ጋር ያነጻ

በማርከስ፣ ባለመታመናቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ
እየባሱ ሄዱ።

## የኢየሩሳሌም መውደቅ

36፥17-20 ተጓ ምብ —2ነገ25፥1-21፤ኤር52፥4-7
36፥22-23 ተጓ ምብ — ዕዝራ1፥1-3

[15]የአባቶቻቸው *አምላክ* እግዚአብሔር ለሕዝቡና
ለማደሪያው ስላዘነ፣ መልእክተኞቹን ይልክ
ነበር፤ [16]እነርሱ ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በሕዝቡ
ላይ እስኪነሣና ፈውስም እስከማይገኝላቸው
ድረስ በእግዚአብሔር መልእክተኞች ላይ ተሳለቁ፤
ቃሉን ናቁ፤ ነቢያቱንም አቃለሉ። [17]ስለዚህ
የባቢሎናውያንን[a] ንጉሥ አመጣባቸው፤ እርሱም
ወጣቶቻቸውን በቤተ መቅደሱ ውስጥ
በሰይፍ ፈጀ፤ ወጣቱንም ሆነ ወጣቲቱን፣
ሽማግሌውንም ሆነ በዕድሜ የገፋውን አላስ
ቀረም፤ እግዚአብሔር ሁሉንም ለናቡከደነፆር
አሳልፎ ሰጠው። [18]እርሱም ትልልቁንም ሆነ
ትንንሹን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ዕቃ
በሙሉ፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ
ሀብት፣ የንጉሡንና የሹማምንቱን ሀብት
ሁሉ ወደ ባቢሎን አጋዘ። [19]የእግዚአብሔርን
ቤተ መቅደስ በእሳት አቃጠሉ፤ የኢየሩ
ሳሌምን ቅጥሮች አፈረሱ፤ ቤተ መንግሥ
ቶቹን በሙሉ አቃጠሉ፤ በዚያ የነበረውንም
የከበረ ዕቃ በሙሉ አጠፉ።
[20]ከሰይፍ የተረፉትን ቅሬታዎች በምርኮ
ወደ ባቢሎን ወሰዳቸው፤ እስከ ፋርስ መንግሥት
መነሣትም ድረስ የእርሱና የልጆቹ አገልጋዮች
ሆኑ። [21]ምድሪቱም የሰንበት ዕረፍት አገኘች፤
በኤርምያስ የተነገረው *የእግዚአብሔር* ቃል
ይፈጸም ዘንድ፣ ሰባው ዓመት እስኪያበቃ
ድረስ፣ ባድማ በነበረችበት ዘመን ሁሉ ዐረፈች።
[22]በኤርምያስ የተነገረው *የእግዚአብሔር*
ቃል ይፈጸም ዘንድ፣ በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ
ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ዓመት፣ በግዛቱ
ሁሉ ዐዋጅ እንዲያስነግርና ይህም እንዲጻፍ
*እግዚአብሔር* የፋርስን ንጉሥ የቂሮስን
መንፈስ አነሣሣ፤ እርሱም እንዲህ አለ፤
[23] "የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ እንዲህ
ይላል፤" 'የሰማይ *አምላክ* እግዚአብሔር የም
ድርን መንግሥታት ሁሉ ሰጥቶኛል፤ በይሁዳ
በምትገኘው በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ
እሠራለት ዘንድ አዝዞኛል፤ ከሕዝቡ በመ
ካከላችሁ የሚገኝ ማናቸውም ሰው፣
*እግዚአብሔር* አምላኩ ከእርሱ ጋር ይሁን፤
እርሱም ወደዚያው ይውጣ።' "

36፥15 ኢሳ5፥4፤ 44፥26፤ኤር7፥13፡25፤11፥7፤25፥3-4፤ 35፥14፡15፤44፥4-6 ሐጌ1፥13፤ዘካ1፥4፤ ሚል2፥7፤3፥1፤ ማቴ5፥12
36፥16 2ነገ2፥23፤ ዕዝ5፥12፤ነህ9፥30፤ ኢዮ8፥2፤ምሳ1፥30-31፤29፥1፤ ኢሳ28፥14፡ 22፤ 29፥20፤57፥4፤ ኤር5፥13፤7፥26፤ 20፥8፤25፥4፤30፥12፤ 43፥2፤44፥3፤ዳን9፥6፤ ሚክ2፥11፤ዘካ1፥2
36፥17 ዘዳ10፥10፤ ዘዳ32፥25፤ዕዝ5፥12፤ኤር6፥11፤9፥21፤ 18፥21፤32፥28፤ 44፥7፤ 51፥22፤ ሰቆ2፥21፤ ሕዝ9፥6፤23፥47
36፥18 ቍጥ7፡10፤ ኤር27፥20
36፥19 1ነገ9፥8-9፤2ነገ14፥13፤መዝ79፥1-3፤ ኤር11፥16፤17፥27፤ 21፥10፤14፤22፥7፤32፥29፤39፥8፤ ሰቆ2፥6፤4፥11፤ ሕዝ20፥47፤አሞ
36፥20 ዘሌ26፥44፤ 2ነገ24፥14፤ዕዝ2፥1፤ ነህ7፥6፤ኤር27፥7
36፥21 ዘሌ25፥4፤ 1ዜና22፥9፤ ኤር1፥1፤ 25፥11፤ 27፥22፤ 29፥10፤ 40፥1፤ዳን9፥2፤ዘካ1፥12፤7፥5
36፥22 ኢሳ44፥28፤ 45፥1፡13፤ዳን1፥21፤6፥28፤10፥1

[a]17 ወይም *ከለዳውያን*

ጽሩ)። ሴዴቅያስ የግብፅን ርዳታ ለማግኘት በናቡከደነፆር ላይ ዐመፀ ባቢሎናውያንም ፈጣን ርምጃ ወሰዱ፤ ከዚህም የተነሣ በ588 ዓ.ቅ.ክ ላይ ኢየሩሳሌም ተከበበች (ኤር21፥3-7)። በ586 ዓ.ቅ.ክ. ከመደ ምሰሷ በፊት፣ ለሁለት ዓመት ያህል ጥቃቱን ለመከላከል ሞክራለች።

36፥11 *ዐሥራ አንድ ዓመት፤* ከ597-586 ዓ.ቅ.ክ. ማለት ነው።

*36፥15-16፤* 24፥19 እና ማብ ይመ።

36፥20-21፤ የሁለቱ ታሪኮች ድምዳሜ መለያየት የሚያስ ደንቅ ነው፤ የመጽሐፈ ሳሙኤልና የመጽሐፈ ነገሥት ጸሐፊ ዎች፣ እስራኤላውያን በምርኮ የተወሰዱት በምን ምክንያት እንደሆነ እንዲሁም በምርኮ እስከተወሰዱበት ጊዜ ድረስ የነበረውን አለመ ታዘዝ፣ በተጨማሪም ራሳቸው ጸሐፊዎቹ የነበሩበት ዘመን ምን እንደሚመስል የማሳየት ፍላጎት ነበራቸው። ይህም እንኳ ጸሐፊው እግዚአብሔር ለዳዊት የገባለትን ቃል ኪዳን (2ነገ 25፥27-30) ለመፈጸም ሲል ለዘሮቹ ያደረገውን በጎነት ገልጾአል የጸሐፊው አስተሳሰብ በመከራ ተፈትነው ያለፉት ቅሬታዎች ወደ ዐላማ ወደ ኋላ መለስ ብሎ በምርኮኞች ላይ ወደ ጸዳቸው ምድር መመለሳቸው (ቍ22-23)፣ አዲስ የተስፋ ዘመን መጀመሩን የሚያመለክት ነው። ምርኮውና ስደቱ የመከራን ጊዜት የጨለጠበት ፍርድ ብቻ ሳይሆን፣ ምድሪቱም የሰንበት ዕረፍት ያደረገችበት ዘመን በመሆኑ በረከትም ነው (ዘሌ26፥40-45)። እግዚአብሔር ኪዳኑን አስቦ (ዘሌ26፥45)፣ ሕዝቡን ወደ ቀድሞ ርስታቸው መልሶአቸዋል (የሚቀጥለውን ማብ ይመ)።

*36፥22-23፤* የመጽሐፈ ነገሥቱ ጸሐፊ ታሪኩን የሚደ መድመው፣ ከምርኮ ከመመለስ በፊት ባለው ጊዜ በመሆኑ፣ በዚህ ክፍል የተጻፈውን ታሪክ አልዘገበውም፤ ይሁን እንጂ ይህ ክፍል በመጽሐፈ ዕዝራ መጀመሪያ ላይ (1፥14) ተደግሞ መጻፉ፣ ማለትም ዜና መዋዕሉ ያቆመበትን ሐሳብ መጽሐፈ ዕዝራ ይዞ መነሣቱ፣ የዜና መዋዕሉንና የዕዝራን መጽሐፍ የጻፈው አንድ ሰው ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አሳድሮአል። የኤር ምያስን ትንቢት ይመ (ኤር25፥1-14) እንዲሁም ከዳን 9 ጋር ያነጻጽሩ። ቂሮስ ከምርኮ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ዐዋጅ ያወጣው ለአይሁድ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ምርኮኞች ጭምር ነበር።